ስለ እርሱ ሥራና ስለ አስከተለውም ጉዳት ተነግሮ አያልቅም፡፡ ይልቅስ ስለ ሰይጣን በደል ትተን ስለ ሰው ኃጢአትና ውድቀት እንመልከት፡፡

የሰው ልጆችን ኃጢአት በሁለት ዓይነት ለይተን እንማራለን፡፡ አንደኛው ዓይነት፡- የአዳም ኃጢአት ወይም ጥንተ አብሶ ማለት የመጀመሪያው በደል በመባል የታወቀው ነው፡፡ ሁለተኛው፡- እኛው ራሳችን በገዛ ፈቃዳችን በነፃ ምርጫችን የምንፈጽመው ኃጢአት ነው፡፡

<u>ጥንተ አብሶ የምንለው፡-</u> የአዳም ኃጢአት በእኛ ውስጥ እንዳለ የምንናገረው፥ በዘር ቁራኘነት ከመጀመሪያው አባታችን ከአዳም ሲወርድ ሲዋረድ መጥቶ ከእኛ የደረሰውን፥ በኋላም ወደ ልጆቻችን የሚተላለፈውን የውርስ እዳ በደልን፥ ፍዳና መርገምን የሚያመለክት ነው፡፡ ሥጋና ነፍሳችንን ከአንድ ከአባታችን ከአዳም እንደ ወረስን እንደዚሁም የእርሱ የሆነውን ኃጢአቱንና ሞቱንም ወርሰናል፡፡[51] "በዓመፃ ተፀነስሁ፥ እናቴም በኃጢአት ወለደችኝ" (መዝ.50፥5) የተባለውን እናስተውል፡፡ እንግዲህ በአንድ ሰው በአዳም የተነሣ ኃጢአት ወደዚህ ዓለም እንደገባና በኃጢአት ምክንያትም ሞት እንደ መጣብን በሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ትምህርት የተረጋገጠ ነው (ሮሜ 5፥12-14)፡፡

ቅዱስ አቡሊዲስ ዘሮም "መጀመሪያ የበደለ አዳም ነው፤ አዳምም በበደለ ጊዜ የመሰሉትን ያን ጊዜ ወለደ" በማለቱ በበደል፥ በኃጢአት አዳም አባታቸውን አክለውና መስለው ልጆቹ እንደ ተወለዱ ያስረዳል፡፡ ቀጥሎ "በዚያን ወራት አዳምን መሬት ነህ ወደ መሬትነትህ ተመለስ የሚል ከእግዚአብሔር የታዘዘ አንድ አዋጅ በሁሉ ላይ ተነገረ፡፡" በማለት የሞት አዋጅ በአዳምና በደሉንና እርግማኑን በወረሱት ልጆቹ ላይ ሁሉ ተፈጻሚነት እንዳለው ይገልጽልናል (ሃይ.አበው ገጽ 145)፡፡

ከአዳም የወረስነው ኃጢአት ልክ እንደ ራሳችን ኃጢአት ስለ ሚቆጠር በደለኞች ነን፡፡ ስለዚህ የአዳም ዘር ሁሉ ከእግዚአብሔር እንደ ተጣላና እንደ ተለየየ ነው፡፡ ሁሉም በመጀመሪያው እርግማን ሥር ነው ማለት ነው፡፡ ነገር ግን በምሥጢረ ጥምቀት በውርስ ያገኘነው ኃጢአት ተሠርዮልን የልጅነት ጸጋ ተሰጥቶናል፡፡ ምንም ያልበደሉ ሕፃናት ጥንተ አብሶ ስላለባቸው በጥምቀት

[51] "ወንድም [ሆይ]፥ አዳም ኃጢአት በሠራ ጊዜ፥ እርሱ ተቀጥቶ በነበረ ጊዜ እና ሞትም ባገኘው ጊዜ አንተ በአዳም ወገብ ውስጥ ነበርህ፡፡ ስለሆነም የእርሱ አካል እንደ መሆንህ መጠን ይህንን ሁሉ ወርሰሃል፥ እንድትሞትም ተፈርዶብሃል፥ ኃጢአትም በአንተ ባሕርይ ውስጥ ገባች፥ የመለኮትንም [የእግዚአብሔርን] አርአያ አጣህ፡፡ ከዚህ ከከባዱ ጥንተ አብሶ [ከመጀመሪያው በደል] እና ከእርሱም [በእርሱ ሳቢያ ከመጡት] ውጤቶችና ቅጣቶች ሁሉ አንተ መዳን ያስፈልግሃል" በማለት የግብፅ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ስለ ጥንተ አብሶ ታስተምራለች፡፡

"Brother, you were in the loins of Adam when he sinned, when he was punished and when death found access to him. So, you inherited all this, being part of him, was condemned to die, sin entered into your nature and you lost the divine image.

You became in need for salvation from this original serious sin and from all its consequences and punishments." H.H. Pope Shenouda III, <u>The Heresy Of Salvation In A Moment</u> (Dar El Tebaa El Kawmia, December 1991), p.106

ልጅ በአባት "ወገብ" ስለ መሆኑ ሌላ ማስረጃ አለ፡፡ "አሥራትን የሚያስወጣ ሌዊ እንኳ በአብርሃም እጅ አሥራትን ሰጥቷል፤ መልከ ጼዴቅ በተገናኘው ጊዜ ገና በአባቱ ወገብ ነበረና" የሚለውን ቃል እናስተውል (ዕብ.7፥9 እና 10)፡፡ ነቢዩ ሕዝቅኤል "ልጅ የአባቱን ኃጢአት አይሸከምም፥ አባትም የልጁን ኃጢአት አይሸከምም" ያለው የግል ኃጢአትን እንጂ ጥንተ አብሶን አይመለከትም (ሕዝ.18፥20-32)፡፡



የኃጢአትን ሥርየትና የልጅነትን ጸጋ ያገኛሉ፡፡ እኛም ካደግን በኋላ የተጠመቅን ከሆነ የውርስም ሆነ የራሳችን ኃጢአት ማለት እስከ ተጠመቅንበት ጊዜ ድረስ ያለው ኃጢአት ሁሉ ይሠረያል፡፡ ከጥምቀት በኋላም የፈጸምነው ኃጢአት ቢኖር በምሥጢረ ንስሐና በምሥጢረ ቁርባን የኃጢአት ሥርየት ይገኛል፡፡

በአዳም በደልና ኃጢአት የሰው ልጆች ውርደትና ውድቀት ደርሶባቸዋል፡፡ የኃጢአት ውጤት የሆኑትም ፈተናና ችግር ቀሪ ገንዘቡ ሆነዋል፡፡ የነበረውን መልካሙን ነገር አጥተዋል፤ ያልነበረውም ክፉና ከባድ የኑሮ ሸክም ተጭኗቸዋል፡፡ በመጀመሪያ የነበረውን ጥበብና እውቀት በማጣት ዛሬ የአዳም ዘርያዎች በድንቁርና ጨለማ ውስጥ ይገኛሉ፡፡ እውቀት እንኳ አለ ቢባልም ከበደል በፊት ከነበረው እጅግ ያነሰ ነው፡፡ ስለዚህ ነው ዛሬ ስለ እግዚአብሔርና ስለ መንፈሳዊ ነገሮች የምንገነዘብበት እውቀት ጉድሉ የምናየው፡፡ በትምህርት፥ በታምራት፥ በምስክርነት እንኳ እየተደገፈ የሰው ልጅ እምነትና ስለ ፈጣሪው ያለው እውቀት እንደ ሚገባው ሆኖ አልተገኘም፡፡ ስለዚህ ነው ክርስቶስ ወንጌልን እንድናስተምር በማዘዙ በኃጢአት የመጣውን ድንቁርና እንድንቋቋመውና የወንጌልም እውቀት ተስፋፍቶ ከጨለማ ወደ ብርሃን እንድንሸጋገር ያደረገው፡፡ ሁልጊዜ እውነትን በመማርና በማስተማር ድንቁርናን ለመቀነስ፥ እውቀትን ለመጨመር ይቻላል፡፡ ይህም የሚፈጸመው በቃለ እግዚአብሔር ላይ ተመሥርተን የሠራን እንደሆነ ነው፡፡

የሰው ልጅ እውቀቱ ብቻ አይደለም በኃጢአት ምክንያት የተቀነሰው፥ የመወሰን ኃይሉም ማለት ሐሳበ ጠንካራነቱም ደከመ፥ ላላ፡፡ ይህም ሁለተኛው ነገር ነው አዳም ከጥንተ አብሶ በፊት ከነበረው ጸጋ ያጐደለው፡፡ በዚያን ጊዜ ምድርንና በምድር ላይ የተፈጠሩትን ሁሉ ያዝና ይናዝዝ፥ ይገዛና ይነዳ ነበር፡፡ ከበደል በኋላ ይህን ሁሉ አጥቶ ራሱንም እንኳ ለመቆጣጠር አዳገተው፡፡ የነበረው የመንፈስ ብርታትም ተቀነሰ፡፡ የሰው ልጅ ዛሬ በጉውን ከክፉው ለመምረጥ እውቀትም ቢኖረው እንኳ ጠንካራ ፈቃድ ስለ ሌለው የመረጠውን መልካም ነገር በተግባር ለማዋል አጋዥ ከሌለው በስተቀር ያዳግተዋል፡፡ ሳይወድ በድካሙ ምክንያት ለክፉ ነገር ስለሚገዛ ፍጹም የነበረውን የመጀመሪያውን ነፃነቱን አጥቷል፡፡

ጥንተ አብሶ ያመጣብን ሦስተኛው ጠንቅ ፍትወት ማለት ክፉ ምኞት ወይም በሰው የሚገኘው የኃጢአት ዝንባሌ ነው፡፡ አራተኛው፡- በዓለም ውስጥ ስንኖርና ስንሠራ የሚደርስብን ፈተና፥ ችግርና መከራ ሁሉ በአዳም በደል እንደ መጣብን እናስተውላለን፡፡ አምስተኛውና የመጨረሻው፡- የበደል ውጤት ወይም የኃጢአት ዋጋ የተባለው ሞተ ሥጋና ሞተ ነፍስ መሆናቸው በቅዱሳት መጻሕፍት የተጻፈ ነው (ዘፍ.2፥17፤ሮሜ 6፥23፤ ያዕቆብ 1፥15)፡፡
(ስለ ጥንተ አብሶ፣ ጥምቀትና መንፈሳዊ ተጋድሎ ከገጽ 204-207 ተመልከት)

## *<u>የኃጢአት ዓይነትና ደረጃ</u>*

የኃጢአት ዓይነት ሁለት እንደሆነ ከላይ ተመልክተናል፡፡ አንደኛ የአዳም ኃጢአት፤ ሁለተኛ የእኛ ኃጢአት መሆናቸውን እናስታውሳለን፡፡ የአዳም ኃጢአት የተባለው በውርስ ያገኘነው ሲሆን፥ እኛ ደግሞ በገዛ ፈቃዳችን የምንፈጽመው ክፉ ነገር ሁሉ የግል ኃጢአታችን ነው፡፡ የግል ኃጢአታችንንም የምንፈጽመው በሦስት ዓይነት መንገድ ነው፡- በሐሳብ፥ በቃልና በሥራ ነው፡፡ ክፉ በማሰብና በመመኘት ማለት የማይገባውን በማሰብና በመመኘት፥ በልቡና ኃጢአት ይፈጸማል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የሚገባውን መልካሙን ነገር አለማሰብም ኃጢአት ይሆናል፡፡ በቃልም ክፉ ነገር ይሠራል፡፡ ስድብን በመናገር፥ ወይም የማይገባውን፥ ሰውን የሚጐዳውን ነገር በመሠወር ፈንታ ገልጸ

www.ethiopianorthodox.org

በመናገር፥ በመጻፍ፥ በማሳወቅ የቃል ኃጢአት ይደረጋል፡፡ እንደዚሁም ደግሞ የሚገባውን ያለመናገር፥ መመስከር የሚገባውን በእውነት ሳይመሰክሩ መቅረትና በዚህም የተነሳ በሰው ላይ ጉዳት የሚደርስ ከሆነ ታላቅ በደል እንደ ተፈጸመ ይቆጠራል፡፡ በሥራም፥ እንደዚሁ ክፉ ማድረግ የማይገባውን ነገር መፈጸም ኃጢአት ይሆናል፡፡ በአንፃሩም ደግሞ የሚገባውንና የታዘዘውን መልካም ሥራ አለመፈጸም ከባድ ኃጢአት እንደሆነ የታወቀ ነው፡፡

የኃጢአትም ቀላልና ከባድ እንዳለው ከቅዱሳት መጻሕፍት እንማራለን፡፡ ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስ ሞት የማይገባው ኃጢአትና ሞት የሚገባው ኃጢአት መኖሩን እንደሚከተለው ያስረዳናል፡፡ "ማንም ወንድሙን ሞት የማይገባውን ኃጢአት ሲያደርግ ቢያየው ይለምን፥ ሞትም የማይገባውን ኃጢአት ላደረጉት ሕይወት ይሰጥለታል፡፡ ሞት የሚገባው ኃጢአት አለ፤ ስለዚያ እንዲጠይቅ አልልም፡፡ ዓመፃ ሁሉ ኃጢአት ነው፥ ሞትም የማይገባው ኃጢአት አለ" (1ኛዮሐ.5፥16-17)፡፡ እንግዲህ ኃጢአት በሁለት ዓይነት ደረጃ እንደ ተከፈለ ለመገንዘብ እንችላለን፡፡ ሆኖም ሁለቱንም ዓይነት ማለት የትኛው ቀላል፥ የትኛው ከባድ መሆኑን ለይቶ እስከ መጨረሻው ድረስ ዘርዝሮ በጽሑፍ ለማስቀመጥ እጅግ አዳጋች ይሆናል፡፡ ምክንያቱም ቀላል የመሰለው ከባድ፥ ከባድ የመሰለው ቀላል የሚሆንበት ወሳኝ ሁኔታ ስላለ ነው፡፡ ይኸውም በደል ፈጸመ የተባለው ሰው፥ አሳቡና ስሜቱ፥ የአካባቢውና የጊዜው ሁኔታ፥ የበደሉ ዓይነትና ሌሎችም ከዚህ ጋር የተያያዙት ሁሉ ተመርምረውና ተመዛዝነው ካልተገመገሙ በስተቀር የበደሉ ድርጊት ብቻውን ትንሽና ትልቅ ኃጢአት መሆኑን አይወስንም፡፡ የሆነ ሆኖ ሞት የማይገባውና ሞት የሚገባው ኃጢአትና ኃጢአተኛ እንዳለ የታወቀ ነው፡፡ ይህንንም በመጨረሻ የሚፈርደው እግዚአብሔር ስለሆነ እርሱ ባወቀ የኃጢአቱን ከባድነትና ቀላልነት አይቶ የኃጢአተኛውንም ልቡና በጥልቅ መርምሮ እርሱ ባለቤቱ አስፈላጊውን ይፈጽማል፡፡ ሰዎችም ከባድና ቀላል ኃጢአትን ከቅዱሳት መጻሕፍት፥ ከቤተ ክርስቲያን አባቶችና ምሁራን ሊረዱ ይችላሉ፡፡ ስለዚህ ጉዳይ የንስሐ አባቶች ለልጆቻቸው ለምእመናን ሁሉ ማስተማር ይገባቸዋል፡፡

ሦስቱ አርእስተ ኃጣውእ የሚባሉት ከባድ የሆኑትን የኃጢአት ዓይነቶች ያስታውቁናል፡፡ እነርሱም፥ ስስት፥ ፍቅረ ንዋይና ትዕቢት ናቸው፡፡ እነዚህም አርእስት የተባሉበት የብዙ ኃጢአቶች መገኛ ምንጭና ማብቀያ ሥር መሠረት በመሆናቸው ነው፡፡ ጌታችን በእነዚህ ተፈትኖ ድል አድርጓል፡፡ እኛም እርሱን እንድንከተል ምሳሌውን ሰጥቶናል (ማቴ.4፥1-11)፡፡ "በዓለም ሳላችሁ መከራ አለባችሁ፤ ነገር ግን አይዟችሁ፤ እኔ ዓለምን አሸንፌአለሁ" በማለት ያበረታታናል (ዮሐ.16፥33)፡፡ ስለዚህ እኛም ስለ ኃጢአት ማወቅ ብቻ ሳይሆን መታገልም የሃይማኖት ግዴታችን ነው፡፡ "ተጋደልዋ ለኃጢአት ወዕበይዋ" ማለት ኃጢአትን ተጋደሏት አሸንፏትም ተብሎ እንደ ተጻፈ ሁልጊዜ መታገል ይኖርብናል (ዕብ.12፥4)፡፡ ሦስቱን አርእስተ ኃጣውእ ጌታችን እንዴት ድል እንዳደረገ ተመልክተን እኛም የእርሱን አርአያ እንድንከተል ያስፈልጋል፡፡

ጌታችን በስስት የመጣውን ፈተና እንዴት ድል እንደ ነሣው ማስታወስ ይኖርብናል፡፡ "ሰው ከእግዚአብሔር አፍ በሚወጣው ቃል ሁሉ እንጂ በእንጀራ ብቻ አይኖርም" በማለት ጌታችን የስስትን ፈተና በጾምና በትኅርምት በትዕግሥትም ድል ነሥቶታል፡፡ ስስት የመብልና የመጠጥ ፍቅርን ወይም ሆዳምነትን የሥጋ ፍላጎትን ያመለክታል፡፡ አብዝቶ መብላትና መጠጣት ጥጋብን ያስከትላል፤ ጥጋብም የኃጢአት ምንጭ ነው፡፡ ካልጠገቡ አይዘሉ፥ ካልዘለሉ አይሰበሩ እንዲሉ፥ ከጥጋብና ከስካር መከልከል ይኖርብናል፡፡ በመጾምና በመጠኑ በመኖር በመታገሥም ራሳችንን ከክፉ ነገር ለመቆጣጠር እንችላለን፡፡

ነገር ግን ከመጠኑ አሳልፎ ዘወትር መብላትና መጠጣት፥ ሁልጊዜም በጥጋብና በፈንጠዝያ መኖርን መውደድ ጣዖት እንደ ማምለክ ይቆጠራል፡፡ የመኖር ዓላማው ለመብላትና ለመደሰት ብቻ ነው የሚሉ ካሉ "ለክርስቶስ



መስቀል ጠላቶች ሆነዋል፡፡ እንደዚህ ዓይነት ሰዎች መጨረሻቸው ጥፋት ነው፤ ሆዳቸው አምላካቸው ነው፥ ክብራቸው በነውራቸው ነው፥ አሳባቸው ምድራዊ ነው፡፡" በማለት ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ያስረዳናል፡፡ ከዚያ ቀጥሎ ስለ እኛ ተስፋ ይጽፋል፡፡ "እኛ አገራችን በሰማይ ነውና፥ ከዚያም ደግሞ የሚመጣ መድኃኒትን እርሱንም ጌታን ኢየሱስ ክርስቶስን እንጠባበቃለን፤ እርሱም ሁሉን እንኳ ለራሱ ሊያስገዛ እንደ ሚችልበት አሠራር፥ ክቡር ሥጋውን እንዲመስል የተዋረደውን ሥጋችንን ይለውጣል" (ፊልጵ. 3፥18-21)፡፡

ፍቅረ ንዋይም ከባድ ኃጢአት ነው፡፡ "ገንዘብን መውደድ የክፋት ሁሉ ሥር ነውና፥ አንዳንዶችም ይህን ሲመኙ፥ ከሃይማኖት ተሳስተው በብዙ ሥቃይ ራሳቸውን ወጉ" በማለት ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ያስተምረናል (1ጢሞ.6፥10)፡፡ ስለዚህ ክርስቲያን የሆንን ሁሉ እንዳንሳሳት በመጀመሪያ ማፍቀር የሚገባንን ማወቅ ግዴታችን ነው፡፡ ማፍቀር የሚገባን ሁለት ነገሮች ብቻ ናቸው፡፡ እግዚአብሔርንና ሰውን ብቻ እንድናፈቅር ታዘናል፡፡ ሌላውን በዓለም የሚገኘውን ሁሉ ምግብንና ልብስን፥ ወርቅንና ገንዘብን፥ ሀብትን ሁሉ በሚገባውና በአስፈላጊው መንገድ እንድንገለገልባቸው እንጂ እንድንወዳቸውና እንድንደሰትባቸው እንድናመልካቸውም አልተፈጠሩም፡፡ ፍጹም ፍቅራችንና ደስታችን በተለይም አምልኮታችን በፍጡር ላይ ሳይሆን በፈጣሪያችን ላይ ብቻ መመሥረት ይኖርበታል፡፡ ይህንን መተላለፍ ታላቅ ኃጢአት ነው፡፡ ስለዚህ የፍቅረ ንዋይን ፈተና በፍቅረ እግዚአብሔር በፍቅረ ቢጽ ተክተን ገንዘባችንን ደግሞ ሳናፈቅር ግን በትክክል አገልግሎት ላይ እንዲውል ብናደርግ ፈተናውን ድል ነሣነው ማለት ነው፡፡

ሌሎችንም ከባድ የኃጢአት ፈተናዎች ማለት ትዕቢትን በትኅትና፥ ቁጣን በትዕግሥት፥ ዝሙትን በንጽሕና፥ ስንፍናን በትጋት፥ ምቀኝነትን በፍቅረ ቢጽ፥ ሐሰተኝነትን በእውነተኝነት ለመቋቋም ዘወትር መጋደልና ለዚሁም የእግዚአብሔርን ርዳታ መጠየቅ የክርስቲያኖች ሁሉ ሥነ ምግባራዊ ግዴታ ነው፡፡

ከዚህም ጋር በተሳሳተ በተገደፈ ከንስሐ አባት ጋር በመመካከር፥ ፈተናን በበለጠ ለመታገል የሚያስችለንን መንገድ ለመማር እንችላለን፡፡ በቤተ ክርስቲያንም ኃጢአታችንን ለማስወገድና የጸጋ ሕይወትን ለመቀበል የሚያስችሉን ምሥጢረ ንስሐና ምሥጢረ ቁርባን ተዘጋጅተው ይጠብቁናል፡፡

> "ሰዎችን ሁሉ የሚያድን የእግዚአብሔር ጸጋ ተገልጧልና፤ ይህም ጸጋ፥ ኃጢአተኝነትንና ዓለማዊን ምኞት ክደን፥ የተባረከውን ተስፋችንን እርሱም የታላቁን የአምላካችንንና የመድኃኒታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ክብር መገለጥ እየጠበቅን፥ ራሳችንን በመግዛትና በጽድቅ እግዚአብሔርንም በመምሰል በአሁኑ ዘመን እንድንኖር ያስተምረናል፤ መድኃኒታችንም ከዓመፅ ሁሉ እንዲቤዠን፥ መልካሙንም ለማድረግ የሚቀናውን ገንዘቡም የሚሆነውን ሕዝብ ለራሱ እንዲያነፃ፥ ስለ እኛ ነፍሱን ሰጥቷል" (ቲቶ 2፥11-14)፡፡

ኃጢአት በሰው ላይ ሞትን፣ በፍጥረት ላይ እርግማንን ያመጣብን ስለሆነ በክርስትና ሃይማኖት ትምህርት ውስጥ ከፍተኛ ትኩረት የሚሰጠው የትምህርት ዓይነት ነው፡፡ እግዚአብሔር እጅግ መልካም አድርጎ በፈጠረው ዓለም ውስጥ፣ ኃጢአት የአፍራሽነት ኃይሉ አደገኛ በመሆኑ በፈጣሪ ዘንድ በቀላሉ የሚ ታይ ሁኔታ አልነበረም፡፡ ይህም ኃጢአት፣ መልካሙን ዓለም ፈጽሞ ከማጥፋቱ በፊት እግዚአብሔር ኃጢአትን ለማስወገድ አንድ ልጁን ወደ ዓለም ላከ (ዮሐ. 1፥29፤3፥16)፡፡ ከዚህ ቀጥሎ የምንማራቸው አንቀጾች ይህንን ኃጢአት ለማስወገድ ስለ መጣው ስለ ልጁ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስና ስለ ማዳን ሥራው ይሆናል፡፡

www.ethiopianorthodox.org

## አንቀጽ ፪

### "ዓለም ሳይፈጠር ከእርሱ ጋር በነበረ የአብ አንድ ልጅ በሚሆን በአንድ ጌታ በኢየሱስ ክርስቶስም እናምናለን።"

በአንቀጽ ፩ አንድ አምላክ እግዚአብሔር አብ ሁሉን የያዘና ሁሉን የፈጠረ መሆኑን ከማመንና ከመመስከር ጋር ገልጸናል። ከአንቀጽ ፪ ጀምሮ እስከ አንቀጽ ፯ ድረስ ደግሞ አንድ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የአብ አንድ ልጁ፣ ዓለም ሳይፈጠር ከእርሱ ጋር የነበረ፣ በእርሱም ዓለምን የፈጠረ፣ በኋላም ዓለምን ያዳነ መሆኑን አምነን የምንማርበት ክፍል ነው። ስለ ማዳን ሥራው ከመግለጻችን በፊት ክርስቶስ ከእግዚአብሔር ጋር ያለውን መለኮታዊ ግንኙነትና አንድነት እንመለከታለን። ክርስቶስ በእውነት የእግዚአብሔር አንድ ልጁ እንደሆነ እናምናለን። ለእንደዚህ ያለ እምነት መሠረታችን ራሱ ክርስቶስ ነው። አብንና ወልድን ማንም ሊያውቅ አይችልም፣ እርሱ ራሱ ወልድ ከገለጸለት በቀር (ማቴ.11፥27)። ስለዚህ እግዚአብሔር፥ ልጅ እንዳለው እርሱም ሰውን ለማዳን ከሰማይ እንደ ወረደና እንደ ተወለደ የምናውቀው እውቀትና እምነት ከእርሱ ከክርስቶስ መለኮታዊ መገለጥ የተገኘ ነው። ይህም መገለጥ በደቀ መዛሙርቱ ዘንድ ስለ ታወቀ በእግዚአብሔር ልጅ ለማመን በቁ።

ከክርስቶስ መገለጥ በፊት የደቀ መዛሙርቱ እምነት እንደ ሌሎች አይሁዶች አንድ አካል አንድ ገጽ ነው ብለው በሚያምኑት በአንድ አምላክ ብቻ እንጂ አምላክ ወልደ አምላክ መኖሩን አያውቁም ነበር። ነገር ግን ጌታ ራሱን እውነተኛ የእግዚአብሔር ልጅ እንደ ሆነ ለደቀ መዛሙርቱ ስለ ገለጸላቸው እነርሱም የእጁን ታምራት ከማየታቸው የቃሉን ትምህርት ከመስማታቸው ሌላ በታቦር ተራራ ላይ እግዚአብሔር በብሩኅ ደመና ተገልጾ የክርስቶስን ልጅነት የመሰከረውን ቃል በመስማት፣ ክብሩን በመመልከትና ግርማ መለኮቱን በማየት ሊያምኑና ሊያውቁ ችለዋል። ከዚያም በኋላ ትንሣኤውንና ዕርገቱን በማየታቸው ክርስቶስ እውነተኛ አምላክ ወልደ አምላክ መሆኑን የዓይን ምስክሮች በመሆን በመንፈስ ቅዱስ ኃይል የክርስቲያን ሃይማኖት መሥራቾች ለመሆን በቅተዋል። እንግዲህ የሃይማኖታችን ሥረ መሠረት እንደ ሐዋርያው ጴጥሮስ ምስክርነት "ክርስቶስ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ" እንደሆነ ማመን ነው (ማቴ. 16፥16፤ 2ጴጥ.1፥16-18)። ለሃይማኖታቸው ቀናዒ የነበሩት አይሁዳውያን እንኳን ከነበረው መንግሥት ጋር በመተባበር ይህን እምነት ለማጥፋት ቢሞክሩ ጥፋቱ በራሳቸው ላይ እንደ መጣ በታሪክ የተመዘገበ ነው። እስጢፋኖስም በታላቁ በአይሁድ መሪዎች ሸንጎ ስለ ክርስቶስ ሲመሰክር "ሰማያት ተከፍተው የሰው ልጅም በእግዚአብሔር ቀኝ ቆሞ" እንዳየው ቢናገር በድንጋይ ወግረው ገድለውታል (የሐዋ.7፥54-60)። ምስክርነቱን የሰሙ አይሁድ ለሰማይ ደጅ ለእግዚአብሔር ልጅ አበጀለት በማለት አንድ አካል አንድ ገጽ ነው ብለው የሚያምኑትን አምላካቸውን የሚቃወም ስለ መሰላቸው እርሱን ገድለው በኢየሩሳሌም በነበረችው ቤተ ክርስቲያን ላይ ታላቅ ስደት አድርገዋል። "ሁሉም ከሐዋርያትም በቀር ወደ ይሁዳና ወደ ሰማርያ አገሮች ተበተኑ" (የሐዋ.8፥1)። ቤተ ክርስቲያንም ከአይሁድ ሃይማኖት ተለይታ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ ዓለምን ያዳነ እርሱ ብቻ እንደሆነ እያስተማረች፣ እያሳመነችና እያጠመቀች በዓለሙ ላይ ሁሉ ተስፋፋች እንጂ አልጠፋችም።

እንግዲህስ በእግዚአብሔር ልጅ በክርስቶስ ያለንን እምነት እናጸናለን። እንደ ተጻፈው፦ እርሱ መንገድም እውነትም ሕይወትም እንደሆነ እናምናለን (ዮሐ.14፥6)። የእግዚአብሔር ልጅ እውነት እንደሆነና እውነትም እርሱ እንደሆ



ነ ያሳወቀን ክርስቶስ መሆኑን ሐዋርያው ዮሐንስ እንደ ሚከተለው ያስረዳናል። "የእግዚአብሔር ልጅ እንደመጣ፣ እውነተኛም የሆነውን እናውቅ ዘንድ ልቡናን እንደ ሰጠን እናውቃለን፣ እውነተኛም በሆነው በእርሱ አለን፣ እርሱም ልጁ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። እርሱ እውነተኛ አምላክና የዘላለም ሕይወት ነው" (1ዮሐ.5፥20)። ሰዎችን ለማዳን ወደ ዓለም የመጣው ክርስቶስ የእግዚአብሔር አንድያ ልጁ እንደሆነ ይኸው ሐዋርያ ጽፏል (ዮሐ.3፥16)። ተቀዳሚ ተከታይ የሌለው የአብ አንድ ልጁ እንደሆነ ከዚሁ ጥቅስ ለመረዳት እንችላለን። ሌሎች የእግዚአብሔር ልጆች ቢባሉ በጸጋ ያገኙት ልጅነት ነው፣ ክርስቶስ ግን የአብ የባሕርይ ልጁ ነው። ስለዚህ ነው በአንቀጽ ፪ ክርስቶስ የአብ አንድ ልጁ እንደሆነ የተገለጸው።

ወንጌላዊ ዮሐንስም ክርስቶስ ከሥነ ፍጥረት በፊት ከእግዚአብሔር ጋር የነበረ ቀዳማዊ ቃል መሆኑን ገልጾ ጽፏል። እግዚአብሔር በመጀመሪያ ሰማይንና ምድርን በቃሉ ከመፍጠሩ በፊት በመጀመሪያ ቃል እንደ ነበረ በዮሐንስ ወንጌል መጀመሪያ ላይ ተጽፏል። ቃል ሲባልም ዝርው ቃል ሳይሆን እውነተኛ አካላዊና መለኮታዊ ቃል ማለት ነው። በጽርዕ ቋንቋ "ሎጎስ" ይባላል፣ ትርጉሙም ቃል ማለት ሲሆን ጥበብን ወይንም አእምሮን ይጨምራል። እንግዲህ ክርስቶስ "ሎጉስ" ይባላል፤ የእግዚአብሔር ቃሉ፣ ጥበቡ፣ ኃይሉ ለማለት ነው።

እርሱም ከእግዚአብሔር ጋር የነበረው ቀዳማዊ ቃል ነው። "በመጀመሪያው ቃል ነበረ፣ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ፣ ቃልም እግዚአብሔር ነበረ። ይህ በመጀመሪያው በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ" በማለት ወንጌላዊው ዮሐንስ፣ ክርስቶስ ቀዳማዊ ቃል እንደነበረ፣ እርሱም እግዚአብሔር እንደሆነ በማያሻማ መንገድ ገልጾልናል (ዮሐ.1፥1-2)።

## አንቀጽ ፫

### "ከብርሃን የተገኘ ብርሃን፥ ከእውነተኛ አምላክ የተገኘ አምላክ የተፈጠረ ያይደለ የተወለደ በመለኮቱ ከአብ ጋር የሚተካከል"

#### ሀ) ክርስቶስ ከአምላክ የተገኘ አምላክ ነው።

ክርስቶስ ከእውነተኛ አምላክ የተገኘ ስንል የተወለደ ማለታችን ነው፤ ተወለደን ለማስረዳት ደግሞ ተገኘ እንላለን። የመወለድና የመውለድን ሥርዓት ከሥነ ፍጥረት ተምረናል። የሰው ልጆች ብቻ ሳይሆኑ እንስሳትም አእዋፍም ሁሉ በመውለድ በመዋለድ የተገኙ እንደሆኑ እናውቃለን። በዚህም እውቀታችን መውለድ ማለት አንድ ነገር ከአንድ ነገር መገኘቱን ያመለክታል። የተገኘው ነገር ያስገኘውን መስሎና አህሎ ይታያል። ወላጅ ልጅን ያስገኛል። ልጅም ከወላጅ ይገኛል። ልጅም ሲወለድ የወላጁን ባሕርይና አካል ይዞ አባቱን ያክላል፣ አባቱን ይመስለዋል። ስለ ሰው ተፈጥሮ ልደት ሁኔታ ይኸን ያህል እናውቃለን። ነገር ግን ስለ ሰው ልደት አንዱ ከአንዱ እንዴት ይገኛል? የሚለውን ጥያቄ ከሥነ ሕይወት ተመራማሪዎች የተገኘውን ከማስተጋባት በቀር እነርሱም ሆኑ ሌሎች ከዚያ አልፈው የተፈጥሮን ምሥጢር እስከ መጨረሻው ለማወቅ ያዳግታቸዋል።

በመሠረቱ የሰው ልደት ከመለኮት ረቂቅ ልደት ጋር የሚነፃፀር ሆኖ አይደለም፤ ለሰው በሚገባው ቋንቋ፣ በሚያውቀው ነገር ለመግለጽ ያህል ነው እንጅ። የሰው ልደትም እንኳ ቢሆን ምን ያህል ረቂቅ እንደ ሆነ ለማስገንዘብ

www.ethiopianorthodox.org

ጭምር ነው፡፡ የወልድ ከአብ መገኘት ከፀሐይ እንደ ሚፈነጠቅ ጮራ ነው ብለን በምሳሌ ብንናገር እንኳ ይህም ከምሳሌነት አልፎ እውነታውን ወይም አማናዊውን ረቂቅ ልደት ይገልጸዋል ማለት አንችልም፡፡ ሆኖም ቋንቋ እስከ ፈቀደልን ድረስ ወልድ ከአብ እንደ ተገኘ እንናገራለን፡፡ ወልድም በረቂቅ ልደቱ አብን አህሎና መስሎ ከአብ እንደ ተገኘ በሰው ቋንቋና ምሳሌ እናስረዳለን፡፡ ክርስቶስ፣ የእግዚአብሔር የክብሩ ነፀብራቅ መሆኑ ስለ ተጻፈ ከብርሃን የተገኘ ብርሃን እንደ ሆነ እንመሰክራለን (ዕብ.1፥3)፡፡

ስለዚህ ክርስቶስ በቀዳማዊ ልደቱ ከእውነተኛው አምላክ የተገኘ ወልደ አምላክ መሆኑን እናምናለን፡፡ ክርስቶስ ቅድመ ዓለም ከእግዚአብሔር ጋር የነበረ አካላዊ ቃል እንደ ሆነና በእርግጥም ከእርሱ እንደ ተወለደ ቅዱሳት መጻሕፍት ይመሰክራሉ፡፡ በመዝሙረ ዳዊት "ከአጥቢያ ኮከብ አስቀድሞ ከሆድ ወለድኩህ" የሚለው ቃል የወልድን ቀዳማዊ ልደት ይመሰክራል (መዝ.109፥3)፡፡ "ከሆድ ወለድሁህ" ሲል አካል ዘእምአካል ባሕርይ ዘእምባሕርይ መወለዱን ያስረዳናል፡፡ ይህም ማለት ወልድ ከእግዚአብሔር አብ መለኮታዊ ባሕርይ የተወለደ ከረቂቅ አካሉ የተገኘ ማለት ነው፡፡ አለበለዚያማ በጥሬ ንባቡ ብቻ የምንነዳ ከሆነ እግዚአብሔር ግዙፍ፣ ግሡሥ አካልና ሥጋዊ ሆድም ያለው ያስመስልብን የለምን? እንደዚህም ብሎ ማሰብ ድንቁርና ወይም ድፍረት ከዚያም ካለፈ ስድብና ኃጢአት ይሆናል፡፡

እግዚአብሔር በመለኮቱ አይታወቅም፣ አይመረመርም ስንል አትማሩ፣ አትመርምሩ ለማለት ሳይሆን በሰው አእምሮ ተመርምሮ የማይደረስበት ረቂቅና ጥልቅ መሆኑን ለማሳሰብና ስለ መለኮታዊ ልደትም መመራመር ከተፈጥሮ አስተሳሰባችን በላይ መሆኑን ለማስገንዘብ ነው፡፡ እግዚአብሔር ፍጹም የሆነ ረቂቅ መንፈስ ነው፡፡ ከመንፈስም የሚወለድ መንፈስ ነው፡፡ ከሥጋም የሚወለድ ሥጋ ነው (ዮሐ.3፥6)፡፡

ከብርሃን የሚገኝ ብርሃን እንጂ ሌላ ያልታወቀ፣ ብርሃን ያልሆነ እንግዳ ነገር አይወጣም፡፡ ከእውነተኛ አምላክም የሚገኝ አምላክ ቢባል እንጂ ሌላ ፍጥረት ሊሆን አይችልም፡፡ ታዲያ ለምንድነው አርዮስና ተከታዮቹ ወልድን እንደ ፍጡር የተመለከቱት? አርዮስ፥ ወልድ ከእግዚአብሔር የተወለደ የእግዚአብሔር ቃል አንደሆነ አያውቅምን? ይህ አካላዊ ቃል ዓለም ሳይፈጠር፣ ዘመን ሳይቆጠር ከእግዚአብሔር ጋር እንደ ነበረና ቃልም እግዚአብሔር እንደ ሆነ አላነበበምን? (ዮሐ.1፥1-2) ማንበብስ አንብቧል፤ እውነተኛውን ቃል አልተረዳውም እንጂ፡፡ አካላዊ ቃሉንም ስላላወቀው ንባቡ ሁሉ ዝርው ቃል ሆኖበት ተቸግሮ ይሆናል፡፡ ምናልባትም በማይጠቅም ምርምሩ ጥበብን ሲፈልግ የእግዚአብሔር ቃል መለኮትነት ተሠውሮበት ይሆናል፡፡ አርዮስ "ወልድ ፍጡር በመለኮቱ" ሲል ምን ማለቱ ነው? ይህ አባባል በአንድ በኩል ወልድ መለኮትነት እንዳለው ያመለክታል፤ በሌላ በኩል ደግሞ ይኸው መለኮት ፍጡር እንደሆነ ያስረዳል፡፡ ኧረ ለመሆኑ የመለኮት ፍጡር አለውን? ይህ ራሱን በራሱ የሚቃረን ጤናማውን የክርስትና ትምህርት የሚፃረር ስለ ሆነ ከቤተ ክርስቲያን ውጭ ከተጣለ ዘመናት አልፈዋል፡፡ ከ325 ዓ.ም. ጀምሮ ዛሬም በዓለም አብያተ ክርስቲያናት ጉባኤ የአርዮስ ትምህርት እንደተወገዘ ይገኛል፡፡ ሆኖም ተከታዮቹ ዛሬም ስላሉ ነገራቸውን ሳንንቅ በትጋት መከላከል ይኖርብናል፡፡

እንግዲህ በሃይማኖታችን ጸንተን እንቁም፡፡ ከአምላክ የተገኘ አምላክ መሆኑን እናምናለን፡፡ ክርስቶስ ከአምላክ የተገኘ አምላክ ነው፡፡ ክርስቶስ ከአብ ባሕርይ ዘእምባሕርይ አካል ዘእምአካል የተገኘ ስለሆነ ፍጹም መለኮት ነው፡፡ ክርስቶስ የተወለደ እንጂ የተፈጠረ አይደለም፡፡



ስለዚህ ወልድ ፍጡር በመለኮቱ ማለትን እናወግዛለን፡፡ ወልድ በመለኮቱ ፈጣሪ እንደሆነ እናምናለን፡፡

## ለ) ክርስቶስ በመለኮቱ ከአብ ጋር ስለ መተካከሉ

እስካሁን እንደ ገለጽነው ከአንድ ነገር የተገኘው ነገር ያንኑ አስገኚውን መስሎና አህሎ በመገኘቱ ከአስገኚው ጋር ያለውን እኩልነት ያመለክታል፡፡ ምንም በጊዜ ቢቀዳደሙ በሥነ ፍጥረት እንደ ምናየው ልጅ ከአባቱ ጋር በተፈጥሮ እኩል ነው፡፡ እንደዚሁም ወልድ በመለኮቱ ከአባቱ ጋር እኩል ነው፡፡ ሆኖም እንደ ምድራዊ አባትና ልጅ በጊዜ መቀዳደም የለባቸውም፡፡ ምክንያቱም የወልድ ቀዳማዊ ልደት ዓለም ሳይፈጠር ዘመን ሳይቆጠር አስቀድሞ ስለነበረ ነው፡፡ ከሥነ ፍጥረት በፊት ቦታም የለም፣ ጊዜም የለም፡፡ ስለዚህ ዘመናት ሳይኖሩ ስለ ጊዜ ቅደም ተከተል መናገር አይቻልም፡፡ ስለዚህ ነው አባቶች "አሐቲ ቅድምናሆሙ ለሥሉስ ቅዱስ" በማለት አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ያለ ጥንትና ያለ ዘመን የሚኖሩ፣ ከመካከላቸው ወደ ኋላ የሚቀር የሌለ፣ ቅድምናቸውም አንዲትና እኩል መሆኑን የሚመሰክሩት፡፡

የአንቀጽ ፫ ቃለ ሃይማኖት እንደ ሚያመለክተን ከብርሃን የተገኘ ብርሃን ነው በማለት ተገልጿል፡፡ ይህም ማለት አባት ብርሃን ልጅ ብርሃን ማለት ነው፡፡ ሁለቱም ብርሃን ናቸው፡፡ ስለዚህ ሁለቱም እኩል ናቸው፡፡ "እግዚአብሔር የሁለቱም ብርሃንነት በቅዱሳት መጻሕፍት የተመሰከረ ነው፡፡ "እግዚአብሔር ብርሃን ነው" ይላል (1ኛዮሐ.1፥5)፡፡ በተለይም ክርስቶስ ጨለማውን ለማጥፋት ወደ ዓለም የመጣ የሕይወት ብርሃን፣ እውነተኛ የዓለም ብርሃን መሆኑ ተጽፏል (ዮሐ.1፥4-9፤ 3፥19፤8፥12፤ 9፥5፤12፥46)፡፡ እንግዲህ አብም ወልድም ሁለቱም ብርሃን ናቸው እኩልም ናቸው ብለን እናምናለን፡፡ አብና ወልድ በመለኮት አንድነትና እኩልነት እንዳላቸው በምንጭ ውኃና በወራጅ ወንዝ መስለው አባቶች እንዳስተማሩን ወንዙ ከምንጬ ይገኛል፡፡ ከምንጩ የሌለ ውኃ ከወንዙም የለም፡፡ ሁለቱም አንድ ዓይነት ውኃ እንደሆኑ የታወቀ ነው፡፡ እንደዚሁም አብና ወልድ በመለኮት አንድ ናቸው፣ እኩልም ናቸው፡፡ የሕይወት ምንጭ፣ የሕይወት ውኃ ናቸው፡፡

ስለ አብና ወልድ አንድነትና እኩልነት ራሱ ክርስቶስ በቃልም በተግባርም ገልጿል፡፡ "እኔና አብ አንድ ነን" በማለቱ ፍጹም አንድነታቸው ታውቋል፡፡ ፍጹም አንድነትም ፍጹም እኩልነት ነው፡፡ ያለ እኩልነት እውነተኛ አንድነት የለምና (ዮሐ.10፥30)፡፡ "እኔን ያየ አብን አይቷል" በተባለው መሠረት የክርስቶስ ትምህርቱን፣ ታምራቱን፥ ባሕርዩን፥ በጠቅላላውም መለኮታዊ ሥራውን ያዩና የተረዱ ደቀ መዛሙርቱ አብን በወልድ ሕልው ሆኖ ሲሠራ እንዳዩት ይቆጠራል ማለት ነው (ዮሐ.14፥9)፡፡ ይህም ማለት የወልድን ብርሃንነት ካየህ የአብን ብርሃንነት አይተሃል ማለት ነው፡፡ የወልድን መለኮታዊ ሥራ ከተመለከትህ እንደዚሁም የአብንም ተመልክተሃል ማለት ነው፡፡ይህም ወልድ ከአብ ጋር እኩል መሆኑን ያስረዳል፡፡ " የአብ የሆነው ሁሉ የእኔ ነው" በማለት ክርስቶስ የተናገረው ቃል የሚያስረዳን፣ የአብ የሆነው ባሕርይ የወልድ ባሕርይ ነው፣ የአብ መለኮትነት የወልድም ነው፣ የአብ ሥልጣንና ግዛት የወልድም ሥልጣንና ግዛት መሆኑን ያመለክተናል፡፡ እኩልነት ማለትም ይኸው ነው፡፡ ከዚህ የበለጠ ወይም ያነሰ ከሆነ እኩል ሊባል አይቻልም (ዮሐ.16፥15)፡፡

ክርስቶስ ከአብ ጋር ያለውን እኩልነት ሲያስተምር የሰሙ አይሁድ [illegible]ኗል በማለት በድንጋይ ሊወግሩት እንደ ተነሡ ተጽፏል

www.ethiopianorthodox.org

(ዮሐ.10፥31-39)፡፡ ይህ ሁሉ የአይሁድ ተቃውሞ የሚያስረዳን ጌታችን ምን ያህል ራሱን ከአብ ጋር እኩል በማድረግ ለደቀ መዛሙርቱ ብቻ ሳይሆን ለሕዝብ ሁሉ በይፋ መግለጹን ነው፡፡

## ጌታ በሥጋ ባሕርይ ራሱን ዝቅ ማድረጉ

ክርስቶስ በመለኮቱ ከእግዚአብሔር ጋር የተስተካከለ ሲሆን፣ በኃጢአት ፍዳ የተያዙትን የአዳምን ዘር ሁሉ ከወደቁበት ለማንሣት የሞቱትንም ለማዳን የፍጡርን ሥጋ በመዋሐዱ ራሱን ዝቅ አድርጓል፤ የተዋረደውንም የአገልጋዩን የባሪያውን መልክ ይዟል፡፡ ስለዚህ ክርስቶስ በመለኮቱ ከአብ ጋር እኩል በመሆኑ ፍጹም አምላክ ነው ብለን እናምናለን፤ የፍጡርንም ሥጋ በመዋሐዱ ደግሞ ከኃጢአት በስተቀር ፍጹም ሰው መሆኑን እናምናለን፡፡ የፈጣሪና የፍጡር ባሕርያት ማለት ሁለቱ የአምላክ ባሕርይና የሰው ባሕርይ ሳይለወጡ፣ ሳይለያዩ፣ ሳይቀላቀሉ፣ ሳይጠፋፉ በአንዱ በክርስቶስ አካል ተዋሕደዋል፡፡ ስለዚህም ክርስቶስ አንድ አካል አንድ ባሕርይ ነው በማለት የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ እምነታችንን እናስተምራለን፡፡

ከላይ እንደ ጠቀስነው ሰውን ለማዳን ሰው በመሆኑ ራሱን ዝቅ ያደረገው ክርስቶስ ከመለኮታዊው ባሕርዩም ዝቅ አለ ማለት አይደለም፡፡ ከእግዚአብሔር ጋር የሚያስተካክለው መለኮት የባሕርዩ ስለሆነ ክርስቶስ እኩልነት ገንዘቡና መብቱ እንጂ በግድ እንደ ሚወሰድ፣ "መቀማት እንደ ሚገባ ነገር" ሳይቆጥር ነገር ግን ሰው በመሆኑ ምክንያት ራሱን በፈቃዱ እንዳዋረደ ሐዋርያው ጳውሎስ እንደ ሚከተለው ገልጿል፡- "እርሱ [ክርስቶስ] በእግዚአብሔር መልክ ሲኖር ሳለ ከእግዚአብሔር ጋር መተካከልን መቀማት እንደሚገባ ነገር አልቆጠረውም፣ ነገር ግን የባርያውን መልክ ይዞ በሰውም ምሳሌ ሆኖ ራሱን ዝቅ አደረገ፡፡ በምስሉም እንደ ሰው ተገኝቶ ራሱን አዋረደ፣ ለሞትም ይኸውም የመስቀል ሞት እንኳ የታዘዘ ሆነ" (ፊልጵ.2፥6-8)፡፡

እንግዲህ ክርስቶስ በፈቃዱ ሰውን ለማዳን ራሱን ዝቅ አድርጎ ሰው በመሆኑና ከኃጢአት በስተቀር እንደ ሰውነቱ በነፍሱ የደረሰበትን የልብ ኀዘንና ትካዜ፣ በሥጋው የደረሰበትን ሕማምና ሞት፣ በጠቅላላው በምድር ሳለ የተቀበለውን ጸዋትወ መከራ በማስመልከት ክርስቶስን በመለኮቱ ከአብ ያነሰ አስመስሎ ማየት ታላቅ ስሕተት ነው፡፡ ምክንያቱም ክርስቶስ መከራና ውርደት፣ ሕማምና ሞት የደረሰበት በተዋሐደው ሰውነቱ እንጂ በመለኮቱ አይደለም፡፡ ይልቅስ እኛን ጉስቋሎችን ከኃጢአትና ከሞት ለማዳን ሲል ክርስቶስ በፈቃዱ ውርደትና መከራ እንደ ተቀበለ እያሰብን እግዚአብሔርን ማመስገን ይኖርብናል፡፡

ከእኔ አብ ይበልጣል በማለት ክርስቶስ የተናገረውን በመያዝ በስሕተት ትርጉም እንዳትስናከሉ መጠንቀቅ ያስፈልጋል (ዮሐ.14፥28)፡፡ ይህ አነጋገር የክርስቶስን አምላክነት አይመለከትም፡፡ ከላይ እንደ ጠቀስነው ክርስቶስ ራሱን ዝቅ አድርጎ በተዋሐደው ሥጋ በምድር ላይ ሳለ የነበረበትን የሰውነቱን ሁኔታ በማስመልከት የተነገረ ቃል ነው፡፡ "ክርስቶስ አባቴ ከእኔ ይበልጣል ቢል ይህ አነጋገር ሰው ለመሆኑ የሚስማማ ነው" በማለት ቅዱስ ቄርሎስ ያስረዳናል፤ ስለዚሁም ጉዳይ እንደ ሚከተለው ገልጿል፡፡ "ያልተፈጠረ፣ ዓለም ከመፈጠሩ በፊትም ሥጋ ያልነበረው እሱ፣ በኋላ ዘመን ሥጋ ባሕርዩ ሆነ፤ ፍጹም ሰው በመሆኑም በዚህ ሠልክ ሰው ተባለ፤ ስለዚህም በእውነት አባቱን ከእሱ የሚበልጥ ይለዋል፤ ስለመታመሙ፣ ስለመሞቱ ከመላእክት ጥቂት አነሰ ተብሎ የተነገረለት እሱ ነው፡፡ እሱ አባቱን በእውነት ከእኔ ይበልጣል ይለዋል፤ እሱ መላእክትን ፈጥሮ የሚገዛ ሲሆን ስለ ተዋሐደው ሥጋ ይህን ቃል ቢናገርም፣ በተዋሐደው በእግዚአብሔር ፊት እንዲህ አምላክ የተዋሐደው ሥጋን ከፍጡራን መካከል የሚተካከል ምንም የለም" (ሃይማኖተ አበው ገጽ 585)፡፡

እንግዲህ ክርስቶስ በዚህ ... ጊዜ ከእኔ አብ ይበልጣል



የለበት ምክንያቱ ፈተናና ችግር ሕማምና ሞት ያለበትን የተዋረደውን የፍጡርን ሥጋና ነፍስ መዋሐዱን ለማመልከት መሆኑን እያስተዋልን፣ እርሱ ግን በመለኮቱ ከአብ ጋር እኩል መሆኑን እንመን፡፡

በሥጋውማ እንኳን ከአብ ጋር ይቅርና ከመላእክትም ጥቂት እንዳነሰ ተነግሯል፡፡ እንደዚህ የተባለበትም ዋናው ምክንያት ስለ እኛ ስለ ሰዎች ሲል ሰው ሆኖ ሥጋ ለብሶ በፈቃዱ ሕማምና ሞትን የተቀበለበትን ምድራዊ ሕይወቱን የዕለተ ዓርብ ሥራውን ለመግለጽ ነበር፡፡ አሁን ግን በቀደመው ክብሩ ከባሕርይ አባቱ ጋር በእኩልነት ይገኛል፡፡ ሐዋርያው ጳውሎስ እንደ ጻፈው "በእግዚአብሔር ጸጋ ስለ ሰው ሁሉ ሞትን ይቀምስ ዘንድ፣ ከመላእክት ይልቅ በጥቂት አንሶ የነበረውን ኢየሱስን ከሞት መከራ የተነሣ የክብርና የምስጋናን ዘውድ ተጭኖ እናየዋለን" (ዕብ.2፥9)፡፡

ክርስቶስ ፍጹም አምላክና ፍጹም ሰው ሲሆን በተዋሕዶ አንድ አካል አንድ ባሕርይ መሆኑን ከሚያዘናጉ የትምህርት ዓይነቶች፣ የትርጓሜ ስሕተቶች መጠንቀቅ ይኖርብናል፡፡ ቅዱሳት መጻሕፍት አንድ ቦታ ስለ ክርስቶስ አምላክነት፣ ሌላ ቦታ ስለ ክርስቶስ ሰውነት የሚገልጹ አንቀጾች ስላሏቸው አስተውሎ ማንበብ፣ ጠይቆ መረዳት ያስፈልጋል፡፡ ክርስቶስ ስለ እኛ መዳን ራሱን ዝቅ አድርጎ ስለ ተዋሐደው ሥጋ ያደረገውንና የተናገረውን ቃል ለክርስቶስ መለኮታዊ ባሕርይ እንደ ተነገረ አድርጎ መተርጐምና መከራከር የአርዮሳውያን ደቀ መዛሙርት የስሕተታቸው መመሪያና ማስተማሪያ ዋና ዘዴያቸው መሆኑን አውቀን ራሳችንንና ሌሎችንም ከእንደዚህ ዓይነቱ ስሕተት መጠበቅ ክርስቲያናዊ ግዴታችን ነው፡፡

እንግዲህ እንዳንሳሳት ክርስቶስ በመለኮቱ ከአብ ጋር ለዘለዓለም እኩል መሆኑን በማመን፣ ይህንንም የሃይማኖታችን የማይለወጥ ሕግና መመሪያ አድርገን መቀበል አለብን፡፡ ስለ ክርስቶስ ባሕርይ በማወቅም ሆነ ባለማወቅ በስህተት የሚተረጉሙትን አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ከሌሎች ጥቅሶች ጋር በማገናዘብ ሐዋርያትና የእነርሱ ተተኪዎች አበው ቅዱሳን ለቤተ ክርስቲያን በሰጡዋት የሃይማኖት ውሳኔና መመሪያ መሠረት አቃንቶና አስተካክሎ መተርጐም ያስፈልጋል፡፡ ስለ አዳምና ልጆቹ አዝኖ፣ ክርስቶስ በሥጋ ባሕርይ ወደዚህ ዓለም መጥቶ በትሕትና አነጋገር ከአብ ተልኬ መጣሁ፣ ወልድ ከራሱ ሊያደርግ ምንም አይችልም፤ የሚሉትንና የመሳሰሉትን ቃላት ብትሰማ ወይም ቢነገርህ ክርስቶስ በባሕርዩ ሕፀፅ ማለት ጉድለት አለበት አትበል በማለት ቅዱስ ባስልዮስ እንደሚከተለው ይመክረናል፡፡

> "ዓለምን ለማዳን ፈጥሮ በተዋሐደው በሥጋ ስለ እኛ አዝኖ በሥጋ በመገለጡ ተልኬያለሁ፣ ከራሴ አንቅቼ ምንም ምን መሥራት አይቻለኝም፣ ዳግመኛ ትእዛዝ ተሰጥቶኛል እያለ ቢነግርህ፣ ስለዚህና ስለ ሚመስለውም ሁሉ ተቀዳሚና ተከታይ በሌለው በወልድ ባሕርይ ሕፀፅ አለበት አትበል፡፡ ነገር ግን ደካማ ባሕርያችንን ለማዳን ወደዚህ ዓለም ስለ መጣበት ትኅትናው የማይመረመር የማይወሰን ጌትነቱን ሕፁፅ ነው ልንል አይገባም፤ እንደ ጌትነቱ ገናንነት ባሕርዩን እንወቅ እንጂ፡፡ ሰው ሆኖ የተናገረውን እንመን፤ እኛን ለማዳን ስለ አደረገው ስለ ሥጋዊው ነውና፤ እንደ ጌትነቱ መጠን ልንናገር ብንወድ ይህንን ለመናገር ሥልጣን አናገኝም" (ሃይማኖተ አበው፣ ገጽ 113፥ዮሐ.5፥19-47፥ኢሳ.3፥6-15)፡፡

## ጌታ በሥጋ ሥርዓት አባቱን አምላኬ ማለቱ

እንግዲህ "የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ" የሚለውን ቃል ... በትንሣኤው እለት እንደ ተናገረው፣ "ወደ አባቴና

www.ethiopianorthodox.org

ወደ አባታችሁ ወደ አምላኬና ወደ አምላካችሁ ዐርጋለሁ" የሚለውን ስትመለከት ወይም ሌሎች ይህን የመሰሉ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን ስታነብ አስተውለህ መተርጐም አለብህ እንጂ ደረቁን ጥቅስ ብቻውን ይዞ መነዳት ከስሕተት ጉድጓድ ያገባል (ኤፌ.1፥17፤ ዮሐ.20፥17)። ቅርንጫፍ ብቻውን ከግንዱ ከተለየ ይደርቃል። እንደዚሁም መጽሐፍ ቅዱስ ግንድ ነው። የተተከለውም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ነው። ጥቅሶችም ቅርንጫፎች ናቸው። ስለዚህ ጥቅሶች ከጠቅላላው ምንባብ ጋር ተገናዝበው መተርጐም አለባቸው። ለእውነተኛው ትርጉምም የቤተ ክርስቲያን መምህራን ሙሉ ኃላፊነት እንዳላቸው አንዘንጋ።

እንግዲህ የክርስቶስ "አምላኩ" ወይም "አባቱ" የሚል ንባብ ስታገኝ እንዴት በሁለት ዓይነት ሁኔታ ተነገረ ብለህ በነገሩ አትደናገጥ፣ አትደናገርም። ወይም ደግሞ የክርስቶስ አምላኩ በሚልበት ጊዜ ክርስቶስን እንደ ዕሩቅ ብእሲ እንደ ማንኛውም ሰው ፍጡር አስመስለው ብለህ አታስብ። በመጀመሪያ ክርስቶስ ስንል አምላክ ብቻ አይደለም፤ ሰውም ብቻ አይደለም። ክርስቶስ ስንል ከሁለት አካል ከሁለት ባሕርይ ማለት መለኮትና ትስብእት ተዋሕደው አንድ አካል አንድ ባሕርይ የሆነ ሥግው ቃል ነው። ክርስቶስ ቅሉ አምላክና ሰው አንድ የሆኑበት የሥጋዌ ስም ነው። ከሥጋዌ በፊት ወልድ፣ የእግዚአብሔር አካላዊ ቃል ይባል ነበር። ይህ አካላዊ ቃል አምላክ ብቻ እንጂ በዚያን ጊዜ ሰው አልነበረም፤ ገና ሥጋ አልለበሰም ነበርና። በኋለኛው ዘመን ግን የሰውን ሥጋና ነፍስ ስለ ተዋሐደ፣ አምላክ ፍጹም ሰው ፍጹም አምላክ እንደ ሆነ ተነገረ። ሐዲስ ኪዳን ከሥጋዌ በኋላ የተጻፈ ስለ ሆነ የተዋሕዶ ባሕርይን ያንጸባርቃል። ስለዚህ ስለ ጌታ ማንነት በተነገረ ጊዜ በተዋሕዶ ምሥጢር አኳያ አስተውለህ ተርጉም።

ጌታ በትንሣኤው ዕለት ወደ አባቴ ወደ አምላኬ ዐርጋለሁ ያለው በምሥጢረ ተዋሕዶ ሲተረጐም፣ አባቴ ማለቱ ከቅድመ ዓለም ጀምሮ የነበረውን ያለውን የባሕርይ አባትነቱን ያሳያል። አምላኬ ሲል ደግሞ ድኅረ ዓለም ማለት በኋለኛው ዘመን ፈጥሮ የተዋሐደውን የሥጋና የነፍስን ማለት የሰውነትን ባሕርይ ገንዘብ ስላደረገ አምላኬ ሲል እናገኘዋለን። እንግዲህ ሁለቱንም ማለት አባቴና አምላኬ ያለበትን ምክንያት በተዋሕዶ የባሕርይ ምሥጢር መረዳት ይቻላል።

ስለዚህ ጉዳይ ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ የጻፈውን በማስተዋል እናንብበው። "እነሆ እርሱ ጳውሎስ አብን አምላኩ ለክርስቶስ አለው፤ በውኑ ወልድ ክርስቶስ በክብር ከአባቱ ያንሳልን? ከአብ አያንስም፤ ደፍሮ ይህን የሚናገር ማንም ሰነፍ የለም። መጽሐፍ ለአባቱ አንድ ልጅ እንደ መሆኑ እንደ አባቱ ክብር ያለ ክብሩን አየነው ያለ አይደለምን? (ዮሐ.1፥14 ፤ 14፥8-11 ፤ 1ኛቆሮ. 12፥3) ነገር ግን እርሱ በዚህ ክርስቶስ በእውነት ሰው እንደ ሆነ አስረዳ። ዳግመኛም በተነሣ ጊዜ ከዚህ ከአዳም ባሕርይ ሰው መሆኑን አስረዳ። ፈጽሞ ከእርሱ ወዳልተለየው ወደ አብም ከማረጉ አስቀድሞ ለደቀ መዛሙርቱ አምላኬ አምላካችሁ አለ። ይህን በሰሙ ጊዜ ይህን የተናገረ ሥጋ ብቻ እንዳይመስላችሁ፤ ሰው የሆነ እርሱ እግዚአብሔር ቃል አስቀድሞ አቡየ ብሎ፣ ከዚህ በኋላ አምላኪየ አለ እንጂ (ዮሐ.20፥17)። እኔ ሰው የሆንኩ አምላክ ነኝ እኔም አንድ ነኝና ይህንንም ያንንም፣ እኔ እላለሁ ይላል፤ የሰውን ባሕርይ ገንዘብ አድርጌዋለሁና፤ ኃጢአት የሌለበት እርሱ፣ እኔ ነፍስን ሥጋን በእውነት ተዋሕጄአለሁና። ከእኔ ጋር አንድ አካል፣ አንድ ባሕርይ ላደረግሁት ለሥጋ ሥርዓት እንደሚገባ እንዲህ አባቴን፣ አምላኪየ ብዬ ጠራሁት ይላል" (ሃይማኖተ አበው፣ ገጽ 247-248)።

ይህ ዓይነት የተርጉም ስልት የሚያስፈልጋቸው ሌሎች ጥቅሶች አሉ። እነርሱን ሁሉ እየጠቀስን ከቅዱሳት መጻሕፍት እያገናዘብን እንዳንተረጉማቸው ይበዛብናል። ስለዚህ ከዚህ በላይ እንደ ገለጽነው በምሥጢረ ተዋሕዶ የትርጉም ስልት እየተጠቀማችሁ፣ በሃይማኖተ አበው የእምነት ድንጋጌና መመሪያ መሠረት በጥንቃቄና በማስተዋል መጽሐፍ ቅዱስን እያነበባችሁ እንድትተረጉሙ ያስፈልጋል። በትርጉም እንዳትሳሳቱ የቤተ ክርስቲያንን ሊቃውንት ጠይቆ መረዳት መብታችሁና



ግዴታችሁም ነው።

እንግዲህ ክርስቶስ የወደቀውን የሰው ዘር ከፍ ለማድረግ በለበሰው ሥጋ ራሱን ዝቅ አደረገ። በመለኮቱ ግን ዝቅ ማለት የለበትም። ምክንያቱም የአብና የወልድ መለኮታዊ ባሕርይ አንድ ስለሆነ የማይነጣጠልና የማይከፋፈል አንድነት ስላላቸው ነው። አብ ብርሃን ሲሆን ከአብ የተገኘው ወልድም ብርሃን ነው ማለት ነው። ስለዚህ ሁለቱም አንድ መለኮታዊ ብርሃን ናቸው፤ እኩልም ናቸው።

## አንቀጽ ፬

## "ሁሉ በእርሱ የሆነ፣ ያለ እርሱ ግን ምንም ምን የሆነ የለም፣ በሰማይም ያለ በምድርም ያለ"

በሥነ ፍጥረት ታሪክ በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይና ምድርን እንደ ፈጠረ ተምረናል (ዘፍ.1፥1)። "እግዚአብሔር" የሚለው ቃል የአብ የወልድ የመንፈስ ቅዱስ የአንድነት ስማቸው ነው። ስለዚህ እግዚአብሔር ፈጠረ ስንል ሦስቱም በአንድነት እንደ ፈጠሩ እናስተውላለን። በመፍጠር፣ በመሥራት፣ በመግዛትና በመሳሰሉት ሦስቱም አንድ ናቸው። በመፍጠር ሦስቱም በአንድነት መሆናቸውን ለመግለጽ "ሰውን . . . እንፍጠር" የተባለውን ኃይለ ቃል መሠረት በማድረግ በምሥጢረ ሥላሴ ተምረናል (ዘፍ. 1፥26)። "ብርሃን ይሁን" በማለት እግዚአብሔር ብርሃንን በቃሉ እንደ ፈጠረ ተጽፏል (ዘፍ.1፥3)። በቃሉ ፈጠረ ስንል እግዚአብሔር አብ በወልድ ማለት በአካላዊ ቃሉ ሕልው ሆኖ ሁሉን ነገር ፈጠረ ማለት ነው። ቃል የተባለ እግዚአብሔር ወልድ በኋለኛው ዘመን ሰው የሆነው እርሱ ክርስቶስ እንደ ሆነ ተጽፏል (ዮሐ.1፥1-14)። ቃልም እግዚአብሔር በመሆኑ ከሥነ ፍጥረት በፊት ከእግዚአብሔር ጋር ስለነበረ፣ ዓለም የተፈጠረው፣ ሰማዮችም የጸኑት በእርሱ ነው። "በእግዚአብሔር ቃል ሰማዮች ጸኑ"፤ "የሰማይም ጠፈር የእጁን ሥራ ያወራል" ተብሎ ተጽፏል (መዝ.18፥1 ፤ 32፥6)። በጥቅሱ ውስጥ "በእግዚአብሔር ቃል" ወይም "እጅ" ሲባል የወልድን ስምና ተግባር ያስረዳናል።

የአብ አካላዊ ቃል ወልድ ሁሉን እንደ ፈጠረ፣ የሕይወትም ባለቤት እንደ ሆነ ዮሐንስ ወንጌላዊ ምስክርነቱን እንደ ሚከተለው ጽፏል። "ሁሉ በእርሱ ሆነ፣ ከሆነውም አንዳች ስንኳ ያለ እርሱ አልሆነም። በእርሱ ሕይወት ነበረች፣ ሕይወትም የሰው ብርሃን ነበረች" (ዮሐ.1፥3-4)። ስለ ክርስቶስ ፈጣሪነት ሐዋርያው ጳውሎስም እንደ ሚከተለው ይመሰክራል። "እርሱም የማይታይ አምላክ ምሳሌ ነው፤ የሚታዩትና የማይታዩትም፣ ዙፋናት ቢሆኑ ወይም ጌትነት ወይም አለቅነት ወይም ሥልጣናት፣ በሰማይና በምድር ያሉት ሁሉ በእርሱ ተፈጥረዋልና " (ቆላስ.1፥15-16)።

የወልድ ፈጣሪነት በቅዱሳት መጻሕፍት የተረጋገጠ፣ በቅዱሳን አባቶች የተመሰከረ ሲሆን ሳለ፣ አርዮስ ግን "ሁሉ በእርሱ ሆነ" ከሚለው አንቀጽ ውስጥ "በእርሱ" የሚለው ቃል "መሣሪያነትን" ያመለክታል በማለት ፈጣሪ ፈጠረበት እንጂ ወልድ ፈጣሪ አይደለም ሲል በሐሰት ያሰማውን ክሕደት ሳትከፋፈል የነበረችው ዓለም አቀፋዊትና ሐዋርያዊት ቤተ ክርስቲያን አውግዛ ከአንድነቷ ከማኅበርዋ ለይታዋለች። ዛሬም የአርዮስ ተከታዮች ስማቸውን፣ ዝክራቸውንና ታሪካቸውን ለውጠው ክህደታቸውን በልዩ ልዩ ስያሜና አገላለጽ እያስፋፉ ስለሆነ የሐሰት ትምህርታቸውን እንደ ወደቀና እንደ ረከሰ ነገር ቈጥሩት እንጂ ክፉውን ሐሳብ አታስተናግዱ፣ አትወያዩበትም። ምክንያቱም

www.ethiopianorthodox.org

ከእንደዚህ ዓይነት መናፍቃን እንድንርቅ ሐዋርያው ጳውሎስ እንደሚከተለው አስጠንቅቆናል:: “ምርመራን በቃልም መዋጋትን እንደ በሽተኛ ይናፍቃሉ፤ ከእነዚህም ቅንዓትና ክርክር ስድብም ክፉ አሳብም እርስ በርስ መናደድም ይወጣሉ፣ አእምሯቸውም በጠፋባቸው እውነትንም በተቀሙ፣ እግዚአብሔርን መምሰል ማትረፊያ የሚሆን በመሰላቸው ሰዎች ይገኛሉ:: እንደነዚህ ካሉት ራቅ” (1ጢሞ.6፥4-5):: እንግዲህ ከጥንት ጀምሮ ዛሬም የክርክር ሱሰኞች፣ ሃይማኖትን ለጥቅም ማግኛና ገንዘብን ማትረፊያ የሚያደርጉ እንዳሉ እወቁ፤ ከእነርሱም ራቁ::

ሐዋርያው ጳውሎስ ስለ እንደዚህ ዓይነት ሰዎች እምነት ሲናገር “የአምልኮት መልክ አላቸው ኃይሉን ግን ክደዋል፤ ከእነዚህ ደግሞ ራቅ” ይላል:: ስለ ሥራ ስልታቸው ሲገልጽ “ወደ ቤቶች ሾልከው እየገቡ፣ ኃጢአታቸው የተከመረባቸውን በልዩ ልዩ ምኞትም የሚወሰዱትን ሁልጊዜም እየተማሩ እውነትን ወደ ማወቅ ሊደርሱ ከቶ የማይችሉትን ሞኞችን ሴቶች የሚማርኩ ከእነዚህ ዘንድ ናቸውና” በማለት የጻፈው የጊዜያችንን መናፍቃን አቋምና የአሠራር ዘዴ የሚያሳይ ስለ ሆነ ይህንን ጥቅስ መመሪያ በማድረግ ከእነርሱ መራቅ ይኖርብናል (2ኛ ጢሞ.3፥5-7)::

እግዚአብሔር አብ አንድ ልጁን ወደ ዓለም ልኮ ዓለምን “በእርሱ” እንዳዳነ ተጽፏል (ዮሐ.3፥16):: “በእርሱ” የሚለው ቃል በመፍጠር ብቻ ሳይሆን በማዳን ሥራ ውስጥም አለ:: ታዲያ ክርስቶስ “መሣሪያ” ብቻ እንጂ “አዳኝ” አይደለም ማለት አይቻልም:: እንደዚሁም ከእግዚአብሔር ባሕርይ በተገኘው በወልድ ቃልነት ዓለሞች እንደ ተፈጠሩ ማለት ሁሉ ነገር በእርሱ እንደ ሆነ ስንናገር የወልድን መሣሪያነት ሳይሆን የወልድን ፈጣሪነት ያስረዳናል:: እንግዲህ በሥነ ፍጥረት ውስጥ በመሣሪያነት ሳይሆን በፈጣሪነት፣ ዓለምን በማዳን ሥራ ውስጥም በመሣሪያነት ሳይሆን በአዳኝነት ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ሁሉ ነገር በወልድ በክርስቶስ እንደ ሆነ ያለ እርሱም ምንም ምን እንዳልሆነ እናምናለን:: እንደ አርዮሳውያን ትርጓሜ “በእርሱ” የሚለው ቃል መሣሪያነትን ብቻ የሚያሳይ ከሆነ ክርስቶስ መሣሪያ እንጂ አዳኝና የዓለም መድኃኒት እንደሆነ አያምኑም ማለት ነው:: ምናልባት የክርስቶስን ፈጣሪነት እንጂ አዳኝነቱንስ እናምናለን የሚሉ ይኖሩ ይሆናል:: አልሸሹም ዞር አሉ እንደ ተባለው ክርስቶስ ፈጣሪ አምላክ መሆኑን ከካዱ ታዲያ ፍጡር እንዴት አድርጎ ዓለምን ሊያድን ይችላል? ሟች የሆነ ፍጡር እንዴት ሆኖ ከሞት ይነሣል? እንዴትስ በክብር ወደ ሰማይ ሊያርግ ይችላል? እንግዲያስ በፍጡር አዳኝነት የሚያምኑ ከሆነ ገና ወደ እውነተኛው አምላክ አልደረሱም:: እኛስ እንደ ተጻፈው በአንድ በእግዚአብሔር ልጅ በኢየሱስ ክርስቶስ ፈጣሪነትና አዳኝነት እናምናለን (ዮሐ.1፥1፤ 3፥16፤1ኛዮሐ.4፥14)::

## ምዕራፍ ሁለት

## በእግዚአብሔር ፍቅርና በልጁ አዳኝነት እናምናለን

## (ምሥጢረ ሥጋዌና ነገረ መስቀል)

ከአንቀጽ ፩ እስከ ፬ ድረስ ያለው በመሠረቱ ስለ አብና ወልድ ፈጣሪነት፥ በባሕርይና በመለኮት አንድ ስለ መሆናቸው እንዲሁም ከመንፈስ ቅዱስ ጋር በአንድነት በምሥጢረ ሥላሴ ትምህርታችን በአለፈው ምዕራፍ ተገልጿል:: አንቀጽ ፭ ግን ወልድ በተለየ አካሉ ሰው መሆኑን የሚያመለክት ስለሆነ የምሥጢረ ሥጋዌና የነገረ መስቀሉ ትምህርት በአዲስ ምዕራፍ



ከዚህ አንቀጽ ጀምሮ እስከ አንቀጽ ፯ ድረስ ይዘልቃል:: እንግዲህ በምዕራፍ ሁለት የእግዚአብሔርን ፍቅርና የልጁን አዳኝነት መሠረት በማድረግ ስለ ዕምሥጢረ ሥጋዌ፥ ስለ ነገረ መስቀሉ ማለት ስለ ጌታ ሞትና ትንሣኤ፥ ስለ ዕርገቱና ዳግም ምጽአቱ ከብዙው በጥቂቱ እንመለከታለን:: በተጨማሪ በአንቀጽ ፮ “ተሰብአ ወተሠገወ እማርያም ቅድስት ድንግል” የሚለውን መነሻ በማድረግ ስለ እመቤታችን እንዲሁም አንቀጽ ፯ “በከመ ጽሑፍ ውስተ ቅዱሳት መጻሕፍት” የሚለውን መነሻ በማድረግ መጽሐፍ ቅዱስን በተመለከተ አጭር ትምህርታዊ መግለጫ ይቀርባል::

## አንቀጽ ፮

## “ስለ እኛ ስለ ሰዎች ስለ መዳናችን ከሰማያት ወረደ፣ በመንፈስ ቅዱስ ግብር ከቅድስት ድንግል ማርያም ፈጽሞ ሰው ሆነ”

ጌታ ለምን ከሰማየ ሰማያት ወርዶ ከድንግል ማርያም ተወልዶ ሰው ሆነ? ለሚለው ጥያቄ መልሱ ከዚያው ከተጠቀሰው አንቀጽ ውስጥ ይገኛል:: መልሱም ወልደ እግዚአብሔር ሰው የሆነው ሰውን ለማዳን እንደሆነ በግልጽ ተነግሯል:: ነገር ግን እግዚአብሔር ሰውን ለማዳን ለምን ፈለገ? ለሚለው ጥያቄ መልሱ ለብዙዎች የተሰወረ ምሥጢር ይሆንባቸዋል:: የሰው ልጅ መዳን እግዚአብሔር ምኑ ነው? ማለት ካለመዳኑ ምን ይጐድልበታል? ለመዳኑ ለእግዚአብሔር ምን ጥቅም ያገኝበታል? የሚል ሰው ሰውኛ ጥያቄ ይኖራል:: እርግጥ ከመዳኑስ ምን ጥቅም ያገኝበታል? የሚል ሰው ሰውኛ ጥያቄ ይኖራል:: እርግጥ ነው እግዚአብሔር ከሰው የሚያገኘው ጥቅም ባይኖርም ከፈጠራቸው ፍጥረታት ሁሉ አልቆና አክብሮ በራሱ አርአያና አምሳል ሰውን የፈጠረው ስለሆነ ከክብሩ ተዋርዶ በመከራ ውስጥ ወድቆ ጥፋቱንና ሞቱን ማየት አይወድም፤ አያስደስተውምም (ሕዝ.18፥23 እና 32):: ሰው የተፈጠረበትን ዓላማ ስቶ የእግዚአብሔርን ቃል ረስቶ አርአያውን አጥፍቶ ወደ ሞት ጉዳና ጭልጥ ብሎ መሄዱ እግዚአብሔርን ስላሳዘነው ወደ እውነተኛው የሕይወት ጐዳና ሊመልሰው መልካም ፈቃዱ ሆነ:: ሰውን በመፍጠሩ ቢያዝንም የሰው ልጅ ባመጣው ጥፋትና ሞት የሰው ዘር ሁሉ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር ሰው የሚድንበትን መንገድ ከጥንት ጀምሮ አዘጋጅቷል:: ከቅዱሳት መጻሕፍት እንደ ምንማረው የሰው በደልና ዓመፅ በየጊዜው እየበዛና እያደገ ቢሄድም እግዚአብሔር ሰውን ሊያድን የፈቀደበት ዋናው ምክንያት እግዚአብሔር በባሕርዩ መሐሪ ስለሆነና ሰውንም እንዲሁ ስለሚወደው ነው (ዮሐ.3፥16):: ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እንዳለው፦ “እግዚአብሔር በምሕረቱ ባለጠጋ ስለሆነ፥ከወደደን ከትልቅ ፍቅሩ የተነሣ በበደላችን ሙታን እንኳ በሆንን ጊዜ ከክርስቶስ ጋር ሕይወት ሰጠን፥” በጸጋው ማለት በችሮታው እንዲሁ አድኖናልና (ኤፌ.2፥4-5):: ስለዚህ ለምሥጢረ ሥጋዌ ማለት ለሰዎች ልጆች የመዳናቸው ታሪክና ሥራ ሁሉ ሥር መሠረቱ፥መነሻ ምንጩ የእግዚአብሔር ፍቅር ነው::

### ሀ) የእግዚአብሔር ፍቅር በልጁ የማዳን ሥራ ተገለጠ

“ፍቅር የሌለው እግዚአብሔርን አያውቅም፤ እግዚአብሔር ፍቅር ነውና”:: ይህን የተናገረው፥ ጌታ ይወደው የነበረ ደቀ መዝሙር ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስ ነው (1ዮሐ.4፥8):: ነባቤ መለኮት ቅዱስ ዮሐንስ መንፈሳዊ ምሥጢራትን በጥልቀትና በስፋት የሚያውቅ ስለሆነ የእግዚአብሔርን ማንነት በትክክል ገልጾልናል:: እግዚአብሔር ፍቅር እንደሆነና እርሱንም ማወቅ

www.ethiopianorthodox.org

የሚቻለው በፍቅር መንገድ እንደሆነ አስረድቶናል፡፡ የክርስትናን መሠረተ ሃይማኖት ለመረዳት የሚያበቃንና ትምህርተ ወንጌልን በተጨባጭ ሊያስገነዝበን የሚያስችለን ብቸኛ መንገድ ከሁሉ በፊት የእግዚአብሔርን ፍቅር፣የልጁን የማዳን ሥራና የመንፈስ ቅዱስን ጸጋ በተመለከተ እውነተኛ እውቀትና እምነት የምናገኝበት መንገድ ሲኖረን ብቻ ነው፡፡ ስለዚህ ነው ይህንን መንገድ ያስተማረን ሐዋርያ "እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን ፍቅር አውቀናል፤አምነን ማል፡፡ እግዚአብሔር ፍቅር ነው፣በፍቅርም የሚኖር በእግዚአብሔር ይኖራል፤ እግዚአብሔርም በእርሱ ይኖራል" በማለት የተናገረው (1ዮሐ.4፥16)፡፡ ፍቅር የክርስትና ሃይማኖት መሠረት ብቻ ሳይሆን የበጐ ምግባርም ምንጭ ነው፡፡ ምክንያቱም በፍቅር የሚኖር ክርስቲያን ሃይማኖተ ወንጌልንና ምግባረ ወንጌልን አንድ አድርጐ ፈጽሟልና ነው፡፡ እንግዲህ ክርስቲያን ሁሉ የእግዚአብሔርን ፍቅር አውቆና አምኖ በክርስቶስ ፍቅር መኖርና መሥራት ይገባዋል፡፡

የእግዚአብሔር ፍቅር እንዴት እንደ ተገለጠ ከማየታችን በፊት ስለ ፍቅር ምንነት በቅድሚያ እንመለከታለን፡፡

## ክርስቲያናዊ ፍቅር ምን ዓይነት ፍቅር ነው?

ፍቅር ስንል ምን ማለት ነው? የፍቅርን ትክክለኛ ትርጉም በቅድሚያ ማወቅ ይኖርብናል፤ በተለይም በዛሬው ጊዜ ፍቅር ከሃይማኖት ሁኔታ ጋር እየተሰባጠረ በዓለማዊው አስተሳሰብ ያለ ቦታውና ያለ አግባቡ እየተነገረና እየተጻፈ እናገኘዋለን፡፡ በክርስትና ሃይማኖት ፍቅር ስንል ከማንና ከምንም ጋር የማይመሳሰል ልዩ ትርጉም አለው፡፡ በሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት መሠረት ፍቅር ከምድራዊና ከዓለማዊ አስተሳሰብ ተለይቶ በሃይማኖትና በመንፈሳዊ መንገድ የሚታይ ነው፡፡ በጥንቱ የጽርዕ (የግሪክ) ቋንቋ በተጻፈው የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት "ፍቅር" የሚለው ቃል በክርስትና ሃይማኖት ለአለው ለመንፈሳዊው ፍቅር ብቻ ነው፡፡ ይህም ግብዝነት የሌለበት እውነተኛና የተቀደሰውን ፍቅር የሚያመለክት ሆኖ ባልንጀራን እንደ ራስ መውደድን፣ከዚያም በላይ ራስን ለወዳጅ አሳልፎ እስከ መስጠት፣ከዚያም አልፎ ተርፎ ጠላትን እስከ መውደድ ድረስ ይሄዳል፡፡ ይህም ከእግዚአብሔር ያገኘነው ፍቅር ነው፡፡ ሌላው ዓይነት ፍቅር ደግሞ በዓለማችን ሰፍኖ የምናየው ራስ ወዳድነት የበዛበት በጥቅም ላይ የተመሠረተው የፍቅር ዓይነት ነው፡፡ እነዚህ ሁለት ዓይነት ፍቅር እንደ ሰማይና ምድር የተለያዩ ናቸው፤ እርስ በእርሳቸው ይቃረናሉ፡፡ በጽርዕ ቋንቋ (ማለት ሐዲስ ኪዳን በተጻፈበት በጥንቱ ቋንቋ) ለሁለቱም የፍቅር ዓይነቶች ሁለት የተለያዩ ቃላት አሉት፡፡[52] ስለዚህ ሁለቱም በተለያዩ ቃላት ስለ ሚጻፉና ስለ ሚነገሩ ለአንባቢም ሆነ ለሰሚ በቀላሉ ተለይተው ይታወቃሉ፡፡

በአማርኛው ቋንቋ ግን ለሁለቱም የፍቅር ዓይነቶች አንድ ቃል ብቻ በመሆኑ ሁልጊዜ እያሳሳተ ስለ ሚገኝ በቅድሚያ ነገሩን አውቀንና ለይተን የአንዱን ትርጉም ከሌላው ሳንቀላቅል የዓለማዊውን የፍቅር ትርጉም ትተን መንፈሳዊውንና ሰማያዊውን የፍቅር ትርጉም መከተል ይኖርብናል፡፡ ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስ እንዳለው፡-"ፍቅር ከእግዚአብሔር ስለሆነ፣የሚወደውም ሁሉ

[52] Agape (አጋፔ)ማለት መሠረቱና ዓላማው ሃይማኖታዊና መንፈሳዊ ፍቅር ሲሆን Eros (ኤሮስ) ግን ዓለማዊና ሥጋዊ ፍቅርን ራስ ወዳድነትን ያመለክታል፡፡ የአጋፔ ሁለተኛ ትርጉሙ የፍቅርና የወዳጅነት የምግብ ግብዣ ማለት ነው፡፡ ይህ ግብዣ በጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ቁርባን በሚፈጸምበት ዕለት ይደረግ ነበር (1ቆሮ.11፥17-34)፡፡ ከሰባተኛው ምእት ዓመት ጀምሮ ይህ ነገር በብዙዎች ዘንድ እየተረሳ ሄዷል፡፡ በእኛ ቤተ ክርስቲያን ግን ይህ ትውፊት ዛሬም ሲሠራበት ቢገኝም የጥንቶቹ የቆሮንቶስ ክርስቲያኖች ችግር ዛሬም መልኩን ለውጦ በአንዳንድ ቦታ ስለሚታይ እንዲታሰብበት ያስፈልጋል፡፡



ከእግዚአብሔር ስለ ተወለደ እግዚአብሔርንም ስለ ሚያውቅ፣እርስ በእርሳችን እንዋደድ" (1ኛዮሐ.4፥7 )፡፡

እንግዲህ ይህ እውነተኛውና የተቀደሰው ፍቅር ከምድራዊ ሰው የተገኘ ሳይሆን ከእግዚአብሔር የመጣ መሆኑን ከላይ በተጠቀሰው ቃል ለመረዳት ችለናል፡፡ ይህ ዓይነቱ መንፈሳዊ ፍቅር ያለው ሰው ሃይማኖትና ምግባርን አስተባብሮ ይዟል፡፡ ምክንያቱም በፍጹም ፍቅር እግዚአብሔርን የሚወድ ሰው በፈጣሪው ላይ ጽኑ እምነት ይኖረዋል፤ እንደዚሁም በእውነተኛ ፍቅር ባልንጀራውን የሚወድ ሁሉ ፍቅሩን በበጐ ምግባር ይገልጸዋል ማለት ነው፡፡ ነገር ግን ሃይማኖታችንና ምግባራችን ዋጋ የሚያጣበትና ከንቱ የሚሆንበት ጊዜ አለ፤ ይኸውም የእግዚአብሔር ፍቅር በልቡናችን በማይኖርበት ጊዜ ነው፡፡ ለሁሉም ነገር ወሳኙና ታላቁ ነገር የእግዚአብሔር ፍቅር እንደ ሆነ ቅዱሳት መጻሕፍት ያሳስቡናል፡፡ ስለዚህ ነው ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ስለ ፍቅር የበላይነት የጻፈው፤ እንደ እርሱ አገላለጽ በእውነተኛውና በተቀደሰው የእግዚአብሔር ፍቅር ላይ ያልተመሠረተ ሰው ሃይማኖትና ምግባሩ ወይም መንፈሳዊ ሥራና ተጋድሎው ሁሉ ከንቱ እንደሆነና ምንም እንደ ማይጠቅም አስረድቷል (1ቆሮ.13፥1-4)፡፡ ሐዋርያው ይህን ያለበት ምክንያት በእግዚአብሔር ፍቅር ሳይሆን በሌላ ዓይነት ፍቅርና ፍላጐት ላይ የተመሠረተ ሃይማኖትና ምግባር ሁሉ ዋጋ እንደ ሌለው እንደ ጸሐፍትና ፈሪሳውያን የግብዝነት ሥራ እንዳይሆን ነው እንጂ ምግባርና ሃይማኖት አይጠቅምም ማለቱ አይደለም፡፡ ሁሉ እን ይህ ዓይነቱ ፍቅር ከማናቸውም መንፈሳዊ ነገሮችና የጽድቅ ሥራዎች ሁሉ እን ደ ሚበልጥ ይኸው ሐዋርያ ገልጿል (1ቆሮ.13)፡፡ ስለሆነም ከተፈጥሮ በላይ የሆነ ነው ይህ ፍቅር ከእግዚአብሔር ብቻ የተገኘና ለሰዎችም የተሰጠ መሆኑን እንረዳለን፡፡ ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስ "የእግዚአብሔር ልጆች ተብለን ልንጠራ አብ እንዴት ያለውን ፍቅር እንደ ሰጠን እዩ" በማለት እግዚአብሔር ስለ እኛ ያለውን ታላቅ ፍቅር በአንክሮ ያሳስበናል (1ዮሐ.3፥1)፡፡

## የእግዚአብሔር ፍቅር በክርስቶስ እንደ ተገለጠ

እግዚአብሔር ስለ እኛ ያለው ፍቅር እንዴት ታወቀ? በምንስ ሁኔታ ተገለጠ? "በዚህ የእግዚአብሔር ፍቅር በእኛ ዘንድ ተገለጠ፣ በእርሱ በኩል በሕይወት እንኖር ዘንድ እግዚአብሔር አንድ ልጁን ወደ ዓለም ልኮታልና፡፡ ፍቅርም እንደዚህ ነው፤ እግዚአብሔር እርሱ ራሱ እንደ ወደደን ስለ ኃጢአታችንም ማስተሥረያ ይሆን ዘንድ ልጁን እንደ ላከ እንጂ እኛ እግዚአብሔርን እንደ ወደድነው አይደለም" (1ዮሐ.4፥9-10)፡፡ ለጥያቄያችን ይህንን መልስ የሰጠን ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስ እግዚአብሔር ስለ እኛ ያለውን ፍቅር በልጁ የማዳን ሥራ እንደ ገለጠው ማለት እርሱ ራሱን የዓለም መድኃኒት አድርጐ እንደ ላከው ሲመሰክር "እኛም አይተናል አባትም ልጁን የዓለም መድኃኒት ሊሆን እንደ ላከው እንመሰክራለን" ብሏል (1ዮሐ.4፥14)፡፡ ይኸው ሐዋርያ እግዚአብሔር ተቀዳሚና ተከታይ የሌለውን አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ እንደ ወደደና በልጁም የሚያምን ሁሉ እንደ ሚድንና የዘላለም ሕይወት እንደ ሚኖረው በወንጌሉ ገልጿል (ዮሐ.3፥16-17)፡፡

እንግዲህ የእግዚአብሔር ፍቅር በክርስቶስ ፍቅር ታውቋል፡፡ የክርስቶስ የማዳን ሥራ የእግዚአብሔር ፍቅር መግለጫ ነውና፡፡ የክርስቶስ የማዳን ሥራ ማለት ደግሞ ክርስቶስ ሰዎችን በመውደዱ ምክንያት ከኃጢአትና ከሞት ለማዳን ሲል በሥጋው ሕማምና ሞትን በመስቀል ላይ በመቀበሉ ደኅንነትንና የዘላለም ሕይወትን እንዲያገኙ አድርጓቸዋል ማለት ነው፡፡ ስለዚህ በክርስቶስ ፍቅርና በማዳን ሥራው ያመኑትን ሁሉ በመንፈስ ቅዱስ የፍቅሩና የጸጋው ተካ

www.ethiopianorthodox.org

ፋይ እንዲሆኑ አብቅቷቸዋል፡፡ የመዳን ተስፋውንም፥ በሰጠን የፍቅር ጸጋው አረጋግጦልናል፡፡ ምክንያቱም ቅዱስ ጳውሎስ "በተሰጠንም በመንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔር ፍቅር በልባችን ስለ ፈሰሰ ተስፋ አያሳፍርም" ብሏልና (ሮሜ.5፥5)፡፡ በዚህ ፍቅር የሚኖር ወንድሙንም የሚወድ "ከሞት ወደ ሕይወት" መሸጋገሩን ያውቃል፡፡ ይህ ፍቅር የሌለው ሰው ግን ማለት "ወንድሙን የማይወድ በሞት ይኖራል" ተብሎ ተጽፏል፡፡ ስለዚህ እንደ ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስ ትምህርት "ፍቅር" የክርስቶስ ለመሆናችን መታወቂያችን ብቻ ሳይሆን በክርስቶስ ለመዳናችንም ማረጋገጫው ይኸው ፍቅር ነው (ዮሐ.13፥35፤ 1ኛዮሐ.3፥14-18)፡፡

ከመታሰብ በላይ ስለ ሆነው ስለ ክርስቶስ ፍቅርና ስለ ራሱ ስለ ክርስቶስም ለማወቅና ለማመን ችሎታውን እንዲሰጣቸው ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለኤፌሶን ክርስቲያኖች እንዲህ እያለ ይጸልይላቸዋል፤ ይማልድላቸዋልም፦

"በሰማይና በምድር ያለ አባትነት ሁሉ ከሚሰየምበት ከአብ ፊት እንበረከካለሁ፤በመንፈሱ በውስጥ ሰውነታችሁ በኃይል እንድትጠነከሩ ክርስቶስም በልባችሁ በእምነት እንዲኖር እንደ ክብሩ ባለጠግነት መጠን ይስጣችሁ፤ የእናንተ ሥርና መሠረት በፍቅር ይጸና ዘንድ፥ከቅዱሳን ሁሉ ጋር ስፋቱና ርዝመቱ ከፍታውም ጥልቅነቱም ምን ያህል መሆኑን ለማስተዋል፥ ከመታወቅም የሚያልፈውን የክርስቶስን ፍቅር ለማወቅ ትበረቱ ዘንድ፥እስከ እግዚአብሔርም ፍጹም ሙላት ደርሳችሁ ትሞሉ ዘንድ፡፡ . . . ለእርሱ በቤተ ክርስቲያን በክርስቶስ ኢየሱስ እስከ ትውልዶች ሁሉ ከዘላለም እስከ ዘላለም ክብር ይሁን፤ አሜን" (ኤፌ.3፥14-21)፡፡

እንግዲህ የሐዋርያው ጸሎትና በረከት ከሁላችን ጋር ሆኖ ሁልጊዜ የክርስቶስን ፍቅር እያሰብን በፍቅሩ እንድንኖር ያበቃን ዘንድ እየንዳንዳችን አጥብቀን መጸለይ፣ እግዚአብሔርንም ማመስገን ይገባናል፡፡ የክርስቶስን ፍቅር ታላቅነት በተረዳን ጊዜ ነው ክርስቲያናዊ ሕይወታችን የሚታደሰው፥ ሥነ ምግባራችንም የሚሠምረው፥ እንደ ሐዋርያው፦ "የክርስቶስን ፍቅር ማን ያስተወናል?" በማለት በየጊዜው የሚያጋጥመንን መከራና ፈተና ሁሉ ለመቋቋም ቁርጠኛ መንፈስ ሊኖረን የሚችለው (ሮሜ.8፥35-39)፡፡ እርሱ አስቀድሞ ስለ ወደደንና ስለ አዳነን እኛም እንወደዋለን፡፡ ወልደ እግዚአብሔር ከሰማየ ሰማያት ወርዶ ሰውን ያዳነበት ዋና ምክንያት እኛን በመውደዱ ብቻ እንደሆነ ከእንግዲህ ወዲህ መርሳት የለብንም፡፡ ስለዚህ ነው ቅዱስ ሕርያቆስ "ፍቅር ሰሐቦ ለወልድ ኃያል እመንበሩ ወአብጽሖ እስከ ለሞት- ወልድ ኃያልን ፍቅር ከዙፋኑ ሳበው እስከ ሞትም አደረሰው" ያለው (ቅዳሴ ማርያም፣ ቁጥር 127)፡፡

## ለ) ምሥጢረ ሥጋዌ -- "ቃል ሥጋ ሆነ"

ምሥጢረ ሥጋዌ ምን ማለት ነው? ለሚለው ጥያቄ የመጀመሪያ መልስ፦ ምሥጢረ ሥጋዌ ማለት "ቃል ሥጋ ሆነ በእኛም አደረ" በሚለው የወንጌል ቃል ላይ የተመሠረተ ታላቅ የክርስትና ሃይማኖት ምሥጢር ነው (ዮሐ.1፥14)፡፡ ስለሆነም ምሥጢረ ሥጋዌ ማለት የእግዚአብሔር አካላዊ ቃል ወልድ ሰውን ለማዳን ሲል ሰው የሆነበት፣ ሰውንም ያዳነበት፣ መለኮትና ትስብእት በተዋሕዶ አንድ የሆኑበት ምሥጢር ማለት ነው፡፡ እንግዲህ ወልደ አምላክ ሰው የሆነበትን ምክንያት መጠየቅ አያስፈልግም፤ ምክንያቱም መልሱ በአንቀጹ መጀመሪያ ላይ እንደ ተገለጸው "ስለ እኛ ስለ ሰዎች ስለ መዳናችን . . . ከቅድስት ድንግል ማርያም ፈጽሞ ሰው" እንደሆ



ነ ታውቋልና፡፡ ነገር ግን የሰው ልጅ መዳንን ይፈልግ ይሆንን? ለመሆኑ ሰው ምን ሆኖ ነበር መዳን ያስፈለገው? ከምንና ከምን ነገሮች ነው ሰው የሚድነው? የሚሉትን ጥያቄዎች ለመመለስ መሞከር ጠቃሚ ነገር ይሆናል፡፡

መቼም በጨለማ ውስጥ ታሥሮ የሚኖር ሰው ከጨለማ ሥፍራ ነፃ ወጥቶ በብርሃን መመላለስ ይፈልጋል፡፡ ብዙ ጊዜ በሕመም የሚሰቃይ ሰው ከበሽታው ድኖ ጤንነቱን ለማግኘት ይጓጓል፡፡ ዘወትር በችግርና በድህነት ተቆራምዶ የሚኖር ሰው ለችግሩ መፍትሔ አግኝቶ ከድህነቱ ለመላቀቅ ይጥራል፡፡ እንግዲህ መከራና ችግሩ የመንፈስም ሆነ የሥጋ ዓይነቱና ብዛቱ ይለያይ እንጂ ሁሉም ሰው ችግርን ቀምሷል፡፡ ችግርን አልቀመስኩም የሚል ቢኖር የራሱንና የወዳጆቹን ሕይወት ታሪክ የረሳ ነው፡፡ ብዙ ሰዎች የማይረሳ መከራና ችግር እንደ ደረሰባቸው ይወቁ እንጂ የችግሩን መንሥኤ ሥር መሠረት አያውቁም፤ አይጠይቁም፤ ለማወቅም አይፈልጉም፡፡ ተፈጥሮ ሁልጊዜ እንደዚሁ ተስፋ አልባ ይመስላቸዋል፡፡ ከዕለት ዕለት የጭንቀትና የችግር ኑሯቸው ባሻገር የደኅንነትና የተስፋ ሕይወት እንዳለ አያስቡም፡፡ ስለሆነም በኀዘንና በቀቢጸ ተስፋ ውስጥ የሚገኙ ከሀብታምም ከድሆችም ወገን ብዙዎች ሰዎች አሉ፡፡

ነገር ግን እውነተኛውን የሰላምና የደስታ ሕይወት፥ፍቅርና ወንድማማችነት የሰፈነበትን ፍትሐዊ አሠራር ያለበትን ኑሮ የሚፈልጉና የሚያውቁ ሰዎች ከባድ ችግር ሲደርስባቸው፥ የዓመፀኞች ቀንበር ሲጫናቸው፥ግፍ ሲበዛባቸው፡ አግኝተው ሲያጡ፥ መብታቸው ሲገፈፍ፡ ሰው ሠራሽና የተፈጥሮ አደጋ ሲደርስባቸው ወይም ክፋትና ተንኮል የበዛበት የጥፋት ሁኔታዎች ሲያጋጥማቸው ወይም በሌሎች ሲደርስባቸው በማየታቸው ይህ ሁሉ የኑሮ ውጣ ውረድ፥ ፈተናና መከራ ከየት መጣ? እንዴትስ መጣ? እንዴትስ መዳን ይቻላል? ብለው መጠየቃቸው አይቀርም፡፡ ይልቁንም ስለ መኖር ዓላማና ስለ መራራው ሞት ጉዳይ እጅግ የሚያስቡና የሚጨነቁ አጥብቀውም የሚጠይቁና የሚመራመሩ አሉ፡፡ ሆኖም አጥጋቢ መልስ ለማግኘት ስለ ማይችሉ ለጥያቄዎቹ መልስ ለመስጠት ይፈላሰፋሉ፤ አለበለዚያም በሥነ ልቡና መንገድ ራሳቸውን የሚያድኑበት የሚመስላቸውን ጊዜያዊ ዘዴ ይፈጥራሉ፡፡ በብዙዎች ዘንድ እንደምናየው ለችግሩ መፍትሔ ሲያጡ ከዓለሙ ጋር ሆነው የጊዜውን ነፋስ ተከትለው ይሄዳሉ፡፡ ጥያቄውንም በቸልተኝነትና በዝምታ ያልፉታል፡፡ ይህን ቁም ነገር ያለበትን ጥያቄ በማሰብ እንዳይጨነቁ የሚያስረሳቸውን ጊዜያዊና አልባሌ መንገድን ይፈልጋሉ፤ የመረጡትም መንገድ ለጥያቄው መፍትሔና መልስ የሚሰጥ ሳይሆን ወደ ባሰው ችግር ውስጥ ይጥላቸዋል፤ ከድጡ ወደ ማጡ ይገባሉ፡፡

እውነተኛው መልስና መፍትሔ ግን ከሃይማኖት ትምህርት ይገኛል፡፡ በሕይወት ውስጥ የሚያጋጥሙን ፈተና፥ችግር፡መከራ፡ሕማምና ሞት፡የልብ ኀዘንና የአእምሮ ጭንቀት ሌሎችም ይህን የመሳሰሉት ሁሉ የኑሮ ግዴታዎችና የተፈጥሮ ስጦታዎች እንዳልነበሩ እግዚአብሔር ለጥንት አባቶች፥ለነቢያቱና ለቅዱሳኑ ገልጾላቸዋል፡፡ እኛም እንድናውቀው በቅዱሳት መጻሕፍት ተጽፎልናል፡፡ ስለዚህም በሕይወትና በሞት መካከል ሆነው በልዩ ልዩ መከራና ፈተና ለሚሰቃዩት የአዳም ልጆች ሁሉ ለደረሰባቸው ችግሮች መፍትሔ የሚሆኑ፥ አእምሯቸውን ለሚያስጨንቋቸው ጥያቄዎች መልስ የሚሰጡና በጠቅላላው ለሁላችንም የሚበጀውን የደኅንነታችንና የተስፋችንን ጉዳይ በተመለከተ እግዚአብሔር በቅድሚያ አዘጋጅቶልናል፡፡ የእግዚአብሔር ቃል ክርስቶስም ወደዚህ ዓለም በሥጋ ብእሲ የመጣበት ምክንያት ይኸው ነው፡፡ እርሱ ለእኛ ስለ እኛ [illegible] በመሆን የሰው ልጆችን መከራና ፈተና ሁሉ በመቀበል፥

www.ethiopianorthodox.org

ደዌያችንን በመውሰድ፥ ሕማማችንን በመሸከም መፍትሔውን ሰጥቶናል (ኢሳ.53)። እርሱ በእኛ ተገብቶ ኃጢአትንና ሞትን አስወግዶልናል፤ ሞትን በሞቱ ድል ነሥቶ ትንሣኤውን አብሥሮናል። እንግዲህ ክርስቶስ ይህን ታላቅና ድንቅ ሥራ በሰው ልጆች ታሪክ ውስጥ የፈጸመው እኛን ከቀቢፀ ተስፋ አድኖ መከራና ሞት የሌለበትን የዘላለም ሕይወት ለመስጠት ነው።

የመጀመሪያ የሰው ኑሮ መከራና ሞት የሌለበት የደስታ ሕይወት እንደ ነበረና በኋላም ሰው በገዛ ጥፋቱና በሠራው ኃጢአት መከራና ሞትን ራሱ እንደ ጋበዛቸው፣ እንደ ጠራቸውና እንደ ፈጠራቸው እንጂ እግዚአብሔር ሕማምና ሞትን አልፈጠረም (መጽ.ጥበብ1፥3-16)። እንግዲህ ሰው ሁሉ በመከራና በሞት መካከል እንደ ሚኖር አውቆ፣ የደስታ ሕይወትም እንዳለ አምኖ በተስፋው ቃል ተማምኖ ከመከራና ከሞት እንዲድን እግዚአብሔርን ይለምን። አባታችን አዳም የነበረበትን የደስታና የገነትን ኑሮ በማሰብ በጥፋቱ ምክንያትም የደረሰበትን መከራና የሞት ፍርድ አውቆ ተጸጽቶ ንስሐ ገብቶ ፈጣሪውን ከዚህ ሁሉ ክፉ ነገር እንዲያድነው ለመነው። እግዚአብሔርም የመዳንን ተስፋ ሰጠው (ዘፍ.3፥15)። ሆኖም የመዳን ተስፋ በቶሎ የሚደርስ በቀላሉ የሚፈጸም ነገር አይደለም፤ ከፍ ያለ መሥዋዕትነትን የሚጠይቅ ነው። እግዚአብሔር ዓለምን ከፈጠረበት ያዳነበት ጥበቡ ይበልጣልና (መቅድመ ወንጌል ተመልከት)። የእግዚአብሔር የማዳን ጥበቡ በመሐሪነቱ ብቻ የሚወሰን ሳይሆን በፈታሒነቱም ጭምር የሚፈጸም ነው። ምሕረቱ ለዘላለም እንደሆነ እውነተኛ ፍርዱም ለዘላለም ጸንቶ ይኖራል።

## *የእግዚአብሔር ፍርድ ለዘላለም የጸና ነው*

ሰው ባጠፋው ጥፋት ከደስታ ሕይወት ወጥቶ፥ ከክብሩ ተዋርዶና ወድቆ በችግርና በመከራ ኖሮ በመጨረሻ ሥጋው በመቃብር በስብሶ ሲቀር፣ ነፍሱ ደግሞ በሲኦል ስትሠቃይ በማየቱ ወልደ እግዚአብሔር ሰውን ከዚህ ክፉ ነገር ለማዳን ሰው ሆኖ ሕማምና ሞትን ተቀብሎ እንዳዳነው ሁላችንም እናውቃለን። ለምንድን ነው ጌታ ይህንን ያህል ከባድ ሕማምና መራራ ሞት የተቀበለው? ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር እንደሌለ እናምናለን። ታዲያ ለምን ድን ነው ጌታ ሥጋ ሳይለብስና ሳይሞት በቃሉ ብቻ ሊያድነን ያልፈለገው? የሚሉትን ጥያቄዎች መመለስ አስፈላጊ ነው።

የእግዚአብሔር ባሕርይ እንደ ሰው ጠባይ ተለዋዋጭ አይደለም፣ እንደ ሰው በግብታዊነትና በስሜት ተነሣሥቶ አይናገርም፤ እንደ ምድራዊ ገዥና ዳኛ በሕግም ያለ ሕግም የመረጃዎቹንና የምስክሮቹን ትክክለኛነት ሳያውቅ በግምት አይፈርድም። እግዚአብሔር ሁሉን ነገር በቅድሚያ ያውቀዋል። በሰው አእምሮ የሚወጣው የሚወርደው እቅድና ምኞት ሁሉ፣ ወደፊት የሚያደርገውም ሁሉ በእርሱ ዘንድ ግልጽ ሆኖ ይታየዋል። ለእርሱ ጥበብና እውቀት በምልዐትና በፍጹምነት የባሕርዩ ስለሆኑ የተናገረውን አያጥፍም፤ የወሰነውንም አይለውጥም። መለዋወጥ የሚታየው በሰው ባሕርይ ነው። ምክንያቱም ሰው ጥበቡና እውቀቱ ፍጹም ስላልሆነ ስለ ሚሳሳትም ያሰበውንና የወሰነውን በየጊዜው ይለዋውጠዋል። ይህ ዓይነቱ ነገር ለእግዚአብሔር ባሕርይ ስለ ማይስማማ ከቶ ልናስበው አይገባንም። እርሱ በሥራው ሁሉ ስለ ማይሳሳት በአደረገው ነገር አይጸጸትም (1ሳሙ.15፥29፤ ሮሜ.11፥29) ሰማይና ምድር ያልፋሉ ቃሉ ግን አያልፍም (ማቴ.24፥35)።

ስለዚህ እግዚአብሔር ... በማይሻረው ቃሉ ትእዛዝን ሰጠው (ዘፍ.2፥17)። ይህንንም ትእዛዝ ያፈረሰ ቀን



ግን ሞትን እንደ ሚሞት እግዚአብሔር በማይለወጥ ቃሉ በቅድሚያ አስጠን ቅቆት ነበር።

ትእዛዙን ቢጠብቅ በሕይወትና በደስታ ሊኖር፣ ትእዛዙን ቢያፈርስ ሞትን የሚሞት መሆኑ ግልጽ ነው። ነገር ግን አዳምና ሔዋን ትእዛዙን አፈረሱ፤ የዚያኑ ቀን የእግዚአብሔር ጸጋ ተለያቸው ራቁታቸውንም ቀሩ። ሞት ማለት ከእግዚአብሔር ጸጋ መለየት ማለት ነው። የእግዚአብሔር ቃልና ውሳኔ የማይለወጥ ስለሆነ ሞትን ትሞታለህ እንደ ተባለው፣ ሰው በሥጋው ሞቶ ወደ መቃብር፣ በነፍሱም ወደ ሲኦል የሚወርድ ሆኗል።

እንግዲህ የእግዚአብሔር ቃል እንደ ማይለወጥ እንወቅ። እግዚአብሔር ሁሉን ይችላል በሚል ምክንያት እንዴት ቃሉን መለወጥ አይችልም ብለን እናስብ ይሆናል። ቃልን መለወጥ ማለት ራስን በራስ መቃወም ማለት ነው። ሰማይና ምድርን በቃሉ ያጸና አምላክ እንዴት ቃሉን ይለውጣል? ቃሉ የጸናማ ካልሆነ ሰማይና ምድርም እንደ እምቧይ ካብ ይፈራርሳሉ ማለት ነው። እግዚአብሔር የሕግና የሥርዓት አምላክ ነው፤ ሁሉንም በሕግና በሥርዓት ይመራል እንጂ እንደዚህ ዓለም ገዢ በማን አለብኝነት፣ በሕግ አልባነት የፈለገውን እንደ ሚያደርግ አምባገነን መሪ አይደለም።

የእግዚአብሔር ቃልና ውሳኔ የማይለወጥ በመሆኑ አዳምና ሔዋን መለኮታዊውን ሕግ በመሻራቸው በፈጸሙት በደልና ኃጢአት ምክንያት የሞት ውሳኔ በእነርሱና እነርሱን መስለውና አኽለው በተወለዱት ልጆቻቸው ላይ ሁሉ የጸና ሆነ። የሰው ልጆችም ከአዳም ከወረሱት ኃጢአት ሌላ የራሳቸውን በደልና ኃጢአት በመጨመርና በማባዛት ሰው ሁሉ በደለኛ ሆነ። "በጐ ነገርን የሚሠራ የለም፤ አንድም ስንኳ የለም።" ተብሎ እንደ ተጻፈ "ሁሉ ዓመፀ በአንድነት ረከሱ" (መዝ.13፥14፥3፤ ኢዩ.15፥14-16፤25፥4-6፤ ሮሜ.3፥23)። ስለዚህ በዓለም ሁሉ፣ በሰው ልጆች ላይ ሁሉ የሞት ፍርድ ጸና። "ኃጢአት ስላደረገ ሞት ለሰው ሁሉ ደረሰ"። ምክንያቱም "የኃጢአት ዋጋ ሞት ነውና" ተብሎ እንደ ተጻፈ (ሮሜ.5፥12፤6፥23)።

## *ጌታ የአዳምን የሞት ፍርድ በመቀበል እንዳዳነው*

እንግዲህ እግዚአብሔር በማይለወጥ ውሳኔው፣ በመለኮታዊ ሥልጣኑ በማይሻር ቃሉ በትክክለኛ ዳኝነቱ በኃጢአት ላይ ካወጀው የሞት ፍርድ ማን ነፃ ሊያወጣን ይችላል? እንዴትስ ለመዳን እንችላለን? ከአዳም ጀምሮ ሁሉም በኃጢአቱ ተከሣሽ ስለሆነ ማን ተያገር ይሁንለት? ለሠራውስ ጥፋት ምን ዓይነት ካሣ ሊከፍልለት ይችላል? ተያገር እንዲሆን ጥፋተኛ ያልሆነ ጻድቅ ሰው ይፈለግ እንዳይባል ሁሉም በደለኛ ሆኗል። ከዓለመ መላእክትም ማለት ንጹሕ ፍጥረት ከሚባሉትም ውስጥ እንዳይፈለግ ጥፋቱ የተፈጸመበት ቦታ ከዚህ ዓለም ስለሆነ ጥፋተኛውም ሰው በመሆኑ የሌላ ፍጥረት አዳኝነትን ማሰብ የማይሆን ነገር ነው። ለዚህ አዳጋች ነገር መልስ ሊገኝ የሚችለው ከራሱ ከእግዚአብሔር ብቻ ነው። እርሱም የመረጠው ትክክለኛ መንገድ፣ ኃጢአት የሌለበት ንጹሕ ሥጋና ነፍስን በመዋሐድና ሰው በመሆን በበደላቸው ለተከሰሱትና ለተፈረደባቸው ሁሉ ተያዥ ብቻ ሳይሆን በእነርሱ እግር ተተክቶ በእነርሱ ወንጀልና ኃጢአት ተከሥሶ የሞትን ፍርድ በመቀበል ማዳን ነበር። ስለዚህ ነው ቅዱስ አቡሊዲስ ዘሮም መልአክን ወይም ነቢይን በመላክ ሳይሆን እርሱ ራሱ እግዚአብሔር ቃል ወደ እኛ መጥቶ ሰው ሆኖ እንዳዳነን በ8ኛ ድርሳኑ የጻፈው።

... መለኮታዊ አሠራር በጽሞና እናስተውል። "ሞትን

www.ethiopianorthodox.org

ትሞታለህ” በማለት የተወሰነው መለኮታዊ ቃል ሳይሻር ወልደ እግዚአብሔር ቃል በሥጋው በመሞቱ የእግዚአብሔርን ትክክለኛ ፍርድ በአዳም ተገብቶ ፈጽሞታል፤ በዚሁም ሰውን ከሞት አድኖ አዲስ ፍጥረት አድርጐታል፤ የዘላለም ሕይወትን ሰጥቶታል፡፡ አሁንም ልብ እናድርግ፣ የእግዚአብሔር ትክክለኛና እውነተኛ ፍርድ ተፈጻሚነት እንዲኖረውና እንደዚሁም እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ያለው ፍቅር እንዲገለጽ ለማድረግ በመስቀል ላይ ሁለቱም ማለት ፍርዱና ፍቅሩ (ምሕረቱ) በክርስቶስ ሞት ተፈጽመዋል፡፡

ፍርድ ስንል በኃጢአት ላይ የተወሰደውን እርምጃ ማለት በበደል ላይ የተወሰነውን የሞት ቅጣት የሚያመለክተን ነው፡፡ ይህም የእግዚአብሔር የባሕርዩ የሆነውን ትክክለኛ ዳኝነቱን ይገልጽልናል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ኃጢአት የሌለበት ክርስቶስ ኃጢአተኛውን ከዘላለም የሞት ፍርድ ለማዳን በኃጢአተኛው ምትክ ሞትን በፈቃዱ በመቀበሉ የእግዚአብሔርን የፍቅሩንና የምሕረቱን ታላቅነት ያስረዳናል፡፡ እንግዲህ ስለዚህ ነው የእግዚአብሔር ፍርዱና ፍቅሩ በአንድነት በክርስቶስ መሥዋዕትነት በዕለተ ዓርብ በመስቀል ላይ ተፈጸመ የምንለው፡፡

አዳም መለኮታዊ ሕግን በመተላለፉ፣ በደል በመፈጸሙ የሞት ቅጣት ተፈርዶበታል፤ አዳም ከዚህ ዘላለማዊ ቅጣት ለመዳን የሚችለው በፍርድ መንገድ እንጂ በሌላ ሁኔታ መዳን አይቻልም፡፡ ቅጣቱ በፍርድ እንደ ሆነ መዳኑም በፍርድ ይፈጸማል፡፡ ስለዚህ ነው ጌታ ሥጋ ለብሶ ማለት ሰው ሆኖ የአዳምን የሞት ፍርድ በራሱ ሰውነት ተቀብሎ ያዳነው፣ “ወአድኃነነ በፍትሕ ጽድቅ ወርትዕ” ተብሎ እንደ ተጻፈው መዳናችን በፍርድ እንደሆነ እናስተውል (መቅድመ ወንጌል)፡፡ ፍርድም የተፈጸመው በመስቀል ላይ ነው፡፡ እንግዲህ በመስቀል የመዳናችን ነገር አማራጭ የሌለው በእግዚአብሔር የተመረጠ ብቸኛ የጽድቅና የፍትሕ የርትዕ መንገድ እንደሆነ እናምናለን፡፡

ከመስቀል ሌላ የመዳን አማራጭ አለ ብሎ ማሰብ ከእውነትና ከእግዚአብሔር ፈቃድ ውጭ መሆኑን ያመለክታል፡፡ መስቀል አያስፈልገንም ከነ ኃጢአታችን ወደ እግዚአብሔር ለመቅረብ እንችላለን ማለት ዘበት ነው፤ ሐሰት ነው፤ ከእግዚአብሔር ተለይቶ መቅረት ካልሆነ በስተቀር የእግዚአብሔር የቅድስና መለኮታዊ ባሕርዩ የሚያቃጥል እሳት ስለሆነ በክርስቶስ መስቀል በኩል ካልሆነ ማንም ሊድንና ወደ እግዚአብሔር ሊቀርብ አይችልም፡፡ ሐዋርያው ጳውሎስ እንዳለው እግዚአብሔር “አምላካችን በእውነት የሚያጠፋ እሳት ነውና” (ዕብ. 12፥29)፡፡ ደም ካልፈሰሰ የኃጢአት ሥርየት የለም (ዕብ.9፥22)፡፡ የኃጢአት ሥርየት ከሌለ ሰው ከእግዚአብሔር አይታረቅም፡፡ ስለዚህ ይህ የኃጢአት የጥል ግርግዳ እስካለ ድረስ ሰው ሰላም፣ ደስታና ፍቅር የሌለው፣ ተስፋውን ያጣ ጉስቋላ ፍጥረት ሆኖ ይቀራል፡፡ እንግዲህ ተስፋ ያጣ በፍርድ የተቀጣ ሰው ሊድን የሚችለው የእርሱን ቅጣት የሚቀበል ስለ እርሱ መሥዋዕት ሆኖ በፍትሐ እግዚአብሔር ፊት የሚቀርብ ንጹሕ ነገር ያስፈልገዋል፡፡

## የመዳናችን ምሥጢር በመሥዋዕት ስለ መሆኑ

በክርስቶስ የተፈጸመው የመዳናችን ሥራ ማለት የመስቀሉ መሥዋዕት በዘመነ ብሉይ በጥንት ጊዜ ቢደረግ ኖሮ የማዳኑ ምሥጢር ለሰዎች ልጆች ሁሉ ግልጽ ሆኖ ባልታወቀም ነበር፡፡ ነገር ግን እግዚአብሔር በጥበቡ የማዳኑን ምሥጢር እንዴት እንደሆነ ለሰዎች ልጆች ቀስ በቀስ በየደረጃ በተለያየ በምሳሌ በነቢያት ቃል እንዲማሩት ...



በሥጋ መምጣት በተለይም በመስቀል ለሚፈጸመው መሥዋዕት እንዲዘጋጁ አድርጓል፡፡ ይህን ጉዳይ በተመለከተ በተለይም የመዳን ጽንሰ ሐሳብ ከመሥዋዕት ጋር መያያዙን ለማብራራት የግብፅ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መሪ እግዚአብሔርና ሰው በሚለው መጽሐፋቸው በአንዱ ክፍል ውስጥ ካቀረቡት ነጥቦች መካከል የተወሰኑትን በመምረጥ ዋና ዋና ሐሳቡን እንደ ሚከተለው እናሳያለን፡፡[53]

1. የመጀመሪያዎቹ ወላጆቻችን ሕገ እግዚአብሔርን ባፈረሱ ጊዜ ዕራቁታቸውን ሆኑ፥ የተሰጣቸውም ጸጋ ተገፈፈ፡፡ እነርሱም ዕራቁትነታቸውን አውቀው “የበለስ ቅጠሎች ሰፍተው ለእነርሱ ለራሳቸው ግልድም አደረጉ” (ዘፍ.3፥7)፡፡ እግዚአብሔር ግን “ለአዳምና ለሚስቱ የቁርበት ልብስ አደረገላቸው፥ አለበሳቸው” (ዘፍ.3፥21)፡፡ ሳይበድሉ በፊት ጸጋ ያለበሳቸው እግዚአብሔር ከበደሉ በኋላ ከእንስሳት በተገኘው የቁርበት ልብስ ያለበሳቸው በምሳሌ ሲያስተምራቸው ነው፡፡ መቼም የቁርበቱ ልብስ እንዲያው አልተገኘም የእንስሳት ደም ፈስሶ ቆዳው ተገፎ የተገኘ ነው፡፡ እንግዲህ ይህ የመጀመሪያው ትምህርት ነው፤ የመጀመሪያው መመሪያ ነው፤ ይኸውም፡- “ኃጢአት ዕራቁትነትን ያመጣል፥ መሥዋዕትም ኃጢአትን ይሸፍናል” ማለት ነው፡፡

2.. ከዚህ በኋላ መሥዋዕት ማቅረብ እንደ ሚገባ ሰዎች ተማሩ፡፡ በቅዱሳት መጻሕፍት እንደ ተነገረው የመጀመሪያው መሥዋዕት የቀረበው በጻድቁ በአቤል እጅ ነበር፡፡ እርሱም “ከበጎች በኵራትና ከስቡ አቀረበ” (ዘፍ.4፥4)፡፡ እግዚአብሔር የአቤልን መሥዋዕት በመውደዱና በመቀበሉ፥ ሰዎች ሁለተኛውን ትምህርት ተማሩ፤ ይኸውም፡- የሚቀርበው መሥዋዕት ከበኵራቱና ከመልካሙ ነገር መሆን አለበት፡፡

3. አብርሃም ልጁን ይስሐቅን ለሚቃጠል መሥዋዕት እንዲያቀርበው በአዘዘው ጊዜ እንዲህ አለው፡- “የምትወደውን አንድ ልጅህን ይስሐቅን ይዘህ . . . እኔም በምነግርህ በአንድ ተራራ ላይ በዚያ መሥዋዕት አድርገህ ሠዋው” (ዘፍ.22፥2)፡፡ እዚህ ላይ የሰው ልጆች ሦስተኛውን መመሪያ ተማሩ፥ ይኸውም ተወዳጅና አንድያ ልጅን ለመሥዋዕት ስለ ማቅረብ፣

4. በኦሪት ዘፍጥረት መጽሐፍ እንደ ሚታየው የሚቀርበው መሥዋዕት ሁሉ የሚቃጠል መሥዋዕት እንደሆነና ይህም መሥዋዕት እሳት ይበላውና ወደ አመድነት ይለወጣል (ዘሌ.6፥10)፡፡ ከዚህም መሥዋዕት ማንም ሊበላ አልተፈቀደም፡፡

የሚቃጠል መባዕ ሁሉ ለእግዚአብሔር ነበር ይኸውም ልቡን እዲያ ስደስተው በእግዚአብሔር እሳት ይቃጠላል፡፡

የሚቀርበውን መባዕ የሚያቃጥለው ቅዱስ እሳት ነበር፤ እርሱም የሚቃጠለውን መሥዋዕት ሊበላ (ሊያቃጥል) ከሰማይ የወረደው ያው የመጀመሪያው እሳት ነበር፡፡ ይህንንም እሳት ይጠብቁታል፥ ምክንያቱም

---

[53] H.H. Pope Shenouda III, God And Man (Cairo, Dar El Tebba El Kawamia, First edition-December 2000 ), pp.190-201

www.ethiopianorthodox.org

እግዚአብሔር ሌላ እሳት በፊቱ እንዲቀርብ አልፈቀደምና፤ ሌላ እሳት ያቀረቡት በሞት ተቀጥተዋል(ዘሌዋ.10፥1-2)[54]፡፡

5. እግዚአብሔር ለሕዝበ እሥራኤል ስለ ፋሲካ ሕግና ሥርዓት ሰጣቸው፤ የእግዚአብሔር መልአክ በግብፅ ምድር ላይ ያልፋል፡ በኵራትንም ሁሉ ይመታል (ሞተ በኵር)፡፡ ነገር ግን የእሥራኤል በኵራት የዳኑት እንደ እግዚአብሔር ትእዛዝ የፋሲካውን በግ ደም በበሮቻቸው ላይ በመርጨት ነበር፡፡ ጌታ እንዳላቸው "ደሙን ባየሁ ጊዜ ከእናንተ አል ፋለሁ" (ዘጸ.12፥13)፡፡ የፋሲካም በዓል አጀማመር እንደዚህ ነበር፤ ዕብራ ውያንም ከዚህ ትልቅ ትምህርት ተማሩ፤ ይኸውም፡- ደም ከሞት የመዳን ምክንያት ነው፤ የበጉ ደም የፈሰሰው እነርሱን ለማዳን ነበርና፣

እንግዲህ እዚህ ላይ የመዳንን ጽንሰ ሐሳብ "The concept of Redemption" ወይም የመዳንን ምሥጢር ከዚህ ድርጊት እናስተውላለን፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ በኋለኛው ጊዜ እንዳለው "በእውነት ፋሲካችን ክርስቶስ ለእኛ ተሠውቶልናልና" (1ቆሮ.5፥7)፡፡ በመጀመሪያው የአይሁድ ፋሲካ ምክንያት የመዳን ጽንሰ ሐሳብን ለማወቅ ተችሏል፡- የንጹሕ መሥዋዕት ደም ፈሰሰ ለእነርሱም ሞተ፡፡

<u>እንግዲህ መዳን(ደኅንነት) ማለት ንጹሑ (ያልበደለው) ለኃጢአተኛው ምትክ ሆኖ መሞት ማለት ነው፡፡</u>

6. እግዚአብሔር ልዩ ልዩ የመሥዋዕትን ሕግ ሰጠ፡፡ እያንዳንዱም እንደየ ሁኔታው የመዳንን ልዩ ልዩ ገጽታ ያመለክታል፡፡ መሥዋዕት አቅራቢው በመሥዋዕቱ እንስሳ ላይ እጆቹን በመጫን ኃጢአቱን ከተናዘዘ በኋላ እንስሳው ይታረዳል፡፡ ኃጢአትን በፈጸመው ሰው ምትክ መሥዋዕቱ ኃጢአቱን ይሸከመዋል ማለት ነው፡፡ ስለዚህ መሥዋዕት ሆኖ የቀረበው በግ የሚከተለውን ነገር (ሐቅ) ያስገነዝበናል፡-
<u>ንፁሕ፡ ኃጢአት የሌለበት የሌሎቹን ኃጢአት ይሸከማል፤ ንጹሕ፡ ሞት የማይገባው፡ ሞት በተፈረደበት ወንጀለኛ ምትክ ይሞታል፡፡</u>

የመሥዋዕት ሕግ ከተጻፈ ከብዙ ትውልዶች በኋላ ነቢዩ ኢሳይያስ ስለ ክርስቶስ መሥዋዕት እንዲህ ሲል ተናግሯል፡- "እኛ ሁላችን እንደ በጎች ተቅበዝብዘን ጠፋን፤ ከእኛ እያንዳንዱ ወደ ገዛ መንገዱ አዘነበለ፤ እግዚአ ብሔርም የሁላችንን በደል በእርሱ ላይ አኖረ" (ኢሳ.53፥6)፡፡

<u>ይህ እንግዲህ አዳኙ ነው፡ የእኛን ሁሉ ኃጢአት በራሱ ላይ አደረገ፡፡</u>

7. ስለ መዳን ምሥጢር ስለ ደኅንነት ሌላው ትርጉም ደግሞ በቅዱሳት መጻሕፍት ተጽፎ የሚገኘው ታላቁን የሥርየተ ኃጢአት ቀን የሚመለከት ነው (ዘሌዋ.16)፡፡

አሮን ሁለት እጆቹን "በሕያው ፍየል" ራስ ላይ ጭኖ የሕዝቡን ኃጢአ

[54] "እግዚአብሔር የሚያቃጥል እሳት ነው (ዕብ.12፥29)፡ ስለሆነም የሚቃጠለውን መሥዋዕት የሚያቃጥለው እሳት የእርሱ /የእግዚአብሔር/ ምሳሌ ነው (ዘሌዋ.1፥3 እና 13)፡፡ እንደዚሁም፡ በጽንሐ ውስጥ የሚገኘውም እሳት የመለኮቱ ምሳሌ ነው



ቱና በደል፥ ሕግ መተላለፋቸውንም ከተናዘዘ በኋላ ፍየሉን የሕዝቡን በደል ሁሉ እንደ ተሸከመ ጠፍቶ እንዲቀር ወደ በረሐ ይሰደዋል፤ እርሱም እንደገና ፈጽሞ አይታይም (ዘሌ.16፥20-22)፡፡ የዚህንም ትርጉም ነቢዩ ዳዊት ከጌታ ጋር በማያያዝ አስረድቷል፡ "ምሥራቅ ከምዕራብ እንደ ሚርቅ፡ እንዲሁ ኃጢአ ታችንን ከእኛ አራቀ" (መዝ.102፥12)፡፡

8. የመዳን ምሥጢር የደኅንነት ትርጉም ማለት በክርስቶስ ሰውነት የሚቀርበው መሥዋዕት እና የሚከፈለው ካሣ ዓይነትና ሁኔታን ሰዎች ከመረዳታቸውና ከማወቃቸው በፊት ረጅም ክፍለ ዘመን መኖሩ አስፈላጊ ሆኗል፡፡

ስለዚህም ምክንያት ብዙ ትውልዶች አለፉ፡፡ ያለ ደም ሥርየተ ኃጢአ ት እንደ ሌለና እንዲሁም በደለኛና ኃጢአተኛ ሰው ይድን ዘንድ ንጹሕ መሥዋዕት እንደ ሚያስፈልግ የሰው ልጆች ባለፉት ረጅም ዘመናት በቂ ግንዛቤ እንዲያገኙ ሆኗል፡፡ ነገር ግን ያ ንጹሕ መሥዋዕት ማነው? እንዲሞት ከተፈረደበት ከሰው ዘር እንደሆነ በእርግጥ ሰዎች ያውቁ ነበር፤ እርሱም የሰው ልጅ (ወልደ እጓለ እመሕያው) ነው፡፡ እርሱም ከቅድስት ድንግል የሚወለደው መድኃኒታችን እንደሆነ ታወቀ፡፡ "እነሆ ድንግል፡ ትፀንሳለች፡ ወንድ ልጅም ትወልዳለች፡ ስሙን አማኑኤል ብላ ትጠራዋለች" (ኢሳ.7፥14)፡፡

እነዚህና ሌሎችም የትንቢት ቃል እውነተኛውና ንጹሕ አማናዊው መሥዋዕት ክርስቶስ እንደሆነ ይመሰክራሉ፡፡

እንግዲህ እስካሁን ከተ.ቁ.1-8 የተመለከትነው ከጥንት ጀምሮ ሰዎች በፈጸሙት በደል ምክንያት ከእግዚአብሔር ስለተለዩ ለኃጢአታቸው ሥርየት ለበደላቸው ምሕረት የሚያገኙበትን መንገድ ሰውን ወዳጅ እግዚአብሔር በታሪክና በምሳሌ አስተምሯቸዋል፡፡ በነቢያቱም አስረድቷቸዋል፡፡ ይህም መን ገድ የመዳናቸውን ምሥጢር በእንስሳት መሥዋዕት በምሳሌ ሲሠራበት ኖሮ ኖ ሮ በዘመኑ ፍጻሜ በአማናዊው መሥዋዕት በክርስቶስ መስቀል ተደምድሟል፡፡ መሥዋዕት አያስፈልግም ለሚሉት የሃይማኖት ወገኖች ከዚህ በላይ የተመለከት ነው የእግዚአብሔር ቃል ይመሰክርባቸዋል፡፡ እኛስ የእግዚአብሔርን ቃል ምስክርነት እንቀበላለን፤ እንደ ትንቢቱም ቃል ክርስቶስ ለኃጢአታችን ቤዛ ሆኖ አድኖናል፤ ሎቱ ስብሐት፡፡

እንግዲህ ሁሉም ሰው በራሱ ወንጀል እጅ ከፍንጅ በመያዙ ሁሉም በእግዚአብሔር ሕግና ፍርድ ሥር ስለነበር ክርስቶስ እኛ በበደልን እርሱ ካሣ የኃጢአታችንን ዋጋ ሞታችንን በሞቱ ሽሮ እዳችንን በወርቀ ደሙ ከፍሎ አ ድኖናል፡፡ ይህንንም ለማድረግ በመጀመሪያ ሰው ሆነ፡፡ ከሰውም ጋር ተዛመደ፣ የሥጋንና የነፍስን ባሕርይ ገንዘብ አደረገ፡፡ ቃል ሥጋ ሆነ (ዮሐ.1፥14)፡፡ ... በስተቀር ከእኛም እንደ አንዱ ሆነ፡፡ የመለኮቱ ባሕርይ ሳይለወጥ፤ ሳ

www.ethiopianorthodox.org

ይቀላቀል፣ ሳይለያይና ሳይከፋፈል ከሥጋ ጋር ተዋሐደ፡፡ ሥግው ቃል ማለት ሰው የሆነ ቃል፣ መለኮትና ትስብእት ተዋሕደው አንድ አካል አንድ ባሕርይ ሆኑ ማለት ነው፡፡[55] በዚህም አባባል "ክርስቶስ ማለት ፈጣሪና ፍጡር አን ድ አካል አንድ ባሕርይ በመሆን አንድ ሆነ ማለት ነው" ሲል የኑሲስ ኤጲስ ቆጶስ ቅዱስ ጎርጎርዮስ ጽፏል፡፡ ገለጻውንም በመቀጠል እንዲህ ብሏል፡፡ "ዓ ለም ሳይፈጠር የነበረ፣ ለዘላለሙ የሚኖር፣ ያለውን ሁሉ የፈጠረ እርሱ ነውና ስለእሱ ስንናገር ያልተፈጠረ ነው እንላለን (መዝ.102 /101/25፡27፤ ዕብ. 1፡1-14)፡፡ ሰው ነው ያልነውም ስለ እኛ ባደረገው ተዋሕዶ ደካማ ባሕርያችንን ስለ ተዋሐደ ነው" (ሃይማኖተ አበው፣ ገጽ 119)፡፡

እንግዲህ ክርስቶስ በቃልነቱ በመለኮቱ ዓለም ሳይፈጠር የነበረ ከእግዚአብሔርም የተገኘ አምላክ ወልደ አምላክ እንደሆነ ባለፉት አንቀጾች ተመልክተናል፡፡ በሥጋው ደግሞ ከአዳም ተገኝቷል፡፡ እኛን ሰዎችን ለማዳን ከእኛ ጋር ዝምድናን መሥርቷል፡፡ ከቅድስት ድንግል ማርያም ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍሷ ነፍስ ነሥቶ በመንፈስ ቅዱስ ግብር ሰው በመሆኑና በመወለዱ ከአዳም ልጆች ጋር ያለውን ዝምድና በተዋሐደው ሥጋ አጽንቶታል፡፡ ከቅድስት ድን ግል ማርያም በመወለዱ የእግዚአብሔር ልጅ የሰው ልጅ ሆኗል፤ እርሷም የእግዚአብሔርን ልጅ ክርስቶስን በመውለዷ የአምላክ እናት ሆናለች፡፡ ስለዚህ ክርስቶስ ሁለት ልደት እንዳለው እናምናለን፡፡ ቅድመ ዓለም ከአብ ያለ እናት መወለዱ፣ አንድ ልደት፣ ድኅረ ዓለም ከእመቤታችን ያለ አባት መወለዱ፤ ሁለት ልደት፣ ወልደ አብ ወልደ ማርያም በተዋሕዶ ከበረ በማለት የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖታችንን እንገልጻለን፡፡ ከዚህ ቀጥሎ ስለ ጌታችን ሁለተኛ ልደት ከመግለጻችን በፊት መጀመሪያ በሥጋ ስላስገኘችው ስለ ወላጅ እናቱ በጥቂቱም ቢሆን ማወቅ ይገባናል፡፡ ምክንያቱም የሥጋዌ ምሥጢር በድንግል እናቱ አማካይነት የተጀመረ ስለሆነ ነው፡፡ ቃል ሥጋ የሆነው ከእርሷ ነውና፡፡

## ሐ) ስለ ቅድስት ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክ
## ("ሥጋን . . . አዘጋጀህልኝ" ዕብ.10፥5)

ከላይ እንደ ተመለከትነው እግዚአብሔር ሰውን ለማዳን ሰው ለመሆን ስላሰበ በሥጋም በነፍስም ኃጢአት የሌለበትን ንጹሕ ሰውነት ይፈልጋል፡፡ ኃጢአተኛ ሰው ለኃጢአተኞች መድኅን ሊሆን አይችልም፤ በራሱ ኃጢአት ይሞታል እንጂ፣ ለኃጢአተኞች ተላልፎ ሊሰጥ የሚችል በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት ያለው መሥዋዕት ንጹሕ ቅዱስ መሆን አለበት፡፡ የኦሪት መሥዋዕ ትም የእንስሳት መሥዋዕት ስለሆነ የሰውን ልጅ ከኃጢአትና ከሞት ሊያድ

[55] ስለ ክርስቶስ ባሕርይ የሚከተለው የስምምነት ቃል ተዘጋጅቷል፡፡ "ጌታችን አምላካችን መድኃ ኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፤ ሥግው ቃል በአምላክነቱ ፍጹም፤ በሰውነቱም ፍጹም መሆኑን እናምናለን፡፡ ያለ መቀላቀል ፤ያለ መዳበል ፤ ያለ መደባለቅ ሰውነቱን ከመለኮቱ ጋር አንድ አደረገ፡፡ መለኮቱ ከሰውነቱ ለአንድ አፍታ ወይም የዓይን ጥቅሻ ያህል እንኳ አልተለየም፡፡
. . . የሁለቱን የንስጥሮስንና የአውጣኪን ትምህርቶች እናወግዛለን፡፡"

Agreed Statement On Christology

"We believe that our Lord, God and savior Jesus Christ, the Incarnate-Logos is perfect in His Divinity and perfect in His Humanity. He made His Humanity One with His Divinity without Mixture, nor Mingling, nor Confusion. His Divinity was not separated from His Humanity even for a moment or twinkling of an eye.

At the same time, we anathematize th
H.H. Pope Shenouda III, The Nature

www.ethiopianorthodox.org



ነው አልቻለም፡፡ ስለዚህም የኦሪትን "መሥዋዕትንና መብዐን አልወደድህም ሥጋን ግን አዘጋጀህልኝ" ተብሎ እንደ ተጻፈው አካላዊ ቃል ወልድ የሚዋሐደውን ንጹሕ ሥጋ ከየትና እንዴት እንደሚያገኝ እርሱ ባወቀ ሥጋን አዘጋጅቷል (ዕብ.10፥5-7)፡፡ ይችውም ከጥንት ጀምሮ በልበ አምላክ የታሰበች አዲስቱ ሔዋን ቅድስት ድንግል ማርያም ነበረች፡፡ የመጀመሪያይቱ ሔዋን በኃጢአቷ ወድቃ ተረግማ እንዳትቀር ያሳታትን ጠላቷን የሰይጣንን ራስ የሚቀጠቅጥላት፣ እርሷንም የሚያድናት ከዘርዋ እንደሚመጣ እግዚአብሔር ተስፋ ሰጥቷት ነበር (ዘፍ.3፥15)፡፡ ተስፋውም ከእመቤታችን የሚገኝ ሆኗል፡፡ የሴቲቱ ዘር የተባለው ንጹሕ ዘር የተገኘው ከእመቤታችን ሥጋና ነፍስ ነው፡፡ እመቤታችን ከጥንተ አብሶ በፊት እንደ ነበረችው እንደ መጀመሪያይቱ ሔዋን ያለ ኃጢአት ተፈጥራለች፤ ያንንም ንጹሕ ፍሬ መድኃኒታችንን አስገኝ ተለች፡፡ አካላዊ ቃል ወልድ ከእርሷ የነሣውን ማለት የወሰደውን ሥጋንና ነፍስን ተዋሕዷልና፡፡

እንግዲህ አዲሲቱ ሔዋን ከአዳም ኃጢአት ማለት ከጥንተ አብሶና ከሌላውም የኃጢአት ዓይነት ሁሉ የነጻችና የተቀደሰች ነች፡፡ ለምሥጢረ ሥጋዌ በቅድሚያ የተዘጋጀች፣ ከመርገመ ሥጋ ከመርገመ ነፍስ ተጠብቃ በእግዚአ ብሔር ጥበብ የተፈጠረች እርሷ ብቻ ነበረች፡፡ ይህማ ባይሆን ኖሮ መለኮት እን ዲዋሐደው የሚገባ ንጹሕ ሥጋ ከየት ይገኝ ነበር? ከንጹሕ ምንጭ ንጹሕ ውኃ ይቀዳል፡፡ በቆሻሻ ከተበከለ ምንጭ ንጹሕ ውኃ ማግኘት አይቻልም፡፡ ስለዚህ በአዳም ኃጢአት ከረከሰው ምንጭ ንጹሕ ዘር ማግኘት ስለማይቻል እግዚአ ብሔር በጥበቡና በችሎታው አዲሲቱን ሔዋንን ያለ ኃጢአት ንጽሕት ቅድስት አድርጎ ፈጥሯታል፡፡ "ወኢረኰሰት በምንትኒ እምዘፈጠራ" ማለት ከፈጠራት ጀምሮ በምንም በምን /ከድንግልናዋ አልተለወጠችም አላደፈችም/ በማለት ቅዱስ ቴዎዶጦስ መስክሯል (ሃይማኖተ አበው፣ ገጽ 174)፡፡ የአምላክ እናት ድንግል ማርያም በእውነት ያለ አዳም ኃጢአት እንደ ተወለደች እናምናለን፡፡

መለኮታዊ ቃል ከንጽሕት ድንግል ማኅፀን አደረ፤ ለራሱ የሚሆነውን ሥጋን አዘጋጀ (ዕብ.10፥5)፡፡ ይህችንም ንጽሕት ሥጋ የሥራው ሁሉ መጀመሪያ አድርጎ ፈጠራት (ምሳ.8፥22 ግዕዙን ተመልከት)፡፡ ከንጽሕት ድን ግል የነሣውንም ማለት የወሰደውን ሥጋና ነፍስ በመዋሐድ በኀቱም ድንግልና ተፀንሶ በኀቱም ድንግልና ተወልዷል፡፡ "እነሆ ድንግል ትፀንሳለች ወንድ ልጅም ትወልዳለች ስሙንም አማኑኤል ብላ ትጠራዋለች" ተብሎ ነቢዩ ኢሳይያስ እንደ ተናገረው ተፈጸመ (ኢሳ.7፥14)፡፡ ይኸው ነቢይ አሁንም እንዲህ ጽፏል፡ "ሕፃን ተወልዶልናልና፣ ወንድ ልጅም ተሰጥቶናልና፤ አለቅነትም በጫንቃው ላይ ይሆናል፣ ስሙም ድንቅ መካር፣ ኃያል አምላክ፣ የዘላለም አባት፣ የሰላም አ ለቃ ተብሎ ይጠራል" (ኢሳ.9፥6)፡፡ እንግዲህ ከድንግል ማርያም የተወለደው ሥግው ቃል ኢየሱስ ክርስቶስ ስሙ ብዙ ነው፤ ድንቅ መካር፣ ኃያል አምላክ ይባላል፤ እርሷም እመ አምላክ፣ ወላዲተ አምላክ ተብላ ትጠራለች፡፡ በእው ነትም ድንቅ መካር ለሆነው ለኃያል አምላክ እናት ሆናዋለችና፡፡

እመቤታችን የክርስቶስ እናት እንደ መሆኗ መጠን ለእርሱ የሚነገረው የማዕርግ ስም ለእርሷም ለእናትነቷ ይሰጣል፡፡ ልጅዋ ብርሃን ሲባል እናቱ እመ ብርሃን (የብርሃን እናት)፣ ልጅዋ አምላክ ሲባል እናቱ እመ አምላክ (የአምላክ እናት) መባል ይገባታል በማለት የእስክንድርያና የመንበረ ማርቆስ ፓትርያርክ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ሲኖዳ ሣልሣዊ በእንግሊዝኛ በተተረጐመው መጽሐፋቸው ገልጸዋል፡፡[56]

[56] H.H. Pope Shenouda III, Comparative Theology (1988) p.105

በኤፌሶንም በ431 ዓ.ም. በተደረገው በሦስተኛው የቤተ ክርስቲያን ጉባኤ የተሰበሰቡት 200 አበው ሊቃውንት እመቤታችን ሰው ለሆነው አምላክ እናት ነች እንጂ መለኮትነት ለሌለው ሰው ብቻ እናት ነች ማለት ስህተት መሆኑን በመግለጽ፣ ይህን ኑፋቄ የሚያስተምሩትን ንስጥሮስንና ተከታዮቹን አውግዘው፣ እመቤታችን ሰው ለሆነው አምላክ እናት መሆኗን መስክረዋል፡፡ ስለዚህም ወላዲተ አምላክ፣ እመ ብርሃን በማለት በዚሁ ጉባኤ በተወሰነው የሃይማኖት ቀኖና መቅድም ላይ ገልጸዋል፡፡

## ስለ ወላዲተ አምላክ ዘላለማዊ ድንግልና

ቅድስት ድንግል ማርያም የአምላክ እናት በመሆኗ ድንግልናዋ ለዘላለም የተጠበቀ ነው፡፡ እርሷ በሃሳብም በሥጋም ድንግል ነች፡፡ ከመውለዷም በፊት ከወለደችም በኋላ ለዘላለም ድንግል ናት፡፡ ይህ ነገር ከተፈጥሮ ሁናቴ በላይ ነው፡፡ እርሷ እንደ ገለጸችው “ብርቱ የሆነ እርሱ በእኔ ታላቅ ሥራ አድርጓልና” (ሉቃ.1፥49) ያለችው በእርሷ ላይ የተፈጸመውን አምላካዊ ሥራ ያመለክተናል፡፡ የእግዚአብሔር ማደሪያና ማረፊያ የሆነው ሁሉ ለአምላክ አገልግሎት የተለየና የተቀደሰ ሆኖ በታላቅ ክብር ይጠበቃል፡፡ በብሉይ ኪዳን ታቦተ ጽዮን የእሥራኤል አምላክ ማደሪያ ስለ ነበረች በቅድስተ ቅዱሳን ማንም ሳይነካት ትኖር ነበረች፡፡ ሊቀ ካህናቱ ብቻ በዓመት አንድ ጊዜ ይገባ እንደ ነበር ተጽፏል (ዕብ.9፥7)፡፡ እንግዲህ የብሉዩ ይህን ያህል ከተከበረ የሐዲስ ኪዳኑ ምን ያህል ይበልጥ? ስለዚህ የጌታ ማደሪያ የሆነችውን አማናዊቷን ታቦት ማን ደፍሮ ሊቀርባት ይችላል? ለአምላክ የተዘጋጀው ለአምላክ ብቻ እንጂ ለሰው አይሆንም፡፡

እመቤታችን ለአምላክ እናትነት በተለይ በንጽሕናና በቅድስና የተፈጠረች ድንግል እናት ነች፡፡ ሰው የሆነውን አምላክ ወልዳለች እንጅ በሥጋ የወለደችው ሌላ ልጅ ፈጽሞ የላትም፡፡ የአንድ የኢየሱስ ክርስቶስን እናት ሌሎችንም ልጆች እንደ ወለደች አድርጐ እንዴት ይታሰባል? ክርስቶስን ለማዋረድ ወይስ ለማክበር? እኛስ በወንጌል እንደ ተጻፈው አንድ ክርስቶስን ብቻ እንደ ወለደች እናምናለን፡፡ ሌላም ልጅ ልትወልድ አትችልም፡፡ ምክንያቱም ድንግልናዋ የዘላለም ነውና፡፡ እርሷ፣ የእሥራኤል አምላክ በሚተላለፍበት በቤተ መቅደስ በር ትመሰላለች፡፡ ነቢዩ ሕዝቅኤል እንደ ተናገረው በዚች በር ማንም ሰው አይገባም፡፡ ለዘላለም ተዘግታ ትኖራለች በማለት ስለ እመቤታችን የዘላለም ድንግልና መስክሯል፡፡ “ወደ ምሥራቅም ወደ ሚመለከተው በስተ ውጭ ወዳለው ወደ መቅደሱ በር አመጣኝ፤ ተዘግቶም ነበር፡፡ እግዚአብሔር፦ ይህ በር ተዘግቶ ይኖራል እንጂ አይከፈትም፣ ሰውም አይገባበትም፤የእሥራኤል አምላክ እግዚአብሔር ገብቶበታልና ተዘግቶ ይኖራል” (ሕዝ.44፥1-2)፡፡

ይህ ትንቢት የተነገረው ለእመቤታችን ነው እንጂ በድንጋይ ታንፆ ለተሠራ ሕንፃ ቤተ መቅደስ አይደለም፡፡ ምክንያቱም ለዘላለም ተዘግቶ የሚኖርና ሰው የማይገባበት እንደዚህ ዓይነት የመቅደስ በር ታይቶ ተሰምቶም አይታወቅም፡፡ በታሪክ መጽሐፍም አይገኝም፡፡ ስለዚህ ነቢዩ ሕዝቅኤል በራእዩ ያየው ለዘላለም ተዘግቶ የሚኖረው የቤተ መቅደስ በር ስለ እመቤታችን ዘላለማዊ ድንግልና እንደሆነ ግልጽ ነው፡፡

ስለ ቅድስት ማርያም ድንግልና በቅዱሳት መጻሕፍት የተጻፈውንና በጥንቷና በሐዋርያዊቷ ቤተ ክርስቲያንም የተመሰከሩትን ችላ በማለት አንዳንድ ወገኖች በራሳቸው አስተያየትና ግምት የጥንቱን ወንጌል፣ ትላንትና እንደ ተጻፈ



ጋዜጣ በመተርጐም ራሳቸው ተሳስተው ሌሎችንም በአእምሮ ሕፃናት የሆኑትንና እምነተ ደካሞችን ያሳስታሉ፡፡ ቅዱስ ወንጌል በቤተ ክርስቲያን ለቤተ ክርስቲያን የተጻፈ ነው እንጂ ማንም ግለሰብ ወንጌሉ የተጻፈበትን ጊዜና ታሪክ፣ ባሕልና ሥልጣኔ፣ የተጻፈበትንም ቋንቋ ሌሎችንም ነገሮች ሳያገናዝብ እንደ መሰለው በመላና በግምት ቢተረጉም ከታላቅ ስህተት ላይ ይወድቃል፡፡ አይሁድ ጌታችንን ለማጥላላት ይህ ኢየሱስ የአናጢው የዮሴፍ ልጅ አይደለምን? ወንድሞቹና እኅቶቹስ ከእኛ ጋር አይደሉምን? (ማቴ.13፥55) በማለት የተናገሩትን እንደ አብነት እንደ ማስረጃ ይዞ እመቤታችን ልጆች እንዳሏት አስመስሎ መናገር የጌታን ጠላቶች የአይሁድን ምስክርነት መቀበል ነው፡፡ እነርሱ ጌታ ያለ አባት በመንፈስ ቅዱስ ግብር እንደ ተወለደ አያምኑም፡፡ ይህ ዓይነቱ እውነተኛ ምስክርነት የሚገኘው ወንጌልን ከጻፉት ከሐዋርያትና ከደቀ መዛሙርቱ ነው፡፡ ታዲያ ከሐዋርያትና ከቤተ ክርስቲያን ምስክርነት ይልቅ የአይሁድን የሐሰት ቃል መቀበል ምን ይባላል? አይሁድ ጌታ የዮሴፍ ልጅ ነው ቢሉ፣ እመቤታችን ሌሎች ልጆች አሏት ቢሉ፣ የእነርሱን ቃል ማን ያምናል፡፡ እነርሱ በሐሰት መስክረው በሐሰት የሰቀሉት አይደሉምን? ታዲያ ዛሬ የቀደመውን ውሸት ይዘው የሚያስተጋቡት የማን ምስክሮች ይባላሉ? ማንንስ ይመስላሉ?

ስለ ቅድስት ማርያም “ዘላለማዊ ድንግልና” መንፈስ ቅዱስና ሐዋርያት የመሰከሩት የእምነት ቃል ነው እንጂ የሐዋርያትን ትውፊት ያልተቀበሉ፣ ከጥንቷ ሐዋርያዊት ቤተ ክርስቲያን ውጭ የሆኑ ግለሰቦች ጉዳይ አይደለም፡፡ ከክርስቶስና ከሐዋርያት በውርስ በትውፊት ያገኘነው ቅዱሳት መጻሕፍትን ብቻ ሳይሆን፣ ቃል በቃል ተላልፈው የተጻፉትም ያልተጻፉትም የሃይማኖት ትምህርትና ሥርዓት፣ እንደዚሁም በተግባር የሚፈጸሙትን ሁሉ ጥምር ነው፡፡ ስለ ጌታችን እንኳ ሁሉ ነገር በወንጌል አልተጻፈም፡፡ ዮሐንስ ወንጌላዊ ጌታ ኢየሱስ ያደረገው ሁሉ “ቢጻፍ ለተጻፉት መጻሕፍት ዓለም ራሱ ባልበቃቸውም ይመስለኛል” በማለት አስረድቶናል (ዮሐ.21 ፥25)፡፡ ስለዚህ ከጥንት ጀምሮ ከሐዋርያት በደረሰን የቃልና የተግባር ምስክርነት መሠረት የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ስለ እመቤታችን ቅድስናና ድንግልና እውነተኝነት እንደ አባቶቿ እንደ ሐዋርያት ትመሰክራለች፤ ምስክርነቷም የታመነ ነው፡፡

## “የበኩር ልጇን እስክትወልድ” ስለ ተባለውና ስለ ሌሎችም

ስለ እመ አምላክ ዘላለማዊ ድንግልና በመጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈውን ከሐዋርያት ባገኘነው ትርጉም መሠረት እንማራለን እንጂ ከጥንቷ ከሐዋርያዊት ቤተ ክርስቲያን ውጭ በግለሰቦች የፍልስፍና ትምህርት አንመራም፡፡ እነርሱማ “የበኩር ልጅዋን እስክትወልድ ድረስ አላወቃትም” የሚለውን ገጸ ንባብ ብቻ በመመልከት ከሐዋርያት ምስክርነት ውጭ ሌላ ልጅ ሊኖራት ይችል ይሆናል በማለት በልብ ወለድ አስተያየታቸው ሰዎችን ያሳስታሉ (ማቴ.1፥25)፡፡ በኦሪቱ ሥርዓት አንድ እናት፣ አንድ ልጅ ካላት፣ ይኸው ልጇ የበኩር ልጅ ይባላል፡፡ የግዴታ ሌሎች ልጆች እንዲኖሯት አያስፈልግም (ዘፀአ.13፥1-2)፡፡ ሌላው ደግሞ “እስክትወልድ ድረስ አላወቃትም” የተባለው ከወለደች በኋላ አወቃት ለማለት አይደለም፡፡ የሳኦል ሴት ልጅ ሜልኮል እስክትሞት ድረስ ልጅ አልወለደችም ተብሎ ተጽፏል፡፡ ታዲያ ከሞተች በኋላ ወለደች ማለት ነውን? አይደለም (2ሳሙ.6፥23)፡፡ በሴም ቋንቋ የሰዋስው ሕግ መሠረት “እስከ” የተባለው ተውሳከ ግሥ ፍጻሜ ለሌላቸው ነገሮች ይገባል፡፡ ከጥቅሱ ላይ የተመለከተው ፣ ፍጻሜ የሌለው እስከ መሆኑ ግልጽ ነው (ማቴ.1፥25)፡፡ ፍጻሜ የሌለው “እስከ” በሌሎችም ጥቅሶች ይገኛል (መዝ.109፥1፤ማቴ.28፥20)፡፡ የእግዚአብሔር አ

www.ethiopianorthodox.org

ብ አንድ ልጅ በኩር ይባላል፡፡ በኵር ስለተባለም ሌላ ተከታይ ልጅ አለ ማለት አይደለም (ዕብ.1፥6)፡፡ እንደዚሁም እመቤታችን የወለደችው የበኵር ልጇ አንድ ነው፤ ተከታይም የለውም፡፡ እንግዲህ ከሐዋርያት በተላለፈው ምስክርነት መሠረት እመቤታችን በድንግልና የወለደችው አንድ ክርስቶስን ብቻ እንደሆነ እናምናለን፡፡ ለሌሎችም ይህንኑ እንመሰክራለን፣ እናስተምራለን፡፡

ጌታችንም ለእመቤታችን አንድ ለእናቱ ስለሆነ ያዝንላታል፤ ያስብላታል፡፡ በእለተ ዓርብ ሕማምና መከራን እየተቀበለ ሳለ ከመስቀሉ ላይ ሆኖ ለሚወደው ደቀ መዝሙር የእናቱን ነገር በአደራ እንዲጠብቅ ነግሮታል (ዮሐ.19፥26-27 )፡፡ ሌሎች ልጆች ቢኖራት ኖሮ እነርሱ ይጠብቋት ነበር፡፡ ነገር ግን ሌሎች ልጆች ስለሌሉ ዮሐንስ ልጅ እንዲሆናትና እንዲጠብቃት ክርስቶስ ፈቃዱ ሆኗል፡፡ ስለዚህ ክርስቶስ ለሚወዳቸው ክርስቲያኖች ሁሉ የሰማይ አባቱን አባታችን እንዲሆን፣ የወለደችው እናቱንም እናታችን እንድትሆን በመፍቀዱ ሁላችንንም በመንፈስ ቅዱስ ሱታፌ አንድ ቤተሰብ አድርጐናል፡፡

ቅዱስ ዮሴፍ እጮኛዋ የተባለው ለጥበቃ፣ ለእርዳታና አገልግሎት በእግዚአብሔርና በሰው ተመርጦ ኃላፊነት የተሰጠው "ጻድቅ" ሰው ስለ ነበር የእመቤታችንንም ንጽሕናና ድንግልና ስለ ሚያውቅ በድንግልና ሆና መፅነሷን አውቆ እንደሰወራት ተጽፏል (ማቴ.1፥18-25)፡፡ የእግዚአብሔርም መልአክ በሕልም ተገልጾለት በመንፈስ ቅዱስ ግብር እንደ ፀነሰች ምሥጢሩን ገልጾለታል፡፡ ከተወለደም በኋላ፣ ሄሮድስ ሕፃኑን ሊገድለው ስለ ሚፈልግ፣ የጌታ መልአክ ለቅዱስ ዮሴፍ ተገልጾ ሕፃኑንና እናቱን ወደ ግብፅ ይዞ እንዲሸሽ ነግሮታል፡፡ በየጊዜው ከጌታ መልአክ ለዮሴፍ የሚሰጠውን መግለጫና መመሪያ ሁሉ አስተውለንና ተረድተን የእውነትን መንገድ መከተል ይኖርብናል እንጂ ላይ ላዩን በስሜት መጋለብ፣ በግምት መፍረድና የአይሁድን አሉባልታ ማስተጋባት የሐሰተኞች ተባባሪ መሆን ነው፡፡ እንግዲህ ቅዱስ ዮሴፍ በሰው ዘንድ እጮኛዋ በመባል ሲታወቅ፣ በእግዚአብሔር ዘንድ ግን "የእናቱና የሕፃኑ" ጠባቂና ረዳት፣ ሞግዚትና አገልጋይ እንደ ነበረ እንገነዘባለን፡፡ አባ ሕርያቆስም "አ ድንግል አኮ ለዮሴፍ ዘተፍኅርኪ ለተቃርቦ አላ ከመ ይዕቀብኪ ንጹሐ . . . " "ድንግል ሆይ ለዮሴፍ የታጨሽ ለመገናኘት አይደለም፣ ንጹሕ ሆኖ ሊጠብቅሽ ነው እንጂ" (ቅዳሴ ማርያም፣ ቁ.44) ሲል መስክሯል፡፡ የጥንቷ የሐዋርያዊት ቤተ ክርስቲያን ምስክርነትም ይኸው ነው፡፡

የጌታ ወንድሞችና እኅቶች (ማቴ.13፥53-58) ስለ ተባለውም ለመረዳት በቅድሚያ የጥንት የዕብራውያንን ቋንቋና ባሕል ታሪካቸውንም ማወቅ ያስፈልጋል፡፡ በእነርሱ አነጋገር ወንድም ወይም እኅት ማለት ከአንድ አባት ወይም ከአንድ እናት የተወለዱትን ብቻ ሳይሆን ከአንድ አያት የተወለዱትን ቤተ ዘመድና የእንጀራ ልጆችን ሁሉ ያመለክታል፡፡ የአጐት ወይም የአክስት ልጆች ሁሉ ወንዶች ከሆኑ ወንድሞች፣ ሴቶች ከሆኑ እኅቶች ይባላሉ፡፡ የወንድም ወይም የእኅት ልጆችም እንደዚሁ ይጠራሉ፡፡ ስለዚህ ነው የአብርሃም የወንድሙ ልጅ ሎጥ "ወንድሙ" እንደሆነ የተጻፈው፤ ላባም ያዕቆብን ወንድሜ ያለው (ዘፍ.14፥14፤12፥5፤29፥13-15)፡፡

እነ ያዕቆብና ይሁዳ የጌታ ወንድሞች የተባሉበት ምክንያት የሩቅ ዝምድናን ለማመልከት እንደሆነ ግልጽ ነው፡፡ ምክንያቱም ያዕቆብ በመልእክቱ "የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ ባሪያ" እንደሆነ ጻፈ እንጂ ወንድሙ እንደሆነ አልገለጸም (ያዕቆብ 1፥1)፡፡ እንደዚሁም ይሁዳ በመልእክቱ "የኢየሱስ ክርስቶስ ባሪያ የያዕቆብም ወንድም የሆነ ይሁዳ" በማለት ጽፏል (ይሁዳ 1) እንግዲህ እዚህ ላይ አስተውሉ፡፡ መናፍቃን እንደሚሉት ያዕቆብና ይሁዳ የክርስቶስ ወንድሞች ቢሆኑ ኖሮ ይሁዳ ያዕቆብን ወንድሙ እንደሆነ እንደ ገለጸ ጌታም ወንድሙ እንደሆነ ባመለከተ ነበር፡፡ ነገር ግን ይሁዳ ለክርስቶስ አገልጋዩ እንደሆነ መሰከረ እንጂ ወንድሙ እንደሆነ አልጻፈም፡፡



እንግዲህ ጌታን የዮሴፍ ልጅ እንደሆነና ወንድሞችም እንዳሉት የሚናገሩት አይሁድ፤ በክርስቶስ መሰናከላቸው በግልጽ የተጻፈ መሆኑን እያስታወስን፣ ዛሬም ተመሳሳይ ነገርን የሚናገሩ ሁሉ ክርስቶስን የተቀበሉ ሳይሆኑ በክርስቶስ የተሰነካከሉ መሆናቸውን እወቁ፡፡ ስለዚህ ከእንደነዚህ ዓይነቱ አይሁዳውያን መናፍቃን፣ ምእመናን ሁሉ ራሳችሁን እንድትጠብቁ አደራ እንላችኋለን (ማቴ.13፥53-58 ፤ ማር.6፥1-6 )፡፡

## *የጸሎትና የምልጃ ሁኔታዎች*

በቃና ዘገሊላ ለእመቤታችን ልመና ጌታ ሲመልስ "አንቺ ሴት ከአንቺ ጋር ምን አለኝ" በማለቱ ልመናዋን ያቃለለ ወይም የተቃወመ የሚመስላቸው ቢኖሩ ተሳስተዋል፡፡ እንደዚህማ ቢሆን ኖሮ የለመነችውን ባልፈጸመላትም ነበር፡፡ እርሷም ይኸን መልስ ከልጇ እንደ ሰማች ለአገልጋዮቹ፡- "የሚላችሁን ሁሉ አድርጉ" ብላ ባልነገረቻቸውም ነበር፡፡ በአጠቃላይ የታሪኩ ሁኔታ የሚያሳየው ጌታ በአምላክነቱ አገብሮት እንደሌለበት ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ በእመቤታችን አማካኝነት አገልጋዮቹ ጌታ የሚላቸውን ሁሉ አምነው በማድረጋቸው ምልጃው ተፈጻሚነት ማግኘቱን ነው፡፡ ከታሪኩ እንደ ምንረዳው ይህን ተአምራት መፈጸሙን የሚያውቁ አገልጋዮቹ እንጂ አሳዳሪው ወይም ሙሽራው አያውቁም ነበር፡፡ ጌታም ይህን በማድረጉ "ክብሩን ገለጠ፥ ደቀ መዛሙርቱም በእርሱ አመኑ" ተብሎ ተጽፏል (ዮሐ.2 ፥11 )፡፡

እመቤታችን ጸሎቷና ምልጃዋ ለሚገባቸው ሁሉ ይደርሳቸዋል፡፡ እንደዚሁም በእግዚአብሔር ፈቃድና ቸርነት የቅዱሳን ጸሎትና በረከት የማይለያቸው ወገኖች አሉ፡፡ ነገር ግን የቅዱሳን ጸሎትና ምልጃ የማይገባቸው ሰዎችም አሉ፡፡ ለሁሉም እንደየ ሁኔታው እርሱ ባወቀ የሚወስንና የሚፈጽም እግዚአብሔር ብቻ ነው፡፡ ጌታ፥ ወገኖቹ እሥራኤል እንኳ፥ እርሱን ከማምለክ ፈቀቅ ባሉ ጊዜ ፥ ቃል ኪዳኑንም ባፈረሱ ጊዜ በዓመፅም ሥራ በጸኑ ጊዜ ጸሎትና ምልጃ የማይገባቸውና የማያስፈልጋቸው መሆናቸውን ገልጿል፡፡ ስለዚህም ነቢዩ ኤርምያስን እንዲህ አለው፡- "እንግዲህ አልሰማህምና ስለዚህ ሕዝብ አትጸልይ ስለ እነርሱም ልመናና ጸሎት አታድርግ፤ አትማልድላቸው" (ኤር.7፥16፤14፥11-12)፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ይኸው ነቢይ እንዲማልድላቸው ለጠየቁት ጥቂት ከምርኮ የተረፉ የይሁዳ ቅሬታዎች (ትሩፋን) ከአሥር ቀን በኋላ የእግዚአብሔርን ቃል አመጣላቸው (ኤር.42፥2-8)፡፡ የጸሎቱንም መልስ ነገራቸው፡፡

> "እንዲህም አላቸው፡፡ ጸሎታችሁን በፊቱ አቀርብ ዘንድ ወደ እርሱ የላካችሁኝ የእሥራኤል አምላክ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፡- ስላደረግሁባችሁ ክፉ ነገር ተጸጽቻለሁና በዚህች ምድር ብትቀመጡ እሠራችኋለሁ እንጂ አላፈርሳችሁም፥ እተክላችኋለሁ እንጂ አልነቅላችሁም፡፡ ከምትፈሩት ከባቢሎን ንጉሥ አትፍሩ፤ አድናችሁ ዘንድ ከእጁም አስጥላችሁ ዘንድ እኔ ከእናንተ ጋር ነኝና አትፍሩ፥ . . . እናንተ ግን፡- በዚህች ምድር አንቀመጥም ብትሉ የአምላካችሁንም የእግዚአብሔር ቃል ባትሰሙ፥ . . . ወደ ግብጽ ትገቡ ዘንድ በዚያም ትቀመጡ ዘንድ ፊታችሁን ብታቀኑ፥ የምትፈሩት ሰይፍ በዚያ በግብጽ ምድር ያገኛችኋል፥ ስለ እርሱም የምትደነግጡበት ራብ በዚያ በግብጽ ይደርስባችኋል፥ በዚያም ትሞታላችሁ" (ኤር.42፥9-16)፡፡

እንግዲህ የጸሎቱና የምልጃው መልስ እንዲህ መልካም ተስፋ ያለው ሆኖ ሳለ እነርሱ ግን በእምቢተኝነት የእግዚአብሔርን ቃል ባለመስማት ሀገራቸውን ትተው ወደ ግብጽ ስለ ሄዱ በሰይፍ፥በራብና በቸነፈር አልቀዋል (ኤር.

www.ethiopianorthodox.org

13፥46፥13-28)። የታሪኩ ሁኔታ እንደ ሚያስገነዝበን እነዚህ ሰዎች በአንድ በኩል የነቢዩን ጸሎትና ምልጃ ሲጠይቁ በሌላ በኩል ደግሞ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ እ ለመፈጸማቸውን ነው። ይህ ሁኔታ ዛሬም በአንዳንድ ሰዎች ላይ ይታያል። የነቢዩን ወይም የሐዋርያውን ጸሎትና ምልጃ እየተማጸኑ በሌላ ወገን ደግሞ የነቢዩን ወይም የሐዋርያውን ቃል ባለመስማትና ባለመከታተል ተማጽኗቸው ሕፀጽ ያለበት ሆኖ ይቀራል። ስለዚህ እኛም ሁላችን የቅዱሳንን አማላጅነት በምንጠይቅበት ጊዜ እ ስተድመን የእግዚአብሔርን ቃል ከመስማትና ከማድረግ ጋር መሆን እንዳለበት መማርና ማስተማር ይኖርብናል። እኛ ቅዱሳንን በምንለምንበት ጊዜ እነርሱ ደግሞ እኛ እነርሱን እንድንመስላቸውና በግብርም እንድንከተላቸው ይጠይቁናል። ስለዚህ ነው ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ "እኔ ክርስቶስን እንደምመስል እኔን ምሰሉ ብሎ የጻፈው" (1ቆሮ.11፥1)።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ስለ እኛ ያማልዳል። አማላጅም እንደሆነ እርሱ ራሱ ገልጿል። ስለ እርቅ ብሎ ሰዎችንም እግዚአብሔርንም ይለምናል። "እንግዲህ እግዚአብሔር በእኛ እንደሚማልድ ስለ ክርስቶስ መልእክተኞች ነን፤ ከእግዚአብሔር ጋር ታረቁ ብለን ስለ ክርስቶስ እንለምናለን።" ብሎ ያለው ስለ ቆሮንቶስ ምእመናን ብቻ ሳይሆን ስለ መላዋ ቤተ ክርስቲያን ነው (2ቆሮ. 5፥20)። የርሱ ምልጃ የሚገባቸው ሰዎች የእርሱን ትምህርትና ምክር የሚሰሙና የሚፈጽሙ ብቻ ናቸው። ነገር ግን ቃሉን የሚቃወሙትንና ክፉ የሚያደርጉትን፥ እንኳን ሊያማልድላቸው ይቅርና ከማኅበረ ምእመናኑ መካከል እንዲገኙ አይፈልግም። ስለዚህ ነው ለቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ሲጽፍ ክፉውን ከመካከላቸው እንዲያስወግዱ፥ ከእነርሱም ጋር እንዳይተባበሩ የነገራቸው (1ቆሮ. 5፥1-13)። ሆኖም ይህንን ጥቅስና ሌሎችንም በጽሞና ብናነባቸው ክፉ ሥራን የፈጸመ አማኝ በሥጋው ቅጣት ተቀብሎ ነፍሱ በጌታ ቀን እንድትድን የሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ፍላጎትና ጸሎት እንደሆነ እን ማራለን። ከዚህ ሁናቴ የምናየው ነገር ቢኖር ተጸጽቶ ለሚመለስ ሁሉ የጽድቅ በር ሁልጊዜ ክፍት ሆኖ እንደሚጠብቀው ነው (1ቆሮ.5፥5፤ 2ቆሮ.2፥5-11)።

እስካሁን እንደ ተመለከትነው የቅዱሳን ጸሎትና ምልጃ የማይገባቸው ሰዎች እንዳሉ ተምረናል። ለእንደዚህ ዓይነት ሰዎች ማንም ሰው እንዲጸልይላቸው ጌታ አ ይፈቅድም (ኤር.15፥1)። ሞት የማይገባውን ኃጢአት ለሠሩ እንድንጸልይላቸው እንጂ ሞት የሚገባውን ኃጢአት ለሠሩ እንድንጸልይላቸው አልተባለም (1ዮሐ.5፥16-17)። እንዲያውም በአንዳንድ ሁኔታ በክፉ አድራጊዎች ላይ ሊጸለይባቸው የሚገባ ጊዜ አለ። ምሳሌ አድርገን የምንጠቅሰው በዐላውያን ነገሥታት የተገደሉ የሰማዕታት ነፍሳት፥ እግዚአብሔር ገዳዮቻቸውን እንዲበቀልላቸው መለመናቸውን ነው (ራእይ 6፥9-10)።

እንግዲህ ይህን ሁሉ የጠቀስነው የቅዱሳን ምልጃ ክፉ ላልሠሩ ሰዎች እንጂ ለኃጥአን አይገባቸውም አያስፈልጋቸውም ለማለት አስበን አይደለም። እንዲያውም ጸሎት የሚያስፈልገው ለኃጥአን እንደሆነ ግልጽ ነው። ነገር ግን ሁለት ዓይነት ኃጢአተኞች አሉ። አንደኛው ወገን በሠራው ክፉ ነገር የሚጸጸትና የሚመለስ ነው፤ ሌላው ወገን ግን ክፉን ነገር ደስ እያለው የሚያዘወትር፥ ልቡ በትዕቢት የተወጠረ፤ እውነትንና ንስሐን የሚጠላ፥ ሐሰትን የሚወድ፥ በሐሰትም ሥራ የጸና፥ ከላይ እንደ ጠቀስነው ሞት የሚገባውን ኃጢአት የፈጸመ እርሱ ነው።

ስለ በደላቸው ተጸጽተው የሚመለሱት ኃጢአተኞች ሁሉ የቅዱሳን ጸሎትና በረከት አይለያቸውም። እንደነዚህ ዓይነት ተነሣሒያን የካህኑን ምክርና ጸሎት በመጠየቅ የኃጢአት ሥርየትን ያገኛሉ።ነገር ግን ንስሐ የማይገቡት፥ የቅዱሳንን እርዳታ ለማይጠይቁት፥ በክፉ ሥራቸው ለጸኑት፥ እግዚአብሔርን ለካዱት የጥፋት ልጆች በሰማይም በምድርም እነርሱን የሚረዳ መንፈሳዊ ኃይልና ጸጋ ሊኖር አይ ችልም። እነርሱ እንዲህ ከእምነትና ከምግባር ውጭ ሆነው ሳለ በቅዱሳን አማላጅነት ብቻ ይድናሉ የሚል ሰው የሚኖር አይመስለንም። "እኛም ማንም ሰው ቢሆን ከኃጢአቱ ተመልሶ ንስሐ ገብቶ ጸልዩልኝ አማ



ልዱልኝ ሳይል እርሱ በኃጢአት ባሕር እየዋኘ ሌላው ቢጸልይለት ይድናል ብለን አናምንም፥ለሌላውም አናስተምርም" (ኍኆሐ ሃይማኖት፣ ገጽ 169)።

ወደ ቃና ዘገሊላው ታሪክ ወደ እመቤታችን አማላጅነት ስንመለስ ከሌሎቹ የምልጃ ሁኔታዎች ሁሉ የተለየ ሆኖ እናገኘዋለን። ምክንያቱም የእመቤታችን ምልጃ ከምሥጢረ ሥጋዌ ጋር የተያያዘ በመሆኑ ነው። የእርሷ ሕይወትና አኗኗር ከልጇ ሕይወትና ሥራ ጋር የተዛመደ ሆኖ ስለ ተገኘ የል ጇ የደኅንነት ጸጋ ለሰው ሁሉ እንዲዳረስ ትጸልያለች። ይልቁንም የልጇን ጸዋትወ መከራ እያሰቡ ለሚለምኗት ሁሉ የእግዚአብሔር ቸርነትና ረድኤት እን ዳይለያቸው ዘወትር ትማልዳለች። ስለዚህ ነው ምእመናን ሁሉ የአዳኛቸውን የክርስቶስን ሕማምና ሞት እያሰቡ ሰአሊ ለነ ቅድስት (ቅድስት ሆይ ለምኝልን) እያሉ ዘወትር የሚጸልዩት።

## ለእመቤታችን ክብርና ሰላምታ ይገባታል

የአምላክ እናት ስለሆነች እመቤታችንን በከፍተኛ ደረጃ እናከብራታለን። እርሷን ማክበር የጀመረው እግዚአብሔር እንጂ ሰው አይ ደለም። ጌታ ራሱ ነው መጀመሪያ የመረጣትና የለያት፡የቀደሳትና ያከበራት። እግዚአብሔር የሰጣትን ክብር የገለጠልን መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ነበር። እር ሱ ነው ከእግዚአብሔር ሞገስ እንዳገኘች፥ ምልዕተ ጸጋ እንደ ሆነች፥ ለጌታ እናትነትም እንደ ተመረጠች የተናገረው። እኛም እርሱን ተከትለን በእግዚአ ብሔር መልአክ ሰላምታ ሰላም እንላታለን። ለእርሷም የሚገባውን ክብርና ምስጋና እናቀርባለን (ሉቃ.1፥28-35)።

እንግዲህ ለምንድን ነው ተቃዋሚዎች ይህን ሥርዓታችንን የሚነቅፉት? የጌታን እናት ማክበር ከቃለ እግዚአብሔር ውጭ መሆን ማለት ነውን? ምን አልባት ካልሻራችሁት ከአሥሩ ቃላት አንዱ አባትና እናትህን አክብር የሚል ነው። አባትህንና እናትህን የምታከብር ከሆነ እንዴት የአምላክህንና የአ ዳኝህን እናት አብልጠህ አታከብርም! ምናልባት በዘመናዊ ሥርዓትህ በአዲሱ ወግህ የእግዚአብሔርን ቃል ሽረኸው ይሆንን? ወይስ ደግሞ ጌታን ብቻ እንደ ግል አዳኜ ከተቀበልሁ እናቱን ከማክበር ነፃ ነኝ ብለህ አስበሃልን? እርግጥ ነው የሃይማኖት ሥራ ሁሉ በነፃ ፈቃድ የሚፈጸም ነው። ሆኖም ከእግዚአብሔር ትእዛዛት ግማሹን መቀበል ግማሹን መተው አይገባም። ጌታን የወደደ ሁሉ የጌታ የሆነውን ሁሉ መቀበልና ማክበር ይኖርበታል። የጌታን እናትና የጌታን ወዳጆች እየተውና እየናቁ ጌታን ብቻ እወዳለሁ፥እርሱን ብቻ አከብራለሁ ማለት ጌታን የሚያስደስተው ነገር አይሆንም። ጌታ በፈቃዱ ሰውን ለማዳን ወደዚህ ዓ ለም መጥቶ ከሰው ጋር ተዛምዶ አንድ የተቀደሰ ቤተሰብን መሥርቷል። እን ግዲህ በዚህ ቤተሰብ ውስጥ በተፋቅሮና በአክብሮት ሥርዓት መኖር እንጂ እየተናናቅንና እየተነቃቀፍን በእግዚአብሔር ቤት መኖር አይቻልም።

መቼም በመካከላችን ያለውን የእምነትና የሥርዓት ልዩነት ለመጥቀስ ያህል ይህን ጉዳይ አነሣን እንጂ የጌታን እናት ይብዛም ይነስም የማያከብር ክርስቲያን አይገኝም። ይህም ሁኔታ በዓለም አብያተ ክርስቲ ያናት አንድነት ማኅበር አባላት መካከል ቀስ በቀስ እያደገና እየተሻሻለ የሚሄድ ነገር ሆኗል። እንዲህ ሊሆን የቻለው በኦርቶዶክሱ አባላት ጥረት መሆኑ የታወቀ ነው። ነገር ግን ከተቃዋሚዎቹ መካከል አንዳንዶቹ ሲናገሩ ኦርቶዶ ክሶች ለእመቤታችን የሚያቀርቡት ጸሎት፥አክብሮትና ሰላምታ እንደ አምልኮ ይቆጠራል ይላሉ። እኛም ይህ እውነት እንዳልሆነ በምናስረዳቸው ጊዜ ነገሩን ይቀበሉና ወዲያውኑ ሌላ ሃሳብ ያመጣሉ። እርግጥ ነው በሊቃውንቱ መካከል ትክክለኛና ከወሰን በላይ ያልተጋነነ የክብረ ቅዱሳን ሥርዓት ሊኖር ይችላል፥ይላሉ። ነገር ግን በምእመናኑና ትምህርት በጉደላቸው ግለሰቦች ደረጃ

www.ethiopianorthodox.org

ለእመቤታችን፥ለመላእክትና ለቅዱሳን የሚቀርበው አክብሮትና ጸሎት ለእግዚአብሔር እንደ ሚቀርብ አምልኮትና ስግደት የሚቆጠር ነው በማለት ይከራከራሉ፡፡

እኛም ይህ እንዳልሆነና መሆንም እንደ ሌለበት ለእነርሱ በሚስማማ መንገድ መልሳችንን አቅርበናል፡፡ ከእውነተኛውና ከጤናማው የትምህርተ ሃይማኖት ክልልና ወሰን ሳይወጣ (1ጢሞ.6፥3_5) ማንም ክርስቲያን ቢሆን በመጀመሪያ ለእግዚአብሔር የሚገባውን አክብሮትና የአምልኮት ሥርዓት መፈጸም አለበት፡፡ ይህም ማለት አንድ ምእመን ከሁሉ አስቀድሞ ለእግዚአብሔር ቆሞ በሚጸልይበት ጊዜ እርሱ አምላክ፥ ፈጣሪና አዳኝ መሆኑን አምኖና ተማምኖ በአክብሮትና በፍርሃት መጸለይና መስገድ እንዳለበት ይነገረዋል፡፡ ለእመቤታችን ደግሞ ሲጸልይ እርሷ የአምላክ እናት መሆኗን አምኖ የልጇን ጸዋትወ መከራ እያሰበ፥ ከልጇ ጸጋና ምሕረትን እንድታሰጠው ይለምናታል እንጂ ለልጇ የሚገባውን አምልኮና ስግደት ለእርሷ አያቀርብም፡፡ ለእርሷ የሚገባውን ሰላምታ፥ አክብሮትና የጸጋ ስግደት ያቀርባል፡፡ እመቤታችን ከመላእክት ዓለም ወይም ከሰማያዊ ሥፍራ የተገኘች እንዳልሆነች፥ እሷ ግን ከአዳም ዘር የተፈጠረች መሆኗን እናስረዳለን፡፡ በተጨማሪ ደግሞ እርሷ የጌታ እናት እንደ መሆኗ መጠን የአዳም ኃጢአትና መርገም እንደ ሌለባት ምእመናን እንዲማሩት ማድረጋችንን ለተቃዋሚዎች እንዲያውቁት ገልጸናል፡፡

ሆኖም እመቤታችን የአዳም ኃጢአት የለባትም በማለታችን ተቃዋሚዎች ጥያቄ ያነሣሉ፡፡ የእኛ መልስ ግን ንጹሐ ባሕርይ አምላክ የሚያድርባት መቅደስ ፈጽሞ ንጽሕትና ቅድስት መሆን አለባት፡፡ ምክንያቱም እርሱ ባደፈ በጐደፈ በኃጢአት በተበከለ ሰውነት የማያድር ስለሆነ ነው፡፡ ስለዚህም እግዚአብሔር በጥበቡና በኃይሉ እመቤታችንን የራሱ ማደሪያ አድርጐ ስለ መረጣት እርሱ ከአዳም ኃጢአት ነፃ አድርጐ ፈጠራት እንላለን፡፡ የእመቤታችንን ክብርና ልዕልና ከፍ ከሚያደርገው ምክንያት አንዱ ይኸው ን ጽሕናዋና ቅድስናዋ ነው፡፡ እርሷ በልጇ ምክንያት በነፍስም በሥጋም ኃጢአት ስለማታውቅ በመንግሥተ ሰማያት በክብር ቦታ ትገኛለች፡፡ በዮሐንስ ራእይ ለ ሴቲቱ "ክንፎች ተሰጣት" የተባለው ክብሯንና ልዕልናዋን እንዲሁም የእግዚአብሔር ጥበቃ ያልተለያት መሆኑን ሲያመለክት በሌላ በኩል ደግሞ ፍልሰተ ሥጋዋን በክብር ወደ ሰማይ ማረጓን ያስገነዝበናል (ራእይ. 12፥14)፡፡

እንግዲህ ሁላችን ክርስቲያኖች ለጌታ እናት የሚገባውን ክብርና ሰላምታ ለማቅረብ እንስማማለን እንጂ አንጣላም፡፡ ምክንያቱም "ክብር ለሚገባው ክብርን ስጡ" ተብሎ ስለ ተጻፈ ብቻ ሳይሆን ክርስቲያናዊ ኅብረተ ሰብ እርስ በእርሱ በመፈቃቀር በትኅትናና በመከባበር የተመሠረተ ስለሆነ ነው (ሮሜ.13፥7)፡፡ አንዱ ሌላውን ማክበር ማለት በትኅትና መተሳሰብ ማለት ስለ ሆነ እውነተኛ መንፈሳዊነትን ያሳያል፡፡ በዚያውም የክርስቶስን ትኅትና መከተላችንን ያመለክታል፡፡

ስለ እመቤታችን ክብርና ብፅዕና ስንናገር አንድ ቅሬታ እንዳላቸው ተቃዋሚዎቹ በግልጽ ይናገራሉ፡፡ ጌታ በሚያስተምርበት ጊዜ "አንዲት ሴት ድምጿን ከፍ አድርጋ፥የተሸከመችህ ማኅፀንና የጠባሃቸው ጡቶች ብፁዓን ናቸው" ብትለው "ብፁዓንስ የእግዚአብሔርን ቃል ሰምተው የሚጠብቁት ናቸው" በማለቱ የእመቤታችንን ብፅዕና ያሳነሰ ስለ መሰላቸው ይህንን የጌታን ቃል ይጠቅሳሉ (ሉቃ.11፥27-28)፡፡ ነገር ግን ጌታ ይህን ቃል ለጠየቀችው ሴት ሲመልስ ለእርሷ ማለት ለጠያቂዋ አሳብና ስሜት የሚስማማ ምክርና መልእክት እንጂ ስለ እመቤታችን ብፅዕና የተሰጠ መልስ እንዳልሆነ ከሁኔታው



መረዳት ይቻላል፡፡ ጌታችን በሌላ ቦታ ለጠያቂዎቹ መልስ በሚሰጥበት ጊዜ የጠያቂዎቹን ልቡናና ስሜት የማወቅ ኃይል ስላለው ለእነርሱ ግንዛቤ በሚስማማ መንገድ የተዛባውን አመለካከታቸውን ለማረም ሲል ይመልሳል፡፡ ስለዚህ ጌታ ለጠያቂዋ ሴት የመለሰው እርሷን የሚመለከት ብቻ ነበር፡፡ ይኸውም እርሷ ፥ጌታ የሚያስተምረውን ቃል እየሰማች እንድትፈጽመው የሚያበረታታ መልስ ሲሆን በዚሁም ወደ ብፅዕናው ተስፋ እንድትደርስ በማለት ነው፡፡

እመቤታችንማ የእግዚአብሔርን ቃል ሰምተው ከሚጠብቁት በላይ የጠበቀች አይደለችምን? እርሷ ከሁሉ አስቀድማ የሰዎችን የመዳን ቀን ያወቀች፥ የጌታን ቃል ያመነች ብፅዕት መሆኗ በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት እንደ ተነገረላት አታውቁምን? ቅድስት ኤልሳቤጥ ስለ እመቤታችን ከተናገረችው አንዱ ይህ ነበር፡፡ "በኤልሳቤጥም መንፈስ ቅዱስ ሞላባት፥ በታላቅ ድምጽም ጮኸ እንዲህ አለች፦ . . . ከጌታ የተነገረላት ቃል ይፈጸማልና ያመነች ብፅዕት ናት" (ሉቃ.1፥41-45)፡፡ እንግዲህ እንድታምነው ከጌታ የተነገረላት ቃል ምንድነው? መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል በድንግልና ወንድ ልጅ እንደ ምትወልድ፥ እርሱም የልዑል ልጅ እንደ ሚባል በሰማች ጊዜ ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር እንደሌለ አምና መቀበሏን የሚያመለክት ቃል ነው፡፡ "እነሆኝ የጌታ ባሪያ እንደ ቃልህ ይሁንልኝ" በማለቷ እመቤታችን በታላቅ ሃይማኖትዋና ትሕትናዋ ለክርስቲያኖች ሁሉ አርአያ ሆናለች (ሉቃ.1፥38)፡፡ ስለዚህ እመቤታችን በእናትነትዋ ብቻ ሳይሆን በታላቅ እምነቷና ፍቅሯ፥ ትሕትናዋና በጎ ምግባሯ በሁሉ ዘንድ የተመሰገነች ብፅዕት ናት፡፡

እንግዲህ የእመቤታችን ክብርና ምስጋና በመላእክትና በቅዱሳን መካከል እጅግ ከፍ ያለ ነው፡፡ ስለዚህም በቅዱስ ገብርኤል ሰላምታ፥ ሰላም እንበላት (ሉቃ.1፥28-30)፡፡ እንደ ቅድስት ኤልሣቤጥም "የጌታዬ እናት" እያልን እናክብራት፥ እናመስግናትም (ሉቃ.1፥42-45)፡፡ እግዚአብሔር ለእመቤታችን ታላቅ ሥራ አድርጎላታልና ትውልድ ሁሉ ብፅዕት ይሏታል (ሉቃ.1፥48-49)፡፡

"ላቲ ይደሉ ክብር ወስብሐት ወለወልዳ አምልኮ ወስግደት በምድር ወበ ሰማያት በባሕር ወበቀላያት ለዓለመ ዓለም፤ አሜን፡፡ ለእርሷ ክብርና ምስጋና ለልጇም አምልኮና ስግደት . . . ይገባል" እንደ ተባለው ከልጇ ቀጥለን ለእርሷ ከፍተኛ ምስጋና እናቀርባለን፡፡ የእርሷ ማዕረግ ከጌታችን በታች ከመላእክትና ከቅዱሳን ሁሉ በላይ ስለሆነ ለእርሷ የሚቀርበው ክብርና ምስጋና በዚሁ መጠን ከፍ ያለ ነው፡፡

## መ) ጌታ ሰው ስለ መሆኑ፣ የቅዱስ ገብርኤል ምሥራች

"በመንፈስ ቅዱስ ግብር ከቅድስት ድንግል ማርያም ፈጽሞ ሰው ሆነ" በማለት ከላይ በአንቀጹ የተገለጸው፣ የእግዚአብሔር ልጅ ያለ አዳም ኃጢአትና ያለ ዘርዐ ብእሲ ስለ እኛ ስለ መዳናችን ሲል እንደ እኛ ፈጽሞ ሰው መሆኑን የምንመሰክርበት የሃይማኖት ድንጋጌ ነው፡፡ ከሁለት ነገሮች በስተቀር እንደ እኛ እንደ ሰው በመሆኑ ከሰውነት ባሕርይ የጐደለው ነገር የለም፡፡ የመጀመሪያው ሰው አዳም ከሁለቱ በስተቀር ማለት ያለ ዘርዐ ብእሲና ያለ ኃጢአት ተፈጥሯል፡፡ ክርስቶስም ያለ ዘርዐ ብእሲና ያለ ኃጢአት ከእመቤታችን ተወልዷል፡፡ ስለዚህም ክርስቶስ በሰውነቱ ዳግማዊ አዳም ይባላል፡፡ በሥጋም በነፍስም ከበደል በፊት እንደ ነበረው እንደ መጀመሪያው ሰው ነው፡፡ ከኃጢአት በስተቀር ፈጽሞ እንደ እኛ ሰው ሆነ፡፡ ትእዛዙንና ቃል [illegible] በማፍረሳችን የእግዚአብሔር ጠላቶች ስንሆን፣ እርሱ ግን እኛን [illegible] እኛ ጋር ወዳጅነትን መሠረተ፡፡ በሥጋም በነፍስም እንድን

www.ethiopianorthodox.org

## ሠ) ጌታ በሥጋ ስለ መገለጡ--ልደቱ
## (ነበልባል በለምለሙ ቁጥቋጦ ውስጥ መታየቱ)

በአንቀጸ ሃይማኖት ውስጥ "ፈጽሞ ሰው ሆነ" ሲባል በመጀመሪያ በፅነ ሰቱ በኋላም በልደቱ አምላክ ወልደ አምላክ በሥጋ መገለጡን ያመለክታል። በድንግል ማኅፀን ሳለ ጥቂት ቅዱሳን ብቻ ያውቁ ነበር፤ ከልደቱ በኋላ ግን ለዓ ለም ሁሉ ተገለጠ፡፡ ሕዝብ አሕዛብም የሚያዩት የሚዳስሱት ሰውነት ያለው ሆኖ በአጭር ቁመት በጠባብ ደረት ተወስኖ እንደ ሰው ተገልጧል፡፡ የአሁን አ መጣጡ በሥጋ በመገለጥ ነው፤ የቀድሞው አመጣጡ ግን በመለኮታዊ እሳት አ ምሳል ስለነበር ማንም ሊቀርበው አይችልም ነበር፡፡ ያን ጊዜ የእግዚአብሔር መገለጥ በሚታይ በነበልባል ውስጥ ነበር፡፡ በእሾህ ቁጥቋጦ መካከል በሚነደው እሳት የተገለጠው አምላክ ለሙሴ ብቻ ነበር፡፡ ወደ ተቀደሰውም ቦታ ጫማውን አውልቆ እንዲቀርብ ለሙሴ ተነግሮት፣ እርሱም በፍርሃትና በመደነቅ ለምለሙ ቁጥቋጦና ነበልባሉ ተዋሕደው ወደ ሚታዩበት ኅብረ ትርኢት ተጠግቶ የአምላክን መገለጥ አይቶ የዘላለም ስሙም "ያለና የሚኖር" እርሱ የአ ብርሃም የይስሐቅና የያዕቆብ አምላክ እንደሆነ ለማወቅ በቅቷል (ዘጸ.3፥1-15)። ይህ የብሉይ ኪዳን መገለጥ ነበር፡፡

በሐዲስ ኪዳን ደግሞ የታየው የአምላክ መገለጥ በሥጋ ነበር፡፡ ይህም ሥጋ ከእመቤታችን ተገኝቷል፡፡ ስለዚህ እመቤታችን እንደ ለምለሙ ቁጥቋጦ ትመሰላለች፤ እንደ እሳቱ ነበልባልም በማኅፀኗ ያደረው መለኮት ነው ማለት ነው፡፡ ነበልባሉ ለምለሙን ቅጠል እንዳላቃጠለው፣ እንደዚሁም በእመቤታችን ያደረው እሳተ መለኮት ሥጋዋን እንዳላቃጠለው ከምሳሌው እንረዳለን፡፡ እግዚአ ብሔር በሥጋ የተገለጠባት የሐዲስ ኪዳኗን ቁጥቋጦ ለማየት የሚጠጋ ሁሉ ጫማውን አውልቆ በአክብሮት ይመለከታታል፡፡ ይህን ለማየት እድል የተ ሰጣቸው የመጀመሪያዎቹ ቅድስት ኤልሳቤጥና ቅዱስ ዮሴፍ ነበሩ። የእመቤታችንን ድምጽ ስትሰማ የኤልሳቤጥ ጽንስ ከማኅፀንዋ ሆኖ በደስታ ዘለለ፤ በአክብሮት ሰገደ፡፡ ይህ ታላቅ ተአምር ነው፡፡ ስለዚህ ነው ዘመድዋ ኤ ልሳቤጥ "የጌታዬ እናት ወደ እኔ ትመጣ ዘንድ እንዴት ይሆንልኛል?" በማለት በታላቅ ድምጽ ጮኻ የተናገረችው (ሉቃ.1፥39-45)፡፡ ስለዚህ ነው ቅዱስ ዮ ሴፍም በፍርሃትና በአክብሮት እመቤታችንን የሚጠብቃትና የሚያገለግላት፡፡

በአራት፣ ታላቁ የእግዚአብሔር መገለጥ በሲና ተራራ ነበር፡፡ ያን ጊዜ ቃለ አብ ሕያው በተራራው ራስ ላይ ወርዶ በሚነደውና በሚያስፈራው እሳት መካከል ሲገለጥ የነጐድጓዱና የመለከቱ ድምጽ፣ የመሬቱ መናወጥ፣ የጭጋጉና የጨለማው ሁኔታ በተራራው ሥር ለነበሩት የእሥራኤል ሕዝብ ሁሉ ሲታይ እጅግ የሚያስደነግጥ እንደ ነበረ ተጽፏል (ዘጸ.19፥16)፡፡ በወንጌል የታየው መገለጥ ግን በሚያስደነግጥ ሁኔታ ሳይሆን፣ በአትኅቶ ርእስ፣ በአርአያ ገብር በሥጋ የተገለጠው የጌታ ልደትና የጌታ ሰው መሆን ነበር፡፡ እርሱም በሲና ተራራ ላይ የወረደ፣ ከእመቤታችንም በሥጋ የተወለደ የአብ ሕያው ቃል ነበር፡፡ ስለዚህ ነው እመቤታችን "ደብር ነባቢት በትኅትና" የተባለችው። ይህም ማለት በትኅትና የምትገኝ፣ የምትና...
የተቀደሰች ተራራ እመቤታችን መሆናን የሚያመለክት ቃል ነው፡፡ ...



"በዚያም ወራት ዓለሙ ሁሉ እንዲጻፍ ከአውግስጦስ ቄሣር ትእዛዝ ወጣች፡፡ ቄሬኔዎስ በሶርያ አገረ ገዥ በነበረ ጊዜ ይህ የመጀመሪያ ጽሕፈት ሆ ነ፡፡ ሁሉም እያንዳንዱ ይጻፍ ዘንድ ወደ ከተማው ሄደ፡፡ ዮሴፍም ደግሞ ከዳዊት ቤትና ወገን ስለነበረ ከገሊላ ከናዝሬት ከተማ ተነሥቶ ቤተ ልሔም ወደ ምትባል ወደ ዳዊት ከተማ ወደ ይሁዳ፣ ፀንሳ ከነበረች ከእጮኛው ከማርያም ጋር ይጻፍ ዘንድ ወጣ፡፡ በዚያም ሳሉ የመውለጃዋ ወራት ደረሰ፣ የበኵር ልጅዋንም ወለደች፣ በመጠቅለያም ጠቀለለችው በእንግዶችም ማደሪያ ስፍራ ስላልነበራቸው በግርግም አስተኛችው፡፡

"በዚያም ምድር መንጋቸውን በሌሊት ሲጠብቁ በሜዳ ያደሩ እረኞች ነበሩ፡፡ እነሆም፣ የጌታ መልአክ ወደ እነርሱ ቀረበ የጌታ ክብርም በዙሪያቸው አበራ፣ ታላቅ ፍርሃትም ፈሩ፡፡ መልአኩም እንዲህ አላቸው፦ እ ነሆ፣ ለሕዝቡ ሁሉ የሚሆን ታላቅ ደስታ የምሥራች እነግራችኋለሁና አትፍሩ፣ ዛሬ በዳዊት ከተማ መድኃኒት እርሱም ክርስቶስ ጌታ የሆነ ተወልዶላችኋልና፡፡ ይህም ምልክት ይሆንላችኋል፤ ሕፃን ተጠቅልሎ በግርግም ተኝቶ ታገኛላችሁ፡፡ ድንገትም ብዙ የሰማይ ሠራዊት ከመልአኩ ጋር ነበሩ፡፡ እግዚአብሔርንም እያመሰገኑ፣ ክብር ለእግዚአብሔር በአርያም ይሁን ሰላምም በምድር ለሰውም በጎ ፈቃድ አሉ" (ሉቃ.2፥1-14)፡፡

## ጌታ በበረት ስለ መወለዱ

ከጌታ የልደት ታሪክ ጋር በተያያዘ ጥናታችን በአራት ታላላቅ ትምህርቶች ላይ ያተኩራል፡፡ በመጀመሪያ ጌታችን በበረት ውስጥ ስለ መወለዱ እንመለከታለን፡፡ የጌታችን ቀዳማዊ ምጽአቱ ማለት የመጀመሪያ አመጣጡ፣ በሥጋ መገለጡ፣ ከሰማያዊ ዙፋኑ መውረዱ፣ ከበረት ውስጥ መወለዱ እንዴት የሚያስደንቅ ነገር ነው! ከአንድ ድሀ ቤት እንኳ ቦታ ጠፍቶ እንዴት ከከብቶች ማጉሪያ ከበረት ውስጥ ተወለደ! ለወፎች ጐጆ፣ ለቀበሮችም ጉድጓድ አላቸው ለ ሰው ልጅ ግን ራሱን የሚያስጠጋበት ስፍራ የለውም የተባለውን ያስታውሰናል (ማቴ.8፥20)፡፡ እርሱ የጌቶች ጌታ ሲሆን በዝቅተኛ ስፍራ በመገኘት የድሆች ድሀ በመሆን በአንድ ትንሽ ሕፃን መልክ በጨርቅ ተጠቅልሎ በበረት ተጥሎ የተገለጠበት ምክንያት ከቶ ምን ይሆን? መልሱም እንደ ሚከተለው ነው፡፡ የወደቀውንና የተዋረደውን የጠፋውን አዳምን በመፈለግ እርሱን መስሎ፣ እር ሱን አኽሎ የፍጡርን ሥጋ ለብሶ ወደዚህ ዓለም የመጣው እርሱንና ልጆቹን ለማዳን ነው፡፡ ከገነት በመውጣቱ በልቡ ያዘነውንና የተከዘውን አዳምን ወደ ቀደመው ክብሩ ጌታ ሊመልሰው ስለ ወደደ የእርሱንና የልጆቹን ውርደትና ኃጢአት ተሸክሞ ሊያድናቸው ከሰማየ ሰማያት ወረደ፤ ከበረት ውስጥ ተወለደ፡፡ የሰው ልጆችን ልቡና ለመንካት በእንዴት ያለ ትኅትና በዝቅተኛ ሁኔታ እንደ ተወለደ ተመልከቱ፡፡ ይህንንም ያደረገበት ምክንያቱ የወደቀውን የሰው ልቡና ለማደስና ለማንሣት ነው፡፡ አዲስ ልቡናን ሊፈጥርልን፣ ትንሣኤ ልቡናን ሊሰጠን ፈልጐ በሥጋ ተገለጠ፡፡ እኛ የእርሱን ቅዱስ መንፈስ ለመቀበል እን ድንችል እርሱ የእኛን ሥጋ ወሰደ፡፡ የእርሱን ልዕልና እንድንወርስ ሕይወትም እንድናገኝ እርሱ የእኛን ውርደትና ሞት በሥጋው ተሸከመ፡፡ እንደዚህም በማድረጉ ሁላችንንም አዲስ ፍጥረት አደረገን፡፡ ስለዚህ ነው በማዳን ሥራው ሁላችንን እንደገና ሊፈጥረን አስቦ ጌታ ሥራውን ሁሉ ከመጀመሩ በፊት ጥበብን ፈጠረ ተብሎ በቅድሚያ በመጽሐፈ ምሳሌ የተነገረው፤ ይህም ማለት በሥጋ መወለዱን ለማብሠር ነው (ምሳ.8፥22-25 ግዕዙን ከነትርጓሜው ...

www.ethiopianorthodox.org

## የጌታ ልደት ለእረኞች ስለ መገለጡ

ቀጥሎ የምንማረው ሁለተኛ ትምህርት፣ ይህን የጌታ ልደት፣ የሰው ልጆች በተአምራዊ ሁኔታ እንዲያውቁትና እንዲያምኑት መደረጉ ነው፡፡ ፀጥ ባለው ሌሊት በሜዳ ላይ ለሚገኙ እረኞች ጨለማውን አርቆ ከሰማይ የወረደላቸው ብርሃን የጌታን ክብርና ልዕልና የሚያስረዳ ሲሆን፣ የጌታ መልአክም ተገልጸ ነቢይና ሐዋርያ በመሆን ለሕዝቡ ሁሉ የሚሆነውን ታላቅ ደስታ አብሥሯቸዋል፡፡ ለእነርሱ መዳን ሲል የመጣውን ጌታ ክርስቶስ በዳዊት ከተማ መወለዱን ነገራቸው፡፡ ሄደውም ለማየት እንዲችሉ ሕፃኑ በጨርቅ ተጠቅልሎ በግርግም ላይ ተኝቶ ታገኙታላችሁ በማለት ምልክቱን አስታወቃቸው፡፡ የጌታን ልዕልናና ትኅትና በአንድ ጊዜ ለማየት የሚችሉ በድንገት ብዙ ሠራዊተ መላእክት ተገልጠው፣ ጌታን ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር በመንበሩ ላይ ሆኖ በሰማያት ስላዩት “ክብር ለእግዚአብሔር በአርያም (በሰማያት) ይሁን” አሉ፣ ደግሞም ከታች በትኅትና በምድር ላይ ሆኖ በግርግም ላይ ተኝቶ በማየታቸው፦ “ሰላምም በምድር ለሰውም በጎ ፈቃድ” በማለት ለጌታ ልደት የሚገባ ምስጋናና መዝሙር አቅርበዋል፡፡ ዛሬም በቤተ ክርስቲያናችን ይህ ምስጋና ዘወትር በቅዳሴ ሰዓት በዜማ ይባላል፡፡

እረኞችም ይህንን ሁሉ ታላቅ ታምራት አይተውና ሰምተው ዝም አላሉም፡፡ በተሰጣቸው ምልክት መሠረት ከቤተ ልሔም ፈጥነው በመሄድ እንደ ተጻፈው “ማርያምንና ዮሴፍን ሕፃኑንም በግርግም ተኝቶ አገኙ፡፡ አይተውም ስለዚህ ሕፃን የተነገረላቸውን ነገር ገለጡ፡፡ . . . እረኞችም እንደ ተባለላቸው ስለ ሰሙትና ስላዩት ሁሉ እግዚአብሔርን እያመሰገኑና እያከበሩ ተመለሱ (ሉቃ.2፥16-20)፡፡ እነርሱም በጌታ መልአክ የተሰበኩ የመጀመሪያው አማኞች ነበሩ፡፡ ያዩትንና የሰሙትን ሁሉ ለሰዎች በመንገራቸው ለጌታ ልደት ምስክሮች ሆነዋል፡፡ እኛም ለሰዎች መዳን ይህን ታላቅ ተአምር ያደረገውን፣ በሥጋና በደም የተገለጠውን ጌታ ከቤተልሔም ማለት ከቤተ ክርስቲያን ሄደን እንፈልገው፤ ሥጋውንና ደሙን በመቀበል እንወቀው፣ እንመነው፡ም እናክብረውም “ስብሐት ለእግዚአብሔር በሰማያት ወሰላም በምድር ሥምረቱ ለሰብእ” በማለት ሁል ጊዜ በጸሎተ ቅዳሴ እናመስግነው፡፡

## ሰብአ ሰገል

ስለ ጌታ ልደት በማቴዎስ ወንጌል የተጻፈውን መሠረት በማድረግ ሦስተኛውን ትምህርት እንቀጥላለን (ማቴ.2፥1-12)፡፡ ጌታ በተወለደ ጊዜ በምድር ብቻ ሳይሆን፣ በሰማይም ላይ አዲስ ተአምር ታየ፡፡ ለዓለሙ ሁሉ የሚታይ አዲስ ኮከብ ተወለደ፡፡ የጌታ መልአክ ለእረኞቹ ስለ ጌታ ልደት እንደ ነገራቸው፣ እንደዚሁም ኮከብ በመታየቱ ብቻ ለአሕዛብ ሁሉ ልደቱን አበሠረ፡፡ በኮከቡም እየተመሩ ሰብአ ሰገል የተባሉ የምሥራቅ ጠቢባን (ነገሥታት) ኢየሩሳሌም ደረሱ፡፡ የአይሁድ ንጉሥ የት እንደ ተወለደ በመጠየቃቸው በዘመኑ የነበረው ንጉሡ ሄሮድስና የኢየሩሳሌም ከተማ ሁሉ በሰሙት አዲስ ዜና ተደናገጡ፡፡ በትንቢት እንደ ተነገረው ከቤተ ልሔም እንደሚወለድ ስለ ተረዱ ሰብአ ሰገል ከቤተ ልሔም ከተማ ገቡ፡፡ ያዩትም ኮከብ ሕፃኑ እስከ ሚገኝበት ቦታ ድረስ መራቸው፡፡ “[illegible] ከእናቱ ከማርያም ጋር አዩት፣ [illegible]



## ስለ ጌታ ወደ ግብፅ መሰደድ

ከሰብአ ሰገል ታሪክ ቀጥሎ የምንማረው አራተኛው የትምህርት ርእስ ስለ ጌታችን ወደ ግብፅ መሰደድ ነው፡፡ ከማቴዎስ ወንጌል እንደ ምናነበው ታላቁ ሄሮድስ የአይሁድ ንጉሥ የጌታችንን በቤተ ልሔም መወለድ በምሥጢር እንደ ተረዳ ሊገድለው አስቦ በቤተ ልሔም አካባቢ የሚገኙትን ሕፃናት ሁሉ አስገደለ፡፡ ነገር ግን ቅዱስ ዮሴፍ ቀደም ብሎ በጌታ መልአክ ትእዛዝ መሠረት ሕፃኑንና እናቱን ይዞ ወደ ግብጽ ሸሸ፤ ከዚያም ወደ ናዝሬት እስኪመለሱ ድረስ ስደተኛ በመሆን ቆይተዋል (ማቴ.2፥13-23)፡፡ በስደታቸውም ጊዜ ብዙ መከራና ችግር ደርሶባቸዋል፡፡ እንግዲህ ወልደ እግዚአብሔር ፍጹም ሰው በመሆን ገና በበረት ከመወለዱ ጀምሮ በኋላም በስደቱ መከራ መቀበሉ ስለ እኛ ስለ ሰዎች ደኅንነት መሆኑን ማስታወስ ይኖርብናል፡፡

በቤተ ክርስቲያናችንም የሕፃኑንና የእናቱን የስደት መከራ ለማስታወስ በየዓመቱ ከመስከረም 26 ቀን ጀምሮ እስከ ኅዳር 6 ቀን ድረስ ይታሰባል፡፡ በየዓመቱ ካህናቱም እሑድ እሑድ በማኅሌተ ጽጌ ያከብሩታል፡፡ ምእመናንም በየዓመቱ ይህንን ዘመነ ጽጌ ተብሎ የሚታወቀውን ጊዜ በማስታወስ የቤተ ክርስቲያን ሕይወት ተሳታፊነታቸውን በበጎ ምግባራቸው ይገልጻሉ፡፡ የጠፋውን አዳም ሊፈልግና ሊያድነው ሰው ሆኖ የመጣው ክርስቶስ በመጀመሪያ የደረሰበትን ችግርና መከራ በጽሞና በማሰብ ትሩፋትን የሚያዘወትሩ ክርስቲያኖች ከክርስቶስ ሕይወት ጋር ያላቸውን አንድነት ለመግለጽ በጾም በጸሎት ይተጋሉ፡፡

## ሕግ ጠባይዓዊና ሕግ መጽሐፋዊ

ከጌታ ልደትና የሕፃንነት ታሪክ ጋር አያይዘን የምንማራቸው ሁለት ነገሮች አሉ፡፡ በመጀመሪያ በአንቀጸ ሃይማኖት ላይ እንደ ተገለጸው ጌታ “ፈጽሞ ሰው ሆነ” የተባለውን የምንረዳው “ሕግ ጠባይዓዊን” እየፈጸመ ቀስ በቀስ ማደጉን የሚያመለክት ነው፡፡ “ሕግ ጠባይዓዊ” ማለት የሰውነትንና የተፈጥሮን ሕግጋት በመጠበቅ ከመፀነስና ከመወለድ ጀምሮ ሕፃን ሆኖ ጡት እየጠቡ ቀስ በቀስ ማደግንና እስከ አቅመ አዳም መድረስን፣ መራብና መጠማትን፣ መከራና ኀዘንን፣ መብላትና መጠጣትን፣ መተኛትና መነሣትን፣ መድከምና መበርታትን ሌሎችንም የመሳሰሉትን ሁሉ ያጠቃልላል፡፡ ምንም ያለ ዘርዐ ብእሲ ቢፀነስም ሥጋን በመዋሐዱ ጌታ ሕግ ጠባይዓዊን ከኃጢአት በቀር በየደረጃው ፈጽሞታል፡፡

ሁለተኛው፦ “ሕግ መጽሐፋዊ” ይባላል፡፡ ይህም ማለት ጌታችን ሕገ ኦሪትን እየፈጸመ ማደጉን የሚያስረዳን ነው፡፡ በስምንተኛው ቀን መገረዝን፣ በአርባኛው ቀን ቤተ መቅደስ መግባትን፣ በዓመት ሦስት ጊዜ ወደ ኢየሩሳሌም መሄድንና ሌሎችንም የኦሪት ትእዛዛት ሁሉ ጌታችን እንደ ፈጸማቸው ተጽፏል (ሉቃ.2፥21- 52)፡፡ ጌታ ሕግን ሁሉ የፈጸመው እኛ ሕግ አፍራሾችን በእርሱ እምነትና ጸጋ ሥር ያለነውን ፥ በእርሱ መንፈስ የምንመላለሰውን ሁሉ እንደ [illegible] አስቦ ነው (ሮሜ.8፥1-4)፡፡ እንዲህም በማድረጉ [illegible] መጣብን ፍርድና ኩነኔ ነፃ አውጥቶናል፤ አድኖናል፡፡

www.ethiopianorthodox.org

በምናከብርበት ጊዜ ጌታ ስለ እኛ ሰው ሆኖ ሕግጋትን በመፈጸሙ እንዳዳነን ማስታወስ ለአማኞች ሁሉ አስፈላጊ ነገር ነው:: ወንዶች ልጆች በአርባ ቀናቸው፣ ሴቶች ሕፃናት በሰማንያ ቀናቸው ወደ ቤተ ክርስቲያን በመሄድ የጥምቀትን ሕግ መፈጸማቸው ከዚሁ ታሪክ ጋር የተያያዘ መሆኑን እንረዳለን::

## ረ) ጌታ በውኃና በመንፈስ ስለ መምጣቱ-ጥምቀቱ

"በውኃና በደም የመጣ ይህ ነው፤ እርሱም ኢየሱስ ክርስቶስ በውኃና በደም በመንፈስ እንጂ በውኃው ብቻ አይደለም" በማለት ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስ የጻፈውን መነሻ በማድረግ ስለ ጌታ ጥምቀት ዓላማ ለማስረዳት እን ጀምራለን (1ኛዮሐ.5፡6):: ሐዋርያው፡ ጌታ በውኃና በደም መጣ ማለቱ ስለ ጌታችን ጥምቀትና በመስቀል ላይ ደሙን ስለ እኛ ኃጢአት ማፍሰሱንና መሞቱን ለማስረዳት ነው:: ይህም ከቀኝ ጐኑ የፈሰሰውን ውኃና ደም ያመለክተናል (ዮሐ.19፡34):: ውኃና ደም ከአንድ ቦታና በአንድነት መውጣታቸው የጌታ ጥምቀትና ሞት የተያያዙ መሆናቸውን ያስገነዝበናል:: እነርሱም ለምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን ሁሉ መሠረት ናቸው:: ጌታም "የምጠመቃት ጥምቀት አለችኝ፡ እስክትፈጸም ድረስ እንዴት እጨነቃለሁ?" በማለት የተናገረው ስለ ሞቱ ነበር (ሉቃ.12፡50)::

እንግዲህ የጌታ አመጣጥ በመጀመሪያ በውኃና በመንፈስ ነው:: ይህም ማለት ጌታችን ሰውን ለማዳን በዕለተ ዓርብ በመስቀል ላይ ሊፈጽም ያለውን የሕማሙና የሞቱን ሥራ የጀመረው ራሱን ዝቅ በማድረግ በሏጥምቁ ዮሐንስ እጅ በዮርዳኖስ ወንዝ በመጠመቅ ነበር ለማለት ነው:: ስለዚህ ጌታ በውኃና በመንፈስ መምጣቱ በእርሱ ሕማምና ሞት አምነው ለሚጠመቁ ሁሉ የኃጢአት ሥርየትን፡ በመንፈስ ቅዱስ ጸጋ አዲስ ልደትን፡ አዲስ ሕይወትን፡ትንሣኤ ልቡናን ለመስጠት ነው::

## የጌታ ጥምቀት ሕማምና ሞቱን ያመለክታል

የጌታ ጥምቀት እንዴት ነበር? ለምንስ ተጠመቀ? የሚሉትን ጥያቄዎች በልቡናችን ይዘን መልሱን እንፈልግ:: ጌታን ያጠመቀው ነቢየ ልዑል ዮሐንስ ሰዎችን ሁሉ ወደ ንስሐ እየጠራ ያጠምቃቸው ነበር:: ክርስቶስን ግን ሊያጠምቀው አልደፈረም፤ የክርስቶስንም ማንነት ስለ ሚያውቅ በሕዝቡ ፊት እንዲህ እያለ ይመሰክር ነበር::

> "እኔስ ለንስሐ በውኃ አጠምቃችኋለሁ፤ ጫማውን እሸከም ዘንድ ከማይገባኝ ከእ ኔ በኋላ የሚመጣው ግን ከእኔ ይልቅ ይበረታል፤ እርሱ በመንፈስ ቅዱስ በእሳ ትም ያጠምቃችኋል፤ መንሹም በእጁ ነው፡ አውድማውንም ፈጽሞ ያጠራል፡ ስንዴውንም በጐተራው ይከታል፤ ገለባውን ግን በማይጠፋ እሳት ያቃጥለዋል" (ማቴ.3፡11-12)::

በተጨማሪ የዓለምን ሁሉ ኃጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ እርሱ ክርስቶስ መሆኑን ዮሐንስ መጥምቁ አስተምሯል (ዮሐ.1፡29):: ታዲያ ይህን ሁሉ ምስክር የሰጠ መጥምቁ ዮሐንስ እንዴት ጌታን አጠመቀው? ጌታስ ለምን ተጠመቀ ለተባሉት ጥያቄዎች መል[illegible]
[illegible]



ነው:: ስለዚህ ነው ዮሐንስ መጥምቅ እነሆ የእግዚአብሔር በግ የዓለምን ኃጢአ ት የሚያስወግድ በማለት ኃጢአታቸውን እየተናዘዙ ለሚጠመቁት ሁሉ የተናገረው:: ይህም ያለ ምክንያት አልተነገረም:: ጥምቀትና ሞት ትርጓሜያቸው የተያያዘና የተገናዘበ ስለሆነ ነው::

እንግዲህ በዕለተ ዓርብ ከጐኑ በሚወጣው ውኃና ደም የዓለምን ኃጢአ ት የሚያስወግድ መሆኑን ጌታ በጥምቀቱ ገልጾታል:: ስለዚህ በጥምቀት የኃጢአት ሥርየትን እንድናገኝ እርሱ ራሱ ተጠምቆ እንድንጠመቅ ሥርዓተ ጥምቀትን መሥርቶልናል:: ዛሬ በቤተ ክርስቲያን በሚፈጸመው ምሥጢረ ጥምቀት አማካኝነት ከጌታ ጐን በፈሰሰው ማየ ሕይወት ተጠምቀን ከኃጢአትና ከመርገም እንድናለን::

የጌታን ጥምቀት ትርጉም በይበልጥ ለመረዳት በወንጌላዊ ማቴዎስ የተጻፈውን በጽሞና እንመልከት:

> "ያን ጊዜ ኢየሱስ በዮሐንስ ሊጠመቅ ከገሊላ ወደ ዮርዳኖስ መጣ:: ዮሐንስ ግን ፡ እኔ በአንተ ልጠመቅ ያስፈልገኛል አንተም ወደ እኔ ትመጣለህን? ብሎ ይከለክለው ነበር:: ኢየሱስም መልሶ፡ አሁንስ ፍቀድልኝ፡ እንዲህ ጽድቅን ሁሉ መፈጸም ይገባናልና አለው:: ያን ጊዜ ፈቀደለት:: ኢየሱስም ከተጠመቀ በኋላ ወዲያው ከውኃ ወጣ፤ እነሆም፡ ሰማያት ተከፈቱ የእግዚአብሔርም መንፈስ እን ደ ርግብ ሲወርድ በእርሱ ላይም ሲመጣ አየ፤ እነሆም፡ ድምጽ ከሰማያት መጥቶ፡ በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው አለ" (ማቴ.3፡13-17)::

ከዚህ የወንጌል ቃል የምንማረው ብዙ ምሥጢር አለ:: ክርስቶስ የተጠመቀው ጽድቅን ሁሉ ሊፈጽም እንደሆነ ተገልጿል:: በመሠረቱ ክርስቶስ ወደዚህ ዓለም የመጣው በኃጢአት የተበላሸውን ዓለም በጽድቅ ሥራው ሊቀድሰውና ሊያድሰው አዲስ ፍጥረትም እንዲሆን ለማድረግ ነው:: መቼም ቢሆን ጌታ ለራሱ ጥቅም ብሎ ወደዚህ ዓለም አልመጣም:: የሚያደርገውም ነገር ሁሉ ለራሱ ጥቅም ሳይሆን ለሰዎች ልጆች ሲል መሆኑን በአንቀጸ ሃይማኖት ተምረናል::

እንግዲህ ጌታ በተጠመቀ ጊዜ የጽድቅን፡ የሕይወትን በርና መንገድ ከፈተልን፤ አዲስ ሰዎች ሆነን የምንወለድበትን እምነትንና የጥምቀትን ሥርዓት መሠረተልን:: ሁሉም ሰው በክርስቶስ አምኖ ከኃጢአቱ ነጽቶ ወደ ፈጣሪው የሚሄደው ክርስቶስ በከፈተለት በጥምቀት በር በኩል ነው:: ጌታ በውኃና በመን ፈስ የመጣው እኛ ከውኃና ከመንፈስ በመወለድ አዲስ ፍጥረት ሆነን ለመን ግሥተ ሰማያት የበቃን ሊያደርገን ነው (ዮሐ.3፡5)::

## ጌታ በጥምቀቱ ምሥጢረ ጥምቀትን መሠረተልን

የጌታ ጥምቀት፡ ምሥጢረ ሥላሴ የተገለጸበት፡ ምሥጢረ ሥጋዌ የተረጋገጠበት፡ ምሥጢረ ጥምቀት የተቋቋመበት በመሆኑ ለእምነታችንና [illegible] መሠረት ሆኗል:: ጌታ በመጠመቁ ይህን ሁሉ አ [illegible]
[illegible]

www.ethiopianorthodox.org

ምሥጢረ ጥምቀትን ከመሠረተልን በኋላ ማንኛውም ሰው ከውኃና ከመንፈስ ካልተወለደ በስተቀር መንግሥተ ሰማያት የማይገባ መሆኑን ጌታ ለኒቆዲሞስ እንዲህ ሲል አስረድቶታል፡፡

> "እውነት እውነት እልሃለሁ፥ ሰው ዳግመኛ ካልተወለደ በቀር የእግዚአብሔርን መንግሥት ሊያይ አይችልም አለው፡፡ ኒቆዲሞስም፦ ሰው ከሸመገለ በኋላ እንዴት ሊወለድ ይችላል? ሁለተኛ ወደ እናቱ ማኅፀን ገብቶ ይወለድ ዘንድ ይችላልን? አለው፡፡ ኢየሱስም መለሰ፥ እንዲህ ሲል፦ እውነት እውነት እልሃለሁ፡ ሰው ከውኃና ከመንፈስ ካልተወለደ በቀር ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሊገባ አይችልም፡፡ ከሥጋ የተወለደ ሥጋ ነው፥ ከመንፈስም የተወለደ መንፈስ ነው፡፡ ዳግመኛ ልትወለዱ ያስፈልጋችኋል ስላልሁህ አታድንቅ፡፡ ነፋስ ወደ ሚወደው ይነፍሳል፥ ድምጹንም ትሰማለህ፥ ነገር ግን ከወዴት እንደመጣ ወዴትም እንዲሄድ አታውቅም፤ ከመንፈስ የተወለደ ሁሉ እንዲሁ ነው" (ዮሐ.3፥3-8)፡፡

ከላይ ከጥቅሱ እንደ ተመለከትነው ዳግመኛ መወለድ ስለ ተባለው ኒቆዲሞስ እንደ ተቸገረ ሁሉ ዛሬም ለአንዳንዶች ነገሩ ሳይከብዳቸው አይቀርም፡፡ በመሠረቱ የጌታችን ወደዚህ ዓለም መምጣት በኃጢአት የጠፋውን ዓለም፡ በሥጋዊ ሥራ የተበላሸውን የሰውን ልጅ ሁሉ ሊያድነውና ሊያድሰው በሚችልበት በእግዚአብሔር ጸጋ አዲስ ልደትንና አዲስ ሕይወትን ለመስጠት ነው፡፡ አሮጌውን ለመተውና አዲስ ሕይወትን ለማግኘት የምንችለው ከውኃና ከመንፈስ በተወለድን ጊዜ ነው፡፡ ከውኃና ከመንፈስ መወለድ ማለትም የጌታችን ሕማምና ሞት ስለ እኛ ኃጢአት መሆኑን ማመንና እኛም የሞቱና የመቃብሩ ተባባሪዎች መሆናችንን እንዲሁም በመንፈስ ቅዱስ የትንሣኤው ተሳታፊዎች መሆናችንን በቃልና በተግባር በመግለጽ አዲስ መንፈሳዊ ሕይወትን መኖር ማለት ነው፡፡

ስለዚህ ነው ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ከውኃ መወለድን ማለት ጥምቀትን ከጌታ ሞትና ትንሣኤ ጋር ያስተባበረው፡፡

> "ከክርስቶስ ኢየሱስ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ የተጠመቅን ሁላችን ከሞቱ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ እንደ ተጠመቅን አታውቁምን? እንግዲህ ክርስቶስ በአብ ክብር ከሙታን እንደ ተነሣ እንዲሁ እኛም በአዲስ ሕይወት እንድን መላለስ፥ከሞቱ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ በጥምቀት ከእርሱ ጋር ተቀበርን፡፡ ሞቱንም በሚመስል ሞት ከእርሱ ጋር ከተባበርን ትንሣኤውን በሚመስል ትንሣኤ ደግሞ ከእርሱ ጋር እንተባበራለን፤ ከእንግዲህስ ወዲያ ለኃጢአት እንዳንገዛ የኃጢአት ሥጋ ይሻር ዘንድ አሮጌው ሰዋችን ከእርሱ ጋር እንደ ተሰቀለ እናውቃለን፤ የሞተስ ከኃጢአቱ ጸድቋልና፡፡ ነገር ግን ከክርስቶስ ጋር ከሞትን ከእርሱ ጋር ደግሞ በሕይወት እንድንኖር እናምናለን፤" (ሮሜ.6፥3-8)፡፡

እንግዲህ ክርስቶስ ተጠምቆ እንድንጠመቅ ያደረገን ከሞቱና ከትንሣኤው ተሳታፊዎች እንድንሆን ነው፡፡ ጌታ በጥምቀቱ ለሰዎች ልጆች ሁሉ ኃጢአት በመስቀል ላይ መሞቱን ያስረዳናል፡፡ እኛም በጥምቀታችን ከጌታ ጋር ተባባሪ ስንሆን ለኃጢአት መሞታችንን ማለት ከክፉ ሥራ መለየታችንን ለመንፈስ ቅዱስ መገዛታችንን በአኗኗራችን የምንመሰክርበት ነው፡፡ ከኃጢአት ሕይወት ወደ ጸጋ ሕይወት የምንተላለፍበት እውነተኛ መንገድ ነው፡፡ ኢያሱ ዮርዳኖስን ተሻግሮ እሥራኤልን ሁሉ እንዳሻገረና [illegible] እንዲሁም ጌታችን ተጠምቆ እንድንጠመቅ በማድረጉ [illegible]

www.ethiopianorthodox.org



## አንቀጽ ፮

## ሰው ሆኖ በጳንጤናዊ በጲላጦስ ዘመን ስለ እኛ ተሰቀለ፥ ታመመ፥ ሞተ፥ ተቀበረም፡፡ በሦስተኛውም ቀን ከሙታን ተለይቶ ተነሣ፥ በቅዱሳት መጻሕፍት እንደ ተጻፈ፡፡

በዚህ አንቀጽ ውስጥ የጲላጦስ ስም የተጠቀሰበት ምክንያት የጌታ ሞትና ትንሣኤ የተፈጸመበትን ዘመን ለማመልከት፥ የድርጊቱን ታሪካዊነትና እውነተኛነት ለመግለጽ ነው፡፡ እሥራኤል የሮማ ቅኝ ግዛት በነበረችበት ዘመን የጢባርዮስ ቄሣር እንደራሴ ጳንጤናዊ ጲላጦስ አገሪቱን ይገዛ በነበረ ጊዜ የጌታችን ሕማምና ሞት በእርሱ ዳኝነት ተፈጸመ፡፡

ይህ ታላቅ ነገር በዓለማችን ውስጥ በአንድ ክፍለ ዘመን በአንድ ክፍለ ሀገር የተከናወነ እውነተኛ ታሪክ መሆኑን እንገነዘባለን፡፡ የክርስትና አጀማመር በክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ ላይ የተመሠረተ ነው፡፡ በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ አዲስ የታሪክ ምዕራፍን ከፍቷል፡፡ ከጳንጤናዊ ጲላጦስ ጀምሮ የዚህ ዓለም ገዦች ክርስትናን ወይም ቤተ ክርስቲያንን በዓይነ ቁራኛ ይመለከቷታል፤ ክርስቲያን መሪዎች እንኳ ቢሆኑ ለራሳቸው ጥቅምና አገልግሎት እንድትውል ያደርጓታል፤ ሌሎች ደግሞ ይፈርዱባታል፤ ያሳድዷታልም፡፡ እግዚአብሔር ግን እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ይጠብቃታል፡፡

በአንቀጽ ፮ ውስጥ የምንማረው በመጀመሪያ ክርስቶስ ስለ ኃጢአታችን ሕማማትንና ሞትን መቀበሉን፥ ሁለተኛ ጌታ በአካለ ነፍስ ወደ ሲኦል ወርዶ ነፍሳትን እንዳዳነ፥ ሦስተኛ ስለ ክርስቶስ ትንሣኤ ሲሆን በመጨረሻ ስለ ቅዱሳት መጻሕፍት በአጭሩ እንመለከታለን፡፡

### ሀ) ጌታ ስለ ኃጢአታችን በሥጋ ስለ መሞቱ

ጌታ በመስቀል ላይ ሲሞት በለበሰው ሥጋ እንጂ በመለኮቱ አይደለም፡፡ ክርስቶስ በአምላክነቱ ሞት የለበትም (1ኛጴጥ.3፥18)፡፡ ጌታችን ሰው የሆነው የሰውን ኃጢአትና ሞት ለማስወገድ ነው፡፡ ስለዚህም ጌታችን በለበሰው ሥጋ እንደ ሚታረድ በግ ለኃጢአታችን መሥዋዕት ሆኗል፡፡ እነሆ የእግዚአብሔር በግ የዓለምን ሁሉ ኃጢአት የሚያስወግድ በማለት ስለ ክርስቶስ ተጽፏል (ዮሐ.1፥29)፡፡ ስለዚህም ክርስቶስ የዓለምን ሁሉ ኃጢአት በመሸከም በእኛ ፈንታ ተተክቶ በመስቀል ላይ ሞቶልናል፡፡ አዳም በበደለ መድኃኒ ዓለም ካሣ የተባለው እውነት ነው፡፡

አዳም፥ የፈጠረውንና የሚወደውን አምላኩን በመበደሉና ትእዛዙን በመጣሱ ከእግዚአብሔር ተጣልቶና ተለይቶ ይኖር ነበር፡፡ በዚህም የተነሣ [illegible] የእግዚአብሔርም ቁጣና እርግማን በበደለኛው

www.ethiopianorthodox.org

ግዲህ ወደ እግዚአብሔር ማን ይቀርባል? ማንስ ያስታርቃል? የእግዚአብሔር ፍርድ አይሻር፤ የአምላክ ቃል አይለወጥ።

## የእግዚአብሔር ቅድስናና የሰው ኃጢአት

ማንም ቢሆን ከነ ኃጢአቱ ወደ እግዚአብሔር ሊቀርብ የሚችል የለም። የእግዚአብሔር ባሕርዩ ፍጹም ቅድስና የተሞላበት በመሆኑ እጅግ የሚያስፈራ ነው። ከሰውም ሆነ ከመላእክት ወገን ከነ ኃጢአቱ ከእግዚአብሔር ጋር የኖረ የለም። የመላእክት አለቃ የነበረው ሳጥናኤል ቢበድል ከእግዚአብሔር ፊት ወድቆ ከነ ሠራዊቱ እንጦርጦስ ወርዷል (2ኛጴጥ.2፥4)። አዳም ቢበድል ከገነት ወጥቶ ከነ ልጆቹ በነፍሱ ሲኦል ገብቷል። ኃጢአት ከእግዚአብሔር የሚለየን፥ የችግራችንና የመከራችን ሁሉ መነሻና መሠረት መሆኑን ማስተዋል ይገባናል።

የኃጢአትን አደገኛነት በቀላሉ የሚመለከቱ ወገኖች አሉ። ነገር ግን በእግዚአብሔር ዘንድ እንዲህ አይደለም። ኃጢአት፥ ከእግዚአብሔር መጣላትን ፥ መከራና ሞትን እንዳመጣብን ቅዱሳት መጻሕፍት ይመሰክራሉ። ሆኖም አን ዳንድ የሃይማኖት ወገኖች በሰው ሰውኛ አስተሳሰብ በግል አስተያየታቸው ብቻ እየተመሩ የኃጢአት ሥርየት የለም፥ ከኃጢአታችንም የሚያድነን፥ ከእግዚአ ብሔርም የሚያስታርቀን አያስፈልግም ብለው ያምናሉ። እንደ እውነቱስ እንደ ተገለጸው የእግዚአብሔር ቃል ከሆነ የኃጢአት ሥርየት ከሌለ ማንም ወደ እግዚአብሔር ሊቀርብ ከቶ አይችልም። እውነተኛው አምልኮ በዚህ ላይ የተመሠረተ ነው። በኦሪት ሕግ የመሥዋዕቱና የቁርባኑ ሥርዓት ሁሉ የሚያስተምረን ስለ ኃጢአት ሥርየት ነው። " ደምም ሳይፈስ ሥርየት የለም" እንደ ተባለ በኦሪት ሥርዓት መሠረት የእንስሳት ደም በመሠዊያው ላይ እየፈሰ ሰ የሰዎችን ኃጢአት ሁሉ ለአማናዊው መሥዋዕት ምሳሌ በመሆን ያስተሠርይ ነበር (ዕብ.9፥6-22፤ ዘሌዋ.17፥11)።

እውነተኛው የእግዚአብሔር በግ በመሠዊያው ላይ ደሙን እስኪያፈስ ድረስ በኦሪቱ የፈሰሰው የእንስሳት ደም ሁሉ ምሳሌና ትንቢት ነበር። የእግዚአ ብሔር በግ ክርስቶስ የሰዎችን ልጆች ሁሉ ኃጢአት ለማስተሥረይ በመስቀል መሠዊያ ላይ ደሙን አፍስሶ የኃጢአት ሥርየትን አስገኝቶልናል። እንግዲህ ሰዎች ፍጹም ቅዱስ ከሆነው እግዚአብሔር ጋር ሊታረቁና ሊቀርቡ የሚችሉት በክርስቶስ መሥዋዕትነት ባገኙት የኃጢአት ሥርየት ነው። "ኃጢአተኞችን ሊያድን ክርስቶስ ኢየሱስ ወደ ዓለም መጣ የሚለው ቃል የታመነና ሁሉ እን ዲቀበሉት የተገባ ነው" በማለት ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ያስገነዝበናል (1ኛጢሞ.1፥15)። እኛም በክርስቶስ በማመን "ስለ እኛ ተሰቀለ፥ታመመ፥ ሞተ ተቀበረም፤ በሦስተኛውም ቀን ከሙታን ተለይቶ ተነሣ" በማለት አንቀጸ ሃይማኖታችንን እናጠናክራለን።

እንግዲህ በሰዎችና በእግዚአብሔር መካከል አንድ መካከለኛ (አሐዱ ኅሩይ) ሆኖ ክርስቶስ እንዳስታረቀን ማመን አለብን፤ ያለ እርሱ ማለት እርሱ በሥጋ መምጣቱን በማመን፥ የእርሱን ሥጋና ደም በመቀበል . . . ካልሆ ነ በቀር ማንም ወደ ቅዱስና ፍጹም አምላክ ሊደርስ አይችልም። አንዳንድ የሃይማኖት ወገኖች ወይም የፍልስፍና ሰዎች የሚሉትን በመከተል ማንም ሰው ብቻዬን ወደ እግዚአብሔር እደርሳለሁ ቢል [illegible] የሃይማኖት ነገር [illegible]
[illegible] ሥጎየል አምላክን መልዕልተ ባሕርይ [illegible]



ወይም አስታራቂነት፥ በክርስቶስ የማዳን ሥራና ቤዛነት ላይ የተመሠረተ ነገር እንደ ሆነ ከሐዋርያው ቃል ለመረዳት እንችላለን።

በወንጌልም ያለ ክርስቶስ ወደ እግዚአብሔር የሚቀርብ እንደ ሌለ ተጽፏል። እርሱ ወደ እግዚአብሔር የሚያደርስ እውነተኛ መንገድና በር ነው። ያለ እርሱ መንገዱም በሩም በኃጢአት ግርግዳ የተዘጋ ነው። በእርሱ ባገኘነው የኃጢአት ሥርየት የጥሉ ግርግዳ ስለ ፈረሰ ወደ እግዚአብሔር የሚያገናኘው መንገድ ተከፍቷል። እርሱ ራሱ "መንገድም፥እውነትም ሕይወትም " ነውና። በእርሱ በኩል ካልሆነ "ወደ አብ የሚመጣ የለም" (ዮሐ.14፥6)[57] የተባለው በእርሱ ሥጋዌ በማመን፤ እርሱ በከፈተው የጽድቅ መንገድ፤ እርሱ በመስቀሉ ባስገኘው ቤዛ ካልሆነ በቀር በገሐድ በሥጋዌ ያልተገለጠውን አብን የሚያገኘው የለም ማለት ነው። አንድም "ያለ እኔ ወደ አብ የሚመጣ የለም እኔን ተወላዲ ከላለ አብን ወላዲ የሚለው የለም" ማለት ነው (ዮሐ.14፥6 ትርጓሜውን ተመልከት)።

በመሠረቱ ሰው ወደ እግዚአብሔር መቅረብ የሚችለው ሰው በሆነው በክርስቶስ በኩል ነው። ከዚያ በፊት ግን ሰው መጀመሪያ ወደ ክርስቶስ ለመ- ቅረብና እርሱን ለማመን የሚችለው የእግዚአብሔር ረድኤት፥ የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ ወደ ክርስቶስ ሲስበው ነው። በመሆኑም ክርስቶስ፦ "አልቦ ዘይክል መጺአ ኀቤየ እመ ኢሰሐቦ አብ ዘፈነወኒ -- የላከኝ አባቴ በሀብት ስቦ በረድኤት አ ቅርቦ ካልሰጠኝ በኔ ማመን የሚቻለው የለም" ብሏል (ዮሐ.6፥44 ትርጓሜውን ተመልከት)። እንግዲህ ራሱ እግዚአብሔር እኛ ሰዎችን፥ ኃጢአተኞችን ከራሱ ጋር ለማስታረቅና ለማቅረብ ያሰበውና ያዘጋጀው የጽድቅ መንገድ፥ የሕይወት መንገድ በልጁ ሰው መሆን ማለት በምሥጢረ ሥጋዌና በነገረ መስቀል እንደ ተገለጸው ተፈጽሟል። በሥጋዌ፥ ወልደ እግዚአብሔር ክርስቶስ የሰውን ባሕርይ ባሕርዩ በማድረጉ ያን ጊዜ ባሕርያችንን ከእግዚአብሔር ጋር አስታርቋል። ስለዚህ ነው " የአብ ሊቀ ካህናት የሚሆን እርሱ የሰውን ባሕርይ ከእግዚአ ብሔር ጋር አስታረቀ" እያልን በሐዋርያት አመክንዮ እምነታችንን የምንገልጸው (ሥርዓተ ቅዳሴ፤ ቁጥር 43 ተመልከት)። በመስቀሉ ደግሞ ነፍሱን ስለ ሁላችን ቤዛ አድርጎ በመስጠቱ ሰውን ከእግዚአብሔር አጣልቶና አርቆት የነበረውን ኃጢአትን አስወግዶ እርቅና ሰላምን አስገኝቶልናል። ክርስቶስ ስለ ኃጢአታችን መሥዋዕት በመሆኑ እውነተኛ አስታራቂያችን ሆኗል። ቤተ

---

[57] ወደ እግዚአብሔር የሚያደርሰን አማናዊው መንገድ ("ፍኖተ ጽድቅ ወሕይወት") የተባለው የክርስቶስ ሥጋና ደም ነው። እግዚአብሔር ወደ አለበት ወደ ቅድስት ለመግባት የምንችለው በክርስቶስ ሥጋ በኩል እንደ ሆ ነ ቅዱስ ጳውሎስ ለዕብራውያን ክርስቲያኖች ሲጽፍ፦ " እንግዲህ፥ ወንድሞች ሆይ፥ በመረቀልን በአዲስና በሕያው መንገድ ወደ ቅድስት በኢየሱስ ደም በመጋረጃው ማለት በሥጋው በኩል እንድንገባ ድፍረት" እንዳለን ና እንዲሁም "በእግዚአብሔርም ቤት ላይ የሆነ ታላቅ ካህን" እንዳለን ገልጾልናል። "ወደ ቅድስት በኢየሱስ ደም በመጋረጃው ማለት በሥጋው በኩል እንድንገባ ድፍረት ስላለን" የሚለውን የሐዋርያውን ቃል ትርጉም ወይም ምሥጢር የምንገነዘበው፥ ሰው በሠራው በደልና ኃጢአት ምክንያት ከእግዚአብሔር ተለይቶ በፍርሃትና በጭንቀት ሲኖር ሳለ ክርስቶስ ሰው ሆኖ ደሙን አፍስሶ ኃጢአቱን አስወግዶ ከራሱ ጋር አስታርቆ "ወደ ቅድስት የሚወስደው መንገድ" እንዲከፈት አድርጎ ወደ ሰማያዊው መቅደስ ወደ ጸጋው ዙፋን ወደ እግዚአ ብሔር ለመምጣት፥ ለመግባት መብትን (ድፍረትን) እንዲሁም የጸጋ ልጅነትን እንዲያገኝ ሥልጣንን እንደ ሰጠው በማመን ነው (ዕብ.10፥19-22፤ 9፥8-28፤ 4፥16፤ ዮሐ.1፥12)። የቀድሞው የብሉይ ኪዳን መንገድ ወይም ሥርዓት የሰውን ኃጢአት ስለ ማያስወግድ ከእግዚአብሔርም ስለ ማያስታርቅ እግዚአብሔር በፈቀደውና በደደው "በአዲስና በሕያው መንገድ" ወደ እርሱ እንድንመጣ አድርጎናል። ይኸውም መንገድ በኦሪቱ ሊቀ [illegible] በኩል ሳይሆን ክርስቶስ በሰውነቱ (በሥጋው) በኩል በፈጸመው መሥዋዕትነትና [illegible] ለዕብራውያን በጻፈው መልእክቱ አረጋግጦልናል።
ሊቀ ካህናትነት [illegible]

www.ethiopianorthodox.org

ክርስቲያንም በእርሱ ስም፥ በእርሱ መሥዋዕት የማስታረቁን ሥራ እርሱ ዳግመኛ እስኪመጣ ድረስ በኃላፊነት እንድትሠራ ታዛለች (2ቆሮ.5፥18-21፤ 1ቆሮ.11፥23-26፤ ማቴ.28፥19-20)፡፡ ስለዚህ ነው ክርስቶስ "ከጥንት ጀምሮ እስከ ዘላለሙ ድረስ አስታራቂ ሆነን" ተብሎ የተጻፈው (ሄኖክ 13፥9)፡፡

«እንደ መልከ ጼዴቅ ባለ ሹመት የዓለም ካህን እንደ ሆንክ» የተባለለት «እሱ... ለዘለዓለም ይኖራል፤ ክህነቱ አይሻርምና፡፡ ዘወትር በእሱ በኩል ወደ እግዚአብሔር የሚቀርቡትን ሊያድናቸው ይቻለዋል፤ ለዘለዓለም ሕያው ነውና ያስታርቃቸዋል፡፡ እንዲህ ያለ የካህናት አለቃ ይገባናል... ከሰማያት በላይ የሆነ... ኦሪትስ የሚሞት ሰውን ሊቀ ካህናት አድርጋ ትሾማለች፤ ከኦሪት በኋላ የመጣው የእግዚአብሔር የመሐላ ቃሉ ግን ዘለዓለም የማይለወጥ ፍጹም ወልድን ካህን አድርጎ ሾመልን» (ዕብ.7፥20-28 የግዕዙን ትርጉም ተመልከት)፡፡

ክርስቶስ "መካከለኛ" የተባለበት አዳምና ልጆቹ ሁሉ በኃጢአት ምክንያት ከእግዚአብሔር ጋር ተጣልተው፥ ተለይተውና ርቀው የነበሩትን በማስታረቁና በማቅረቡ ነው፡፡ "ወኮነ ዐራቄ ለሐዲስ ኪዳን በውኂዘ ደሙ ቅዱስ አንጽሖሙ ለመሃይምናን ወለሕዝብ ንጹሐን" እንዲል፤ "ለወንጌል ሊቀ ካህናት፤ ለመንግሥተ ሰማያት አስታራቂ ሆነ . . . በከበረ ደሙ ፈሳሽነት በዓለመ ሥጋ በዓለመ ነፍስ ያሉትን አዳናቸው" አነጻቸው ወደ ቅዱስ እግዚአብሔርም አቀረባቸው (ዕብ.12፥24 እና የእሑድ ውዳሴ ማርያም ትርጉም ተመልከት)፡፡ በቅድሚያ እርሱ ራሱ በተዘምዶተ ሥጋ ማለት ሰው በመሆኑ ወደ እኛ ቀርቧል፤ ከእኛም ጋር ታርቋል፡፡ እንግዲህ እርሱ ራሱ በሰውነቱ ቀርቦ አቅርቦናል፥ ታርቆ አስታርቆናል፡፡

## ነገረ መስቀል

ክርስቶስ የአዳምን ዘር ሁሉ ከእግዚአብሔር ጋር እንዴት አድርጐ ነው ያስታረቀው? ለሚለው ጥያቄ መልሱ ወደ ነገረ መስቀል ይወስደናል፡፡ ነገረ መስቀልን ለማወቅ፥ የመስቀሉን ነገር ለመረዳት የክርስቲያንን ሃይማኖት መሠረታዊ ምሥጢር መመርመር ያስፈልጋል፡፡

የምሥጢረ ሥጋዌም ዓላማ በነገረ መስቀል ይተረጐማል፡፡ እንግዲህ ከሁሉ በፊት መረዳት ያለብን ከጥንተ ፍጥረት የነበረውን የፈጣሪንና የፍጡሩን የሰውን ግንኙነት ነው፡፡ እግዚአብሔር በቸርነቱ ሰውን ከሁሉ ፍጥረት አልቆ በራሱ አርአያና አምሳል ፈጥሮ ገነትን ያህል ቦታ አዘጋጅቶ በተድላ በደስታ እንዲኖርና ሌሎች ፍጥረታትንም እንዲገዛ ሥልጣንም ጭምር ሰጥቶት ነበር(ዘፍ.1፥28)፡፡

አዳም ግን የእግዚአብሔርን ሕግ በማፍረስ በደለ፥ ከፈጣሪውም ጋር ራሱን ለማስተካከል በማሰቡ ይቅርታ የማይገባውን ዓመፅ ፈጸመ፡፡ እንደዚህ በማድረጉ ከእግዚአብሔር ተጣላ፥ ከፊቱም ተባረረ፥ ከገነትም ወጣ፥ ሁለት ዓይነት ሞት ተፈረደበት በሥጋው ወደ መቃብር በነፍሱ ወደ ሲኦል ወረደ፡፡

እግዚአብሔር ርኅሩኅ ስለሆነ የፍጡሩ የሰው ሥቃይ ስላሳዘነው ከራሱ ጋር የሚታረቅበትን መንገድ አዘጋጀ፡፡ ስለዚህም የእግዚአብሔር ቃል ... መጣ፤ ቃሉም ሥጋ ሆነ፡፡ ሁለተኛው አዳም በመባል ክርስቶስ ኃጢአት



... ክርስቶስ በአዳም ምትክ ባይሞት ... (ቆላ.1፥19-20፤ 2፥14-15)፡፡ ... የአዳም ኃጢአት እንደ ተያዘ፥ የሞት ፍርዱም እንደ ጸና ለዘላለም ይቀር... ነበር፡፡

ነገረ መስቀልን አንዳንድ ወገኖች ለመረዳት አስቸጋሪ ይሆንባቸዋል፡፡ እን... እነርሱ አስተሳሰብ እግዚአብሔር ከሰማይ እንዳለ በቃሉ ብቻ በመናገር ለሰ... ልጆች የኃጢአት ሥርየትን፥የምሕረት ጸጋን ሊሰጥ ይችላል በማለት ...ናገራሉ፡፡ ነገር ግን የሰው ሐሳብና የእግዚአብሔር ሐሳብ የተለየ ነው፡፡ ...እግዚአብሔር የተሻለውንና የሚገባውን መንገድ መርጧል፡፡ አሁንም ቢሆን ...ምሕረትን ያገኘነው በእግዚአብሔር ቃል ነው፡፡ የእግዚአብሔር ቃል ሥጋን ...ለብሶ ሰው ሆኖ የምሕረትን ጸጋ ሰጠን፡፡ የምሕረቱ አዋጅ በንግግር ብቻ ...የሚገለጽ ይልቅ ሰው በሆነው በእግዚአብሔር ቃል በሥጋና በደም ኪዳን ...መጽናቱ እጅግ የበለጠ ነው፡፡ መለኮታዊ ቃሉ ሰው ሆኖ በሰው መካከል በመ... ...ኖሩ የእግዚአብሔርን ጸጋና ምሕረት በማብሠር የእግዚአብሔር ፍቅር በሰ... ...ላለስ የእግዚአብሔርን ... ልቡና በጋለ ስሜት እንዲመሠረት አድርጓል፡፡

በሩቅ ከመናገር ይልቅ ሰውን መስሎ ሰውን አህሎ እንደባልንጀራ ሆኖ በቅርቡ በመነጋገር ሥግው ቃል ክርስቶስ አዲስ ልቡና አዲስ መንፈስን ለሰው ልጆች ሊሰጥ አስችሎታል፡፡ እስከ ሞት ድረስ ሰውን መውደዱን በሰውነቱ ገልጾታል፡፡ በንግግር ብቻ ቢሆን ነቢያት ሁሉ የተናገሩትና የአስተማሩት በቂ ...ሆን ነበር፡፡ ነገር ግን በእግዚአብሔር ዘንድ ይህ በቂ አልነበረም፤ ለሚመጣው እውነተኛ ነገር መንገድ የሚያዘጋጅ ነበር እንጂ፡፡ እውነተኛው ነገር አካላዊ ቃል ሰው በሆነ ጊዜ ሰው ሁሉ ሙሉ ምሕረትንና ደኅንነትን አግኝቷል፡፡ የሰ...ውንም ሕማምና ሞት ተቀብሎ ትንሣኤ ሙታንን በተጨባጭ ለማብሠር የቻለው በለበሰው ሥጋ ነው፡፡

እንግዲህ የእግዚአብሔር ቃል በነቢያት አማካኝነት ስለ ኃጢአት ሥርየትና ስለ ዘላለም ሕይወት በቃል ብቻ ተነግሮ ከሚቀርና የእግዚአብሔር አካላዊ ቃል ሥጋ ለብሶ ሰው ሆኖ የሰውን መከራና ሞት ቀምሶ በመጨረሻም ከሞት ተነሥቶ በድርጊት ከማሳየት የቱ ይበልጣል? በድርጊት የተፈጸመው እንደ ሚበልጥ የታወቀ ነው፡፡ ሩኅሩኅና አዛኝ ፈጣሪያችን የፍቅሩን በተጨባጭ የተስፋውን መልእክት ለዓለም ሁሉ በገሐድ ያስታወቀውና በሞቱ የኃጢአት ሥርየትን ያረጋገጠው በክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ ነው፡፡ በሞቱ የኃጢአት ሥርየትን እናገኛለን፤ ከሞት ፍርድ እንድናለን፤ በትንሣኤውም የዘላለም ሕይወትን ተስፋ እናደርጋለን፡፡ እንግዲህ የመስቀሉ ነገር ለማያምኑት ሞኝነት ይመስላል፥ ለሚያምኑት ግን የእግዚአብሔር ጥበብና ኃይል የተገለጸበት ነው (1ቆሮ.1፥18-25)፡፡

የእግዚአብሔር ቃል ወልደ አምላክ ሰው ሆኖ በመስቀል ላይ መሞቱን ስንናገር ለአንዳንድ ወገኖች ይህ ዓይነቱ ትምህርተ ሃይማኖት የእግዚአብሔርን ክብር የሚያዋርድ መስሎ ይታያቸዋል፡፡ ክርስቶስ በሥጋው ውርደትን የተቀበለበት ምክንያት የተዋረደውንና የወደቀውን የአዳምን ዘር ወደ ቀደመው ክብሩ ለመመለስ ነው፡፡ ሰው በአርአያ ሥላሴ በክብር የተፈጠረ ሲሆን የትም ... ክርስቶስ ሁለተኛ አዳም በመሆን ራሱን ዝቅ በማድረግ ... የወደቀውን ሰው ከፍ ከፍ አድርጎታል፤ ጸጋና

www.ethiopianorthodox.org

ፈሳዊ አኗኗርን አሳይቶናል፡፡ የሰው ልጆችም የርሱን አርአያ ቢከተሉ እንከን የሌለበት እውነተኛውን ማኅበራዊ ኑሮ ይመሠርታሉ፡፡ ለመንግሥተ ሰማያትም የበቁ ይሆናሉ፡፡ እንግዲህ የክርስቶስ ውርደት ለኛ ክብርን አስገኝልን፤ የክርስቶስ መሞት ለእኛ ሕይወትን አሰጠን፤ የርሱ ድሀ መሆን ለእኛ ብልጽግና ሆነን (2ኛቆሮ.8፥9፤ ፊልጵ.2፥6-11)፡፡ ስለዚህ ክርስቶስ ውርደትንና ሞትን የተቀበለው ለእኛ ደኅንነት መሆኑን እያስታወስን እርሱ ግን በመለኮቱ ለዘላለም የከበረና የተመሰገነ መሆኑንም እያመንን ከክርስቶስ መስቀል ጠላቶች ራሳችንን እንጠብቅ (ፊልጵ.3፥17-21)፡፡

ኦሪት በእንጨት ተሰቅሎ የሞተ ሁሉ የተረገመ ነው ስለሚል የጌታ አሟሟት ውርደት የበዛበት፥ እርግማን ያለበት መሆኑን እንገነዘባለን (ዘዳግ.21፥22-23)፡፡ ታዲያ እኮ ጌታ ይህን ሁሉ ያደረገው የእኛን ውርደት ወስዶ የእርሱን ክብር ሊያጐናጽፈን ነው፡፡ እኛ በበደላችን የተነሣ በእንጨት ላይ ተሰቅለን ሕማምና ሞትን መቀበል ሲገባን እርሱ በእኛ እግር ተተክቶ ስለ ተቀበለልን እኛን ከበደልና ከመርገም አድኖናል (ገላ.3፥13-14)፡፡ በዚህም የእግዚአብሔር ቸርነትና ርኅራኄ ተገልጧል፡፡ እንግዲህ የመስቀሉ ነገር የእግዚአብሔርን ርኅራኄና አዘኔታ፥ፍርዱንና ጽድቁን የሚያመለክት እንጂ የእግዚአብሔርን ክብር የሚያሳንስ አይደለም፡፡

## ጌታ ከተቀበለው ጸዋትወ መከራ ጥቂቶቹ

ከዚህ ቀጥሎ የክርስቶስ ሕማምና ሞት እንዴት እንደ ተፈጸመ በአጭሩ እንመለከታለን፡፡ ክርስቶስ ከበረት ከተወለደበት ጊዜ ጀምሮ ሕማምና መከራ አልተለየውም፡፡ በትንቢተ ኢሳይያስ ምዕራፍ 53 እንደ ተጻፈው፥ ክርስቶስ የመከራ ሰው የተባለበት ምክንያት ሕማማችንን የተቀበለ ኃጢአታችንን ሁሉ የተሸከመ በመሆኑ ነው፡፡ ነቢዩ ኢሳይያስ የክርስቶስን ሕማምና ሞት እንዴት እንደሆነና ለምን እንደሆነ ድርጊቱ ከመፈጸሙ ሰባት መቶ ዓመት በፊት እንደ ሚከተለው በትክክል ጽፎታል፡፡

> “በእውነት ደዌያችንን ተቀበለ ሕማማችንንም ተሸከሟል፤ እኛ ግን እንደ ተመታ በእግዚአብሔርም እንደ ተቀሰፈ እንደ ተቸገረም ቆጠርነው፡፡ እርሱ ግን ስለ መተላለፋችን ቆሰለ፥ ስለ በደላችንም ደቀቀ፤ የደኅንነታችንም ተግሣጽ በእርሱ ላይ ነበረ፥ በእርሱም ቁስል እኛ ተፈወስን፡፡ . . . ተጨነቀ ተሠቃየም አፉንም አልከፈተም፤ ለመታረድ እንደሚነዳ ጠቦት፥ በሸላቾቹም ፊት ዝም እንደሚል በግ፤ እንዲሁ አፉን አልከፈተም፡፡ በማስጨነቅና በፍርድ ተወሰደ፤ ስለ ሕዝቤ ኃጢአት ተመትቶ ከሕያዋን ምድር እንደ ተወገደ ከትውልዱ ማን አስተዋለ? ከክፉዎች ጋር መቃብሩን አደረጉ . . . ”(ኢሳ. 53፥1-12)፡፡

በጸሎተ ኀሙስ ምሽትና በስቅለት ዓርብ ጌታ ከተቀበላቸው ጸዋትወ መከራ ጥቂቶቹን እንመለከታለን፡፡

## ጌታ በጸሎተ ኀሙስ ምሽት ስለ ተቀበለው ፈተናና መከራ

ጌታ በዚያች ምሽት ከደቀ መዛሙርቱ አንዱ አሳልፎ እንደሚሰጠውና በእርሱም ምክንያት ፈተናና መከራ እንደሚደርስበት አውቆ እንዲህ አላቸው፡፡ “እኔ የመረጥኋቸውን አውቃለሁ፤ ነገር ግን መጽ... ላይ ተረከዙን አነሣብኝ የሚለው የሚፈጸም ዘንድ ነው፡፡ በሆነ ጊዜ እኔ እንደሆንሁ



ብር ለመሸጥ ወደ አይሁድ ሊቃነ ካህናት በሌሊት ሄደ (ዮሐ. 13፥18-30)፡፡ ይህንን ሁሉ አሳዛኝ ሁኔታ ጌታ በቅድሚያ ስለ ሚያውቅ “በመንፈሱ ታወከ” ተብሎ የተነገረው ለዚህ ነው፡፡

ነቢዩ ኢሳይያስ እንደ ተናገረው “የሕማም ሰው ደዌንም የሚያውቅ” እርሱ ነው (ኢሳ.53፥3)፡፡ ጌታ መከራ የተቀበለው በሥጋው ብቻ ሳይሆን በነፍሱም ነው፡፡ ስለዚህ ሕማማትን ለሥጋው፥ ኀዘንና ትካዜን ለነፍስ ሰጥተን እንናገራለን፡፡ ነገር ግን ፈተናና መከራው የሁለቱም በአንድነት መሆኑ አይዘነጋም፡፡ “አሁን ነፍሴ ታውካለች ምንስ እላለሁ? አባት ሆይ፥ ከዚህ ሰዓት አድነኝ፡፡ ነገር ግን ስለዚህ ወደዚህ ሰዓት መጣሁ” በማለት ጌታ የተናገረው ስለ ዕለተ ዓርብ ተልእኮው ነበር (ዮሐ.12፥27)፡፡ ከዚህ ሰዓት አድነኝ በማለቱ ስለ መጀመሪያው አዳም ይጸልያል፡፡ ዳግማዊ አዳም እንደ መሆኑ ስለ ቀዳማዊ አዳም መዳን ሲል በዚች ሰዓት የሞት ጽዋ ለመቀበል እንደ መጣ እንረዳለን፡፡ ስለዚህ በእርግጥ በነፍሱ እንዳዘነ በመንፈሱ እንደ ታወከ ከጥቅሱ ለመማር እንችላለን፡፡ ጌታ ነፍሴ ታውካለች ብሎ ሲናገር “ሰውነቴ ሁከት መንፈሳዊ ታወከችብኝ፤ አድርጋት አትተዋት የሚል ሁከት ተነሣችብኝ፡፡ ወምንተ እብል (ምን እላለሁ)? አባቴ ሰውነቴን ከዚህ ሰዓት አድናት እላለሁን? አልልም፡፡ ወባሕቱ (ነገር ግን) አድናትስ እንዳልል፥አድናትም እንዳልል ስለዚህ ሰው ሁኛለሁ ከጊዜውም ደርሻለሁ፡፡” ማለቱ እንደሆነ ግልጽ ነው (ዮሐ.12፥27 ትርጓሜ ወንጌል)፡፡

ጌታ ሕማምና ሞቱ በተቃረበ ጊዜ በመጀመሪያ ምሥጢረ ቁርባንን የጸሎተ ኀሙስ ማታ መሠርቶታል፡፡ በዚህ ጊዜ የፋሲካን መሥዋዕት ፈጽሞ በምትኩ የሐዲስ ኪዳንን መሥዋዕት ሠርቷል፡፡ ኅብስቱንና ወይኑን ለውጦ በዕለተ ዓርብ በመስቀል ላይ የተሠዋውን ሥጋውንና ደሙን አድርጎ ለሐዋርያቱ ሰጥቷቸዋል (ሉቃ.22፥19-20)፡፡ ይህንንም የሐዲስ ኪዳን መሥዋዕት እስከ ክርስቶስ ዳግም ምጽአት ድረስ ቤተ ክርስቲያን እንድትፈጽመው ታዝዛለች (1ኛ ቆሮ.11፥20)፡፡ ዛሬ በቤተ ክርስቲያናችን የቅዱስ ቁርባን መሥዋዕት በቀረበ ጊዜ በዕለተ ዓርብ በመስቀሉ ላይ የተሠዋውን የጌታን ሥጋና ደም ሆኖ በንስሐ ለተዘጋጁ አማኞች ይሰጣል፡፡

ጌታ ይህንን የመሥዋዕተ ቁርባንን ሥርዓት የመሠረተበት ዋና ምክንያት እርሱ ወደዚህ ዓለም የመጣበትን፥ሥጋም የለበሰበትን ዓላማና ተግባር ለመግለጽ ነው፡፡ ይህም የመስቀል መሥዋዕት ከኃጢአት የሚያድነን፥ የዘላለም ሕይወትን የሚሰጠን ስለሆነ ቤተ ክርስቲያን በዘወትር ቅዳሴዋ ሥጋውና ደሙን ምእመናን እንዲቀበሉ ታደርጋለች፥ በዚህም የክርስቶስ አካልና አባል መሆናቸውን ታረጋግጣለች፥ አንድነታቸውን ታጠናክራለች፥ ኃጢአታቸውን ታስተሠርይላቸዋለች፥ ተስፋቸውን ታድስላቸዋለች፡፡

ጌታ በዚያች ምሽት፥ የዓለምን ኃጢአት ለማስወገድ ለአዳምና ለልጆቹ መራራ የነበረውን የሞት ጽዋ ለመቀበል ተዘጋጀ፡፡ በነፍስም በሥጋም መከራን ... መከራዋ ኀዘንና ትካዜ ነውና ነፍሱም “እስከ ሞት ድረስ ... (ማቴ.26፥37-38)፡፡

www.ethiopianorthodox.org

> ነርሱም የድንጋይ ውርወራ ያህል ራቀ፥ ተንበርክኮም፡- አባት ሆይ፡- ብትፈቅድ ይህን ጽዋ ከእኔ ውሰድ፤ ነገር ግን የእኔ ፈቃድ አይሁን የአንተ እንጂ እያለ ይጸልይ ነበር ከሰማይም መጥቶ የሚያበረታው መልአክ ታየው፡፡ ፈራ፤ መላልሶም ጸለየ፤ ወዙም በምድር ላይ እንደ ሚወርድ እንደ ደም ነጠብጣብ ነበረ፡፡ ከጸሎትም ተነሥቶ ወደ ደቀ መዛሙርቱ መጣና ከኀዘን የተነሣ ተኝተው ሲያገኛቸው፡- ስለምን ትተኛላችሁ? ወደ ፈተና እንዳትገቡ ተነሥታችሁ ጸልዩ አላቸው" (ሉቃ.22፥39-46)፡፡

"መንፈስስ ተዘጋጅታለች ሥጋ ግን ደካማ ነው፡፡" በማለት ጌታችን ደቀ መዛሙርቱ እንዲተጉና እንዲነሡ የሥጋንም ደካማነት እንዲቋቋሙ ወደ ፈተና እንዳይገቡ አበረታታቸው (ማቴ.26፥40-41)፡፡ በፈተናም ጊዜ ተግተው መጸለይ እንዳለባቸው አስተማራቸው፡፡ እርሱም በጸሎቱ እንደ ገለጸው በአባቱ ፈቃድ በራሱ ፈቃድ የሞትን ጽዋ ለመቀበል ተዘጋጀ፡፡

ጌታ የሞት ጽዋ ለመቀበል የመጣ ሆኖ ሳለ ታዲያ ለምንድን ነው "ይህቺን ጽዋ ከእኔ ውሰድ" ወይም "ይህቺ ጽዋ ከእኔ ትለፍ" በማለት ደጋግሞ የጸለየው? በማለት የሚጠይቅ ይኖራል (ማቴ. 26፥39)፡፡ በእርግጥ ጌታ ይህ የሞት ጽዋ እንድታልፍ መጸለዩ ተገቢ ነው፡፡ ምክንያቱም ጌታ ወደዚህ ዓለም የመጣው ይህቺን በአዳም ላይ የተጣለችውን የዘላለም ሞት ሊያሳልፋት እንደሆነ ግልጽ ነው፡፡ ጌታም በለበሰው ሥጋ ስለ አዳም በደል ካሣ ሊከፍል የመጣ ስለሆነ በምር እየደጋገመ መልሶ መላልሶ ይጸልያል፤ በአዳም ላይም የተወሰነው የሞት ፍርድ እንዲነሣለት ይለምናል፡፡ ወዙም በምድር ላይ እንደ ደም ነጠብጣብ እየወረደ መጸለዩ ጌታ ለአዳም በደል ካሣ የመክፈሉን ሁኔታ በግልጽ ያሳየናል፡፡ ጌታ ሰው ከሆነበት ጊዜ ጀምሮ ካሣ እየከፈለ ነው፡፡ ክርስቶስ በሞቱ ብቻ ሳይሆን ካሣ የከፈለው፥ በሕይወቱ ሙሉ በተቀበለው መከራና ፈተና ሁሉ ካሣ ከፍሏል፡፡ እንግዲህ ጌታ ይህቺ ጽዋ ትለፍ ማለቱ "በእኔ ሞት የዓለም ድኅነት፥ በእኔ ኀሣር የዓለም ክብር የሚቻልስ ከሆነ እኔ ከሞትሁላቸው ከእኔ ሞት የተነሣ ይህ ጽዋ ሞት ይቅርላቸው፡፡" ብሎ ለአዳምና ለልጆቹ መጸለዩ ነው (ማቴ.26፥39 ትርጓሜ ወንጌል)፡፡ ዳግመኛም ክርስቶስ የሞት ጽዋ ከእኔ ትለፍ ማለቱ ስለ ራሱ መጸለዩ ሳይሆን ከሰው ሁሉ ሞት እንዲያልፍ ማድረጉ ነው፡፡ የሰውን መከራ መከራው፥ ሞቱን ሞቱ አድርጎ ይቆጥረዋልና (የሐዋ.ሥራ 9፥1-6፤ ማቴ.25፥45)፡፡

"ጌታ ሰው የሆነው ስለ አዳምና ልጆቹ መሆኑን መዘንጋት የለብንም፡፡ ስለዚህ ጌታ የአዳምን ባሕርይ ባሕርዩ አድርጎታል፡፡ ለአዳም ሕይወትን ለመስጠት እርሱ ሞተ፤ ለአዳም ደስታን ለመስጠት እርሱ አዘነ፥ተከዘ፡፡ እንደዚሁም አዳምን ከሞት ፍርሃት ለማዳን እርሱ ደነገጠ፥ ፈራ ስንል በሰው ልማድ ፈራ ማለታችን ሲሆን ይኸን ሁሉ ያደረገው ለካሣ እንደሆነ እንረዳለን፡፡ እንግዲህ ጌታችን ፍጹም ሰው መሆኑና ስለ እኛም ሕማምንና ሞትን እንደ ተቀበለልን እናምናለን፡፡ ጌታም በጸሎተ ኀሙስ ይኸንኑ አረጋግጦልናል፡፡ እርሱ የሥጋን ድካምና ፈተና አሸንፎ ድል አድርጓል፡፡ ስለዚህም ደቀ መዛሙርቱን ከድካማቸውና ከኀዘናቸው፥ ከፍርሃታቸውና ከፈተናቸው ተነሡ፥ ተግታችሁ ጸልዩ እያለ ሲያጽናናቸውና ሲመክራቸው እናያለን፡፡ እርሱ ግን አጽናኝ አይሻም፡፡ ገና ከመጀመሪያው የሰይጣንን ፈተና ድል ያደረገ እርሱ ነው፡፡ በአርባው ጾም ድል የሆነው ሰይጣን "እስከ ጊዜው ከእርሱ ተለየ" ተብሎ የተጻፈው በኋላ እንደ ሚመጣ ያመለክተናል (ሉቃ.4፥13)፡፡ ያን ጊዜ ሰይጣንን ድል ሲያደርግ መላእክት መጥተው እንዳገለገሉት አሁንም በጸሎተ ኀሙስ ለጌታ የተገለጸው መልአክ እርሱን ሊያገለግለው እንደሆነ ግልጽ ነው (ማቴ.4፥11)፡፡ ስለዚህ ነው "ከሰማይም መጥቶ የሚያበረታው መልአክ ታየው" ተብሎ የተጻፈው (ሉቃ.22፥43)፡፡ ጌታ "በዓለም ሳላችሁ መከራ አለባችሁ፤ ነገር ግን አይዟችሁ፤ እኔ ዓለምን አሸንፌዋለሁ" በማለት ደቀ መዛሙርቱን ያበረታታቸው በጸሎተ ኀሙስ [illegible]



ለት፡፡ ኢየሱስ፡- እኔ ነኝ አላቸው፡፡ . . . እንግዲህ፡- እኔ ነኝ ባላቸው ጊዜ ወደ ኋላ አፈግፍገው በምድር ወደቁ" ተብሎ የተጻፈው ቃል የሚያመለክተን በመጀመሪያ ጌታ የሚመጣበትን ነገር ድርጊቱ ከመፈጸሙ በፊት በቅድሚያ ስለሚያውቁ ነው፡፡ ሁለተኛ እንደ ሌባ እንደ ወንበዴ በግድ ተከቦ በኃይል ተሸንፎ የተያዘ ሳይሆን እርሱ ራሱ በፈቃዱ እጁን እንደ ሰጠ የተጠቀሰው ኃይለ ቃል ያስረዳናል(ዮሐ.18፥1-6)፡፡ ቀጥሎ ቅዱስ ጴጥሮስ ሰይፉን መዝዞ የሎሌውን ጆሮ በቆረጠው ጊዜ ጌታ "ሰይፍህን ወደ ሰገባው ክተተው፤ አብ የሰጠኝን ጽዋ አልጠጣትምን?" በማለት ሕማምና ሞትን ሊቀበል መዘጋጀቱን ያረጋግጥልናል (ዮሐ.18፥10-11)፡፡

ጌታም በፈቃዱ እጁን በሰጠ ጊዜ " የሻለቃውና ጭፍሮቹ የአይሁድ ሎሌዎች ኢየሱስን ይዘው አሠሩት፡፡" ወደ ሊቀ ካህናቱም ግቢ ወሰዱት፡፡ ያን ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ ሁሉ ትተውት ሸሹ፡፡ ከቅዱሳን ሐዋርያት ጴጥሮስና ዮሐንስ ብቻ ይከተሉት ነበር (ዮሐ.18፥12-15)፡፡

## የስቅለት ዓርብ

ጌታ ለፍርድ ወደ ሊቀ ካህናቱ ወደ አይሁድ ሸንጎ ቀረበ፡፡ መረመሩትም፥ ጥፋትም አላገኙበትም፡፡ በመጨረሻም የእግዚአብሔር ልጅ ክርስቶስ እንደሆነ ጠየቁት፡፡ እርሱም በእርግጥ ክርስቶስ እንደሆነ መለሰላቸው፡፡ " ከእንግዲህ ወዲህ የሰው ልጅ በኃይል ቀኝ ሲቀመጥ በሰማይም ደመና ሲመጣ ታያላችሁ" በማለት ማንነቱን ገለጠላቸው፡፡ ይህንንም እንደታላቅ ወንጀል ቆጥረው ሞት ይገባዋል ብለው ፈረዱበት፡፡ "በዚያን ጊዜ በፊቱ ተፉበት ጎሰሙትም፤ሌሎችም በጥፊ መትተው ክርስቶስ ሆይ ፡ በጥፊ የመታህ ማን ነው? ትንቢት ተናገርልን አሉ" (ማቴ.26፥57-68)፡፡ ጌታ ኢየሱስን የያዙት ሰዎች ፊቱን ሸፍነው ከመምታታቸውም ሌላ በብዙ ነገር እየተሳደቡ ያፌዙበት ነበር (ሉቃ.22፥63-65)፡፡

የአይሁድ ሸንጎ የሞት ፍርድ ለማስፈጸም ሥልጣን ስለሌለው በዚያን ጊዜ ለነበረው ለሮማዊው የቅኝ ገዢ ለጴንጤናዊ ጲላጦስ ጌታን አሳልፈው ሰጡት፡፡ እነርሱም "ሕዝባችንን ሲያጣምም ለቄሣርም ግብር እንዳይሰጥ ሲከለክል ደግሞም፡- እኔ ክርስቶስ ንጉሥ ነኝ ሲል አገኘነው ብለው ይከሱት ጀመር"፤ ጲላጦስ ግን "አንድ በደል ስንኳ አላገኘሁበትም" በማለት ወደ ሄሮድስ ላከው፡፡ እርሱም "ከሠራዊቱ ጋር ናቀው ዘበተበትም፤ የጌጥ ልብስም አልብሶ ወደ ጲላጦስ መልሶ ሰደደው" (ሉቃ.23፥1-11)፡፡

ከጲላጦስ ፍርድ ችሎት ሁለተኛ በቀረበ ጊዜ ሊቃነ ካህናቱና ሕዝቡ ስቀለው ስቀለው እያሉ ጩኸት ስላበዙ፥ ክርስቶስ በጅራፍ ተገርፎ በራሱ ላይ የእሾህ አክሊል ተደፍቶ ከለሜዳ (ቀይ ልብስ) ለብሶ እንዲሰቀል ጲላጦስ አሳልፎ ለአይሁድ ሰጣቸው፡፡ ጌታችንንም የሚሰቀልበትን መስቀል አሸክመው ወደ ቀራንዮ ኮረብታ እንዲወጣ አደረጉት፡፡ ከዚያም እግሩንና እጁን በቀኖት (በምስማር) ከመስቀሉ ጋር ቸንክረው በሁለት ወንበዴዎች መካከል ሰቀሉት፡፡ የክሱ ጽሕፈትም በመስቀሉ ራስ ላይ "ኢየሱስ ናዝራዊ ንጉሠ አይሁድ" በማለት በሦስት ቋንቋ ማለት በዕብራይስጥ፣ በሮማይስጥና በግሪክ ፊደል ተጽፎ ነበር [illegible]

www.ethiopianorthodox.org

ፍስሲል፡፡ ለሰቀሉት አይሁድ እንኳ "አባት ሆይ የሚያደርጉትን አያውቁ ማራቸው" በማለት ይቅርታን ለምኖላቸዋል (ሉቃ.23፥34)፡፡ ክርስቶስ ለመሥዋ እንደ ቀረበው እንደ እግዚአብሔር በግ ብቻ ሳይሆን እንደ እግዚአብሔርም ሊቀ ህናት በመሆን ራሱን እንደ መሥዋዕት አቅራቢ ሆኖ ለዓለም ሁሉ የኃጢ ሥርየትን አስገኝቷል፡፡ ሰውን ከእግዚአብሐር ጋር አስታርቋል፡፡ ይኸም ሲባል ሰ ከራሱ፥ ከአባቱና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር በሞቱ ማስታረቁን ማስተዋል ይገባ በእግዚአብሔርና በሰው መካከል ያለው መካከለኛ የተባለው እርሱ ሰው የሆነ ክርስ ነው፥ ራሱን ለሁሉም ቤዛ የሰጠ (1ኛጢሞ.2፥5-6)፡፡

ክርስቶስ ወደዚህ ዓለም የመጣበትን፥ ሥጋ የለበሰበትን ዓላማና ተ የፈጸመው የኃጢአት መሥዋዕት በመሆን በዕለተ ዓርብ በመስቀል ላይ ነው፡፡ ስለ ነው በመስቀል ላይ ሆኖ "ተፈጸመ" በማለት የሞትን ጽዋ የተቀበለው፤ "ራሱን አ ብሎ ነፍሱን አሳልፎ" የሰጠው (ዮሐ.19፥30)፡፡ እንግዲህ ክርስቶስ በእግዚአብሔርና ሰው መካከለኛ እንደ መሆኑ ስለ ኃጢአት ምሕረትን የመለመንና የማስታ ሥራውን አንድ ጊዜ በመስቀል ላይ መሥዋዕት በመሆን ፈጽሞታል (ዕብራ.7፥2 9፥12፤ 10፥10-25)፡፡ ይህ ይቅርታን የመለመንና የማስታረቅ ሥራ ከትንሣኤ ላም የክርስቶስ አካል በሆነችው በቤተ ክርስቲያን ጸሎትና ምልጃ እንደዚሁም በ ቀርበው መሥዋዕተ ቊርባን አማካኝነት ቀጥሏል፡፡ ዛሬም ይህ የማማለድና የማስታ ሥራ በሐዋርያዊት ቤተ ክርስቲያን ይሠራበታል፤ "ስለ ክርስቶስ" መልእክተ በመሆን "ከእግዚአብሔር ጋር ታረቁ" እያለች ሰዎችን ትለምናለች፥ እግዚአብ ርንም ታማልዳለች፤ ምክንያቱም የማስታረቁ አገልግሎት ለእርሷ ከእግዚአብሔር ተሰጣት ነው (2ኛቆሮ.5፥18-21)፡፡

ከክርስቶስ ጐን በወጣው ንጹሕ ውኃና ደም የዓለም ሁሉ ኃጢአት ግዷል፡፡ ይህም ውኃና ደም ዛሬም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በመንፈስ ቅዱስ ረድኤት በምሥጢረ ጥምቀትና በምሥጢረ ቊርባን አማካኝነት ይገኛል፤ አምነው ለተ ሉትና ለፈጸሙት ሁሉ የኃጢአት ሥርየትንና የዘላለም ሕይወትን ይሰጣል፡፡ በ ክርስቲያን በምሥጢራት አማካኝነት በዕለተ ዓርብ በክርስቶስ መሥዋዕት የተገኘውን የደኅንነትና የሕይወት ጸጋ ወደ እርሷ ለሚመጡት ሁሉ በነፃ ትሰጣለች ይህንንም ጸጋ እንዲቀበሉ ጥሪ ታደርጋለች፡፡ በጸሎተ ቅዳሴዋም ፈያታዊ ዘየማንን ዳሰብከው አቤቱ እኛንም በመንግሥትህ አስበን እያለች ለሁላችንም ታማልዳለች፡፡

የደኅንነታችን ጸጋ ምንጭ የሆነውን ለሁላችንም የተሠዋውን የእግዚአብሔ በግ ከሰማይ ሠራዊት ጋር በመሆን ቤተ ክርስቲያን እንዲህ እያለች አዲሱን ትዘምራለች፦ "ታርደሃልና፥በደምህም ለእግዚአብሔር ከነገድ ሁሉ ከቋንቋም ከወገንም ሁሉ ከሕዝብም ሁሉ ሰዎችን ዋጅተህ ለአምላካችን መንግሥትና ካህና ይሆኑ ዘንድ አደረግሃቸው . . . የታረደው በግ ኃይልና ባለጠግነት ጥበብ ብርታትም ክብርም ምስጋናም በረከትም ሊቀበል ይገባዋል" (ራእይ 5፥8-14)፡፡

ከሰባቱ አጽርሐ መስቀል[58] አንዱ "ኤሎሄ ኤሎሄ ላማ ሰበቅታኒ ?" የ ነበር፤ ትርጓሜውም "አምላኬ አምላኬ፥ ስለምን ተውኸኝ?" ማለት

58 ሰባቱ አጽርሐ መስቀል የተባሉት ጌታ በመስቀል ላይ ሆኖ የተናገራቸው ናቸው፡፡ (1) የመስቀል መከ ሞትን ላደረሱበት ሰዎች ሁሉ ጌታ እንዲህ አለ፦ "[illegible] በላቸው" (ሉቃ.23፥34)፡፡ (2) በመስቀሉ ሥር ለነበረችው [illegible]



(ማቴ.27፥46)፡፡ በመሠረቱ ይህ ቃል የዕብራይስጥ ሲሆን ሁሉም ሰው እን ጸለየው በመዝሙረ ዳዊት በሁሉም ቋንቋ ተጽፎ ይገኛል (መዝ.21፥1)፡፡ ታም ይህን እንደ ጸሎት በጸሎትነቱ ተናግሮታል፡፡ ሆኖም ጌታ ይህንን ቃል ዚያች ወቅት በታላቅ ድምጽ ጮኾ የተናገረበት ወይም የጸለየበት ምክን ት አለው፡፡ ይህም በኃጢአት ምክንያት እግዚአብሔር የተወውንና የጠፋውን የሰውን ሁኔታ ያመለክተናል፤ እነርሱም አዳምና ልጆቹ ናቸው፡፡ ክርስቶስም የአ ሞን ኃጢአት በራሱ ላይ እንደ መሸከሙ መጠን በአዳም ስም በእርሱ ተገብቶ ለአዳም አምላክ መናገሩን ማለት መጸለዩን የሚያስረዳ ቃል ነው፡፡ እንግዲህ የአ ም አምላክ በኃጢአቱ ምክንያት አዳምን እንዳይተወው ስለ አዳም የቀረበ ቃል ሎት መሆኑን እንረዳለን፡፡ ጌታም የመጣበት ዓላማ ይኸው ነው፡፡ የሰው ልጅ በኃጢአቱ ምክንያት በፈጣሪው ዘንድ ተረስቶና የትምተትቶ እንዳይቀር ጌታ ስለ ሰው በደል በመስቀል ላይ መሥዋዕት በመሆን ካሣ ከፍሎ ይቅርታንና እርቅን አስ ኝቶለታል፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ በኃጢአቱ ምክንያት የተተወውንና የወደቀውን የሰው ሕማምና መከራ ጌታችን በነፍሱም በሥጋውም በእርግጥ የተቀበለው ለመሆኑ የተጠቀሰው ቃለ መስቀል ይመሰክራል፡፡ አዳም በበደሉና በኃጢአቱ ምክንያት ሊቀበል የሚገባውን ሕማምና ሞት ክርስቶስ በመስቀል ላይ የተቀበለው መሆኑን ማመን ይኖርብናል፡፡ ስለዚህም የአዳምን ባሕርይ ገንዘብ በማድረግ በሥጋ ሥርዓት ሁለተኛ አዳም በመሆኑ ኤሎሄ ኤሎሄ ብሎ ተናገረ፡፡ ለተተወው ለአዳም ይቅር ታን ለመነለት፡፡ ለእርሱ ብቻ አይደለም ለተተውት ሁሉ ይለምናል፡፡ "በኀጹጋኑ ተገብቶ ይጸልያል" ተብሎ እንደ ተተረጐመ አስተውል (ማቴ.27፥46 ትርጓሜ ወን ጌል)፡፡ "በኀጹጋኑ" ማለት "በተተውት" ሰዎች ስም ከመጸለዩ ጋር የእነርሱን የበደላቸውና የኃጢአታቸው ውጤት የሆነውን ሕማምና መከራ በመሸከሙ በነፍሱ ኀዘን በሥጋው ደግሞ ሕማም በእርግጥ እንደ ተሰማው እንረዳለን፡፡ ፍጹም ሰው የሆነ አምላክ ስለሆነ በሥጋውም ከኃጢአት በስተቀር እንደ ሰው በመሆኑ በነፍሱ ከባድ ፈተናና ኀዘን እንደ ደረሰበት፥ በሥጋውም የመገረፍና የቅንዋተ መስቀል መከራን ስለ ተቀበለ እጅግ ከፍተኛ ሕማም እንደ ተሰማው እናምናለን፡፡ ይህንን አለማመን የጌታ ሰውነት፥ እንደ ተወገዙት መናፍቃን፥ ምትሐታዊ ሁኔታ እንዳለበት ያስመስልብናል፡፡ ጌታ የተራበ የተጠማ ይመስላል፤ ሕማምና ሥቃይ አይሰማውም ብሎ መናገር ወልድ ሥጋን አልተዋሐደም የሥጋን ባሕርይ ገንዘብ አላደረገም ብሎ እንደመካድ ይቆጠራል፡፡ ጌታ በእውነት በሥጋው ሕማምና ሞትን ካልተቀበለ እንደምን አድርጐ የአዳምን በደል ለመካሥ ወይም ለዓለም ቤዛ ለመሆን ይችላል? በኃጢአት ላይስ የተወሰነው የእግዚአብሔር ፍርድ እንዴት ይፈጸማል?

ጌታ ቅድስት ነፍሱን ከቅድስት ሥጋው ከለየ በኋላ መለኮት ያልተለየው ሥጋው ለጥቂት ጊዜ በመስቀል ላይ ቆይቷል፡፡ ራሱን ዘንበል አድርጐ፥ ከእንጨት መስቀሉ ጋር የተቸነከሩ እጆቹን ዘርግቶ፥ በቀኖት የተቸነከሩት ሁለቱን እግ ሮቹን አነባብሮ እስከ ምሽት ድረስ ቆይቷል (ማቴ.27፥57)፡፡ በዚህ ጊዜ ውስጥ ነበር ከጭፍሮቹ አንዱ ጐኑን በጦር የወጋው (ዮሐ.19፥31-37)፡፡

"ከዚህም በኋላ አይሁድን ስለ ፈራ በስውር የኢየሱስ ደቀ መዝሙር የነበረ የአርማትያስ ዮሴፍ የኢየሱስን ሥጋ ሊወስድ ጲላጦስን ለመነ፥ ጲላጦስም ፈቀደለት፡፡" ዮሴፍና ኒቆዲሞስ የጌታን ሥጋ ከመስቀል አውርደው " እንደ አይ ሁድ አገናነዝ ልማድ ከሽቱ ጋር በተልባ እግር ልብስ ከፈኑት፡፡ በተሰቀለበትም ስፍራ አትክልት ነበረ፥ በአትክልቱም ማንም ገና ያልተቀበረበት አዲስ መቃብር ነበረ፡፡" በዚያም አኖሩት፡፡ የመቃብሩንም ደጃፍ በታላቅ ድንጋይ ገጠሙት ([illegible] 57-61)፡፡

[illegible] የክብሮት አለቆችና ፈሪሳውያን

www.ethiopianorthodox.org

ትመው መቃብሩን አስጠበቁ" (ማቴ.27፥62-66)።

## ለ) ጌታ ነፍሳትን ከሲኦል እንዳወጣ

ጌታችን በሥጋው በመስቀል ላይ ሞተ፤ ወደመቃብርም ወረደ። በነፍሱ ደግሞ በታላቅ ግርማ መለኮት በመገለጥ ከአዳም ጀምሮ በዲያብሎስ ግዛትና በሲኦል ግዞት ውስጥ ለነበሩት ነፍሳት ሁሉ ነፃነትን ሰበከላቸው። የኃጢአታቸውን ቅጣትና የሞት ፍርዳቸውን በራሱ ሰውነት ተቀብሎ ዓርብ በዘጠኝ ሰዓት በመስቀል ላይ በመሞት ስለ እነርሱ የተሠዋው ሥጋው በመስቀል ላይ እንዳለ፤ ጌታ በአካለ ነፍስ ከሲኦል ወርዶ ነፍሳትን ከጨለማው ግዛት አውጥቶ ከእውነተኛው የተስፋ ሀገር ከገነት አግብቷቸዋል። በአዳምና ሔዋን የተዘጋችው ገነት የስቅለት ዓርብ ተከፈተች። "ዛሬ ከኔ ጋር በገነት ትሆናለህ" በማለት ክርስቶስ ለፈያታዊ ዘየማን የሰጠው ተስፋ በዚያን ጊዜ ተፈጸመች (ሉቃ.23፥43)።

የነፍሳት ከሲኦል ነፃ መውጣት ትንቢቱና ምሳሌው በኦሪት ዘጸአት ተገልጿል። በሙሴ አማካኝነት እስራኤል ከባርነት ቤት፤ ከፈርዖን ግዛት ነፃ ወጥተው፥ ቀይ ባሕርን ተሻግረው፥ በረሓውን አቋርጠው ዮርዳኖስን ተሻግረው ወደ ምድረ ርስት እንደገቡ እንደዚሁ በክርስቶስ አማካኝነት በጥምቀቱና በሞቱ ነፍሳትን ከሲኦል ወኅኒ ቤት ነፃ አውጥቶ የሞት ባሕርን አሻግሮ ወደ ሀገረ እግዚአብሔር ገነት አስገብቷቸዋል። ጌታ በሥጋ ስለ መሞቱና በአካለ ነፍስም ወደ ሲኦል መውረዱን በማስመልከት ቅዱስ ጴጥሮስ እንደ ሚከተለው ጽፏል። "ክርስቶስ ደግሞ ወደ እግዚአብሔር እንዲያቀርበን እርሱ ጻድቅ ሆኖ ስለ ዓመፀኞች አንድ ጊዜ በኃጢአት ምክንያት ሞቷልና፤ በሥጋ ሞተ በመንፈስ ግን ሕያው ሆነ፥ በእርሱም ደግሞ ሄዶ በወኅኒ ለነበሩ ነፍሳት ሰበከላቸው" (1ኛጴጥ.3፥18-19)። ሰበከላቸው ማለት ነፃነትንና ደኅንነትን አወጀላቸው ማለት ብቻ ሳይሆን ነፃ አወጣቸው ማለት ነው።

እንግዲህ በዘመነ ብሉይ ያሉት ነፍሳት ሁሉ ነፃ ወጥተዋል፤ ነገር ግን ሁሉም ከነአብርሃም ጋር ገነት ገብተዋል ማለት አይደለም። እንደነፈርዖን እንደ ነሄሮድስ በኋላም እንደነአስቆሮቱ ይሁዳ የመሳሰሉት ሁሉ እጣ ፋንታቸው ንስሐን ከማያውቀው በትዕቢቱና በዓመፁ በጸናው ከዲያብሎስ ጋር መሆኑ የታመነ ነው (መቅድመ ወንጌል ተመልከት)።

ሲኦል ሲባል ከአዳም ጀምሮ ነፍሳት ሁሉ ክርስቶስ በመስቀሉ እስኪያድናቸው ድረስ በግዞት የነበሩበት ስፍራ ሲሆን፥ ለሰይጣንና ለሠራዊቱ የተዘጋጀው ስፍራ ግን እሳቱ የማይጠፋ ትሉ የማያንቀላፋ እንደሆነ ከወንጌል ቃል እንማራለን። በአጠቃላይ አነጋገር ሁሉም የሲኦል ግዛት ይባላሉ። ሆኖም የአብርሃም ነፍስ በደኅና ቦታ እንደ ነበረችና ድሀው አልዓዛርም በሞተ ጊዜ ነፍሱ ከአብርሃም አጠገብ እንደ ተቀመጠች፥ ክፉ የሠራው ባለጸጋ (ነዌ) ሲሞት ግን ነፍሱ በእሳት እንደምትሠቃይ ክርስቶስ በወንጌሉ እንደ ሚከተለው አስተምሮናል።

> "ድሀውም ሞተ፥ መላእክትም ወደ አብርሃም እቅፍ ወሰዱት፤ ባለጠጋው ደግሞ ሞተና ተቀበረ። በሲኦልም በሥቃይ ሳለ አሻቅቦ አብርሃምን በሩቅ አየ። አልዓዛርንም በእቅፉ። እርሱም እየጮኸ፦ አብርሃም አባት ሆይ፥ ማረኝ፥ በዚህ ነበልባል እሠቃያለሁና የጣቱን ጫፍ በውኃ ነክሮ መላሴን እንዲያበርድልኝ አልዓዛርን ስደድልኝ አለ። አብርሃም ግን፦ ልጄ ሆይ፥ አንተ በሕይወትህ ሳለህ መልካም እንደ ተቀበልህ አስብ አልዓዛርም እንዲሁ ክፉ፤ [illegible]
> [illegible] ከዚህም ሁሉ ጋር ከዚህ ወደ እናንተ ሊያልፉ የሚፈልጉ እን



> ሰሙ ከሆነ፥ከሙታንም እንኳ አንድ ቢነሣ አያምኑም አለው" (ሉቃ.16፥19-31)።

እንግዲህ ከሉቃስ ወንጌል እንደምንማረው ገነት ከመከፈቱ በፊት ነፍሳት በተለያዩ ስፍራዎች እንደነበሩ ነው። ከኃጢአትና ከሞት የሚያድነው መሢሕ (ክርስቶስ) ይመጣል ብለው የሚያምኑትና በተስፋውም የጸኑ የብሉይ ኪዳን ቅዱሳን ነፍሳት የነበሩበት ስፍራ በአጠቃላይ ስሙ ሲኦል ወይም ወኅኒ የግዞት ቦታ ቢባልም በእግዚአብሔር ጥበቃ ከሥቃይና ከመከራ ነፃ እንደ ነበር የታመነ ነው። ሌላው ስፍራ ግን የጨለማ ጉድጓድ እንጦርጦስ የሚባለው ነው። ይህም "እግዚአብሔር ኃጢአት ላደረጉት መላእክት ሳይራራላቸው ወደ ገሃነም ጥሎ በጨለማ ጉድጓድ ለፍርድ ሊጠበቁ አሳልፎ" የሰጣቸው የሥቃይ ቦታ እንደ ነበር ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ በመልእክቱ ገልጦታል (2ጴጥ.2፥4)።

በዕለተ ዓርብ በክርስቶስ ገነት ከተከፈተች በኋላ የቅዱሳን ነፍሳት እስከ መንጻግም ምጽአት የሚቆዩበት ስፍራ ከዚያው ከገነት ሲሆን በመጨረሻ ደግሞ መንግሥተ ሰማያት ይገባሉ። የኃጥአን ነፍሳት ግን ለጊዜው በሲኦል ቆይተው በመጨረሻው ፍርድ ቀን ለሰይጣንና ለሠራዊቱ ከተዘጋጀው ገሃነመ እሳት ሁለተኛ ሞት ካለበት የእሳት ባሕር እንዲገቡ ይፈረድባቸዋል (ራእይ.20፥14)። ሁሉም እንደ እምነቱና እንደ ሥራው ፍርድን ይቀበላል (ሮሜ.2፥6-10፤ ማቴ.25፥41)።

በክፉ ሥራቸው ተጸጽተው ንስሐ ገብተው የአዳኛቸውን ሥጋና ደም የተቀበሉ ሁሉ የሰላምና የደስታ ሕይወት ከገነት ይጠብቃቸዋል። በአመፃቸው ጸን ተው ንስሐ ያልገቡ በሰማይም በምድርም ምሕረት አያገኙም። ምክንያቱም በምድር ከኃጢአታቸው አልተፈቱምና ነው። ኃጢአታቸው በምድር የተያዘባቸው ከሆነ በሰማይም እንደ ተያዘባቸው ይቀራል (ዮሐ.20፥23)።"እውነት እላችኋለሁ፤ በምድር የምታሥሩት ሁሉ በሰማይ የታሠረ ይሆናል" ብሎ ጌታ ለሐዋርያት የተናገረው ቃል ይጸናባቸዋል። (ማቴ.18፥18፤ 16፥19)።

ነገር ግን አንዳንድ አማኞች በክፉ ሥራቸው ከልባቸው ተጸጽተው ንስሐ ገብተው ቀኖናቸውን ጀምረውት ቢሞቱ ሳይጀምሩትም ቢሞቱ በምድር የኃጢአታቸውን ፍትሐት ስላገኙ ከኃጢአታቸው እንዳልተፈቱት ከሃድያንና ዓመፀኞች እንጦርጦስ አይወርዱም። «መካነ ንስሐ» አለ ከዚያ ቀኖናቸው ከተፈጸመ በኋላ ይወጣሉ (ትርጓሜ ወንጌል፤ ማቴ.12፥32 ተመልከት)።

«መካነ ንስሐ» ማለት የንስሐ ቦታን ብቻ ሳይሆን የንስሐ ሁኔታንም ያመለክታል። በንስሐ በቀኖና ውስጥ የሆነ ሰው በአፀደ ሥጋም ሆነ በአፀደ ነፍስ ያለበት ቦታ ብቻ ሳይሆን የገባበትም የመንፈስ ሁኔታ መካነ ንስሐ ሊሆን ይችላል። እንግዲህ "መካነ ንስሐ" ሲባል አዳም በሥጋም በነፍስም ከሚኖርባት ከገነት በጥንተ አብሶ ምክንያት ከተባረረ ጊዜ ጀምሮ በሥጋውም በነፍሱም መከራና ፈተና ከሚቀበልባት ከዚህች ምድር ማለት ከምድረ ፋይድና ከሲኦል ሌላ የተለየ የቅጣት ቦታ አለ ማለት አይደለም፤ እነዚሁ ቅሉ የንስሐ የቀ ኖና /የቅጣት/ መቀበያ ቦታዎች /ሁኔታዎች/ ይሆናሉ ማለት ነው እንጂ። «እግዚአብሔር ይገላል ያድናልም፤ ወደ ሲኦል ያወርዳል፥ ያወጣል» ተብሎ እንደተጻፈ ንስሐቸውን ሳይጨርሱ ከዚህ ዓለም በሞት ለተለዩት ሰዎች እግዚአብሔር ለነፍሳቸው ምሕረትን ሰጥቶ ከሲኦል ያወጣቸው ዘንድ ካህናት /የንስሐ አባቶች/ ይጾሙላቸዋል ይጸልዩላቸዋል፥ ወዳጅ ዘመድም ምጽዋት ያደርጉላቸዋል ቁርባን ያስቆርቡላቸዋል፤ ቤተ ክርስቲያንም ጸሎተ ፍትሐት በየጊዜው ታደርስላቸዋለች /1ሳሙ.2፥6፤1ቆሮ.5፥3-5፤11፥30-32፤1ጢሞ.1፥20፤ያዕ.5፥14-16፤2ተሰ.3፥14-15/።

ንስሐ የገቡ ኃጥአን በሚመጣው ዓለም ከሰማይ ምሕረትን እንደ ሚያገኙ የሚያመለክተንን የወንጌል ቃል እንጠቅሳለን። ይኸውም መንፈስ ቅዱስን የሰደበ "በዚህ ዓለም ቢሆን ወይም በሚመጣው አይሠረይለትም" በማለት ክርስቶስ [illegible] (ማቴ.12፥31-32)። እንግዲህ በሚመጣውም ዓለም አይሠ

www.ethiopianorthodox.org

ለሌላው ይጸልያል፡፡ ለሞት የማያደርስ ኃጢአት ለሠሩት ሁሉ መጸለይ እንደ ሚገባን ተጽፏልና (1ኛዮሐ.5፥16-17)፡፡

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም በዚያ ታላቅ የፍርድ ቀን ምሕረት እንዲያገኝ በሞት ለተለየው ለሄኔሲፎሩ ጸልዮለታል (2ጢሞ.1፥16-18፤ 4፥19)፡፡ በሰማይ የኃጢአት ስርየት እንዳለ በማመን ቤተ ክርስቲያናችን ለሙታን ነፍሳት ጸሎተ ፍትሐት ታደርጋለች፡፡ በጸሎተ ቅዳሴዋም የሙታንን ነፍሳት ታስባለች፡፡ ይህም ከሐዋርያት ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ የቤተ ክርስቲያን ትውፊት ነው፡፡

በእሥራኤል ታሪክ ውስጥ ይሁዳ መቃቢስ የተባለ መሪ፥ ጣዖትን እን ዲያመልኩና እግዚአብሔርን እንዲክዱ ካስገደዳቸው ከአንጥያኮስ ሠራዊት ጋር ሲዋጉ ለሞቱ ጭፍሮቹ ጸሎትና የኃጢአት ማስተሥረያ መሥዋዕት በኢየሩሳሌም በሚገኘው ቤተ መቅደስ እንዲቀርብላቸው አድርጓል፡፡ ይህም ታሪክ በሰባው ሊቃናት ተተርጉሞ በጽርእ ቋንቋ በተጻፈው ሁለተኛ መቃብያን ምዕራፍ 12 ከቁጥር 38 እስከ 45 ድረስ ተጽፎ ይገኛል፡፡[58.1] ለሞቱ ነፍሳት መጸለይ እንደ ሚገባ በዲድስቅልያ መታዘዙና ዛሬም በጥንታውያን ማለት ሐዋርያዊ መንበር ባላቸው አብያተ ክርስቲያናት ሲሠራበት መታየቱ የጸሎተ ፍትሐትን እውነተኛነት ያስገነዝበናል (ሲራክ 38፥23)፡፡

እርግጥ ነው ጸሎተ ፍትሐት የተደረገለት ሁሉ የኃጢአት ሥርየት አግኝቶ ሁሉም ገነት ወይም መንግሥተ ሰማያት ይገባል ብሎ ማረጋገጥ አይቻልም፡፡ ሟች በሕይወቱ ሳለ ስለ ኃጢአቱ ከልቡ ተጸጽቶ በንስሐ ላይ እንዳለ ቢሞት የቤተ ዘመ ዶቹና የክርስቲያን ወንድሞቹ ጾምና ምጽዋት፥ የቤተ ክርስቲያን ጸሎትና ምልጃ ለነፍሱ ምሕረትን እንዲያገኝ ይረዳል፡፡ ነገር ግን አንድ አማኝ የነበረ፥ ንስ ሓን ንቆ ሃይማኖቱን ክዶ ከቤተ ክርስቲያን ርቆ የሚገኘውን ወይም ራሱን በራሱ ሕይወቱን ያሳለፈውን ሰውና ለመሳሰሉት ሁሉ ቤተ ክርስቲያን ጸሎተ ፍትሐት አ ታደርስም፡፡

## ሐ) ስለ ክርስቶስ ትንሣኤ

"በሦስተኛውም ቀን ከሙታን ተለይቶ ተነሣ በቅዱሳት መጻሕፍት እንደ ተጻፈ" የተባለው ቃለ ሃይማኖት ኢየሱስ ክርስቶስ በአካለ ነፍስ ሲኦል ወርዶ ነፍሳትን ነፃ አውጥቶ ገነት ካስገባቸው በኋላ ሞተ ነፍስን ድል እንዳደረገ እን ደዚሁም ሞተ ሥጋን ድል በማድረግ ከመቃብር ተነሥቷል በማለት እምነታችንን ይገልጻል፡፡ የክርስቲያን ሃይማኖት በክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ ላይ የተመሠረተ መሆኑን እናምናለን፡፡ በሞቱ የኃጢአት ሥርየት አግኝተን ከእግዚአብሔር ጋር የታረቅንበት ነው፡፡ በትንሣኤው እምነታችንና ተስፋችን ፍጹም እውነት መሆኑን የምንመሰክርበት ነው፡፡ በክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ የነፍስና የሥጋ ትንሣኤ እን ዳለ አመንን፡፡ የክርስቲያን ሃይማኖት ትንሣኤ ሙታን መኖሩን የሚያምነውና የሚያስተምረው በቃል በማወጅ ብቻ አይ ደለም፡፡ ነገር ግን የክርስቶስ ሥጋ ሞቶ መነሣቱን ምስክር በማድረግ ነው፡፡ እርሱ ክርስቶስ የሙታን ሁሉ በኩር ሆኗል፡፡ ከእርሱ በፊት ሞቶ የተነሣ የለም፤ በእግዚአብሔር ተአምራት የተነሡት ሁሉ እን ደገና ወደ መቃብር ወርደዋል፡፡ ክርስቶስ ግን ከሙታን ተነሥቶ ለዘላለም ሕያው ነው፡፡ እርሱም በመጨረሻው ቀን ለሚፈጸመው የሙታን ትንሣኤ የመጀመሪያው ሆኗል፡፡



ትጽበት ድል ተመትቷል፡፡ በሞቱ ሞትን ደምስሶታልና፡፡ በዕለተ ዓርብ ነፍሳት ከሲኦል እንደ ወጡ ሁሉ ብዙዎችም በሥጋቸው ከመቃብር ወጥተዋል፥ ተነሥተዋል፡፡ በቅድስት ከተማም እንደ ታዩ ተጽፏል (ማቴ.27፥52-53)፡፡ የጌታ ሥጋ ገና ሳይነሣ ሙታን ከመቃብር መነሣታቸው የእርሱ ሞት የእኛ ትንሣኤ መሆኑን ያሳየናል፡፡ ክርስቶስ፥ እንደ ታረደ በግ በእፀ መስቀል ላይ ራሱን ዘንበል አድርጎ መሥዋዕት በሆነ ጊዜ በአዳም የመጣብንን መርገመ ሥጋና መርገመ ነፍስ ማለት በኃጢአት ምክንያት የተፈረደብንን የሞት ፍርድ በራሱ ሞት አጥፍቶ የነፍስና የሥጋን ትንሣኤ የሰጠን ዓርብ ዕለት ነው፡፡ ይህንኑ በመስቀሉ ያስገኘውን ታላቅ ድል ጌታ በሦስተኛው ቀን ከሙታን ተለይቶ ሲነሣ አረጋግጦታል፡፡

"ሞት ሆይ፥ መውጊያህ የት አለ? ሲኦል ሆይ፡ ድል መንሣትህ የት አለ? የሞት መውጊያ ኃጢአት ነው የኃጢአትም ኃይል ሕግ ነው፤ ነገር ግን በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ድል መንሣትን ለሚሰጠን ለእግዚአብሔር ምስጋና ይሁን" (1ቆሮ.15፥55-57)፡፡

## ለዓለም ሁሉ የሚሰጥ እውነተኛ የትንሣኤ ምልክት

ከሞቱና ከትንሣኤው በፊት አይሁድ ጌታን ልዩ ምልክት (ተአምራት) እንዲያሳያቸው በጠየቁት ጊዜ የነቢዩ ዮናስን ሁኔታ አስመልክቶ ስለ ትንሣኤው እንዲህ ሲል ነግሯቸው ነበር፦ "ክፉና አመንዝራ ትውልድ ምልክት ይሻል፥ ከነቢዩም ከዮናስ ምልክት በቀር ምልክት አይሰጠውም፡፡ ዮናስ በዓሣ አንባሪ ሆድ ሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት እንደ ነበረ፥ እንዲሁ የሰው ልጅ በምድር ልብ ሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት ይኖራል" (ማቴ.12፥38-40)፡፡ ይህንንም የሰሙ አይሁድ ጌታ በሦስተኛው ቀን ይነሣል በማለት መቃብሩን አሽገው በወታደሮች ያስጠብቁ ነበር (ማቴ.27፥62-66)፡፡ ጌታ ግን እንደ ተናገረው ዓርብን በከፊል ቅዳሜን በሙሉ እሑድን በከፊል በመቃብር ከቆየ በኋላ ቅድስት ነፍሱንና ቅድስት ሥጋውን በማዋሐድ በሦስተኛው ቀን መግነዝ ፍቱልኝ፡መቃብር ክፈቱልኝ ሳይል ተነሥቷል፡፡

ይህንንም ካዩት ወታደሮች የመቃብሩ ጠባቂዎች አንዳንዶች ወደ ከተማ ሄደው የክርስቶስን ትንሣኤ ለካህናት አለቆች ቢነግሯቸው ነገሩ እውነት መሆኑን ቢያውቁም ሊቀበሉት አልፈለጉም፡፡ ምክንያቱም ፍርድና ሞት ነገ በራሳቸው ላይ ቢመጣ የማይፈሩ ብቻ ሳይሆን የእውነትና የጽድቅ ጠላቶችም በመሆናቸው ጭምር ነበር፡፡ ስለዚህም የመቃብር ጠባቂዎቹን በማባበልና ብዙ ገንዘብ በመስጠት ሐሰት እንዲናገሩ አስተማሯቸው፡፡ "እኛ ተኝተን ሳለን ደቀ መዛሙርቱ በሌሊት መጥተው ሰረቁት በሉ" አሏቸው (ማቴ.28፥11-15)፡፡ ኧረ ለመሆኑ የተኛ ሰው፥ እንቅልፍ የወሰደው ምን አይቶ ይመሰክራል? ይህን አይቻለሁ ቢል እንኳ፥ ተኝ ቻለሁ እንቅልፍ ወስዶኛል አላልክም ነበርን? እንዴት ልታይ ቻልክ ተብሎ ሐሰቱ ተመልሶ ወደ ራሱ ይመጣል፡፡

እውነቱ ግን ክርስቶስ ከሙታን ተለይቶ ተነሥቷል፡፡ ለአይሁድም ሊሰጣቸው የነገራቸው ታላቁ ምልክት ትንሣኤው ነበር፡፡ እነርሱ ግን ከእውነት ይልቅ ሐሰትን ስለፈለጉ አላመኑትም፡፡ ዛሬም ለዓለም ሁሉ የሚሰጠው ታላቁ ምልክት የክርስቶስ ትንሣኤ ነው፡፡ ሐዋርያትም ይህንኑ የትንሣኤ ወንጌል ሲሰብኩና ሲመሰክሩ ነው ሕይወታቸውን በዓላውያን ነገሥታት ፊት እስከ ማሳለፍና ደማቸውንም እስከማፍ

www.ethiopianorthodox.org

በመጀመሪያው የትንሣኤ እሑድ በጠዋት ወደ መቃብር ሄደው ለሚያለቅሱት ለማርያም መግደላዊትና ለሌሎችም ከሙታን የተነሣው ጌታ ተገልጾላቸዋል፡፡ እነርሱም የመጀመሪያውን የትንሣኤ ዜና ለሐዋርያት አብሥረዋል (ሉቃ. 24፥10)፡፡ ይኸንን የሰሙ ቅዱሳን ጴጥሮስና ዮሐንስም በፍጥነት ከመቃብር ቢደርሱ መቃብሩ ባዶ ሆኖ አግኝተውታል፡፡ የመግነዙም ልብስ ከነበረበት ቦታ በትክክል ተጠቅልሎ እንደ ተቀመጠ አዩ፡፡ ከመቃብሩም እንደ ተነሣ አመኑ፡፡ ሆኖም ክርስቶስን ገና አይተው ለማመን ይፈልጉ ነበር እንጂ "ከሙታን ይነሣ ነበ ዘንድ እንዲገባው የሚለውን የመጽሐፉን ቃል ገና አላወቁም ርና" (ዮሐ.20፥1-10)፡፡

በዚያች ቀን ማለት በትንሣኤ ዕለት እሑድ ጠዋት ማርያም መግደ ላዊት ከመቃብሩ በስተ ውጭ እያለቀሰች ቆማ ነበር፡፡ ጌታም ተገለጸላት፥ወደ ደቀ መዛሙርቱም ላካት፥ እንዲህም አላት፡- "ወደ ወንድሞቼ ሄደሽ፡- እኔ ወደ አባቴና ወደ አባታችሁ ወደ አምላኬና ወደ አምላካችሁ ዓርጋለሁ ብለሽ ንገ ሪያቸው አላት" (ዮሐ.20፥11-18)፡፡ ጌታም እንደዚህ መናገሩ ማለት በአንድና በብዙ አድርጎ አባቴ አባታችሁ፥አምላኬ አምላካችሁ ማለቱ ለምንድን ነው? ብሎ የሚያስብ ሰው ቢኖር ነገሩንም ለመረዳት ቢፈልግ የጌታንና የእኛን ሁኔታ ለይቶ ማወቅ ይኖርበታል፡፡ "አባቴ" ብሎ የእርሱን ልደት ተናገረ፡፡ "አባቴ" ያለው የርሱ የባሕርይ ነው፡፡ "አባታችሁ" ያለው የእኛ የጸጋ ነው፡፡ "አ ምላኬ" አለ በሥጋ ይፈጥረዋልና፤[59] "አምላካችሁ" አለ በጥንተ ተፈጥሮ በሐዲስ ተፈጥሮ ይፈጥረናልና በማለት አባቶች ሊቃውንት ያስረዳሉ (ዮሐ.20፥17 ትርጓሜ ወንጌል)፡፡

ማርያም መግደላዊትም ጌታን ካየችና መልእክቱንም ከተቀበለች በኋላ ደቀ መዛሙርቱ ወደ ተሰበሰቡበት ሄደች፡፡ የጌታንም ከሙታን መነሣትና ሕያው ሆኖም እንደ አየችው ገለጸችላቸው፡፡ መልእክቱንም ነገረቻቸው፡፡ እርሷም ከደቀ መዛሙርቱ ቀድማ ለጌታ ትንሣኤ ምስክር ሆነች (ዮሐ.20፥18)፡፡

> በዚያው ቀን ምሽት ማለት በመጀመሪያው የትንሣኤ ዕለት "ደቀ መዛሙርቱ ተሰብስበው በነበሩበት፥አይሁድን ስለ ፈሩ ደጆቹ ተዘግተው ሳሉ፥ ኢየሱስ መጣ፤ በመካከላቸው ቆሞ፥ ሰላም ለእናንተ ይሁን አላቸው፡፡ ይህንም ብሎ እጆቹንም ጎኑንም አሳያቸው፡፡ ደቀ መዛሙርቱም ጌታን ባዩ ጊዜ ደስ አላ ቸው፡፡ ኢየሱስም ዳግመኛ፡-ሰላም ለእናንተ ይሁን፤ አብ እንደ ላከኝ እኔ ደግሞ እልካችኋለሁ አላቸው፡፡ ይህንንም ብሎ እፍ አለባቸውና፡- መንፈስ ቅዱስን ተቀበሉ፡፡ ኃጢአታቸውን ይቅር ያላችኋቸው ሁሉ ይቀርላቸዋል፤ የያዛችሁባቸው ተይዞባቸዋል አላቸው" (ዮሐ.20፥19-23)፡፡

በመጀመሪያ ጌታችን እጁንና ጐኑን ማሳየቱ የሰው ልጆችን ኃጢአት ለማስወገድ በመልዕልተ መስቀል የተሰቀለው እርሱ መሆኑንና ከአብ የተላከበትን እር ም ሥራ ማከናወኑን ይገልጻል፡፡ ከዚያ ቀጥሎ ክርስቶስ ከአብ እንደ ተላከ በመን ሱም ሐዋርያትን ኃጢአትን የማስተሥረይ ሥልጣን በመስጠት ላካቸው፤ ፈስ ቅዱስም ቀባቸው፡፡ እንግዲህ ኃጢአት ለማስተሥረይ የሚያበቃ ሥልጣን ለማን ነበር የሚሰጠው? በእግዚአብሔር ትእዛዝ መሠረት ለአሮንና ለቤተሰቦቹ ብቻ እንደ ነበረ በቅዱሳት መጻሕፍት ተጽፏል (ዘፀ.28፥1-3፤ ዕብ.5፥4)፡፡

እንደዚሁም እውነተኛ የኃጢአት ሥርየትን የማስጡትን ሐዋርያትን ባ ታችን መርጦ የክህነት ሹመት በመንፈስ ...



በመጀመሪያው የትንሣኤ ዕለት ነው፡፡ ጌታ ለሐዋርያት የሰጣቸው ሥልጣን ለሐዋርያት ተተኪዎች ለጳጳሳትና ለቀሳውስት በአንብሮተ እድ በመንፈስ ቅዱስ ጸጋ እየተላለፈ መጥቶ እስከ ዘመናችን ደርሷል፡፡ እንደ ጥንታውያን አብያተ ክርስቲያናት፥ ሐዋርያዊትና ጥንታዊት የሆነችው ቤተ ክርስቲያናችን ይህንን ሃይማኖታዊ ሥልጣን እየሠራችበት ትገኛለች፡፡

እንግዲህ ለቤተ ክርስቲያን ኃጢአትን የማስተሥረይ ሥልጣን ሲሰጣት ለኃጢአተኞች ሁሉ እግዚአብሔር ያዘጋጀው ታላቅ የተስፋና የምሕረት ጸጋ መሆኑን እናምናለን፡፡ "ፋሲካችን ክርስቶስ ታርዷልና" (1ቆሮ.5፥7)፡፡ ስለዚህ ቤተ ክርስቲያናችን የኃጢአትን ሥርየት እየሰበከች፣በጸሎተ ቅዳሴዋ በመስቀል ላይ የተሠዋውን የፋሲካችን የክርስቶስን ሥጋና ደም እያቀረበች በንስሐ ሆነው ለሚቀበሉት ሁሉ የኃጢአት ሥርየትን የዘላለም ሕይወትን ታሰጣለች፡፡ ይህ ሁሉ በጌታችን ሞትና ትንሣኤ የተገኘ ነው፡፡ ኃጢአትን የማስተሥረይ ሥልጣን ማለት የክህነት ሥልጣን በትንሣኤ ዕለት እንደ ተሰጠ ተረድተናል፡፡ እንግዲህ የክህነት ሥልጣን የጌታን የማዳን ሥራ የሚፈጽምና የሚያስፈጽም የመንፈስ ቅዱስ የጸጋ ስጦታ ነው፡፡ ስለዚህም ስጦታ እግዚአብሔርን ማመስገን ይገባናል፡፡

## ለሁለተኛና ለሦስተኛ ጊዜ የጌታ መገለጥ

ጌታችን በአርባው ቀናት ውስጥ ለአንዱ ወይም ለጥቂቶቹ ደቀ መዛሙርት፥ በውጭም ሆነ በቤት፡ በግልም ሆነ በቤተሰብ በየጊዜው እንደ ተገለጠላቸው የቤተ ክርስቲያን አባቶች ያስተምሩናል፡፡ ሐዋርያት በአንድነት ሆነው ሳሉ ጌታ የተገለጠላቸው ጊዜያት ግን በቁጥር የታወቁ ናቸው፡፡ ለሁለተኛ ጊዜ ጌታ ለሐዋርያት በአንድነት ተሰብስበው ሳለ የተገለጠላቸው የትንሣኤ ሳምን ት ነበር፡፡ እስከዚያን ቀን ድረስ ትንሣኤውን ያላየው ሐዋርያው ቅዱስ ቶማስም በመካከላቸው ተገኝቶ ነበር፡፡ አሁንም በዝግ ቤት ተገልጦ ሰላም ለእናንተ ይሁን ካላቸው በኋላ ያላመንህ አትሁን ብሎ እጆቹንና ጐኑን እንዲዳስሰው ፈቀደለት፡፡ እርሱም ጌታዬ አምላኬም በማለት አምላክነቱን መስክሯል፤ እም ነቱን አጽንቷል፡፡ ጌታም "ስለ አየኸኝ አምነሃል፤ ሳያዩ የሚያምኑ ብፁዓን ናቸው" በማለት በሐዋርያትና በቤተ ክርስቲያን ምስክርነት በጌታ ትንሣኤ የሚያምኑትን ሁሉ አመስግኗል (ዮሐ.20፡24-29)፡፡

በጥብርያዶስ ባሕር ሐዋርያት ዓሣ በማጥመድ ላይ ሳሉ ጌታ ለሦስተኛ ጊዜ ተገለጠላቸው፡፡ ቅዱስ ጴጥሮስንም ትወደኛለህ በማለት ጌታ ሦስት ጊዜ መላልሶ ጠየቀው፡፡ እርሱም አዎን ጌታዬ ሆይ እንድወድህ አንተ ታውቃለህ ብሎ መልሷል፡፡ ጌታም፡- "ግልገሎቼን አሰማራ . . . ጠቦቶቼን ጠብቅ . . . በጎቼን አሰማራ" በማለት ሦስት ጊዜ ደጋግሞ አዟል (ዮሐ.21፥1-17)፡፡ ግልግሎቼ፥ ጠቦቶቼና በጎቼ የተባሉት ከትንሽ እስከ ትልቅ ያሉትን በክርስቶስ የሚያምኑትን ሁሉ የሚያመለክት ነው፡፡ የምእመናንን መንፈሳዊ ሕይወት ለመጠበቅና ለመምራት የኖሎት ማለት የነፍሳት እረኝነት ሥራና ሥልጣን ለጊዜው ለቅዱስ ጴጥሮስና ለሐዋርያት ቢሆንም ፍጻሜው ለቤተ ክርስቲያን መሪዎችና አስተዳዳሪዎች ማለት ለፓትርያርኮች፥ ለሊቃነ ጳጳሳትና ለኤጲስ ቆጶሳት፥ ለቆሞሳት እና ለቀሳውስት፤ ለካህናት ሁሉ በየደረጃው የተሰጠ መሆኑ በታሪክ የተረጋገጠ ነው፡፡

ስለዚህ ነው ... ቤተ ክርስቲያናችን በየሀገሩ ስብከቱ የሚገኙትን

www.ethiopianorthodox.org

በምክረ ካህን በፈቃደ ካህን እንዲኖሩ ቤተ ክርስቲያን ሁሉንም አደራ ትላለች።

## ጌታ ለሐዋርያትና ለሌሎች ብዙ ሰዎች ስለ መገለጡ

በአርባው ቀን ውስጥ ደግሞ ጌታ በገሊላ ተራራ ላይ ለአሥራ አንዱ ደ
መዛሙርት ተገልጾላቸዋል። ያንጊዜ ነበር ጌታ ለሐዋርያት ወንጌልን የማስተማ
ሥልጣን የሰጣቸው። እንዲህም አላቸው "እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአ
በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው፥ ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እ
ዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው፤ እነሆም እኔ እስከ
ለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ" (ማቴ.28፥16-20)።

በዚህም ትእዛዝ መሠረት ሐዋርያት የመንፈስ ቅዱስን ኃይል ካገኙ በኋ
በብዙ የአሕዛብ ሀገሮች እየተዘዋወሩ ወንጌልን በመስበክ ብዙዎችን አሳምነው አ
ምቀዋል። ስለ ክርስቶስ ሲመሰክሩ ሕይወታቸውን በሰማዕትነት አሳልፈዋል። ጌ
ግን እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ከእናንተ ከሐዋርያት ጋር ነኝ ማለቱ ምንድነው
እነርሱ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ አልቆዩም? ብሎ ለሚጠይቅ ሁሉ መልሱ ዛሬም
ሐዋርያዊ ሥራ የሚሠሩ ሐዋርያት የክርስቶስ ደቀ መዛሙርት ስላሉ ነው። ሐዋ
ያዊት ቤተ ክርስቲያን ዛሬም የሐዋርያትን ሥልጣን ይዛ የሐዋርያትን ሥራ እ
ሠራች ትገኛለች። ስለዚህም ክርስቶስ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ከእርሷ ጋር ነው።

ከአርባው ቀን ውስጥም ሆነ ውጭ፥ ጌታ ለብዙዎቿ በየጊዜው ተገለ
ጧል። በተለይም ከአምስት መቶ ለሚበዙ ሰዎች በአንድ ጊዜ እንደ ተገለጠላቸው
ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ጽፏል (1ኛቆሮ.15፥6)።

ጌታ "አርባ ቀን እየታያቸው ስለ እግዚአብሔርም መንግሥት ነገር እ
ነገራቸው፥ በብዙ ማስረጃ ከሕማማቱ በኋላ ሕያው ሆኖ ለእነርሱ ራሱን አሳ
ያቸው።" (የሐዋ.1፥3) ተብሎ እንደ ተጻፈ ሐዋርያት በዚሁ ጊዜ ውስጥ ከጌ
ብዙ የሃይማኖትን ምሥጢር እንደ ተማሩ፥ ከእርሱም ትእዛዝና ሥልጣን እንደ
ተቀበሉ፥ ይህንንም ከጊዜ በኋላ ለተተኪዎቻቸው በቃልም በመጣፍም እን
ዳስተላለፉላቸው የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ምስክር ነው። እንግዲህ ጌታ ለሐዋርያት
የሰጠው ሥልጣንና ተግባር ሁሉ የቤተ ክርስቲያን ነው ማለት ነው።

ስለዚህ ዛሬ ቤተ ክርስቲያናችን የሐዋርያትን ኃላፊነት በመረከብ ከላይ
የጠቀስናቸው ሦስት ዐበይት ሥራዎች ይኖሩዋታል። በመጀመሪያ ለሕዝቡ የኃ
ጢአት ሥርየትን ማስገኘት (ዮሐ.20፥23)። ይህም በምሥጢራተ ቤተ ክርስ
ቲያን አገልግሎት ይፈጸማል። ሁለተኛው ወንጌልን ማስተማር ሲሆን፥ ሦስተኛው
ምእመናንን የመጠበቅና የመምራት ኃላፊነት ነው። እነዚህን የክርስቶስ ትእዛዛት
ለመፈጸም እንዲችሉ ለሐዋርያት ኃይልን የሰጣቸው መንፈስ ቅዱስ፥ ዛሬም በቤተ
ክርስቲያን ተገኝቶ በልዩ ልዩ ስጦታው ሐዋርያዊ ኃላፊነቷን እንድትወጣው መን
ፈሳዊና ማኅበራዊ ሥራዎቿን እንድታከናውን ይረዳታል።

## መ) ቅዱሳት መጻሕፍትንና ምስክርነታቸውን በትክክል ስለ መረዳት

"... በቅዱሳት መጻሕፍት እንደ

www.ethiopianorthodox.org



እንዲህ አላቸው። "እናንተ የማታስተውሉ፥ ነቢያትም የተናገሩትን ሁሉ ልባ
ችሁ ከማመን የዘገየ፤ ክርስቶስ ይህን መከራ ይቀበል ዘንድና ወደ ክብሩ ይገባ
ዘንድ ይገባው የለምን? አላቸው። ከሙሴና ከነቢያት ሁሉ ጀምሮ ስለ እርሱ
በመጻሕፍት ሁሉ የተጻፈውን ተረጐመላቸው" (ሉቃ.24፥25-27)።

እንግዲህ ከዚህ ቃል የምንማረው ቅዱሳት መጻሕፍት የሃይማኖታችን
መሠረት የሆነውን የክርስቶስን ሕይወት፥ ሞትና ትንሣኤ የሚመሰክሩ ሆኖ ሳ
ለ፣ አንባብያን ግን ይኽን የተጻፈውን አንብበው ለመረዳትና ለማመን የሚያ
ዳግታቸው መሆኑን ነው። ስለዚህ ነው ጌታችን መጻሕፍትን እየተረጐመ ያስ
ረዳቸው። ጌታችንም ለሁለቱ ደቀ መዛሙርቱ ይኽንን ካስረዳቸው በኋላ "እርስ
በርሳቸውም፦ በመንገድ ሲናገረን መጻሕፍትንም ሲከፍትልን ልባችን ይቃጠ
ልብን አልነበረምን? ተባባሉ" (ሉቃ.24፥32)። ጌታችን ለሁለቱ ብቻ አልነበረም
መጻሕፍትን እንዲያስተውሉ የረዳቸው ለአሥራ አንዱ ሐዋርያትና ከእነርሱም
ጋር ለነበሩት ሁሉ ገለጸላቸው፤ እንዲህም አላቸው፦

> "ከእናንተ ጋር ሳለሁ በሙሴ ሕግና በነቢያት በመዝሙራትም ስለ እኔ የተጻፈው ሁሉ ይፈጸም ዘንድ ይገባል ብዬ የነገርኋችሁ ቃሌ ይህ ነው አላቸው። በዚያን ጊዜም መጻሕፍትን ያስተውሉ ዘንድ አእምሯቸውን ከፈተላቸው፤ እንዲህም አላቸው፦ ክርስቶስ መከራ ይቀበላል በሦስተኛውም ቀን ከሙታን ይነሣል፥ በስሙም ንስሐና የኃጢአት ሥርየት ከኢየሩሳሌም ጀምሮ በአሕዛብ ሁሉ ይሰበካል ተብሎ እንዲሁ ተጽፏል" (ሉቃ.24፥33-49)።

እንግዲህ የቅዱሳት መጻሕፍት ባለቤት የሆነው ጌታ ራሱ ካልገለጸልን
በስተቀር እንደ ዓለማውያን መጻሕፍት በየግላችን ካለመንፈስ ቅዱስ ረድኤት
ብቻችንን በማንበብ ትክክለኛውን ትርጓሜ አውቀን ለመጠቀም አንችልም።
ይህማ ቢሆን ኑሮ አይሁድ ሁሉ ኦሪትንና ነቢያትን መዝሙራትንም አንብበው
ጌታን ባመኑት ነበር።

አይሁድማ ቅዱሳት መጻሕፍት ለማን እንደ ሚመሰክሩ አልተረዱም።
ስለዚህም ጌታ እንዲህ አላቸው፦ "እናንተ በመጻሕፍት የዘላለም ሕይወት እን
ዳላችሁ ይመስላችኋልና እነርሱን ትመረምራላችሁ፤ እነርሱም ስለ እኔ የሚመ
ሰክሩ ናቸው፤ ነገር ግን ሕይወት እንዲሆንላችሁ ወደ እኔ ልትመጡ አት
ወዱም" (ዮሐ.5፥39-40)።

ዛሬም እንደ ጥንቶቹ አይሁድ የዘላለም ሕይወትን ያገኙ እየመሰላቸው
ወይም እውቀትን ለማግኘት ብቻ ብለው ቅዱሳት መጻሕፍትን ሲማሩና ሲመ
ረምሩ ቆይተው ወደ ክርስቶስ እምነትና ጸጋ ሳይደርሱ ከመንገድ ይቀራሉ።
ምክንያቱም እነርሱ የቤተ ክርስቲያንን ርዳታና የመንፈስ ቅዱስን ጸጋ ሳይፈልጉ
በራሳቸው ምርምርና አስተያየት ብቻ ስለሚተማመኑ ነው። ቅዱሳት መጻሕፍት
በሰው ፍላጐትና አስተያየት
በመንፈስ ቅዱስ አነሣሽነት የተጻፉ እንጂ
የተጻፉ አይደሉም። ስለዚህ የመጽሐፉ ባለቤት ጌታ ራሱ ካልረዳ በስተቀር
የቅዱሳት መጻሕፍትን ትርጓሜና ምስክርነት ለመረዳት አይቻልም። መጻሕፍቱ
ምንም በሰው እጅ የተጻፉ ቢሆኑ በጌታ ትእዛዝ እንደ ተጻፉ እናምናለን።

በመጀመሪያ አሥርቱ ቃላትን እግዚአብሔር በሁለቱ ጽላት ላይ ጽፎ
... አድርጐታል። በኋላም በእግዚአብሔር መንፈስ አ
... መዝሙራትና ነቢያት በመጨረሻም ወንጌልና
... በልዩ ልዩ ...

ኪዳን መጻሕፍት በጸሎትና በአክብሮት፥በጥንቃቄና በማስተዋል ማንበብ የመ[illegible] መሪያው ግዴታችን ነው፡፡

## *መጽሐፍ ቅዱስን ለመረዳት የሚያግዙን የትምህርት ዓይነቶች*

ቅዱሳት መጻሕፍትን አንብበን ለመረዳት እንድንችል አንዳንድ ነገሮች[illegible] ማወቅ ይኖርብናል፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈበት ቋንቋ፥ጊዜና ሁኔታ፥የጽሕፈ[illegible] ምክንያትና ዓላማ ማለት ለምን ለማን እንደ ተጻፈ፥ እንደዚሁም በዘመኑ የነበረ[illegible] የታሪክ፥ የሃይማኖት፥ የማኅበራዊ ኑሮ፥ የሥነ ጽሑፍ፥ የፍልስፍናና የመሳሰሉት[illegible] ማጥናት ለነገረ መለኮት ምሁራን ብቻ የሚተው ሳይሆን ሁላችንም ጥቂት ግንዛ[illegible] ካገኘን በኋላ መጽሐፍ ቅዱሳችንን ብናነበው ሊገባንና ወደ ትክክለኛውም ትርጓ[illegible] ለመድረስ ያግዘናል፡፡

የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት በልዩ ልዩ ጊዜያት የተጻፉ ልዩ ል[illegible] መጻሕፍትን የያዙ ናቸው፡፡ የሙሴ መጻሕፍት ማለት የመጀመሪያዎቹ የብሉ[illegible] ኪዳን መጻሕፍት ከክርስቶስ ልደት በፊት ከ15-13 ምዕት ዓመት ገደማ ጀም[illegible] ሮ የተጻፉ ሲሆን የሐዲስ ኪዳን የመጨረሻው መጽሐፍ ከክርስቶስ ልደት በኋላ እስከ 100 ዓ.ም. ገደማ የተጻፈ ነበር፡፡ አብዛኛዎቹ መጻሕፍት ደግሞ በዚህ ጊዜያት መካከል ተጽፈዋል ማለት ነው፡፡ በቋንቋ የሄድን እንደሆን ብሉይ ኪዳን በዕብራይስጥ፥ ሐዲስ ኪዳን በጽርእ (በግሪክ) ተጽፈዋል፡፡ በሥነ ጽሑፍ ሥርዓት የመጽሐፍ ቅዱስን ይዞታ የተመለከትን እንደሆነ ታሪክ፥ሕግ፥ቅኔና መዝሙር፥ ምሳሌና ጥበብ፥ ትንቢትና ራእይ፥ የጌታና የቅዱሳን የሕይወት ታሪክ፥ የምሥራች ቃልን፥ ልዩ ልዩ መልእክታትንና የመሳሰሉትን ሁሉ ያካተተ ነው፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ በተጻፈበት ዘመን የነበረው የዓለም ታሪክ፥ የሕዝቦች ባሕልና አምልኮ[illegible] ወግና ልማድ፥ የሥነ ጽሑፋቸው ዓይነትና የመሳሰሉትን ሁሉ ማወቅ ለቅዱሳት መጻሕፍት ትርጓሜ አስተዋጽኦ ያደርጋል፡፡ ከዚህም ሁሉ ጋር ከላይ እንደ ተጠቀ ሰው የመጽሐፉን ባለቤት እግዚአብሔርን በጸሎት በመጠየቅ በእርሱ ረድኤት ወደ እውነተኛ ትርጓሜ ለመድረስና የእርሱንም ፈቃድ በተግባር ለመፈጸም ያበቃናል፡፡

እንግዲህ የቅዱሳት መጻሕፍት ሁኔታ እንደዚህ ሆኖ ሳለ፥ አንዳንድ ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስን ትናንት ታትሞ እንደ ወጣ አዲስ መጽሐፍ በመቁጠር እያነበቡ በእግዚአብሔር ቃል ላይ እስከ መጣላት የደረሰ ክርክርና ጭቅጭቅ ሲያነሱ ማየት እጅግ ያሳዝናል፡፡ ይህም መንፈሳዊነት የጐደለው ዓለማዊ አሠራርን ይመስላል፡፡ እነዚህን በመሰሉ ሰዎች ምክንያት የክርስቲያን ሃይማኖት እንዳይሰደብ ያሰጋል፡፡ ስለዚህ እውነትን የሚፈልጉ ምእመናን ከእንደዚህ ያለው ነገር እንዲርቁ ያስፈልጋል፡፡

ይልቅስ በግብረ ሐዋርያት እንደ ተጻፈው የኢትዮጵያ ጃንደረባ ያልገባውን የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ጠይቆ እንደ ተረዳ እንዲሁም ምእመናን ከቅዱሳት መጻሕ ፍት ውስጥ ያልገባቸው ምንባብ ሲኖር የቤተ ክርስቲያንን ሊቃውንት ጠይቀው መረዳት ይኖርባቸዋል (የሐዋ.8፥26-40)፡፡ በመንፈስ ቅዱስ ተመርቶ የሐዋርያትን ትውፊት ጠብቆ ቅዱስ ፊልጶስ የትንቢቱን መጽሐፍ በትክክል ተርጉሞ ከላይ የተጠቀሰውን ኢትዮጵያዊ እንዳስተማረውና እንዳጠመቀው ዛሬም እንደዚሁ ቤተ ክርስቲያናችን በመንፈስ ቅዱስ እየተመራች ሐዋርያዊውን ትውፊት በመጠበቅ ቅዱሳት መጻሕፍትን በትክክል ተርጉማ ታስተምራለች፥ ታጠምቃለችም፡፡ ይህንን ም ማድረግ የቅድስት ቤተ ክርስቲያን ሥልጣንና ኃላፊነት መሆኑን ምእመናን ሁሉ አውቀው እንዲያሳውቁ፥ ሥርዓቱን ጠ[illegible] መብታቸውና ግዴታቸው ነው፡፡ ምክንያቱም ቤተ ክርስቲያናችን ዛሬ በመ[illegible]



## *ሐዋርያዊ ትውፊት*

እንግዲህ ሐዋርያዊ ትውፊት ምን ማለት እንደሆነ ክርስቲያኖች ሁሉ [illegible]ውቁት ይገባል፡፡ ትውፊት ማለት ምሥጢሩ በክብር የተቀበሉትን የተቀደሰ [illegible]ርስ በክብር ለሌላው ማስተላለፍን ያመለክታል፡፡ ትውፊት ስንል ውርሱን በማ[illegible] [illegible]ተላለፍ ብቻ የተወሰነ ቃል ሳይሆን ውርስንም ጭምር ያጠቃልላል፡፡ ይህም [illegible]ተቀደሰ ውርስ የተባለው ይዘቱ የጌታን ትምህርትና ሥራ፥ ሕማሙንና ሞቱን [illegible] ትንሣኤውና ዕርገቱን እንደዚሁም የሐዋርያትን ምስክርነታቸውን፥ ስብከ[illegible]ቸውን፥የጥምቀትና የቁርባን፥ የጸሎትና የአምልኮት ሥርዓታቸውን፥ እና [illegible]ራቸውና በጐ ምግባራቸውን ሁሉ የሚያጠቃልል ነው፡፡

እንግዲህ በትውፊት የተገኘው ውርስ የጌታንና የመጀመሪያዋን ቤተ ክርስቲያን ሙሉ የሕይወት ታሪክ የያዘ ሲሆን ከዚህ ውስጥ በከፊል ከብዙ ዓመ[illegible]ት በኋላ በጽሑፍ ላይ ውሏል፡፡ እነዚህም የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ነበሩ፡፡ [illegible]ህም ማለት ሐዋርያት ከጌታችን በቃል የተቀበሉትን በመንፈስ ቅዱስ ኃይል በቃላቸው ያስተምሩ ነበረ እንጂ በጽሑፍ ከጌታ የተቀበሉት መጽሐፍ አል ነበረም፡፡ የእነርሱ መጽሐፍ ቅዱስ የብሉይ መጻሕፍት ብቻ ነበሩ፡፡ ከሐዋር[illegible]ትና ከአርድእት አንዳንዶቹ ወንጌልን ለአያሌ ዓመታት በየሀገሩ እየተዘዋወሩ በቃል ካስተማሩ በኋላ በተለያየ ጊዜና ቦታ በልዩ ልዩ ሀገር ለሚኖሩ አማኞች ወንጌልንና መልእክታትን ጽፈዋል፡፡

ከላይ እንደ ጠቀስነው የተጻፈው ነገር ከጠቅላላው ሐዋርያዊው ትውፊት መካከል መንፈስ ቅዱስ ባወቀ የተወሰነ ክፍል ብቻ ነበር፡፡ ለዚህም ወንጌላዊው ቅዱስ ዮሐንስ ምስክርነቱን ሲሰጥ "ኢየሱስም በዚህ መጽሐፍ ያልተጻፈ ሌላ ብዙ ምልክት በደቀ መዛሙርቱ ፊት አደረገ፤" ብሏል (ዮሐ.20፥30)፡፡ ቀጥሎም "ኢየሱስም ያደረገው ብዙ ሌላ ነገር ደግሞ አለ፤ ሁሉ በእያንዳንዱ ቢጻፍ ለተጻፉት መጻሕፍት ዓለም ራሱ ባልበቃቸው ይመስለኛል፡፡" በማለት አስረድቷል (ዮሐ.21፥25)፡፡

ሐዋርያዊ ትውፊት ስንል በቃልና በጽሑፍ የተወረሱት በተግባርም የታዩትን ሁሉ ያጠቃልላል፡፡ ስለዚህ ነው ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ "እን ግዲያስ፥ወንድሞች ሆይ፥ጸንታችሁ ቁሙ፥በቃላችንም ቢሆን ወይም በመልእ ክታችን የተማራችሁትን ወግ ያዙ" በማለት ለተሰሎንቄ ሰዎች በቃል ስላስተማ ራቸው ወግ የጠቀሰው (2ተሰ.2፥15)፡፡ ከዚህ ላይ "ወግ" የሚለው ቃል የጽር ዑን "ፓራዶሲስ" (paradosis) የሚለውን ይተረጉማል፡፡ ሆኖም ትክክለኛ ትርጉሙ "ትውፊት" ማለት ሲሆን እርሱም ሐዋርያዊ ውርስን ያመለክታል፡፡ ሐዋርያዊ መንበር ያላቸው ታላላቅ አብያተ ክርስቲያናትም በዚሁ ፍቺና ትርጉም ይጠቀማሉ፡፡

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ "ወግ" የሚለውን ቃል ትውፊት በሚለው ትርጉሙ በሌላ ቦታ ገልጾታል፡፡ " ወንድሞች ሆይ፥ ከእኛ እንደ ተቀበለው ወግ ሳይሆን ያለ ሥርዓት ከሚሄድ ወንድም ሁሉ ትለዩ ዘንድ በጌታችን በኢየ ሱስ ክርስቶስ ስም እናዛችኋለን፡፡ እኛን ልትመስሉ እንዴት እንደሚገባችሁ ራሳ ችሁ ታውቃላችሁና፤ በእናንተ ዘንድ ያለ ሥርዓት አልሄድንምና፤ ከእናንተ ዘን [illegible]በድበት፥ ሌሊትና ቀን በድካምና በጥረት እየሠራን

www.ethiopianorthodox.org

እርሱ ራሱ በተግባር ሠርቶ ያሳየውን መልካም አርአያና በጐ ሥራንም ሁሉ እንደሆነ ከምንባቡ ለመረዳት እንችላለን (1ቆሮ.11፥1-2፤ ፊልጵ.4፥8-9)።

እንግዲህ ሐዋርያዊ ትውፊት በመጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈውን ብቻ ሳይ ሆን ቃል በቃል ሲወርድ ሲዋረድ የመጣውንም ሐዋርያዊ ውርስ የሚጨም ነው። ስለዚህም ሐዋርያዊው ትውፊትና መጽሐፍ ቅዱስ እንደ ሁለት የተለዩ ነገሮች ሳይሆኑ ከአንድ እውነተኛ ምንጭ ከጌታና ከሐዋርያት ጀምሮ በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት ሲያያዝ እንደመጣ እንደ አንድ የተቀደሰ ውርስ አድርገን እን ቀበለዋለን። በመጽሐፍ ቅዱስ ያልተጻፈው ማለት ቃል በቃል ሲወርድ ሲዋረ የመጣው ሐዋርያዊ ውርስ የት ይገኛል? በምንስ ሁናቴ ልንገነዘበው እንችላለን ለሚለው ጥያቄ ሁላችንም ምላሹን ማወቅ ይኖርብናል። በመሠረቱ ከጥንት ጀም ሮ ሐዋርያዊ መንበር ባላቸው አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ ዛሬም እንደ ጥንቱ ሲሠራበት ይገኛል። በነዚህም አብያተ ክርስቲያናት በቃልና በተግባ የተላለፈውን ሐዋርያዊ ውርስ ቢያንስ በሦስት ሁኔታዎች እናገኘዋለን፤ አ ራሩንም በማየት ለመገንዘብ እንችላለን።

በመጀመሪያ ከሐዋርያት በቃል ሲተላለፍ የነበረው ከሐዋርያት ቀጥሎ በተነሡት ቅዱሳን አበው በጻፉት መጻሕፍት ውስጥ ይገኛል። በሐዋርያት ትውፊት ላይ የተገነባው የአበው ትውፊት የተባለውም የተቀደሰውን ውርስ አ ጉልቶና አሳድጐ ያሳየናል። እነዚህ የቤተ ክርስቲያን አባቶች የጻፏቸው መጻሕፍትም በልዩ ልዩ ቋንቋ ተተርጉመው በዩኒቨርስቲዎችና በታላላቅ የትምህርት ማዕከሎች ሳይቀር ለማግኘት ይቻላል።

ሁለተኛው፥ ቤተ ክርስቲያን ከመከፋፈሏ በፊት ማለት እስከ አምስ ተኛው ክፍለ ዘመን ድረስ የተደረጉት ሲኖዶሶች ባስተላለፏቸው የሃይ ማኖት ውሳኔዎች፥ልዩ ልዩ ደንቦችና ሥርዓቶች ውስጥ የሐዋርያዊ ትውፊት ጥንተ ነገ ሮች ይገኛሉ። ስለዚህም የኒቅያን፥ የቁስጥንጥንያንና የኤፌሶንን ጉባኤ ዎች እን ቀበላለን። የዓለም አብያተ ክርስቲያናትም ተቀብሏቸዋል።

ሦስተኛው፥ በቤተ ክርስቲያን ሀልዎት፥ በሥርዓተ አምልኮዋ፥ በበዓ ላትዋና በአጽዋማትዋ፥ በበጐ አድራጐትዋና በሥነ ምግባርዋ በጠቅላላው በመን ፈሳዊ ሕይወትዋና ታሪኳ በቃልም ሆነ በጽሑፍ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣው የሐዋርያዊው ትውፊት ጥንተ ነገሮች ይገኛሉ፤ በተግባርም ይታያሉ። እያንዳን ዱን በዝርዝር ለመግለጽ ይረዝምብናል። እዚህ ላይ መገንዘብ የሚኖርብን በኋላ ዘመን የመጡት ልዩ ልዩ ወጎችና ሥርዓቶች በልዩ ልዩ ሀገሮች ታሪክና ባሕል ላይ ተመሥርተው ለሚገኙት አብያተ ክርስቲያናት እንደ ራሳቸው ትውፊቶች ስለ ሚቆጥሯቸው ከአንጻሩ ከተቀደሰው ሐዋርያዊ ትውፊት የተለዩ መሆናቸውን ነው።

ከላይ እንደ ተጠቀሰው የአበው ትውፊት ሲባል በሐዋርያዊ ትውፊት ላይ ተመርኩዞ የመጣውን የቤተ ክርስቲያንን እምነትና ሥርዓት፥ ታሪክና ትምህርት ሌሎችንም ሁሉ ያጠቃልላል። ይኸውም ከመሠረቱ ከጌታና ከሐዋ ርያት ጀምሮ ቤተ ክርስቲያን እስከ ተከፋፈለችበት ጊዜ ድረስ ያለው ነው። በዚያን ጊዜ የተጻፈው ሃይማኖተ አበው ለኦርቶዶክስ ትምህርትና እምነት መሠ ረት ሆኗል። በተጠቀሰው ዘመን የነበሩት የቤተ ክርስቲያን ... መጻሕፍትን በትክክል በመተርጐምና በማስተማር የተቀደሰውን ሐዋርያዊ



የመጣውን ወጋቸውንና ሥርዓታቸውን ከመጠን ያለፈ በማጋነናቸውና ...በራቸው የተነሣ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ እንዲዘነጉ አድርጓቸዋል። ስለዚህም ጌታችን እነርሱን ግብዞች እንደሆኑ ገልጾ ወጋቸውም ሕገ እግዚአ ብሔርን የሚቃወም መሆኑን አስረድቷል። ደቀ መዛሙርቱንም ከእንደዚህ ዓይ ነቱ ፈሪሳዊ እርሾ ( ትምህርት) ራሳቸውን እንዲጠብቁ አስጠንቅቋቸዋል (ማቴ.15፥3_9፤ 16፥6-12)። ስለዚህ ሐዋርያዊ ትውፊት ከጌታችንና ከመንፈስ ቅዱስ የተገኘ እንደ መሆኑ መጠን እውነተኛነት ሳይኖራቸው መንፈሳዊ ...ሰለው ወደ እውነተኛው የእግዚአብሔር ሕግና ሥርዓት የሚጠጉትን እርሱንም የሚቃወሙትን ሰው ሰውኛ ወጐችና ሥርዓቶችን ያስወግዳል እንጂ አይ ቀበልም።

እንግዲህ ሐዋርያዊ ትውፊት የወንጌልን ቃል የሚጠብቅና የሚያ ስጠብቅ፥ በትክክል የሚተረጉምና የሚያስተምር፥ በቤተ ክርስቲያንም ውስጥ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ በተግባር እንዲውል የሚያደርግ የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ያለበት አሠራር ነው። የተቀደሰው ትውፊት፥ በኋላ ዘመን የመጡትን ሰው ...ራሽ ወግና መናፍቃዊ ትምህርቶችን ሁሉ እየጣራ የሚለይ የመንፈስ ቅዱስ ...ማሪያ ነው። ስለዚህ ነው ሐዋርያዊ ትውፊት በመንፈስ ቅዱስ ረድኤት ተጠብቆ የሚኖር ነው የሚባለው። ያለ ሐዋርያዊ ትውፊትና ያለ መንፈስ ቅዱስ ኃይል ቤተ ክርስቲያን ባንድ በኩል የልዩ ልዩ መናፍቃን መናኸሪያ ...ሌላ በኩል የብሔሮች ባሕላዊ ሥርዓቶችና ወጐች የሚከበሩባት አደባባይ ሆና ...ቀር ነበር። ይህ ዓይነቱ ሁኔታ ከጥንት ጀምሮ ቢኖርም በተለይ በዛሬ ጊዜ ...በለጠ በብዙ ቦታዎች እየታየ ነው።

ጌታችን በቃል ያስተማረው ወንጌል፥ በሕይወቱና በሥራው የገለጸውና ያቋቋመው ሥርዓት ሁሉ ለዘላለም ተጠብቆ እንዲኖር አካሉ ለሆነችው ቤተ ክርስቲያን በኃላፊነትና በአደራ የሰጠው በሐዋርያዊ ትውፊት አማካኝነት ነው። ...ህም ማለት ጌታችን ለሐዋርያት ያስተላለፈውን ሁሉ እነርሱ ደግሞ በበኩላቸው የተቀበሉትን ሁሉ ሳያስቀሩ በአፍ በመጣፍ ከአደራና ከማስጠንቀቂያ ጋር በመስጠት ወንጌልን እንዲያስተምሩ፥ ኃጢአትን እንዲያስተሠርዩና መን ጋውን እንዲጠብቁ የሐዋርያዊነትንና የክህነትን ሥልጣን በአንብሮተ እድ ተተኪዎቻቸው ለነበሩት ለቤተ ክርስቲያን መሪዎች ለጳጳሳት አስተላልፈዋል ማለት ነው። ለዚህም ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን መሪዎች ያደረገው የመሰነባበቻ ቃለ ምልእክት ይመሰክራል፤

> "በጉባኤም በየቤታችሁም አወራሁላችሁና አስተማርኋችሁ እንጂ፥ ከሚጠቅማችሁ ነገር አንዳች ስንኳ አላስቀረሁባችሁም አሁንም እነሆ እኔ በመንፈስ ታስሬ ወደ ኢየሩሳሌም እሄዳለሁ፥ በዚያም የሚያገኘኝ ምን እንደ ሆነ አላውቅም፤ ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ፡ እስራትና መከራ ይቆይሃል ብሎ በየከተማው ሁሉ ይመሰክርልኛል። ነገር ግን ሩጫዬንና ከጌታ ከኢየሱስ የተቀበልሁትን አ ገልግሎት እርሱም የእግዚአብሔርን ጸጋ ወንጌል መመስከር እፈጽም ዘንድ ነፍ ሴን በእኔ ዘንድ እንደማትከብር እንደ ከንቱ ነገር እቆጥራለሁ። አሁንም፥እነሆ፥ እኔ የእግዚአብሔርን መንግሥት እየሰበክሁ በመካከላችሁ የዞርሁላችሁ ከእንግዲህ ወዲህ ፊቴን እንዳታዩ አውቃለሁ። . . . የእግዚአብሔርን ምክር ሁሉ ነግሬአ ችኋለሁና፥ ምንም አላስቀረሁባችሁም። በገዛ ደሙ የዋጃትን የእግዚአብሔርን ... ትጠብቋት ዘንድ መንፈስ ቅዱስ እናንተን ጳጳሳት አድርጐ ...

www.ethiopianorthodox.org

ሕይወቱም አርአያ በመሆን እኔ ክርስቶስን እንደ መሰልኩት እናንተም እኔን ምሰሉ እያለ አስተምሯቸው አልፎአል፡፡ እንግዲህ ከመልእክቱ ጋር ይህን የመሳሰሉት ናቸው ከዘመነ ሐዋርያት ጀምሮ ሲወርድ ሲዋረድ የመጡት ሐዋርያዊ ውርስ የምንላቸው፡፡ የሐዋርያትም ሥልጣን ለተተኪዎቻቸው ለጳጳሳት በመተላለፍ በአንብሮተ እድ በመንፈስ ቅዱስ እየተሾሙ መንጋውን እንዲጠብቁ ማድረግ ከከፍተኛ ሐዋርያዊ ትውፊት አንዱ ክፍል ነበር፡፡ ይህም ሐዋርያዊ ውርስ ከጥንት ጀምሮ ሳያቋርጥ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ የቤተ ክርስቲያን ሀብት ነው፡፡ ስለዚህ ዛሬ ሐዋርያዊ መንበር ባላቸው በጥንት አብያተ ክርስቲያናት ይህ የተቀደሰው ትውፊት እየተሠራበት ይገኛል፡፡

"መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ" ይበቃናል፣ ሌላ ነገር አያስፈልገንም የሚሉት ወገኖች እንኳ ከቤተ ክርስቲያን ትውፊት ሙሉ በሙሉ የተለዩ አይመስሉም፡፡ ምክንያቱም እነርሱ የተለዩዋትን ቤተ ክርስቲያን በመቃወም አንፃር ይቁሙ እንጂ በመጠኑም ቢሆን የትውፊቱ ተካፋዮች እንደ ሆኑ በአንዳንድ ሁኔታዎች ይታወቃል፡፡ እንዲያውም ከመካከላቸው ቤተ ክርስቲያን ከመከፋፈሏ በፊት የነበረውን ሃይማኖታዊ ውሳኔ ሁሉ የሚደግፉ አሉ፡፡ እነርሱ በአጠቃላይ ሲገልጹ ከመጽሐፍ ቅዱስ ውጭ የተጋነነውንና የተትረፈረፈውን ትምህርትና ሥርዓት፣ ትሕርምት የበዛበትን መንፈሳዊ አኗኗርም በኋላ ዘመን እንደ መጣ እንደፈረሳዊ ወግ ይቆጥራሉ፡፡ እንደዚህ ያሉበትም ምክንያት የወንጌልን ሕግና ሥርዓት የጣሰ ስለመሰላቸው ይሆናል፡፡ ስለዚህ ትውፊት ብለን ስንናገር ሕገ እግዚአብሔርን የሚያስተው መስሎ ይታያቸዋል፡፡ ነገር ግን ትውፊትና መጽሐፍ ቅዱስ ከላይ እንደ ጠቀስነው ከአንድ ምንጭ የፈለቁ ስለሆነ ይተባበራሉ እንጂ አይጣሉም፡፡[60] ሁለቱንም ከጌታና ከሐዋርያት የተቀበልናቸው ስለሆነ ሁለቱንም አክብረን እንይዛቸዋለን እንጂ አንዱን ብቻ ይዘን ሌላውን የምንተውበት ምክንያት የለንም፡፡

ሐዋርያት ለጸሎትና ቃሉን ለማገልገል እንደ ሚተጉ፣ እንጀራንም አብረው እንደ ሚቆርሱና ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያንንም እንደ ሚፈጽሙ ተጽፏል (የሐዋ.2፥41-47፤ 6፥4፤ 1ቆሮ.11፥17-34)፡፡ ይህም ማለት ለመጀመሪያዎቹ ምእመናን በሐዋርያት የሚሰጠው አገልግሎት ቃሉን መስበክ ብቻ ሳይሆን የምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን አገልግሎትም እንደሚሰጥ እንረዳለን፡፡ ከዚህ ጋር ልዩ ልዩ ጸሎት በተወሰነ ሰዓት እንደሚደርስ የታወቀ ነው፡፡ እነዚህና የመሳሰሉት ሁሉ ቀድሞ በሐዋርያት የተፈጸሙ፣ ዛሬም በቤተ ክርስቲያናችን የሚፈጸሙት ከሐዋርያዊ ትውፊት የተገኙ ናቸው፡፡

መጽሐፍ ቅዱስን መስበክ ከዚህ ውስጥ አንዱ የትውፊት ክፍል ነው፡፡ እንግዲህ መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ ይበቃናል፣ እርሱን ብቻ ካስተማርንም ሌላ ነገር አያስፈልግም በማለት እጅ እግርን አጣምሮ መቀመጥ አይገባንም፡፡ ምክንያቱም ከሐዋርያት የወረስነው ስብከተ ወንጌል ብቻ አይደለም፡፡ እንደ ሐዋርያት በየጊዜው ተሰብስቦ ጸሎት ማድረስ፣ መባና መሥዋዕትን ማቅረብ፣ ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያንን መፈጸም፣ ለተቸገሩ መርዳትና የመሳሰሉትን ሁሉ ማድረግ የአብያተ ክርስቲያናት ሁሉ መብትና ግዴታ ነው፡፡ ይህንን የማትፈጽም ቤተ ክርስቲያን ሐዋርያዊት አይደለችም፡፡ የተቀደሰውም

[60] "የትውፊት ርቱዕነት (እውነተኝነት) መመዘኛው ከመጽሐ... ...በሰዎች የተዘጋጁትን ሐሰተኛ ትውፊቶች (ወጎች) ወይም የመጽሐፍ ቅዱስ



ትውፊት ከእርሷ ዘንድ አይገኝም፡፡

ከቅዱሳት መጻሕፍት ጋር የተቀደሰው ሐዋርያዊ ትውፊት ለቤተ ክርስቲያን ትምህርተ ሃይማኖቷን ብቻ ሳይሆን ሥርዓተ አምልኮትዋንና በጐ አ...ሩትዋን፣ አኗኗርዋንና ሥነ ምግባሯን የሚገልጽና የሚወስን የሚመራም ስለሆነ ለሚቀበሉት ሁሉ የተሟላ መንፈሳዊ ሕይወትን ይሰጣል፡፡ ምክንያቱም ...መለኮታዊ መገለጥ እውቀት በምልዐት የተላለፈው በዚሁ መንገድ ስለሆነ ነው፡፡ ከሐዋርያዊ ትውፊት ተከፍሎ የመጣውን ቅዱሳት መጻሕፍትን እንደ ተቀበልን እንዲሁም ከሐዋርያት በቃል ለተላለፈው ትውፊት መታዘዝ ክርስቲያናዊ ግዴታችን ነው፡፡ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለተሰሎንቄ ሰዎች እንደ ጻፈው መልእክቱን ብቻ ሳይሆን በቃልም በተግባርም ያስተላለፈውን ወግ ማለት ትውፊት ሁሉ አጥብቀው እንዲይዙ ከምክርና ከአደራ ጋር አስታውቋቸዋል (2ኛ ተሰ.2፥15፤ 3፥6-15)፡፡

ስለዚህ መጽሐፍ ቅዱስን በምናጠናበት ጊዜ መላውን ሐዋርያዊ ትውፊት አብሮ መማር ይኖርብናል፡፡ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚገኘውን ሐዋርያዊ ትውፊት ብንማረውና ብንመራበት በመንፈስ ቅዱስ ረድኤት መጽሐፍ ቅዱስን አንብበን በትክክል ለመረዳት እንችላለን፡፡

"መጽሐፍ ቅዱስን በእውነት መረዳት የሚቻለውና እርሱም የሚገኝበት ቦታ፣ የተቀደሰው ትውፊትና ሐዋርያዊ ትምህርተ ሃይማኖት በሚጠበቅበት በቤተ ክርስቲያን ብቻ ነው፡፡" በማለት ቅዱስ ሄሬኒዎስ ያረጋግጣል፡፡ ቀጥሎም "ቤተ ክርስቲያን እንደ ገነት በዚህ ዓለም ውስጥ ተተክላለች፤ ስለዚህም መንፈስ ቅዱስ እንዲህ ይላል፣ ከአትክልት ቦታ ከሚገኘው ከማንኛውም ዛፍ በነፃ ብላ (ዘፍ.2፥16)፡፡ ይህም ማለት ከማንኛውም ከጌታ ቅዱሳት መጻሕፍት ብላ፣ ነገር ግን በትዕቢት በተወጠረ ልቡና አትብላ፣ የትኛውንም መናፍቃዊ ቅራኔን አትንካ፡፡ ምክንያቱም እነዚህ ሰዎች እነሱ ራሳቸው የደግና የክፉ እውቀት ባለቤቶች እንደ ሆኑ ይናገራሉና ነው፤ እንደዚሁም የራሳቸው የሆነውን አምልኮ ቢስ ልቡናቸውን ከፈጠራቸው ከእግዚአብሔር በላይ አድርገዋልና፡፡" ሲል ይህ በሁለተኛው ክፍለ ዘመን የነበረ የቤተ ክርስቲያን አባት፣ መናፍቃንን በመቃወም የጻፈውን በመጥቀስ አባ ታድሮስ ማላትይ የግብፅ ኦርቶዶክስ መምህር በእንግሊዝኛ በጻፉት መጽሐፋቸው ገልጠውታል[61]፡፡

www.ethiopianorthodox.org

## አንቀጽ ፲

## በክብር ወደ ሰማይ ዐረገ፥ በአባቱም ቀኝ ተቀመጠ ዳግመኛ ሕያዋንን ሙታንንም ይገዛ ዘንድ በጌትነት ይመጣል:: ለመንግሥቱም ፍጻሜ የለውም::

ከልደት እስከ መቃብር ጌታችን ፈተናና ኀዘን፥ መከራና ሕማም አል
ተለየውም ነበር:: ከትንሣኤው በኋላ ግን ሕማምና ሞት ፈጽሞ አ.የገኙትም።
እርሱ ለዘላለም ሕያው ሆኖ በደስታና በክብር ይኖራል:: "በክብር ወደ ሰማይ
ዐረገ" ስንል ጌታችን በሚያስደንቅ ተአምራዊ ሁኔታ ከመሬት ከፍ ከፍ በማለት
ወደ ሰማይ ወጣ፥ ከብሩህ ደመና ውስጥ ገባ፥ ከዓይንም ተሰወረ ማለታችን
ነው:: እንደ ሄኖክ በመሰወር እንደ ኤልያስም በእሳት ሠረገላ ሳይሆን በራሱ
መለኮታዊ ሥልጣን በተዋሐደው ሥጋ ዐርጓል ብለን እናምናለን:: እንደዚህም
በማድረጉ ከአብ የተላከበትን ዓላማ ታላቁን የማዳን ሥራ በመስቀል ላይ ፈጽሞ
ወደ አብ መመለሱን እንገነዘባለን:: ጌታ በቀደመው ክብሩ በሰማያዊ መንበሩ
ተቀምጧል:: ከአብ ዘንድ ክብርንና ምስጋናን አግኝቷል የተባለበትም ምክንያት
ጌታ ለዘላለም የተዋሐደው ሥጋ መለኮታዊ ክብርን ማግኘቱን ለመግለጽ ነው
(ዮሐ.17፥3-5፤ 2ጴጥ.1፥17)::

"ዳግመኛ ሕያዋንን ሙታንንም ይገዛ ዘንድ በጌትነት ይመጣል::
ለመንግሥቱም ፍጻሜ የለውም::" ተብሎ የተገለጸው ቃለ ሃይማኖት የጌታችንን
የኢየሱስ ክርስቶስን ሁለተኛ ወደዚህ ዓለም መምጣት ያስረዳናል:: ዳግመኛ
ይመጣል የተባለውም ከዚህ ቀደም መጥቶ እንደ ነበር ያመለክተናል:: ያንጊዜ
ደዌያችንንና ሕማማችንን በመሸከም እኛን ለማዳን የባሪያውን መልክ ይዞ ራ
ሱን ዝቅ አድርጐ መጥቶ ነበር:: የአሁኑ አመጣጥ ደግሞ ሰዎችን ሁሉ ለመግ
ዛትና በዓለምም ላይ ፍርድ ለመስጠት በታላቅ ክብርና ጌትነት ይሆናል::
ይህቺ ቀን ለፍጥረት ሁሉ የምታስጨንቅና እጅግም የምታስፈራ ጊዜ ነች::
በነቢያትም በሐዋርያትም የተተነበየላት ታላቅ የፍርድ ቀን መሆኗ የታወቀ
ነው::

ስለዚህም የሰው ልጆች መጨረሻ የሕይወት ሁሉ መዳረሻ ይህ
ስለሆነ በምድር የሚገኝ ማንኛውም ሰው የኑሮውን ዓላማ በምርና በቁም ነገር
ማሰብ ይኖርበታል:: ምክንያቱም የሃይማኖት ወገኖች ብቻ ሳይሆኑ
በሃይማኖትም የማይኖሩት አሕዛብም ሁሉ ከዚያች የፍርድ ቀን የማያመልጡ
ስለሆነ ነው:: ስለዚህ ነው ሕያዋንንና ሙታንን ይገዛ ዘንድ በጌትነት ይመጣል
የተባለው:: "ሕያዋን" የተባሉት ሕያው እምነትና በጎ ምግባር ያላቸው ሲሆኑ
"ሙታን" የተባሉት ደግሞ እምነት የሌላቸው ብቻ ሳይሆኑ እምነት ኖሯቸው
በጐ ምግባር የሌላቸው በተለይም እውነትንና የጽድቅ ሥራን የሚጠሉና በአመፅ
ሥራ ላይ የተሰለፉት ሁሉ ናቸው:: ሌላው ትርጉም ደግሞ "ሕያዋን"
የማባሉት በዕለተ ምጽአት በምድር ላይ ...



## ከሚመጣው በስተቀር የሚመጣበትን ቀን የሚያውቅ የለም

"ስለዚያች ቀን ወይም ስለዚያች ሰዓት ግን የሰማይ መላእክትም ቢሆ
ኑ ልጅም ቢሆን ከአባት በቀር የሚያውቅ የለም:: ጊዜው መቼ እንዲሆን አ
ታውቁምና ተጠንቀቁ፤ ጸልዩም:: . . . . ለእናንተም የምነግራችሁን ለሁሉ
እላለሁ ትጉ" በማለት ክርስቶስ ለዚያች ቀን በጸሎት ተግተን፥ በንስሐ
ተዘጋጅተን እንድንጠብቀው ሐዋርያትን ብቻ ሳይሆን ሁላችንም እንድንጠነቀቅ
ያስተምረናል (ማር.13፥32-37):: ያችን ቀን ማወቅ የእግዚአብሔር ድርሻ ነው፤
የእኛ ፈንታ ግን ተዘጋጅቶ መኖር መሆኑን እንረዳለን::

እርሱ ለሁለተኛ ጊዜ ከአብ ዘንድ የሚመጣው ክርስቶስ ያችን ቀን
እርሱ ለሁለተኛ ጊዜ ከአብ ዘንድ የሚመጣው ክርስቶስ ያችን ቀን ... ቢሆኑ አ
ያውቃታል:: ሌሎች ግን መላእክትም ቢሆኑ የሰው ልጆችም ቢሆኑ አ
ያውቋትም:: እርሱ ተመልሶ የሚመጣው ክርስቶስ የሚመጣበትን ጊዜ
ምልክቶቹን ሁሉ አስታውቋቸዋል፤ በቅድሚያም ሁሉን ነግሯቸዋል
(ማር.13፥23):: ክርስቶስ ሁሉን ነገር የሚያውቅ ሲሆን ሁሉንም ምሥጢር አል
ነገራቸውም:: ምክንያቱም አንዳንድ መገለጽ የማይገባቸው ነገሮች ሰውን ስለ
ሚጐዱ አይነገሩም:: አንዳንድ ነገሮች ደግሞ ቢነገሩ አድማጮች ሊቀበሉት
የማይችሉት ወይም ለአእምሯቸው የማይስማማ ሆኖ ሊከብዳቸው ይችላል::
ስለዚህ ነው ጌታ ሐዋርያትን "የምነግራችሁ ገና ብዙ አለኝ፥ ነገር ግን አሁን
ልትሸከሙት አትችሉም::" ብሎ ያላቸው (ዮሐ.16፥12)::

እንግዲህ ያችን ሰዓት ልጅም ቢሆን ከአብ በቀር የሚያውቅ የለም
ብሎ ጌታችን የተናገረው ዓለምንና ጊዜያትን ሁሉ የፈጠረና በኋላም ሊያሳ
ልፋቸው የሚችል ፈጣሪ ብቻ ሁሉን የማወቅ ሥልጣን እንዳለው ሊገልጽልን አ
ስቦ ነው:: ጌታም ከአብ ጋር አንድ ስለሆነና የአብ የሆነው ሁሉ እውቀትም
ሥልጣንም የእርሱ ስለሆነ ስለዚያች ቀን እርሱም ያውቃል:: ምክንያቱም
ወልድ በመለኮቱ ከአብ ጋር እኩል ነውና:: እንግዲህ ክርስቶስ ሁሉን እያወቀ
ራሱን ከአብ ለይቶ ያችን ቀን እንደማያውቅ የተናገረበት ምክንያት እርሱ ከአብ
ተለይቶ ማለት ወልድ በተለየ አካሉ ቅድመ ተዋሕዶ የነበረ አላዋቂ ሥጋን እን
ደ ተዋሐደ ለማስረዳት ነው:: ይህም ማለት ክርስቶስ ፍጹም ሰው በመሆኑ ለ
ሰው ልጆች ሁሉ ወገናዊነቱን ያመለክተናል:: ከእኛ ጋር ያለውን ዝምድና
ይገልጻል:: እርሱ ሰው ሆኗልና፥ የሰው ልጅም ተብሏልና:: ክርስቶስ ፍጹም
ሰውና ፍጹም አምላክ በመሆኑ በመለኮቱ ከአብ ጋር አንድ ሲሆን በሰውነቱ
ደግሞ ከሰዎች ጋር አንድ ሆኗል:: ስለዚህም ዳግማዊ አዳም ተብሏል:: ምክን
ያቱም ... ጋና ነፍስ የተዋሐደ ፍጹም አምላክ ነውና::

www.ethiopianorthodox.org

የሚመጣበትን ቀን ወስነው በሐሰት በመናገራቸው ብዙ ወገኖች በችግር ውስጥ እንደ ወደቁ እንሰማለን፡፡ በሐዋርያት ዘመን የነበሩ የተሰሎንቄ ሰዎችም ዳግም ምጽአት በዘመናቸው እንደሚፈጸም በማሰብ ተሸብረው ነበር፡፡ ሐዋርያው ጳውሎስ ግን አእምሯቸው እንዳይታወክ የሚከተሉትን የምክር ቃላት ጽፎላቸዋል፡፡

> "ወንድሞች ሆይ፣ ስለ ጌታችን ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ መምጣትና ወደ እርሱ ስለ መሰብሰባችን፣ በመንፈስ ወይም በቃል ወይም ከእኛ እንደሚመጣ በመልእክት፡ የጌታ ቀን ደርሷል ብላችሁ፡ ከአእምሯችሁ ቶሎ እንዳትናወጡ እንዳትደነግጡም እንለምናችኋለን፡፡ ማንም በማናቸውም መንገድ አያስታችሁ፤ ክህደቱ አስቀድሞ ሳይመጣና የአመፅ ሰው እርሱም የጥፋት ልጅ ሳይገለጥ፣ እ ይደርስምና፡፡ እኔ እግዚአብሔር ነኝ ብሎ አዋጅ እየነገረ በእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ እስኪቀመጥ ድረስ፣ አምላክ ከተባለው ሁሉ፣ ሰዎችም ከሚያመልኩት ሁሉ በላይ ራሱን ከፍ ከፍ የሚያደርገው ተቃዋሚ እርሱ ነው፡፡ . . . የዓመፅ ምሥጢር አሁን ይሠራልና፤ ብቻ ከመንገድ እስኪወገድ ድረስ አሁን የሚከለክል አለ፡፡ በዚያን ጊዜ ጌታ ኢየሱስ በአፉ መንፈስ የሚያጠፋው የሚሸረው ዓመፀኛ ይገለጣል፤ ይድኑ ዘንድ የእውነትን ሲመጣም በመገለጡ የሚሽረው ዓመፀኛ ይገለጣል፤ ይድኑ ዘንድ የእውነትን ፍቅር ስላልተቀበሉ ለሚጠፉ፡የእርሱ የዓመፀኛው መምጣት በተአምራት ሁሉና በምልክቶች በሐሰተኞች ድንቆችም በዓመጽም መታለል ሁሉ እንደ ሰይጣን አ ሠራር ነው" (2ተሰሎ.2፡1-12)፡፡

እንግዲህ በዚህ ቃል መሠረት ሐዋርያው እንዳስተማረንና እንደ መከረን ስለ ጌታ ቀን መድረስ ሳንደናገጥ ራሳችንን በእውነትና በመልካም ሥራ አዘጋጅተን እንድንኖር ያስፈልገናል፡፡ ምክንያቱም ከላይ እንደ ተጠቀሰው እንደ ሰይጣን ሥራ የረቀቀው የዓመፅ ምሥጢር አሁን በሥራ ላይ ስለሆነ በሐ ሰት ምልክቶችና ድንቆች ሊያስቱን እየተዘጋጀና ብዙዎችንም ከእውነተኛው መንገድ እያወጣቸው በመሆኑ ነው፡፡ ስለዚህ በሚያባብለው በሰይጣን ሽንገላ ሳን ታለልና ከዓመፀኞችም የስውር ሥራ ሳንተባበር እንደ ጌታ ቀን የሚያስፈራውን ና በድንገትም የሚመጣውን ዕለተ ሞታችንን እያሰብን በእውነተኛው ሃይ ማኖትና በጐ ምግባር ጸንተን ለመገኘት ዘወትር ተግተን መጸለይ ይኖርብናል፡፡

## ስለ ጌታ ዘላለማዊ መንግሥት

"ለመንግሥቱ ፍጻሜ የለውም" ተብሎ በአንቀጸ ሃይማኖት የተገለጸው ቃል የክርስቶስን ዘላለማዊ መንግሥት የሚያመለክት ነው፡፡ ሥጋ ለብሶ በዕ ለተ ዓርብ መሥዋዕት ሆኖ በደሙ ያዳናቸውን የሰውን ልጆች ሁሉ ከሰይጣን ግዛት አውጥቶ ለእግዚአብሔር መንግሥት እንዲገዙ አድርጓቸዋል፡፡ ከአባቱም ጋር የሰውን ልጆች በማስታረቅ ለአባቱ ተገዢዎች እንዲሆኑ ሰጥቷቸዋል፡፡ በዕ ለተ ዓርብ ከሰአል ያወጣቸውን ነፍሳት ሁሉ



ርቡም ተልእኮ ፍጻሜ ማግኘቱን ያስረዳናል፡፡

ወልድ ሰው የሆነበትን ዓላማ ፈጽሞ የመጨረሻውን ጠላት ሞትን ደምስሶ ከአበቃ በኋላ በመጨረሻ እግዚአብሔር ሁሉ በሁሉ ይሆን ዘንድ የራሱ የሆነውን ሁሉ ለአባቱ ያስገዛል፡፡ እርሱም ከአባቱ ጋር በአንድነት ይገዛል፡፡ "ለመን ግሥቱም ፍጻሜ የለውም" ተብሎ እንደ ተጻፈ ወልድ ከዘላለም እስከ ዘላለም ይገዛል፡፡ ፍርድንና ግዛትን አብ ለልጁ ሰጥቷልና (ኢሳ.9፥6-7፤ 1፥33፤ ዮሐ.5፥27)፡፡

ስለዚህ ነው የመጨረሻውን ነገር በተመለከተ ስለ ክርስቶስ እንዲህ ተብሎ የተጻፈው፡፡

> "በኋላም፥ መንግሥቱን ለእግዚአብሔር ለአባቱ አሳልፎ በሰጠ ጊዜ አለቅነትንም ሁሉና ሥልጣንን ሁሉ ኃይልንም በሻረ ጊዜ፣ ፍጻሜ ይሆናል፡፡ ጠላቶቹን ሁሉ ከእግሩ በታች እስኪያደርግ ድረስ ሊነግሥ ይገባዋልና፡፡ የኋለኛው ጠላት የሚሻረው ሞት ነው፤ ሁሉን ከእግሩ በታች አስገዝቷልና፡፡ ነገር ግን፦ ሁሉ ተገዝቷል ሲል፥ ሁሉን ካስገዛለት በቀር መሆ ኑ ግልጥ ነው፡፡ ሁሉ ከተገዛለት በኋላ ግን እግዚአብሔር ሁሉ በሁሉ ይሆን ዘንድ በዚያን ጊዜ ልጁ ራሱ ደግሞ ሁሉን ላስገዛለት ይገዛል" (1ኛቆሮ.15፡24-28)፡፡

ክርስቶስ "ሁሉ ከተገዛለት በኋላ . . . ሁሉን ላስገዛለት ይገዛል" የተባለው መገዛቱ ለማን እንደሆነ? መቼ እንደ ሆነ? እንዴት እንደ ሆነ? የሐዲሳት መጻሕፍት መምህራን እንደ ሚከተለው ያስረዱናል፡፡ "ወአመ ኮሉ ገነየ ሎቱ - ኹሉ በተገዛለት ጊዜ - ይእተ ዕለተ ወልድኒ ይገኒ ለዘአግነየ ሎቱ ኮሎ - ያን ጊዜ ወልድም ኹሉን ላስገዛለት ለሞት ተገዝቷል የዕለተ ዓርቡን መናገር ነው፡፡ (ከመ ይኩን እግዚአ) የኹሉ ገገ ጌታ ይኾን ዘንድ፡ ወልድ ነው፡፡

"እንድም ወአመ ይቤ ኮሉ ይግርር ሎቱ -- ለወልድ ኹሉ ይገዛለት ባለ ጊዜ (ይገርር) ኹሉ ይገዛለታል፡፡ ወባሕቱ ይትዐወቅ ከመ ይንዕስ እምዘአ ግረረ ሎቱ ኮሎ (ማቴ.11፡27)፡፡ ነገር ግን ኹሉን ካስገዛለት ከአብ ወልድ እን ዲያንስ ይታወቃል፡፡ ሐማሚ መዋቲ በመኾን ነው፡፡ ወአመ ኮሉ ገነየ ሎቱ -- ለወልድ ኹሉ በተገዛለት ጊዜ - ይእተ ዕለተ ወልድኒ ይገኒ ለዘአግነየ ሎቱ ኮሎ -ያን ጊዜ ወልድም ኹሉን ላስገዛለት ለአብ ይገዛል አለ፤ በዕለተ ምጽአት ዐሠረ ቀኖትን፥ ዐሠረ ርግዘትን ሳያጠፋ በዕለተ ዓርብ ያደረገውን ተልእኮ ስለገለጠ፡፡ ከመ ይኩን እግዚአ በኵሉ ወላዕለ ኵሉ -- ለኹሉ ገገ ይሆን ዘን ድ" (1ኛቆሮ.15፡28 ትርጓሜውን ተመልከት)፡፡

እንግዲህ ከአባቶች ትርጓሜ እንደ ምንማረው ወልድ ከአብ አነሰ መባሉ ለሞትም መገዛቱ በሰውነቱ "ሐማሚ መዋቲ በመኾኑ ነው"፤ ይህም ማለት ሥጋን የለበሰ፣ መከራን የተቀበለ፥ የሞተ፣ የተቀበረ ወልድ እንጂ አብ ባለመሆኑ ነው፡፡ ነገር ግን ወልድ በመለኮቱ በባሕርዩ ከአብ ጋር አንድ ነው፤ አይበላለጡም (ዕሩየ መለኮት ስለ መሆኑ ጸሎተ ሃይማኖት አንቀጽ ፫ ተመልከት)፡፡ "እነሆ፥ ከደመና ጋር ይመጣል፤ ዓይንም ሁሉ የወጉትም ያዩ ታል፥ የምድርም ወገኖች ሁሉ ስለ እርሱ ዋይ ዋይ ይላሉ" የሚለው ቃል ጌታ ዓርቡን ሥራ፥ በሰውነቱ የፈጸመውን ሥራ፥ አድርጎ "በምስሉም

www.ethiopianorthodox.org

በሞት አገዛዝ ሥር ያሉትን ሁሉ በትንሣኤ ዘጉባኤ ነፃ አውጥቶ "ንዑ ኀበ ቡሩካኑ ለአቡየ" በማለት ሁሉም በደመ ፈሳሽነት መዳናቸውንና ወደ እግዚአብሔር መንግሥት መግባታቸውን ለማብሠር ነው፡፡ በዕለተ ዓርብ ለሞት በመታዘዝና በመገዛት የፈጸመውን የማዳን ሥራ የማይቀበሉትን ግን "ሑሩ እም ኔየ" ብሎ ያሰናብታቸዋል፡፡ "የሰው ልጅም ስለሆነ ይፈርድ ዘንድ /አብ/ ሥልጣንን ሰጠው፤ የእግዚአብሔር ልጅ የሰው ልጅ ነውና" (ዮሐ.5፥27-29)፡፡ ሥጋ የለበሰው ክርስቶስ በሥጋ ለባሽ ላይ ሁሉ ይፈርድ ዘንድ ሥልጣን አለው፡፡ ክፉውም ደጉም ፍጥረት ሁሉ በእግዚአብሔር ፍርድና ግዛት ሥር እንዲውሉ ያደርጋል፡፡

"እግዚአብሔር ሁሉ በሁሉ ይሆን ዘንድ" ሁሉም ነገር በክርስቶስ አማካኝነት ለአብ ይገዛል (ኤፌ.1፥10)፡፡ የማዳን ሥራ ብቻ ሳይሆን ፈጥሮ መግዛትም አድኖ መግዛትም በክርስቶስ በኩል የሚፈጸም ነው፡፡ ያለ ክርስቶስ ምንም ምን የተደረገ የለም፡፡ "ሁሉም በእርሱ ሆነ፡ ከሆነውም አንዳች ስንኳ ያለ እርሱ አልሆነም" ተብሎ ተጽፏልና (ዮሐ.1፥3)፡፡ ስለዚህ በዓለም ፍጻሜ በክርስቶስ በኩል በሐዲስ ተፈጥሮ አሮጌው ፍጥረት "ፊተኛው ሰማይና ፊተኛይቱ ምድር" ከአለፉ በኋላ የእግዚአብሔር መንግሥት በአዲሱ ሰማይና ምድር ተገልጾ ሥልጣንና ግዛቱ ከዘላለም እስከ ዘላለም ለሁሉም በይፋ የታወቀ ይሆናል፡፡ በዚያን ጊዜ የማይታዘዝና የማይገዛ ፍጡር የለም፡፡ የሰይጣንም መንግሥት ጠፍቷል፡፡ የዚህ ዓለምም መንግሥት ፈርሷል፡፡ የመጨረሻው ጠላታችን ሞት በትንሣኤ ዘጉባኤ ተደምስሷል፡፡ "ሞትና ሲኦልም በእሳት ባሕር ውስጥ ተጣሉ" (ራእይ20፥14)፡፡ እንግዲህ እግዚአብሔር ሁሉ በሁሉ ይሆናል፡፡ ያን ጊዜ በሰማይም በምድርም ያለው ሁሉ ኃይልም፡ ሥልጣንም፡ መንግሥትም ለዘላለሙ የአብ ነው፡፡ የአብ የሆነው ሁሉ የወልድም ነው (ዮሐ.16፥15)፤ በመለኮት በአገዛዝ በሥልጣን አንድ ናቸውና፡፡ ስለዚህ ነው የክርስቶስ መንግሥት መጨረሻ የለውም ተብሎ የተጻፈው (ሉቃ.1፥33)፡፡

ስለ ጌታችን መምጣት፡ ከቅዱሳት መጻሕፍት እንደ ተማርነው ጊዜውንና ሰዓቱን የሚያውቅ ከፍጡር ወገን ከቶ አይገኝም፡፡ ሆኖም መምጣቱ የማይቀር ነው፡፡ እስከዚያው ድረስ የደኅንነት ሥራ እንዲስፋፋ፡ ወንጌልም በዓለም ሁሉ እንዲሰበክ ያስፈልጋል፡፡ እግዚአብሔር የሰውን ልጅ መመለሱን እንጂ ጥፋቱን አይወድም፡፡ ስለዚህ ሰዎች ሁሉ ንስሐ እንዲገቡ፡ አምነው እንዲድኑ ጌታ በታላቅ ቸርነቱና ትዕግሥቱ ይጠባበቃቸዋል፡፡ ጌታ ይመጣል፤ ትክክለኛውንም ፍርድ ይሰጣል፡ ለመንግሥቱም ፍጻሜ የለውም እያልን እምነታችንንና ተስፋችንን ለጌታችን እንገልጻለን፡፡ ጌታም እንዲህ ይለናል፡- "እነሆ፥ በቶሎ እመጣለሁ፥ለእያንዳንዱም እንደ ሥራው መጠን እከፍል ዘንድ ዋጋዬ ከኔ ጋር አለ፡፡ አልፋና ዖሜጋ፡ ፊተኛውና ኋለኛው፥ መጀመሪያውና መጨረሻው እኔ ነኝ፡፡" ቤተ ክርስቲያንም ጌታ ሆይ ና ትላለች፡፡ "መንፈሱና ሙሽራይቱም፡-ና ይላሉ፡፡ የሚሰማም፡-ና ይበል

www.ethiopianorthodox.org



## ምዕራፍ ሦስት

## በእግዚአብሔር መንፈስና በቤተ ክርስቲያኑ እናምናለን

### (የመዳናችንና የመቀደሳችን ምሥጢር)

ይህ ምዕራፍ ከአንቀጽ ፳ እስከ ፳፪ ያሉትን ያጠቃልላል፡፡ በአለፈው ትምህርታችን በምዕራፍ ሁለት እንደ ተመለከትነው "እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን ፍቅር" በምሥጢረ ሥጋዌ የገለጠው በልጁ የማዳን ሥራ ነው፡፡ ለእርሱ ክብር ምስጋና ይግባውና ይህንን የማዳን ሥራውን ጌታችን በመዋዕለ ሥጋዌው በነበረበት ጊዜ ለአንዴና ለዘለዓለም ፈጽሞታል፡፡ እንግዲህ ከፅንስ እስከ ዕርገት በተለይም በመስቀሉና በትንሣኤው የፈጸመው ታላቁ የእግዚአብሔር የማዳን ሥራ ፍሬ ማለት ጸጋው ለሁሉም ፍጥረት እንዲዳረስና ሁሉም ሰው የድኅነት ጸጋና በረከት ተካፋይ እንዲሆን ለማድረግ የሚያስችል መንገድ ምንድን ነው? ሐዋርያውስ የት ነው? ለሚለው ጥያቄ መልስ በመፈለግ ወደ ምዕራፉ ዐቢይ ርእሰ ትምህርት እንደርሳለን፡፡ ስለዚህ በአንቀጽ ፳ ስለ መንፈስ ቅዱስ የተነገረውን ትምህርት የሃይማኖት ቃል መሠረት በማድረግ በአጭሩ ከተመለከትን በኋላ ቀጥሎ ከላይ ለተገለጠው ጥያቄ መልስ ለመስጠት እንሞክራለን፡፡ በመጨረሻ በአንቀጽ ፳፪ እና [illegible] ስለ ቤተ ክርስቲያንና ስለ ሥርየተ ኃጢአት ከሙሉ በከፊሉ ከብዙ በጥቂቱ እንገልጻለን፡፡

### አንቀጽ ፳

### "ጌታ ማኅየዊ በሚሆን ከአብ በሠረፀ በመንፈስ ቅዱስም እናምናለን፡፡ እንሰግድለትና እናመሰግነውም ዘንድ ከአብና ከወልድ ጋር፤ በነቢያት የተናገረ፡፡"

ይህ አንቀጽ መንፈስ ቅዱስን የሚመለከት ነው፡፡ ስለ መንፈስ ቅዱስ ማንነት በምሥጢረ ሥላሴ የተገለጠ ቢሆንም ከዚህ ደግሞ የአንቀጹን ኃይለ ቃል በመከተል፡-

(ሀ) የመንፈስ ቅዱስ ከአብ መሥረፅና አካላዊነት፡
(ለ) የመንፈስ ቅዱስ አምላክነትና ሕይወት ሰጭነት በሚሉ አርእስተ ትምህርት በተለየ መንገድ ቀርበዋል፡፡ እነዚህ አርእስት በአብዛኛው ስለ መንፈስ ቅዱስ ማንነት በአንቀጽ ፮ ከተገለጹት በተጨማሪ ያመለክቱናል፡፡ ከዚያ ቀጥሎ ግን የመንፈስ ቅዱስን ሥራና ስጦታ በማስመልከት፡-
(ሐ) በመንፈስ ቅዱስ የመዳናችንና የመንጻታችን ወይም የመቀደሳችን ምሥጢር ማለት የጸጋው አሰጣጥና የሥራው አፈጻጸም እንዴትና የት እንደሆነ በአጭሩ እናሳያለን፡፡

#### ሀ) የመንፈስ ቅዱስ ሠራፂነትና አካላዊነት

ስለ መንፈስ ቅዱስ ሠራፂነት

www.ethiopianorthodox.org

የተገኘ ነው ማለታችን ነው፡፡ ወልድ ከአብ እንደ ተገኘ መንፈስ ቅዱስም ከአብ ተገኝቷል፡፡ ወልድ ተወለደ መንፈስ ቅዱስ ሠረፀ (ወጣ) ስንል ሁለቱም ከአብ እንደተገኙ ለመግለጽ ነው፡፡ ለሁሉም መገኛና ምንጭ፥ ሥርና መሠረት አብ ነው፡፡ ለሥላሴ መሠረቱ አንድ ነው እርሱም አብ ነው እንደ ተባለ (አንቀጽ ለ (ለ)ተመልከት)፡፡ ከፀሐይ አካል፥ ብርሃንና ሙቀት እንደሚገኙ ወልድና መን ፈስ ቅዱስም ከአብ አካል መገኘታቸው በዚሁ ምሳሌ ልንረዳው እንችላለን፡፡ ተፈጥሯዊ ምሳሌዎችና ማስረጃዎች ብቃት ስለሌላቸው መለኮታዊውን ምሥጢር በትክክል አይገልጹልንም፡፡

ስለዚህ በቅዱሳት መጻሕፍት በተጻፈው መሠረት መንፈስ ቅዱስ ከአብ መሥረፁን (መውጣቱን) እናምናለን፡፡ ከዚህ አልፈን ተርፈን የወልድና የመንፈስ ቅዱስ ከአብ መገኘት እንዴት ይሆን? ብለን መለኮታዊ ምሥጢርን መመራመር አይጠቅመንም፡፡ የአምላክነትን ምሥጢር ከመመራመር ይልቅ የአ ምላክን ትእዛዛት መፈጸም እጅግ አድርጐ ይጠቅመናል፡፡ "ልደተ ወልድ ወፀአ ተ መንፈስ ቅዱስ እምአብ ይትነከር ወኢይትነገር" እንደተባለው የመንፈስ ቅዱስ ከአብ መገኘት እንደምን ነው ቢሉ፥ አይመረመርም እፁብ ድንቅ ነው እንጂ በማለት አባቶቻችን ሊቃውንት ለሃይማኖት ትምህርታችን ወሰን አ ድርገውለታል፡፡

ከላይ እንደገለጽነው የመንፈስ ቅዱስ መውጣት ወይም መገኘት ከአ ብ ብቻ ነው፡፡ ለዚህም ምስክሩ፦ "እኔ ከአብ ዘንድ የምልክላችሁ አጽናኝ እር ሱም ከአብ የሚወጣ የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ እርሱ ስለእኔ ይመሰክራል፤" ተብሎ የተጻፈው ነው (ዮሐ.15፥26)፡፡ "ከአብ የሚወጣ የእውነት መንፈስ" ማለት ከአብ የሠረፀ መንፈስ ቅዱስ ማለት ነው፡፡ በዚሁ ቃል ላይ በመመሥረት በቁስጥንጥንያ በ381 ዓ.ም. የተሰበሰቡት ቅዱሳን አባቶች መንፈስ ቅዱስ ከአብ መሥረፁን በሃይማኖት ውሳኔያቸው ላይ ገልጸዋል፡፡ እኛም ይህንኑ እናምናለን፡፡ መንፈስ ቅዱስ ከአብ ብቻ የሠረፀ ነው ቢባልም፥ መንፈስ ቅዱስ የአብም የወልድም የባሕርይ ሕይወታቸው የባሕርይ እስትንፋሳቸው መሆኑን እናምናለን፡፡

## ስለ መንፈስ ቅዱስ አካል

መንፈስ ቅዱስ የራሱ የሆነ የተለየ አካል እንዳለው እናምናለን፡፡ ታዲያ ይህ የመንፈስ ቅዱስ አካል ምን እንደሆነ እናውቃለን? መቼም ቢሆን መንፈስ ቅዱስ በዓይን የሚታይ፥ በእጅ የሚዳሰስና የሚጨበጥ ወርድና ቁመት፥ ግዘፍና ክብደት ያለው አካል ማለታችን እንዳልሆነ የታወቀ ነው፤ ወይም ነፍስና አእምሮ፥ ሕይወትና ስሜት የሌለው እንደማይታዩና እን ደማይታወቁ የተፈጥሮ ኃይላት አይደለም፡፡ የመንፈስ ቅዱስ አካል በምንልበት ጊዜ የማይታይና የማይዳሰስ ብቻ ሳይሆን ሕይወት ያለው ባለአእምሮ፥ፈቃድና ኃይል ያለው ከአብና ከወልድ ጋር በተለየ ሁኔታ በተለየ መልክ የሚታወቅ መሆኑን አጉልቶ ለማሳየት ነው፡፡

እንግዲህ እንደ አብና እንደ ወ[illegible] ራሱ የሆ ኑ አካል እንዳለው እናምናለን፡፡ ነገር ግን [illegible]



ብሔርንም እንደ ተሳደቡ ይቆጠራል፡፡ ምክንያቱም እግዚአብሔር መንፈስ ነውና (ዮሐ.4፥24)፡፡ መንፈስ ቅዱስንም የሚሳደብ ኃጢአቱ አይሠረይለትም (ማቴ.12፥31-32)፡፡ እኛስ መንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔር መንፈስ እንደ ሆነ እናምናለን፤ የተለየ አካልም እንዳለው እናምናለን፡፡ ለእርሱም እንሰግዳለን፡፡

አካል ስንል ምን ማለታችን እንደሆነ በትክክል መረዳት ይኖርብናል፡፡ በትምህርተ ሃይማኖት አካል ሲባል "ፍጹም ገጽ ፍጹም መልክ ያለው፡ራሱን የቻለ ለራሱ የበቃ፤ እኔ የሚል ህላዌ፡ ነባቢ፤ ቁመት ቁመና፤ የባሕርይ የግብር የስም ባለቤት፤ እገሌ የሚባል፡፡ እኔ ማለትም የሚገባ ዕውቀት ቀዋሚነት ላላቸው ለማይሞቱና ለማይጠፉ ለሦስት ብቻ ነው፤ ለአምላክ ለመልአክ ለነፍስ"፡፡[62] ስለዚህ አካል ስንል በተለምዶ አነጋገር ግዑዙን ግዙፉን ግሡሡን ዓለም እንዳልሆነ ማስተዋል ይኖርብናል፡፡ በመንፈሳዊ ትምህርታችን ስለ ረቂቁ አካል ስንናገር ከቁስ አካል ጋር ዝምድና የሌለውና ፈጽሞም የተለየ እንዲያውም የሚቃረን መሆኑን በቅድሚያ ማወቅ ከትምህርታችን አንዱ ክፍል መሆን አለበት፡፡

የመንፈስ ቅዱስን "አካል" ለመግለጽ ቅዱሳን አባቶች የተጠቀሙበት የመጀመሪያው ቃል በዮናኒ (በግሪክ) ቋንቋ ሃይፖስታሲስ ይባላል፡፡ በላቲኑ ፐርሶና ይባላል፡፡ ትርጉሙ ሰብእ (ሰው) ከሚለው ጋር የተያያዘ ስለሆነ "ሰብእ ነት" ወይም "ሰብእና" ተብሎ ሊፈታ ይቻላል፡፡ ይህን ቃል ለመንፈስ ቅዱስ ብቻ ሳይሆን ለአብና ለወልድም ይጠቀሙበታል፡፡ የመንፈስ ቅዱስን አካል "ሰብእና" ማለት ሃይፖስታሲስ በሚለው የዮናኒ ቋንቋቸው ሲጠቀሙ መንፈስ ቅዱስ እንደ ሰው የሚዳሰስና የማይዳሰስ ነፍስና ሥጋ የተዋሐደው አካል ወይም ሰውነት አለው ለማለት ሳይሆን፡ ግዑዝ ነገርና ብትን ኃይል አለመሆኑን አሳ ውቀው፥ እርሱ ግን ሕይወትና እውቀት ያለው፡ ነፃ ፈቃድና ችሎታ ያለው፡ እንደ ሰው ነፍስ ወይም እንደ መልአክ አካልና ህላዌ ያለው ረቂቅ መን ፈሳዊ አካል እንደሆነ በማያሻማ ቃል ለማሳየት በማሰብ ነው፡፡ "ሰብእና" ማለት ፐርሶና የተባለው ቃል የሰውን ግዙፍ አካል የሚገልጽ ሳይሆን፡ የሰውን ማን ነት፥ እውቀቱንና ችሎታውን፡ የተለየ ጠባዩንና ዝንባሌውን፡ ነፃ ፈቃዱንና ውሳኔውን የሚገልጽበት፥ እኔነቱን የሚያረጋግጥበት ቃል በመሆኑ የረቂቅ አካ ልን ምሥጢራዊ ትርጉም ለማስረዳት ይረዳናል በማለት የቀድሞውን ቋንቋ ከዚህ ላይ ለመጥቀስ ተገድደናል፡፡

የመንፈስ ቅዱስ አካል እንደ አብና እንደ ወልድ መሆኑን ቅዱሳት መጻሕፍት ያስተምሩናል፡፡ ጌታችን በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም እን ዲያጠምቁ ሐዋርያትን ሲያዛቸው፡ መንፈስ ቅዱስ የተለየ ስም፡ የተለየ አካል የተለየ ግብር እንዳለው ያስረዳናል (ማቴ.28፥19)፡፡ ጌታችን በዮርዳኖስ በተጠ መቀ ጊዜ አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስም በየራሳቸው አካል ተገልጸዋል፡፡ አብ ከሰማይ የምወደው ልጄ ይህ ነው ብሎ ሲናገር የተለየ አካል እንዳለው ታወቀ፡፡ ወልድም በተለየ አካሉ በለበሰው ሥጋ ታይቷል፡፡ መንፈስ ቅዱስም በተለየ አካ ሉ በርግብ አምሳል ተገልጧል (ማቴ.3፥16-17)፡፡ እንግዲህ እግዚአብሔር አን ድ አካል አንድ ገጽ ቢሆን ኖሮ ይህ ዓይነቱ መለኮታዊ መገለጥ ባልሆነና ባልተደረገም ነበር፡፡ እግዚአብሔር ሦስት አካላት ያሉት አንድ አምላክ ነው የምንለው ለዚህ ነው፡፡

[illegible] መገለጥ በኦሪትም የታወቀ ነው፡፡ ለአብርሃም

www.ethiopianorthodox.org

የተለገጡት ሦስቱ እንግዶች ይኸንኑ ያስረዳሉ (ዘፍ.18)፡፡ በወንጌልም ... ስለ መንፈስ ቅዱስ የተናገረው ሁሉ የመንፈስ ቅዱስ አካላዊነትን ይገል... እንጂ ተቃዋሚዎች እንደሚሉት አካላዊነትና ሕይወት የሌለው ጭፍን ኃይል ... ድርጐ የተናገረበት ቦታ የለም፡፡ እንዲያውም ጌታችን ወደ አብ በተመለሰ... ጊዜ ትቷቸው በመሄዱ ብቸኞዎች ለነበሩት ሐዋርያት፥ ወላጆች እንደለ... ልጆች በመቁጠር እንደ አባት እንደ እናት ሆኖ የሚያጽናና የሚያጸና መ... ቅዱስን ላከላቸው፡፡

"አብ በስሜ የሚልከው . . . መንፈስ ቅዱስ የሆነው አጽናኝ እ... ሁሉን ያስተምራችኋል እኔም የነገርኋችሁን ሁሉ ያሳስባችኋል፡፡" ብሎ ጌ... የተናገረለት እርሱ ማነው? (ዮሐ.14፥26)፡፡ የሚያጽናና፥ የሚያስተ... የሚመራ፥ ጸጋን የሚያድል እርሱ ማነው? አእምሮ አልባ ግዑዝ ኃይል ... ሊያደርግ ይችላልን? አይችልም፡፡ ይህን ሊያደርግ የሚችል ሙሉ እ... ያለው፥ፍጹም ርኅሩኅ የሆነ፣ መለኮታዊ ኃይልና ረቂቅ አካል ያለው እ... መንፈስ ቅዱስ ብቻ ነው፡፡ መንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔር የፍቅር መን... ነው፥ የፍቅር ኃይል ነው፡፡ "በመንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔር ፍቅር በልባ... ያድራል" (ሮሜ 5፥5)፡፡ ስለዚህ ነው መንፈስ ቅዱስ ያደረበት ሰው በእግዚ... ብሔር ፍቅር የሚኖረው፥ በፍቅር ኃይልም መልካሙን ለማድረግ የሚተጋው፡፡

## ለ) የመንፈስ ቅዱስ አምላክነትና ሕይወት ሰጭነት

"ጌታ ማኅየዊ በሚሆን ከአብ በሠረፀ በመንፈስ ቅዱስም እናምናለን፡፡ እ... ሰግድለትና እናመሰግነውም ዘንድ ከአብና ከወልድ ጋር" በማለት የተደነገ... ይህ አንቀጸ ሃይማኖት የመንፈስ ቅዱስን አምላክነት ይገልጽልናል፡፡ "ጌ... ማኅየዊ" የተባሉት ቃላት ለአምላክ ብቻ የሚሰጡ ናቸው፡፡ ስለዚህም መንፈ... ቅዱስ "ጌታ ማኅየዊ" መሆኑንና አምላክነቱንም በቅዱሳት መጻሕፍት ቃ... በማረጋገጥ፥ የመንፈስ ቅዱስ ተቃዋሚዎችን የረቱት የጥንቶቹ የቤተ ክርስቲያን አባቶች በአንቀጸ ሃይማኖታቸው ደንግገውልናል፡፡ መንፈስ ቅዱስ ከአብና ከወልድ ጋር እኩል ስለሆነ ከእነርሱ ጋር ልንሰግድለትና ልናመሰግነ... እንደሚገባን አስተምረውናል፡፡

የጥንቷ ዓለም አቀፋዊትና ሐዋርያዊት ቤተ ክርስቲያን እምነት ሆኖ ሳለ በዘመናችን የተወገዘው የኑፋቄ ሐሳብ እንደ አዲስ ሆኖ በልዩ ልዩ መል... መቅረቡ ለምን ይሆን? ምናልባት ከቃለ እግዚአብሔር ይልቅ የራሳቸውን ... ስተ ያየትና አስተሳሰብ የበለጠ አድርገው በመገመት ይሆን? ነገሩ እንደዚህ ይመስላል፡፡ ምክንያቱም ተቃዋሚዎች ከ1950 ዓ.ም. ጀምሮ ባሳተሙት አዲስ ኪዳን ውስጥ የወልድንና የመንፈስ ቅዱስን አምላክነት የሚገልጹትን ቃላትና ዓረ... ፍተ ነገሮች መፋቃቸው፥ የእውነት ጠላቶች መሆናቸውን ስለሚመሰክርባቸው ነው፡፡ ይህንንም በማድረጋቸው ዛሬም በዓለም አብያተ ክርስቲያናት የተወገዙ ናቸው፡፡ የተቆነጻጸለውን መጽሐፍ ቅዱሳቸውን ከራሳቸው አባላት በስተቀር ማን... ም አልተቀበለውም፡፡ የጥንቶቹ መናፍቃን ቢከራከሩ እንጂ ቃለ እግዚአብሔርን እየፋቁ ከቅዱሳት መጻሕፍት አላወጡም፡፡ እንግዲህ ከፊተኛው የኋለኛው እን... ደሚብስ አውቀን ቃለ እግዚአብሔርን ትተ...



... የሚያስቸግር ነገር አለ፥ ያልተማሩትና የማይጸኑትም ሰዎች ... መጻሕፍት እንደሚያጣምሙ እነዚህን ደግሞ ለገዛ ጥፋታቸው ... እንግዲህ እናንተ ወዳጆች ሆይ፥ ይህን አስቀድማችሁ ... በዓመፀኞቹ ስሕተት ተስባችሁ ከራሳችሁ ጽናት እንዳትወድቁ ..." (2ኛጴጥ.3፥16-17)፡፡

ስለዚህ ይኸን የሐዋርያውን ቃል ሰምተን መጽሐፍ ቅዱስን አጣመው ... መቼ ... አስተያየታቸው ከሚተረጉሙ ሁሉ መጠበቅ ይኖርብናል፡፡ ... ን ማጣመም ብቻ! የዛሬዎቹስ የተቀደሰውንና በዓለም አብያተ ... ያናት ሁሉ የታወቀውን ቃለ እግዚአብሔር ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ... አውጥተው የሚጥሉ ናቸው፡፡ ታዲያ እነዚህን የማን ምስክሮች እን ... የሐሰት ምስክሮች ከማለት በቀር፡፡ ምክንያቱም እነርሱ የሐሰት አባት ... የሚጠራውን የእርሱን ፈለግ የሚከተሉ ሆነው ተገኝተዋልና፡፡ እርሱ ሐ... ሁሉ ከራሱ አንቅቶ ይናገራልና ተብሎ እንደ ተጻፈ (ዮሐ.8፥44)፡፡

... የዓለም አብያተ ክርስቲያናት አጠቃላይ ... መንፈስ ቅዱስን በተመለከተ፥ በ1983 ዓ.ም. በተሰበሰበ ጊዜ ... በካምቤራ ከተማ አውስትራልያ በጥር ወር ... ርእስ ሆኖ ቀርቦ ነበር፡፡ በዚህ ዓለም አቀፍ ስብሰባ ኢትዮጵያንም ጨም... ከልዩ ልዩ ሀገሮች የመጡ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ተሳታፊዎች በሚገኙበት ... ስጠው ትምህርት፥ የተካሄደው ውይይት፥ የተላለፈው የጋራ መግለጫ ሁሉ ... መንፈስ ቅዱስን አምላክነት የሚያንፀባርቅና የሚያረጋግጥ ነበር፡፡ ከጥቂት ... ፍቃን በስተቀር በዓለም ዙሪያ የሚገኙት አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ በመን... ቅዱስ አምላክነት ያምናሉ፡፡ ምክንያቱም በቅዱሳት መጻሕፍት የተጻፈ ... ስለሆነ ነው፡፡

ኢዮብ ስለ መንፈስ ቅዱስ ፈጣሪነትና ሕይወት ሰጪነት እንደሚከተለው ... መስክሯል፡፡ "የእግዚአብሔር መንፈስ ፈጠረኝ፥ ሁሉንም የሚችል የአምላክ እስትንፋስ ሕይወትን ሰጠኝ" (ኢዮብ 33፥4)፡፡ እዚህ ላይ የአምላክ እስትንፋስ ... ባል መንፈስ ቅዱስን ማለት መሆኑን መረዳት ይኖርብናል፡፡ ነቢዩ ዳዊትም ... "መንፈስህን ትልካለህ ይፈጠራሉም፥ የምድርንም ፊት ታድሳ... ለህ" (መዝ.103፥30) በማለት ገልጿል፡፡ በተጨማሪም "በእግዚአብሔር ቃል ... ሰማዮች ጸኑ፥ ሠራዊታቸው ሁሉ በአፉ እስትንፋስ፤" ሲል የመንፈስ ቅዱስን መለኮታዊ ኃይል አረጋግጧል (መዝ.32፥6)፡፡

## ሐ) በመንፈስ ቅዱስ የመዳናችንና የመቀደሳችን ምሥጢር

". . . ወይስ ዓመፀኞች የእግዚአብሔርን መንግሥት እንዳይወርሱ አታውቁምን? አትሳቱ፤ ሴሰኞች ቢሆኑ ወይም ጣዖትን የሚያመልኩ ወይም አመንዝሮች ወይም ቀላጮች ወይም ከወንድ ጋር ዝሙት የሚሠሩ ወይም ሌቦች ወይም ገንዘብን የሚመኙ ወይም ሰካሮች ወይም ተሳዳቢዎች ወይም ነጣቂዎች የእግዚአብሔርን መንግሥት አይወርሱም፡፡ ከእናንተም አንዳንዶቹ እንደ እነዚህ ነበራችሁ፤ ነገር ግን በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም በአምላካችንም <u>መንፈስ</u> ታጥባችኋል፥ ተቀድሳችኋል፥ ጸድቃችኋል" (1ኛቆሮ.6፥9-11)፡፡

... የተዘረዘሩትን የዓመፀኞች ሥራዎች፥ ክህደታቸውንና ...

www.ethiopianorthodox.org

(ሮሜ.6፥21)፡፡ ታዲያ እንዴት ነው በኃጢአታችን ቁስል ታምመን ሳንሞት
በፊት ተፈውሰንና ድነን መንግሥተ ሰማያትን ለመውረስ የምንችለው? እንዴት
ነው የመዳናችንና የመቀደሳችንን ጸጋ ለማግኘት የምንችለው? መልሱ ከምንባቡ
እንደተገለጠው "በክርስቶስ ስም በአምላካችንም መንፈስ" ከኃጢአታችን ነጽተን
ድነናል፥ ተቀድሰናል፥ ጸድቀናልም፡፡ ይህም ማለት በምሥጢረ ጥምቀት ኃጢአ
ታችን ተሠርዮልን በመንፈስ ቅዱስ ታድሰን መዳናችንን ያመለክታል፡፡ ይኸው
ሐዋርያ ለቲቶ በጻፈው መልእክቱ በመንፈስ ቅዱስ ጸጋ መዳናችንና
መጽደቃችንን ያስረዳል፡፡

> "የመድኃኒታችን የእግዚአብሔር ቸርነትና ሰውን መውደዱ በተገለጠ ጊዜ፥ እን
> ደ ምሕረቱ መጠን ለአዲስ ልደት በሚሆነው መታጠብና በመንፈስ ቅዱስ
> በመታደስ አዳነን . . . ያን መንፈስም፥ በጸጋው ጸድቀን በዘላለም ሕይወት
> ተስፋ ወራሾች እንድንሆን፥ በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በእኛ ላይ አ
> ትርፎ አፈሰሰው፡፡ ቃሉ የታመነ ነው . . . " (ቲቶ.3፥4-8)፡፡

እንግዲህ በክርስቶስ አምነን በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም ስን
ጠመቅ መዳናችንና መቀደሳችን መጽደቃችንም በእያንዳንዳችን ሕይወት ውስጥ
እውን የሚሆነው በጸጋ መንፈስ ቅዱስ ኃይልና ረድኤት እንደሆነ ከላይ ከተጠቀ
ሱት ምንባቦች ለመረዳት እንችላለን፡፡ ስለዚህ የመዳናችንና የመቀደሳችን
ምሥጢር የሚፈጸመው በግብረ መንፈስ ቅዱስ እንደሆነ እናምናለን፡፡ ከኃጢአ
ት እንጽቶና ቀድሶ ጽድቅን የሚያሠራን እርሱ እንደሆነ እናምናለን፡፡ "ኃጢአ
ተኝነትንና ዓለማዊን ምኞት ክደን . . . ራሳችንን በመግዛትና በጽድቅ እግዚአ
ብሔርንም በመምሰል በአሁኑ ዘመን እንድንኖር" የሚያስተምረንና የሚረዳን፣
ጸጋ እግዚአብሔር፣ ጸጋ መንፈስ ቅዱስ ነው (ቲቶ.2፥11-13)፡፡

## የመዳናችን ሥራ ታሪክና የጸጋው አፈጻጸም

የጌታችን ታሪክ፥ ትምህርትና ሥራ ሁሉ የታወቀው በመንፈስ ቅዱስ
ሥራና ጸጋ ነው እንጂ ነገረ መስቀሉን[63] ሰው በራሱ ጥረት ብቻ ሊረዳው
ባልቻለም ነበር፡፡ በታሪክ ለአንዴና ለዘላለም የተፈጸመው የጌታ የማዳን ሥራ
ልዩ ነው፤ እንደ ሌላው የጥንት ታሪክ በነበር የሚያልፍና በጥንታዊ ከተማ
ፍርስራሽ ውስጥ ተቀብሮ የሚኖር ነገር አይደለም፡፡ የጌታ የማዳን ሥራ ታሪክ
ሞትን የሻረ፥ትንሣኤ ሙታንንና አዲስ ሕይወትን ያስገኘ ስለሆነ በመለኮታዊ
ኃይሉ በጊዜና በቦታ አይገደብም፡፡ ይሁን እንጂ ሰዎች የዚህን የማዳን ታሪክ
የሚያውቁትና የሚያስታውሱት፥ የመዳኑም ጸጋና በረከት ተካፋይ የሚሆኑት
በግብረ መንፈስ ቅዱስ መሆኑን መዘንጋት የለብንም፡፡ ያለ መንፈስ ቅዱስ
ጸጋ፥ምእመናን ሁሉ በእምነት፥በተስፋና በፍቅር ሆነው በክርስቲያናዊ
ሕይወታቸው መከራ ተቀብለው እስከ መጨረሻው በትዕግሥት ጸንተው ለመኖር
ይቅርና ገና ከመጀመሪያው እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ያደረገላቸውን ቸርነት
የሚያውቁበትን ጸጋ ባላገኙም ነበር፡፡ የመንፈስ ቅዱስ የጸጋው ስጦታ
የተጀመረውና የተመሠረተው ከጌታችን የማዳን ሥራ ታሪክ በመነሣት ነው፡፡

እግዚአብሔር በአርአያውና በአምሳሉ የፈጠረው የሰው ዘር ሁሉ በከባድ
መከራና ሥቃይ መኖሩን አውቆ (አባቶች ... እንደሚሉት) እግዚአ



ኀዘኑንና ጭንቀቱን ተመልክቶ
ብሔር የአዳምን ንስሐውንና ልቅሶውን፥ ኀዘኑንና ጭንቀቱን ተመልክቶ
ፍጠረኝ ሳይለኝ የፈጠርኩት አዳም በእግረ አጋንንት እንደ ተጠቀጠቀ በመን
በሬ ደይን እንደ ወደቀ ይቅርን? ብሎ በምሕረቱና በቸርነቱ ብዛት ልጁን
ኃጢአት ባጠቃት ሰውነት አምሳል ልኮ ያችን ኃጢአት ቀጣት ይላሉ
(ሮሜ.8፥3)፡፡ ይህም ማለት የእግዚአብሔር ልጁ ክርስቶስ ስለ ሰው ልጆች
ሰው በመሆን ሰውንም ለማዳን የሰውን ኃጢአትና ቅጣት በሰውነቱ መቀበሉን
ለማስረዳት ነው፡፡ "ነሥአ ደዌነ ወፆረ ሕማመነ፦ ደዌያችንን ወሰደ
ሕማማችንንም ተሸከመ" ተብሎ በትንቢት እንደተነገረው የዘመኑ ፍጻሜ በደረ
ሰ ጊዜ ስለ ኃጢአታችን በኃጢአተኞች እጅ ሕማማተ መስቀልን በፈቃዱ
በመቀበል ሞትን በሞቱ ድል አድርጎታል (ኢሳ.53፤ ገላ.4፥4-5)፡፡ የማዳን
ሥራውንም በትንሣኤውና በዕርገቱ ፈጽሞታል፡፡ ይህ ለአንድ ጊዜ በዕለተ ዓ
ርብ የተፈጸመው የማዳን ሥራውና ጸጋው እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ እን
ዲቀጥል ለማድረግ ክርስቶስ አስፈላጊውን ሁሉ በቅድሚያ አዘጋጅቷል፡፡ ድኅ
ነተ ጸጋው ለሰዎች ሁሉ ተዳርሶ ሰዎች ሁሉ እንዲድኑና እንዲጸድቁ ክርስቶስ
ያዘጋጀው የጸጋው መንገድ ምንድን ነው? የጸጋውስ መገኛ ቦታ የት ነው?
ብሎ ጠይቆ መረዳት አንዱ የትምህርተ ሃይማኖታችን ርእስ ነው፡፡

በሮሙ ቄሣር እንደራሴ በጲላጦስ ዘመን በቅድስት ሀገር በኢየሩሳሌም
የተፈጸመው የክርስቶስ የማዳን ሥራው በዓለም ታሪክ ውስጥ ተወዳዳሪ የሌለው
ታላቅ የእግዚአብሔር መለኮታዊ ሥራ ነበር፡፡ በዚያን ዘመንና ሀገር ነበር የዓ
ለምን ኃጢአት ሁሉ ለማስወገድ ክርስቶስ የእግዚአብሔር በግ የተሠዋው፤ እን
ደ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ አባባል ፋሲካችን ክርስቶስ የታረደው (1ቆሮ.
5፥7)፡፡ እርሱ በሞቱ ሞትን ደምስሶልናል፥ በትንሣኤው አዲስ ሕይወትን
ሰጥቶናል፡፡ እንግዲህ በአዳም በደል ምክንያት ወደ ዓለም ሁሉ የተሰራጨው
የኃጢአት በሽታ፥ ክፉ ደዌና ሕማም የሚወገድበትን ሐኪምና መድኃኒት እ
ነሆ እግዚአብሔር ሰጥቶናል፡፡ ነገር ግን ሰዎች ይህን ሐኪም ካላወቁት
የታዘዘላቸውንም መድኃኒት ካልወሰዱት ሊድኑ አይችሉም፡፡ ሐኪምም መድኃ
ኒትም ሆኖ ከእግዚአብሔር የተሰጠንን ልጁን ኢየሱስንና የማዳን ሥራውን
መቀበል ይኖርብናል፡፡ ኢየሱስ የሚለው ስም ሲተረጐም አዳኝም መድኃኒትም
ማለት እንደሆነ አንዘነጋውም፡፡ በዕለተ ዓርብ በመስቀል ላይ የተፈጸመው
የማዳን ሥራ ለአዳም ዕዳ በደል የተከፈለው ካሣ ዛሬ ለምንገኘው ለእኛ ለራሳ
ችን እንደተደረገ አድርገን አምነን ካልተቀበልነው በቀር ድርጊቱ ብቻውን ያለ
እምነት ጸጋ ሊያድነን አይችልም፡፡ በጥንተ ተፈጥሮ እግዚአብሔር እኛን ያለ
እኛ ፈጥሮናል፤ በሐዲስ ተፈጥሮ ግን እኛን ከእኛ ጋር ሆኖ ፈጥሮናል ማለት
እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ሆኖ (አማኑኤል) አድኖናል፡፡ የእግዚአብሔር የማዳን
ጥበቡ ያለ እኛ ፈቃደኝነትና ትብብር፥እምነትና ፍቅር እንደማይሆን የታወቀ
ነው፡፡

እርግጥ ነው በእግዚአብሔር በኩል የመዳናችን ሥራ ተከናውኗል፤ ጥን
ተ አብሶ ማለት የመጀመሪያው የአዳም ኃጢአት ተሠርዮአል፥ የዕዳ
ደብዳቤያችን ተሠርዟል፥ መርገሙ ተነሥቷል፥ የተዘጋው ገነት ተከፍቷል፡፡
እነዚህን ሁሉ እግዚአብሔር ስለ ሰው ሲል ፈጽሞታል፡፡ ይህን ሁሉ ማለታችን
ሁሉ ነገር አልቋልና የተዘጋውም ገነት ተከፍቷልና ከእንግዲህ ወዲህ የዓለም
... እንደየው ያለ ገደብ መንግሥተ ሰማያት ይገባል ማለት አይ
ደለም፡፡ በዓመተ ... በኋላ በዓመተ ምሕረት በተለይም ከዕለተ ዓርብ በኋላ

www.ethiopianorthodox.org

መልካም ሥራ ሰዎች ደግሞ በበኩላቸው ተገቢውን ምላሽ ማድረግ ይገባቸዋል፡፡ ይህን እስካላደረጉ ድረስ መዳን የለም፡፡ ስለዚህ ሰዎች የሚድኑት እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን ፍቅር አውቀው፥ በአዳኛቸውና በማዳን ሥራው በእርግጠኝነት አምነው በምስጋና በሚቀበሉበት ጊዜ ብቻ ነው፡፡ የዓለም መድኃኒት ኢየሱስ ክርስቶስን አምነውና አውቀው ስሙን ካልጠሩ በቀር ሊድኑ አይችሉም፡፡ "የጌታን ስም የሚጠራ ሁሉ ይድናልና" (ሮሜ.10፥13)፡፡

## ስለ መጀመሪያው ምክንያተ ድኅን

የጌታን ስም ጠርተን ለመዳን የምንችለው በመጀመሪያ እምነት ሲኖረን ነው፡፡ ስለሆነም እምነት እንዴት እንደሚገኝ? በማን በኩል እንደሚመጣልን? ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እንደሚከተለው አስተምሮናል፡

> "እንግዲህ ያላመኑበትን እንዴት አድርገው ይጠሩታል? ባልሰሙትስ እንዴት ያምናሉ? ያለ ሰባኪስ እንዴት ይሰማሉ? መልካሙን የምሥራች የሚያወሩ እግሮቻቸው እንዴት ያማሩ ናቸው ተብሎ እንደ ተጻፈ ካልተላኩ እንዴት ይሰብካሉ? ነገር ግን ሁሉ ለምሥራቹ ቃል አልታዘዙም፡፡ . . . እንግዲያስ እምነት ከመስማት ነው መስማትም በእግዚአብሔር ቃል ነው" (ሮሜ.10፥14-17)፡፡

ከዚህ ምንባብ እንደምንረዳው ሰዎች ሁሉ የእግዚአብሔርን ቃል በመስማት አምነው የጌታን ስም ጠርተው ለመዳን የሚችሉት የምሥራቹን ቃል ለመስበክ የተላኩ ልዑካን ሲኖሩ ብቻ ነው፡፡ለምክንያተ ድኅን የመጀመሪያዎቹ እነርሱ ናቸው፡፡ ስለዚህ ነው ጌታ ሐዋርያትን በመጀመሪያ በስብከተ ወንጌል ሥራ እንዲሠማሩ ያደረገው (ማቴ.28፥19-20)፡፡ እንግዲህ የክርስቶስ የማዳን ጸጋ መንገድ እግዚአብሔር ባወቀ መንፈስ ቅዱስ ባዘጋጃቸው ልዑካን አማካኝነት ነው ማለት ነው፡፡ ማንም ተነሥቶ ራሱን በራሱ የወንጌል መልእክተኛና ሰባኬ ወንጌል አድርጎ መሾም አይችልም፡፡ ምክንያቱም ከላይ ከጥቅሱ እንደተመለከተው ሁሉም ሰው "ለምሥራቹ ቃል አልታዘዙም" ተብሏልና፡፡

## መዳናችንና መቀደሳችን በግብረ መንፈስ ቅዱስ ይፈጸማል

የጸጋ መስጫ መንገድ የተላኩት ልዑካን ናቸው ቢባልም ልዑካኑን ሁሉ የሚልከው እሱ ባለቤቱ ስለሆነ የጸጋ ሁሉ ምንጭና መገኛ እርሱ ብቻ ነው፡፡ ልዑካን መሣሪያዎች ናቸው፡፡ የክርስቶስ ጸጋ ለሰዎች ሁሉ የሚሰጠውና የሚታደለው፥ የድኅነት ጸጋና በረከት ተካፋይ መሆን የሚቻለው በመንፈስ ቅዱስ ኃይልና ረድኤት ነው፡፡ ወደ ክርስቶስ የሚመጣም ሆነ የሚያምን ሁሉ በቅድሚያ "ከእግዚአብሔር አብ የሰማ የተማረም" በጸጋውም የተጠራ መሆን አለበት፡፡ ስለዚህ ነው ጌታችን "አልቦ ዘይክል መጺአ ኀቤየ እመ ኢሰሐቦ አብ ዘፈነወኒ፡ የላከኝ አብ ካልሳበው ወደ እኔ መምጣትን የሚችል የለም" ያለው (ዮሐ.6፥44-45 ትርጓሜውን ተመልከት)፡፡ ይህም ማለት የላከኝ አባቴ በሀብት ስቦ በረድኤት አቅርቦ ካልሰጠኝ በኔ ማመን የሚቻለው የለም ማለት ነው፡፡ ታዲያ ይህን በውል ያልተረዱ አንዳንድ ሰዎች ያለ ጸጋ እግዚአብሔር ማለት ያለ መንፈስ ቅዱስ ጸጋ

www.ethiopianorthodox.org



ነው ማለት አይችልም (1ኛቆሮ.12፥3፤ 1ኛዮሐ.4፥2)፡፡ ማንም ሰው ይህን ካላመነና ካልመሰከረ ደግሞ ሊድን አይችልም፡፡ ስለዚህ ለማመን ልቡናችንን የሚያነሣሣ ካመንና ከተጠመቅን በኋላም በእምነት ለመኖር የሚያጸናንና የሚያጽናናን እርሱ የእግዚአብሔር መንፈስ ነው፡፡ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እንዳለው "ስለ በጎ ፈቃዱ መፈለግንም ማድረግንም በእናንተ የሚሠራ እግዚአብሔር ነውና" (ፊልጵ.2፥13)፡፡ እንግዲህ በክርስቶስ የተገኘው የመዳን ጸጋ ሁሉ በእያንዳንዱ አማኝ ልቡና ውስጥ እውን የሚሆነው በተግባርም የሚተረጎመው በመንፈስ ቅዱስ ረቂቅ ጥበብና ሥራ ነው፡፡ ይህን ረቂቅ የእግዚአብሔር መንፈስ ዓለሙ ፈጽሞ የማያውቀው ቢሆንም አማኞች ግን በውስጣቸው ስለሚኖር ያውቁታል (ዮሐ.14፥17)፡፡

እንግዲህ የእግዚአብሔር መንፈስ የምሥራቹን ቃል እንድንሰማና እንድናምን ይረዳናል፤ በጥምቀትም ሥርየተ ኃጢአትን፥ አዲስ ሕይወትን፥ የጸጋ ልደትን ይሰጠናል፤ እንደ ሥጋዊ ልደታችንና እድገታችን በመንፈሳዊ ሕይወታችንም ቀስ በቀስ በጸጋው እንድናድግ ያበቃናል፡፡ መንፈስ ቅዱስም ይህን ከፈጸመ በኋላ ሥራውን በዚህ አያቆምም፡፡ ሆኖም ይህ የመንፈስ ቅዱስ የመጀመሪያ ሥራ ይሆናል፡፡ ገና በውኃና በመንፈስ አዲስ ልደት አግኝተው በክርስቲያናዊ ሕይወታቸው ካላደጉት ከንዑስ ክርስቲያንነት ጀምሮ ወደ ከፍተኛው ደረጃና ማዕረግ እንዲደርሱ ሁልጊዜ መንፈስ ቅዱስ የአማኞቹን ልቡና ያነሣሣል፡፡ በክርስቶስ ጸጋ አምኜአለሁ ከእንግዲህ ወዲህ ምን እሆናለሁ በማለት አዲስ አማኝ ያለ አግባቡ ራሱን በራሱ በመሸንገልና በመደለል፥ በሐሰት በሚያባብል ስሜት ተነሣሥቶ እንዲያው በከንቱ እንዳይዘናጋና እንዳይዝናና ያስጠነቅቀዋል፤ "የቆመ የሚመስለው እንዳይወድቅ ይጠንቀቅ" ተብሏልና (1ቆሮ.10፥12)፡፡ ከዚህም ጋር መንፈስ ቅዱስ የሰውን ድካሙን ያውቃልና ከፈቃዳተ ሥጋ ጋር መንፈሳዊ ተጋድሎ እንዲያደርግ እንጂ በቸልተኝነት እንዳይኖር ያተጋዋል፡፡ የኃጢአት ዝንባሌውንም በመዋጋት ከበደልና ከፈተናም ሁሉ እንዲድን ተግቶ እንዲጸልይና እንዲጾም ያደርገዋል፡፡ ከበደልና ከክፉ ነገሮች ዓለምንም ከመውደድና ከመምሰል ራሱን እንዲለይ በማድረግ ወደ ቅድስና ኑሮ ይመራዋል፡፡ እንግዲህ በዚህ ሁኔታ የአማኙን መንፈሳዊ እድገት ከፍ በማድረግ በሕይወቱ ውስጥ የመንፈስ ፍሬዎች እንዲያፈሩ ይሆናል፤ መንፈስ ቅዱስ በገለጸለት እውነት እየተመራ በመንፈስ ይኖራል፤ በመንፈስም ይመላለሳል (ገላ.5፥22-25)፡፡

እንግዲህ ሰዎች በክርስቶስ በማዳን ሥራው አምነው እንዲድኑና እንዲጸድቁ እንዲቀደሱም በክርስቲያናዊ ሕይወታቸውም እንዲጸኑ ካደረገ በኋላ መንፈስ ቅዱስ ሥራውን በመቀጠል የዳኑትንና የተቀደሱትን ደግሞ ለበለጠ ሥራና አገልግሎት ያዘጋጃቸዋል፡፡ ለእነርሱ ልዩ ልዩ የአገልግሎት ጸጋ ማለት የማስተማር፥ ትንቢት የመናገር፥ ተአምራት የማድረግና የመሳሰሉት ስጦታዎችን በማደል አሕዛብን አሳምነው እንዲያጠምቁና እንዲያድኑ በማድረግ እንደራሱ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ተባባሪዎች ይሆናሉ እንጂ ያለ ጸጋ ስጦታ እን ... መንፈስ ቅዱስ እንደ ወደደ ለሁሉምና ለእያንዳንዱ

ስለዚህ ነው በመንፈስ ቅዱስ የተላኩ ልዑካን የምሥራቹን ቃል መስበክ፥ ግለ
መንና የመዳንን ጸጋ ማስተላለፍ የሚችሉት፡፡ እነርሱ የመዳናቸውንና የመ
ጻታቸውን ጸጋ ከመንፈስ ቅዱስ ተቀብለውና የእርሱም ማደሪያ በመሆ
ለሌሎች ደግሞ የኃጢአት ሥርየትና የመዳን ጸጋው መስጭያ ምክንያ
መሣሪያ ወይም መንገድ እንዲሆኑ ብቃትን ከላኪያቸው አግኝተዋል፡፡

## ለማዳን ሥራ የተመረጡ መሣሪያዎች

በቅዱሳት መጻሕፍት መሠረት ለማዳኑ ሥራና ጸጋ መሣሪያ በመሆ
የተመረጡ አንዳንድ ሰዎች አሉ፡፡ እነርሱ በመጀመሪያ ከዳኑ በኋላ ለሌሎ
ሰዎች ደግሞ ምክንያተ ድኂን ሆነዋል፡፡ ለምሳሌ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ
ከማመኑ በፊት ሳውል ተብሎ በሚጠራበት ጊዜ ጌታችን በልዩ ተአምራ
ተገልጾ ከይሁዲነት ወደ ክርስትና የመለሰው በተለየ ሁኔታ ነበር፡፡ ለመመለሰ
የመጀመሪያው ምክንያት እርሱ የጸጋው ባለቤት ክርስቶስ ሲሆን ሁለተኛው
ደግሞ ሐናንያ በሚባል ደቀ መዝሙር አማካኝነት ወንጌልን እንዲማር፥ እን
ዲያምንና እንዲጠመቅ በመደረጉ የደኅንነቱ ሥራ ተፈጽሟል፡፡ ጌታ ለሳኦል
በመንገድ መገለጡ ለእምነቱ ጽናት በቂ ተአምራዊ ድርጊት ቢሆነውም ድኅ
ነተ ጸጋን ማግኘትና መንፈስ ቅዱስን መቀበል ያስፈልገው ስለነበር ከሐናንያ
ዘንድ ሄዶ በጌታ ትእዛዝ እንዲጠመቅ ሆኗል (የሐዋ.9፥10-18)፡፡ ጌታ ያመ
ነ የተጠመቀ ይድናል ያለው ተፈጻሚ መሆን አለበት፤ የድኅነተ ጸጋ አማናዊ
መንገድ እርሱ ነውና (ማር.16፥16)፡፡ የመዳን ጸጋ በመሠረቱ የሚገኘው
ከእግዚአብሔር ነው፤ ነገር ግን እግዚአብሔር ጸጋውን የሚያስተላልፍበት መን
ገድ ሰው ነው፤ ለዚህ ለድኅነተ ጸጋ ሥራ የሚልከውን ሰው ይፈልጋል፡፡
የእግዚአብሔር መንፈስ የሚያድርበትን ሰው መርጦ ያድራል፤ ባደረበት
ሰውም አማካይነት ሥራውን ያከናውናል፡፡ ስለዚህም ቅዱስ ጳውሎስ "ንዋይ
ኅሩይ" የተመረጠ መሣሪያ በመሆን ክርስቶስን አገልግሏል (የሐዋ.9፥15)፡፡
እግዚአብሔር ሥራውን በሰዎች ብቻ አይደለም የሚሠራው መላእክቱንም
ለማዳን ሥራ ይልካቸዋል (ዕብ.1፥14)፡፡ ለምሳሌ የኢትዮጵያው ጃንደረባ
ከኦሪት ወደ ወንጌል እምነት የተመለሰው ጌታ መልአኩን ልኮ ፊልጶስን
ባዘዘው ጊዜ ነበር፡፡ ፊልጶስም በመንፈስ ቅዱስ ተመርቶ በሰረገላው ተቀምጦ
የኢሳይያስን መጽሐፍ ያነብብ የነበረውን ኢትዮጳያዊ ትምህርተ ወንጌልን ካስ
ተማረው በኋላ በገዛ ፈቃዱ ለመጠመቅ የሚከለክለኝ ምንድነው? ብሎ ኢየሱስ
ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ አምኛለሁ በማለት ተጠምቋል
(የሐዋ.8፥26-40)፡፡ የቆርኔሌዎስም ታሪክ ይህንን ይመስላል (የሐዋ.10)፡፡

የመዳን ጸጋ ከግቡ ደርሶ ተፈጻሚነት የሚያገኘው ወይም የማያገኘው
እንደ አማኙ ሁኔታ ነው፡፡ የኢትዮጵያው ሰው ከኦሪት ወደ ወንጌል እምነት
የተመለሰው ምንም የመንፈስ ቅዱስ ጸጋና ረድኤት የፊልጶስም የማስተማርና
የማሳመን ግፊት ቢኖርም እርሱ ራሱ በነፃ [illegible]



ምና (2ኛተሰ.3፥1-2)፡፡

## የመዳናችን ምሥጢር የሦስት ወገን ቅንብር

እንግዲህ በጌታ ስም የመዳናችንና የመቀደሳችን ምሥጢር በመሠረቱ
በእግዚአብሔር መንፈስ ኃይልና ረድኤት የሚፈጸም መሆኑን እናምናለን፡፡
ለለዚህ ነው ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ "በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም በአምላካ
ችንም መንፈስ ታጥባችኋል፥ ተቀድሳችኋልም፥ ጸድቃችኋል" ያለው (1ኛቆ
ሮ.6፥11)፡፡ የጸጋው መሰጠት ወይም ጸጋን የመቀበል ሁኔታ የሚከናወነው
በሦስት አቅጣጫ የምናያቸው፥ ግን ዓላማቸው አንድ የሆኑ የሦስት ወገኖች ቅን
ብር ሲኖር ነው፡፡ እነርሱ ከሌሉ የጸጋው ምሥጢር አሰጣጥና አፈጻጸም
የተሟላ አይሆንም፡፡ ለመጀመሪያው ወገን መሠረቱና ምንጩ እርሱ ራሱ እግዚአ
ብሔር ነው፡፡ ሁለተኛው የእምነትና የመዳን ጸጋ መሣሪያ ወይም ምክንያት የሆ
ነውን ወገን ይመለከታል፡፡ ይህ ሁለተኛው ወገን በዓይነቱም ሆነ በብዛቱም
ከሌላው ወገን የተለየ ነው፡፡ በዚህ ወገን የሚገኙት የእምነትና የድኅነተ ጸጋ
ምክንያቶች ከመላእክት ጀምሮ የቃሉ አገልጋዮች እስከ ሆኑት እስከ
ሐዋርያትና አርድእት፥ነቢያትና ካህናት እንዲሁም ልዩ ልዩ ሥራዎቻቸውን ሁሉ
ያጠቃልላል፡፡ ሥራቸውን ስንል በማስተማራቸውና በማጥመቃቸው እንዲሁም
ሌሎች ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያንን በመፈጸማቸው ምክንያት የእምነትና
የመዳን ጸጋ ለብዙዎች እንዲዳረስ ሆኗል ለማለት ነው፡፡ ልዩ ልዩ ተአ
ምራት፥ድንቅ ሥራዎቻቸውና ምልክቶቻቸው ሁሉ ምክንያተ ድኂን በመሆን
ብዙዎች የመዳንንና የመቀደስን ጸጋ በማግኘት ጽድቅን ተጐናጽፈዋል፡፡ በዚህ
በሁለተኛ ወገን የምናያቸውም የማናያቸውም የምናውቃቸውም የማናውቃቸውም
እርሱ እግዚአብሔር ባወቀ የሚያዘጋጀው መንገድ ብዙ ነው፡፡ ሆኖም በእግዚአ
ብሔር የታወቀው በቅዱሳት መጻሕፍት የታዘዘው በይፋ የሚሠራበት መንገድ አ
ለ፡፡ ስለ እርሱ ከመናገራችን በፊት ስለ ሦስተኛ ወገን እንመለከታለን፡፡

በዚህ በሦስተኛ ወገን ነው የመዳን ሥራ ዓላማና ግብ ሁሉ
የሚያተኩረው፡፡ እግዚአብሔር ከጥንት ጀምሮ "እንደ ወደደ እንደ ሐሳቡ
የፈቃዱን ምሥጢር አስታውቆናል በዘመን ፍጻሜ ይደረግ ዘንድ ያለውም ሐሳ
ቡም በሰማይና በምድር ያለውን ሁሉ በክርስቶስ ለመጠቅለል ነው" በማለት
ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እንደገለጸው ሰዎች ሁሉ በክርስቶስ አምነውና ድነው
በመንፈስ ቅዱስ ሱታፌ ሁሉም በአንድነት ተሰብስበው የእግዚአብሔርን ልጅ
ነት አግኝተው የመንግሥተ ሰማያት ወራሾች እንዲሆኑ ነው (ኤፌ.1፥9-10)፡፡
ስለዚህ እግዚአብሔር ሰውን ስለ ወደደ ከአንድ ልጁ ጀምሮ ሁሉም ነገር ለሰው
ልጆች ደኅንነትና ጥቅም እንዲሆን አድርጓል (ዮሐ.3፥16)፡፡ "ነገር ሁሉ የእናንተ
ነውና፤ ጳውሎስ ቢሆን አጵሎስም ቢሆን ኬፋም ቢሆን ዓለምም ቢሆን ሕይወትም
ቢሆን ሞትም ቢሆን ያለውም ቢሆን የሚመጣውም ቢሆን ሁሉ የእናንተ ነው"
የሚለው ቃል ለሦስተኛው ወገን የተነገረ ነው (1ኛቆሮ.3፥21-22)፡፡ ነገር ግን
በመዳኑ ጸጋ መጠቀም ወይም አለመጠቀም ከላይ እንደ ጠቀስነው የሰውን ነፃ
ፈቃድና ውሳኔ የሚጠይቅ ስለሆነ ሁሉም ሰው የጸጋው ተካፋይ ሊሆን አል
ቻለም፡፡ እንግዲህ ሦስተኛው ወገን ወደፊት የሚድኑት ወገኖችን፥ ንዑሰ
[illegible] ንሳሕያንንና ልዩ ልዩ መንፈሳዊ አገልግሎት የሚ

www.ethiopianorthodox.org

የሚያስችል የጸጋውን መንገድና ጸጋው የሚገኝበትን ቦታ ሁሉ በቅድሚያ አ
ጋጅቷል፡፡ ከላይ በሁለተኛው ወገን የተጠቀሰው ክፍል የእግዚአብሔር መንፈስ
ሥራውን የሚሠራበትን መንገድ የሚያመቻች ነው፡፡ ከጥንት ጀምሮ በ
መነ ብሉይ እግዚአብሔር ለቃሉ ማስተላለፊያ እንዲሆኑ የመረጣቸው ነቢያት
ነበር፡፡ መንፈስ ቅዱስ በእነርሱ አድሮ ይናገር ነበር፡፡ ሙሴና አሮንም በእግ
ዚአብሔር ተመርጠው የእግዚአብሔር ቃል በእነርሱ በኩል ለሕዝበ እሥራኤል
ይደርስ ነበር፡፡ በእነርሱ ዘመን አሥራ ሁለቱ ነገደ እሥራኤል ከእግዚአብሔር
ጋር ቃል ኪዳን በመግባት ታላቅ ሕዝብ በእግዚአብሔርም ዘንድ የተወደደ
ወገን ሆኑ፤ " ከአሕዛብ ሁሉ የተመረጠ . . . የካህናት መንግሥት የተቀደ
ሰም ሕዝብ" ተብሎ ተጽፎላቸዋል (ዘጸ.19፥5-6)፡፡ ይህም በዘመነ ሐዲስ
ለሚደረገው ምሳሌ ነበር፡፡

ጌታችንም የምሥራቹ ቃልና የወንጌሉ ጸጋ ለሁሉም ሕዝብ እንዲዳረስ
እርሱ በመዋዕለ ሥጋዌው በፈጸመው በማዳን ሥራና ጸጋው ዓለም ሁሉ
ተጠቃሚ እንዲሆን "በስሙም ንስሐና የኃጢአት ሥርየት" የሚሰብኩ ልዑ
ካንን መርጦ አስቀድሞ አዘጋጀ፡፡ በአሥራ ሁለቱም ነገደ እሥራኤል ምሳሌ
ከብዙ ሕዝብ መካከል አሥራ ሁለቱን ሐዋርያት መርጦ ሾመ (ራእይ.21፥14፤
ሉቃ.6፥12-16)፡፡ ለዚህም የሥራ ተባባሪ የሚሆኑ ሰባ ሁለት አርድእትን
መርጧል፡፡ ከዚያም በኋላ በታሪክ እንደምናውቀው ሠላሳ ስድስት ቅዱሳት አን
ስትን በመምረጥ በጠቅላላው የመቶ ሃያ ቤተሰብን መሥርቷል (ሉቃ.10፥1፤
የሐዋ.1፥15)፡፡ እንግዲህ እነዚህና ከነዚህም ጋር የሚተባበሩ ሁሉ ነበሩ
የእግዚአብሔር ቃልና የክርስቶስ ጸጋ መንገድ በመሆን እስከ ሞት ድረስ
ያገለገሉት፡፡ በተለይም ለሐዋርያነት ሥራ ለተመረጡት ሁሉ የክህነት
ሥልጣንን በመስጠት የእግዚአብሔር ጸጋ "ምሥጢር መጋቢዎች" አድርጓ
ቸዋል (ዮሐ.20፥21-23፤1ቆሮ.4፥1)፡፡ ቤተ ክርስቲያንም የተባለች በክርስቶስ
ራስነት በአሥራ ሁለቱ ሐዋርያት ማዕከልነት የተሰበሰበች ጉባኤ ናት፡፡
ክርስቶስም ቤተ ክርስቲያኑን የሠራው በቅዱስ ጴጥሮስና በሐዋርያት መሠረት
ላይ ነበር (ማቴ.16፥18፤18፥18፤ ኤፌ. 2፥20)፡፡ ስለዚህ የክርስቶስ የማዳኑ
ሥራና ጸጋ ለሰዎች ሊተላለፍ የሚችለው እርሱ ራሱ በደሙ በመሠረታት
ቤተ ክርስቲያኑ ብቻ ነው፡፡ እርሷም አንዲትና ሐዋርያዊት ናት፤ ሌላ ምትክ
የላትም፡፡ ስለዚህ ነው ከቤተ ክርስቲያን ውጭ መዳን የለም የሚባለው፡፡

እንግዲህ ከመጀመሪያው ወገን ማለት ከእግዚአብሔር ቀጥሎ የእርሱ
መሣሪያ በመሆን የሚያገለግሉት ሁለተኛ ወገን ብለን ከላይ የመደብናቸው
በመንፈስ ቅዱስ ጸጋ ተመርጠው ቤተ ክርስቲያንን ወይም ምእመናንን እን
ዲያገለግሉ በክርስቶስ ሥልጣን የተሰጣቸውን የመጀመሪያዎቹን ሐዋርያትን
ና አርድእትን ብቻ ማለታችን ሳይሆን በእነርሱ እግር የተተኩትን ትላንትናም
ዛሬም እስከ ዓለም ፍጻሜ ያሉትን ጳጳሳትንና ቀሳውስትን በአጠቃላይ ካህናተ
ወንጌልን ሁሉ የሚያጠቃልል ነው፡፡ ሦስተኛው ወገን ደግሞ ተገልጋዩ ክፍል
እንደሆነ ተገልጿል፡፡ ሁሉም ወገኖች ከክርስቶስ ከርእሳቸው (ከራሳቸው) ጋር
ተጠቃልለው አንድ በመሆን ቤተ ክርስቲያን ወይም የክርስቶስ አካልና የመን
ፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ ይባላሉ (ኤፌ.1፥22-23፤ 1ቆሮ.3፥16)፡፡

## መንፈስ ቅዱስና ቤተ ክርስቲያን



የተገለጠውና በይፋ የታወቀው በተግባርም የዋለው፡፡ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ
ሉ የተገለጠውና በይፋ የታወቀው በተግባርም የዋለው፡፡ ከዚያን ጊዜ ጀም
ቤተ ክርስቲያን የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ በመሆን የብሉይን ቤተ
መቅደስ በመተካት የምትሠራ ሆናለች፡፡ በመንፈስ ቅዱስ እየተመራች አሕዛብን
እያስተማረችና እያሳመነች በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቀች
የመዳንና የመንጻትን ማለት የኃጢአት ሥርየትንና የልጅነትን ጸጋ ታሰጣለች
(ማቴ.28፥19-20፤ ማር.16፥16፤ ዮሐ.1፥12) በብሉይ ቤተ መቅደስ ይፈጸም የ
በረውን መሥዋዕተ ኦሪት በመተካት ጌታ በጸሎተ ኀሙስ የመሠረተውን
መሥዋዕተ ወንጌል በራስዋ የሐዲስ ኪዳን ቤተ መቅደስ በመፈጸም በምሥጢረ
ሥጋዌ አምነው ማለት ክርስቶስ በሥጋ መምጣቱን አምነውና መስክረው
የጌታን ሥጋና ደም የተቀበሉትን ሁሉ የዘላለም ሕይወት ጸጋ እንዲያገኙ
ታደርጋለች (1ኛዮሐ.4፥2፤ ማቴ.26፥26፤ ዮሐ.6፥53)፡፡

ስለሆነም የክርስቶስን ጸጋ ለማደል ቤተ ክርስቲያን የመንፈስ ቅዱስ
መሣሪያ እንደሆነች እናምናለን፡፡ መንፈስ ቅዱስ ከቤተ ክርስቲያን ጋር በአንድ
ነት ይሠራል፤ ለምእመናንም የሚያስፈልገውን ውሳኔ በአንድነት ይወስናል፡፡
ስለዚህ ነው ሐዋርያት "እኛና መንፈስ ቅዱስ ፈቅደናል" በማለት ውሳኔአቸውን
ለአሕዛብ ወገን ለነበሩት ክርስቲያኖች በጽሑፍ የላኩት (የሐዋ.15፥23-29)፡፡
"እኛና መንፈስ ቅዱስ ፈቅደናል" የሚለው ኃይለ ቃል የሐዋርያት ጉባኤና
መንፈስ ቅዱስ በአንድነት ሆነው መወሰናቸውን ያመለክተናል፡፡ የሐዋርያት
ጉባኤ ማለት ደግሞ ቤተ ክርስቲያን ማለት ነው፡፡ ስለዚህ ነው መንፈስ ቅዱስና
ቤተ ክርስቲያን በዚሁ ምዕራፍ ሥር በአንድነት የቀረቡት፤ ቤተ ክርስቲያንና
መንፈስ ቅዱስ አይለያዩም፡፡ ስለ ጌታም የሚመሰክሩ እነዚሁ ሁለቱ ናቸው
(ዮሐ.15፥26-27)፡፡

የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች ቃሉን በማስተማርና ስለ ክርስቶስ
በመመስከር ምሥጢራትን በመፈጸም በመንፈስ ቅዱስ ኃይልና ረድኤት ልዩ
ልዩ ሀብተ ሥጋና ሀብተ ነፍስ ለምእመናን እንዲሰጣቸው ያደርጋሉ፡፡ እንግዲህ
በመንፈስ ቅዱስ የመዳናችንና የመቀደሳችን ምሥጢር ከቤተ ክርስቲያን
ምሥጢራት ጋር አብሮ የሚሄድ ነው፡፡ ክርስቲያናዊ ሕይወታችን ደግሞ
በምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን ላይ የተመሠረተ ስለሆነ ሁሉም በግብረ መንፈስ
ቅዱስ የተያያዙና የተገናዘቡ ናቸው፡፡ ስለዚህ ይህ ምዕራፍ በተለይም ይህ አን
ቀጽ ከክፍል ሁለትና ከክፍል ሦስት ጋር መሠረታዊ ግንኙነት አለው፡፡

እንግዲህ በክርስቶስ የመጣልንንና በመንፈስ ቅዱስ የተሰጠንን የመዳን
ጸጋ እንዳናጣው በአክብሮት፣ በትጋትና በጥንቃቄ ሆነን ለመዳናችን በርትተን
መሥራት አለብን እንጂ የተሰጠንን ጸጋ በቸልተኝነት ወይም በንቀት ዓይን
ማየት የለብንም፡፡ አለበለዚያ ከጸጋው መውደቅ ይመጣል፡፡ "የሙሴን ሕግ
የናቀ ሰው ሁለት ወይም ሦስት ቢመሰክሩበት ያለ ርኅራኄ ይሞታል፤ የእግዚአ
ብሔርን ልጅ የረገጠ ያንንም የተቀደሰበትን የኪዳኑን ደም እንደ ርኩስ ነገር
የቆጠረ የጸጋውንም መንፈስ ያከፋፋ እንዴት ይልቅ የሚብስ ቅጣት የሚገባው
ይመስላችኋል? . . . በሕያው እግዚአብሔር እጅ መውደቅ የሚያስፈራ ነው"
በማለት ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ የሥጋ ወገኖቹን ዕብራውያንን ያስጠነቅቃል
(ዕብ.10፥28-31)፡፡ ይኸው ሐዋርያ መዳናችንን በእንዴት አኳኋን መፈጸም እን
ዳለብን ሲመክረን፡ "በፍርሃትና በመንቀጥቀጥ የራሳችሁን መዳን ፈጽሙ፤ ስለ
...ማድረግንም በእናንተ የሚሠራ እግዚአብሔር ነውና"

www.ethiopianorthodox.org

በልባችን ስለፈሰሰ ተስፋ አያሳፍርም" ተብሎ እንደ ተጻፈ በልጁ ላመኑት ሁሉ በመንፈስ ቅዱስ የመዳን ተስፋቸውን አረጋግጦላቸዋል (ሮሜ.5፥5)።

በመንፈስ ቅዱስ በኩል በልቡናችን የፈሰሰው የእግዚአብሔር ፍቅር ነው በእምነት ለመዳናችንና ለመልካም ነገር ሁሉ፣ ለልዩ ልዩ የጸጋ ስጦታ ሁሉ መሠረት በመሆን፥ ለትክክለኛው ክርስቲያናዊ ሃይማኖትና ምግባር መመዘኛና ማስመስከሪያ መሆኑ የሚነገርለት። ምክንያቱም ፍቅር የሌለው "እግዚአብሔርን አያውቅም" ተብሏልና (1ኛዮሐ.4፥8)። እንግዲህ በዚህ የመንፈስ ቅዱስ ፍቅር ነው አንድ አማኝ ከእግዚአብሔርና ከሌሎች ጋር አንድነት የሚኖረው፤ መንፈስ ቅዱስ የኅብረትና የቅድስና መሠረት ነውና። ስለዚህ ነው ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ የመንፈስ ቅዱስ ሱታፌ (ኅብረት) ከሁላችሁ ጋር ይሁን የሚለው (2ኛቆሮ.13፥14)።

ይህ የመንፈስ ቅዱስ ሱታፌ ነው የመዳናችንንና የመቀደሳችንን ከኃጢአት የመንጻታችንንም እንዲሁም የፍቅራችንንና የአንድነታችንን፣ የደስታችንንና የሰላማችንን፣ የታማኝነታችንና የትዕግሥታችንን ውጤት ወይም ፍሬ ለክርስቲያናዊ ሕይወታችን ያስገኘልን። የዚህ ሁሉ ምንጩና ሥር መሠረቱ ከእግዚአብሔር ፍቅር ሆኖ በክርስቶስ የማዳን ሥራ በዕለተ ዓርብ በመስቀል ላይ ተፈጽሞ ለአንዴና ለዘላለም ለእኛ ለሰዎች ሁሉ የኃጢአት ማስተሥረያ የዘላለም ሕይወት ማግኛ በመሆን ተሰጥቶናል (1ዮሐ.4፥7-17)። ነገር ግን ድኅነት ጸጋው ለእያንዳንዱ ነፍስ የሚደርሰውና የሚታደለው በመንፈስ ቅዱስና በቤተ ክርስቲያን አማካኝነት መሆኑን ገልጸናል። ስለሆነም በክርስቶስ የተገኘው የመዳን ጸጋ አሰጣጥና አፈጻጸም የሚከናወነው በጸሎትና በቃሉ አገልግሎት ይልቁንም በምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን አማካኝነት በመንፈስ ቅዱስ ኃይልና ረድኤት ነው።

ቤተ ክርስቲያን እንደ እግዚአብሔር መጋቢ ሥራዋን ሁሉ በተሳካ ሁኔታ ለማከናወን የምትችለው ሁልጊዜ ከማይለያት ከአርያም በተሰጣት በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ነው (ሉቃ.24፥45-49፤ የሐዋ.1፥8)። ስለሆነም ቤተ ክርስቲያን የጸጋ መንፈስ ቅዱስ ማደሪያ የእግዚአብሔር ቤት ሆናለች። ስለ እርሷም ሐዋርያው ጳውሎስ ለሚወደው ልጁ ለጢሞቴዎስ ሲጽፍ "በእግዚአብሔር ማደሪያ ቤት መኖር እንዴት እንደሚገባ ታውቅ ዘንድ እጽፍልሃለሁ፤ ቤቱም የእውነት ዓምድና መሠረት፥የሕያው እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን ነው"ብሏል (1ኛጢሞ.3፥15)። እንግዲህ ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔር መንፈስ ማደሪያ የክርስቶስ አካል መሆኗን አምነን በዚህ አንቀጽ የተማርነውን ሁሉ መሠረት በማድረግ ከሚቀጥለው አንቀጸ ቤተ ክርስቲያን ጋር በማገናዘብ መመልከት ይኖርብናል።

## <u>አንቀጽ ፱</u>

### <u>"ከሁሉ በላይ በምትሆን፥ሐዋርያት በሰበሰቧት፥በአንዲት፥ቅድስት ቤተ ክርስቲያን እናምናለን።</u>



ነገሩን አለመጠበቅ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ እንደ ማፍረስ ይቆጠራል። የቤተ ክርስቲያን አባል ሳይሆኑ በብቸኝነትና በግላዊነት ጐዳና እየሄዱ ክርስቲያን ነኝ ማለት አይቻልም። ምክንያቱም እያንዳንዱ ሰው የክርስቶስ አባልነት፣ የመንፈስ ቅዱስ አንድነትን እንዲያገኝ በወንጌል ትምህርት ጥሪ ቀርቦለታል። ይህንን ጥሪ አክብሮ ወደ ቤተ ክርስቲያን መጥቶ ሲጠመቅ ያንጊዜ የክርስቶስ አካልና አባል ይሆናል፤ በመንፈስ ቅዱስም አዲስ ልደትን አግኝቶ ከማኅበረ ክርስቲያኑ ጋር ፍጹም አንድነት ይኖረዋል። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ሕፃን ልጅ ከአባትና ከእናቱ፥ ከወንድሞቹና ከእኅቶቹ መካከል አንድ አካል አንድ አምሳል ሆኖ እንደሚኖር እንዲሁም አንድ አማኝ በአባቱ በእግዚአብሔርና በእናቱ በቤተ ክርስቲያን እቅፍ ሆኖ በመንፈሳዊ ቤተሰቦቹ መካከል የመንፈስ ቅዱስ አንድነት ይኖረዋል።

እንግዲህ በግለኝነት መንፈስ ከእናቱ ከቤተ ክርስቲያን ተለይቶ ያለ ማኅበራዊና መንፈሳዊ ሱታፌ በብቸኝነት እየኖሩ የክርስቲያን ሃይማኖት ተከታይ ነኝ ማለት አይቻልም የተባለው የቤተ ክርስቲያንን ሕግና ሥርዓት ማፍረስ ብቻ ሳይሆን እምነትንም እንደ ማጉደል ስለ ሚቆጠር ነው። ምክንያቱም እንዲህ ዓይነቱ አማኝ ራሱን የክርስቶስ አካልና አባል አድርጎ አለመቀበሉን ያሳየናል። በክርስቶስ ብቻ አምኖ በግለኝነት መኖር በቂ አይደለም፤ የክርስቶስ አካል በሆነችው በቤተ ክርስቲያንም አምኖ አባል መሆን ሃይማኖታዊ ግዴታ ነው።

እንግዲህ ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስ አካል ናት፤ ራስዋም ክርስቶስ ነው (1ኛቆሮ.12፥27-31፤ ኤፌ.5፥23-33)። በቤተ ክርስቲያን ማመን ማለት በክርስቶስና አካሉ በሆነችው በቤተ ክርስቲያን ማመንን ያመለክታል። እውነተኛዋ ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስ አካል መሆኗን ስለምታምን በጌታ ሥጋና ደም ተመሥርታ ሁልጊዜ በምታቀርበው ምሥጢረ ቁርባን አንድነቷን ታጸናለች። እያንዳንዱም አባል ሥጋውና ደሙን በመቀበሉ የክርስቶስ አካልና አባል መሆኑን ይመሰክራል።

በቤተ ክርስቲያን እናምናለን ስንል ክርስቶስ በደሙ የዋጃትና የራሱም አካል ያደረጋት ስለሆነች ለዘላለም በጸጋው ቅድስት መሆኗንም ጭምር እንገልጻለን። ምንም እንኳ ኃጢአተኞች በውስጧ ቢኖሩ ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስ አካል እንደመሆንዋ መጠን ቅድስናዋን የሚያስቀር ነገር የለም። ምክንያቱም በእርሷ ዘንድ የሚገኘው የእግዚአብሔር ቃልና የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ አባሎችዋን በንስሐ እያደሰ ሁልጊዜ ስለሚቀድሳት ነው። ይህም ማለት አዳራው ቅዱስ ከሆነ ማኅደሩም የተቀደሰ ይሆናል ማለት ነው። ስለዚህ ንስሐ የማይገቡትን አንዳንድ አባሎቿን በመመልከት በቤተ ክርስቲያን ተስፋ መቁረጥ የለብንም። ይልቅስ የቤተ ክርስቲያን ራስ የሆነው ክርስቶስ የራሱን አካልና አባላት የሆኑትን በመንፈስ ቅዱስ ጸጋ እንደሚቀድሳቸው በማመን መጽናናት ይኖርብናል።

እውነተኛይቱን ቤተ ክርስቲያን በትክክል ለመረዳት ይህንን አንቀጽ [illegible] ለማገር እንሞክራለን። የመጀመሪያው ክፍል ስለ ቤተ [illegible] ሥሪት ይሆናል። ሁለተኛው፥እውነተኛይቱን ቤተ ክርስቲያን [illegible]

www.ethiopianorthodox.org

## ሀ) የቤተ ክርስቲያን አመሠራረትና ሥሪት

የቤተ ክርስቲያንን የአመሠራረት ታሪክና ምሳሌን ለማወቅ እንዲረዳን በመጀመሪያ “ቤተ ክርስቲያን” የሚለውን የጥንቱን ቃል ትርጉም እን መለከታለን፡፡ በጽርዕ ቋንቋ ኤክሌሲያ ማለት ቤተ ክርስቲያን ማለት ነው፡፡ ትርጓሜውም ለአንድ ዓላማና ሥራ የተመረጡና የተጠሩትን ማኅበር ወይም ጉባኤን ያመለክታል፡፡ በብሉይ ኪዳን፥ የቤተ እሥራኤል ጉባኤ ወይም ስብ ሰባቸው በዚሁ ቃል ይገለጻል፡፡ ቤተ እሥራኤል ለቤተ ክርስቲያን መቋቋም ታሪክና ምሳሌ ሆናለች፡፡ በሙሴ መሪነት እሥራኤል ከግብፅ ወጥተው አንድ ሕዝብ አንድ ማኅበር ሆነው በብሉይ ቃል ኪዳን ጸንተው እንደኖሩ እንዲሁም በክርስቶስ ከኃጢአትና ሞት ነፃ የወጡት ወገኖች ሁሉ ቤተ ክርስቲያን ተብለው አንድ ማኅበር ሆነው በመንፈስ ቅዱስ አንድነት በሐዲስ ቃል ኪዳን ጸንተው ይገኛሉ፡፡

እንግዲህ ቤተ ክርስቲያን ስንል የመጀመሪያው ትርጉሙ ያመኑትን ወገኖች ሁሉ በሰማይም በምድርም የሚገኙትን ማለት በአካለ ነፍስ ያሉትን ማኅበረ ቅዱሳንንና በአካለ ሥጋ የሚኖሩትን ማኅበረ ምእመናንን እንዲሁም ቅዱሳን መላእክትን ሁሉ የሚያጠቃልል ነው፡፡ እነዚህ ሁሉ የክርስቶስ አካል የሆኑባት የአንዲት ቅድስት ቤተ ክርስቲያን አባላት ናቸው፡፡ በሰማይ የምትገኘውና በምድር ያለችው ቤተ ክርስቲያን ብሎ በሁለት አቅጣጫ ለመመልከት ይቻላል፡፡ ነገር ግን በመንፈስ ቅዱስ ሱታፌ በማኅበራዊ አንድ ነታቸው ፈጽሞ አይነጣጠሉም፡፡ ምክንያቱም ሁለቱም የአንድ የክርስቶስ አካ ልና አባላት ናቸውና፡፡

ስለዚህ ቤተ ክርስቲያን ስንል እውነተኛው ትርጉሙ፡ ቤተ ክርስቲያን ስትቋቋም ጀምሮ የነበሩትን አባላት ይልቁንም በገድል በትሩፋት ቤተ ክርስቲያንን አገልግለው ከዚህ ዓለም በሞት የተለዩትን፡ አሁን በአጸደ ነፍስ ከክርስቶስ ጋር ያሉትን በቅድሚያ በማወቅ ላይ የተመሠረተ ነው፡፡ በምድር ያለችው ቤተ ክርስቲያንም እውነተኛውን አቋሟን የምታውቀው ከእነርሱ ጋር ባላት የጠነከረ ግንኙነት ይሆናል፡፡ የነርሱንም አርአያና ምሳሌ በመከተል ብርታትን ታገኛለች፡፡ መንፈሳዊ አንድነታቸውንም ዘወትር ለፈጣሪያቸው በኅብረት በሚያደርጉት ጸሎትና ምልጃ ያጠናክራሉ፡፡ ስለዚህም ሕያዋን ለሙታን፡ ሙታንም ለሕያዋን ይጸልያሉ (ራእይ.6፡10)፡፡

ሁለተኛው የቤተ ክርስቲያን ትርጉም የተቀደሰውን ቦታና ሕንፃ የሚያመለክት ነው፡፡ ይኸውም በኦሪት ድንኳን፥ በሰሎሞን ቤተ መቅደስ አ ምሳያ የተሠራው ሕንፃ ቤተ ክርስቲያን፥ እውነተኛው መሥዋዕት የሚፈጸምበት የሐዲስ ኪዳን ቤተ መቅደስን ያሳየናል፡፡

ቤተ ክርስቲያን ማለት የቃል በቃል ትርጉሙ የክርስቲያን ቤት ማለት ነው፡፡ ሆኖም ቤተ እሥራኤል ስንል ሕዝበ እሥራኤልን እንጂ የኦሪት ድን ኳንን ወይም ቤተ መቅደስን ወይም ምኩራብን ወይም ቤተ ጸሎትን እንደ ማያመለክት እንዲሁም ቤተ ክርስቲያን ባልን ጊዜ በክርስቶስ ክርስቲያን የተባሉትን አማኞች ሁሉ የሚገልጽ ነው፡፡ ይህም ከላይ የተጠቀሰውን የቤተ ክርስቲያንን የመጀመሪያውን ትርጉም ይይዛል፡፡

የሁለተኛው ትርጉም ግን የሚያመለክ[illegible]



(ዮሐ.2፡18-22)፡፡ እርሱም እንደ ሕያው ድንጋይ ነው፡፡ እኛም አባላቱ እንደ ሕያው ድንጋዮች በመንፈሳዊ ሕንፃ ውስጥ ተገንብተናል፡፡ ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ እንዳለው፡- “ እናንተ ደግሞ እንደ ሕያዋን ድንጋዮች ሆናችሁ፥ በኢየሱስ ክርስቶስ ለእግዚአብሔር ደስ የሚያሰኝ መንፈሳዊ መሥዋዕትን ታቀርቡ ዘንድ ቅዱሳን ካህናት እንድትሆኑ መንፈሳዊ ቤት ለመሆን ተሠሩ” (1ኛ ጴጥ.2፡4-5፤ ኤፌ.2፡20-22)፡፡

የሦስተኛው ትርጉም በአንደኛውና በሁለተኛው ላይ ተመሥርቶ የሚነገር ነው፡፡ “ሦስተኛውና የመጨረሻው ፍቺ” ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ እንደገለጹት “የክርስቲያኖች አንድነት የክርስቲያኖች ማኅበር ማለት ነው”፡፡ እነዚህም በአ ጥቢያ፥በብሔርና በሀገር ደረጃ የሚገኙት ማኅበረ ምእመናን፥ ሕዝበ ክርስቲያን ሁሉ በያሉበት ቤተ ክርስቲያን ተብለው የሚጠሩት ናቸው፡፡ ከላይ በአንደኛና በሁለተኛ ስለ ቤተ ክርስቲያን የተሰጠው ትርጉም እንደተጠበቀ ሆኖ በዘርና በጐሳ፥ በብሔርና በቋንቋ፥ በጊዜና በታ ተከፍለው የሚገኙት አ ማኞች ማለት ክርስቲያኖች ሁሉ ምንም በቋንቋም ሆነ በሌላም ሰው ሠራሽ ችግር መገናኘት ባይችሉም እያንዳንዱ በየወገኑ በየክፍሉ ቤተ ክርስቲያን ይባላል፡፡

“ቤተ ክርስቲያን ዘግብፅ፡ ቤተ ክርስቲያን ዘኢትዮጵያ የሚል ንባብ ቢገኝ በግብፅ የሚኖሩ የክርስቲያኖች ማኅበር፥ በኢትዮጵያ የሚኖሩ የክር ስቲያኖች ማኅበር ማለት ነው፡፡ ይኸውም በቅዱስ ጴጥሮስ አነጋገር ይታ ወቃል፤ ቅዱስ ጴጥሮስ በስደት ላሉ ክርስቲያኖች የግብፅን ክርስቲያኖች ሰላ ምታ ሲጽፍ “ትኤምኀክሙ ቤተ ክርስቲያን ቅድስት እንተ ውስተ ባቢሎን” ብሏል፡፡ ማኅበረ ክርስቲያን ዘግብፅ ማለት ነው”፡፡[64]

እንግዲህ የዚህ ሀገር ቤተ ክርስቲያን፡ የዚያ ሀገር ቤተ ክርስቲያን ብለን እንናገራለን፤ ብዛታቸውም ሲገለጽ አብያተ ክርስቲያናት ቢባሉም ሁሉም በክርስቶስ አንድ መንጋ ናቸው (ዮሐ.10፡16)፡፡ ስለዚህም ሁሉም የአንዲት ቤተ ክርስቲያን አባላት ናቸው፡፡ በዚህም ምክንያት ሁሉም ከላይ በገለጽነው በመጀመሪያው የቤተ ክርስቲያን ትርጉም ይጠቃለላሉ፡፡[65]

### ቤተ ክርስቲያን በምሳሌና በትንቢት

እንግዲህ የክርስቶስ አካል በሆነችው ቤተ ክርስቲያን ብናምንና በእርሷም እቅፍ ውስጥ ብንሰበሰብ ከጥፋት ሁሉ እንድናለን፡፡ ይህን የዘነት አንዳንዶች ግን በቤተ ክርስቲያንና በተቀደሰው ሥርዓቷ ባለ መተማመን ያለ መርከብ

---

[64] አባ ጎርጎርዮስ፤ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ በዓለም መድረክ፣ (ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፡ 1978 ዓ.ም.) ገጽ 10

[65] እንደ ግብፅ ቤተ ክርስቲያን ትምህርት፡- “ ቤተ ክርስቲያን የሚለው ቃል ሦስት ነገሮችን ያመለክታል ... (1) ቤተ ክርስቲያን እንደ ሕንፃ ... (ሮሜ 16፡5፤ 1ቆሮ.4፡17) ... (2) ቤተ ክርስቲያን እንደ ጉባኤ ምእመናን ... (የሐዋ.2፡47፤ 8፡1፤ 12፡5፤ 1ቆሮ.11፡18፤ ኤፌ.5፡25-26) ... (3) ቤተ ክርስቲያን እንደ አመራር /አስተዳደር/ ይህም ማለት የተቀደሱት ሥርዓታት (ክህነት/ቤተ ክህነት/ ) ... (ማቴ.18፡17-18)፡፡ እንግዲህ በጸሎተ ሃይማኖት ‘ቤተ ክርስቲያን’ የሚለው ቃል አማኞችና አመራራቸው ማለት ነው”፡፡ "The word ‘Church’ signifies three things . . . The Church as a building . . . (Rom.16:5; 1Cor.4:17) . . . The Church as congregation . . . (Acts 2:47; 8:1; 12:5; 1Cor. 11:18; Eph. 5:25-26) . . . The Church as leadership, that is the Holy Orders (Priesthood) . . . (Mat.18:17-18). So, in the Creed, the word Church means the believers and their leadership.'' H.H. Pope Shenouda III, THE CREED (Cairo, Dar El [illegible] 1990) [illegible]

www.ethiopianorthodox.org

በባሕር ላይ ለመሄድ የሚሞክሩና በዚያው የሰጠሙና የጠፉ ሰዎችን መስለዋል፡፡ ከቤተ ክርስቲያን ውጭ መዳን የለም፡፡ ምክንያቱም ክርስቶስ ሰውን ያዳነበት የጸጋው ምሥጢር በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት የሚሰጠው በቤተ ክርስቲያን ብቻ ስለሆነ ነው፡፡ ከኖኅ መርከብ ውጭ የዳነ ፍጡር የለም፡፡ መርከቧ እንድትሠራና እንድትዘጋጅ ያዘዘ እግዚአብሔር ነው (ዘፍ.8)፡፡ እርሷም የቤተ ክርስቲያን ምሳሌ ሆናለች (1ኛጴጥ.3፥20-22)፡፡ ቤተ ክርስቲያንንም አማኞች እንዲድኑባት ያዘጋጀ እግዚአብሔር ነው፡፡ እርሱ በክርስቶስ መሠረትነት በመንፈስ ቅዱስ አደራጅቶና ቀድሶ እውነተኛይቱን ቤተ ክርስቲያን ሠርቷታል፥ አቋቁሟታል፡፡ ስለዚህ በአንዲት ቅድስት ቤተ ክርስቲያን እናምናለን፡፡

ቤተ ክርስቲያን በኖኅ መርከብና በቤተ እሥራኤል በታሪክና ምሳሌ ከመታወቋም ሌላ ትንቢትም ተነግሮላታል፡፡ "በዘመኑም ፍጻሜ የእግዚአብሔር ቤት ተራራ በተራሮች ራስ ላይ ጸንቶ ይቆማል፥ ከኮረብቶቹም በላይ ከፍ ከፍ ይላል፥ አሕዛብም ሁሉ ወደ እርሱ ይሰበሰባሉ" በማለት ኢሳይያስ የተናገረው ስለ ቤተ እሥራኤል ሳይሆን ስለ ቤተ ክርስቲያን ነው፡፡ ምክንያቱም አሕዛብን ሁሉ የምትሰበስብ ቤተ ክርስቲያን ብቻ ናት፤ የአይሁድ ጉባኤ (ቤተ እሥራኤል) ግን አሕዛብን ስለማይቀበሉ ነው (ኢሳ.2፥2፤54፥2-3)፡፡

ነቢዩ ዳንኤልም የንጉሡን የናቡከደነፆርን ሕልም ሲተረጉም ስለማትፈርሰው መንግሥተ እግዚአብሔርና ስለ መሥራቿ ተናግሯል፡፡

"በእነዚያ ነገሥታት ዘመን የሰማይ አምላክ ለዘላለም የማይፈርስ መንግሥት ያስነሣል፤ ለሌላ ሕዝብም የማይሰጥ መንግሥት ይሆናል፤ እነዚያን መንግሥታት ሁሉ ትፈጫቸዋለች ታጠፋቸውማለች፥ ለዘላለምም ትቆማለች፡፡ ድንጋዩም እጅ ሳይነካው ከተራራ ተፈንቅሎ ብረቱንና ናሱን ሸክላውንና ብሩን ወርቁንም ሲፈጨው እንዳየህ፥ እንዲሁ ከዚህ በኋላ የሚሆነውን ታላቁ አምላክ ለንጉሡ አስታውቆታል፤ ሕልሙም እውነተኛ ፍቺውም የታመነ ነው" (ዳን.2፥44-45)፡፡

እጅ ሳይነካው ከተራራ ተፈንቅሎ የወረደው ድንጋይ ከአብ ወጥቶ ወደ ዓለም የመጣው ክርስቶስ ነው (ዮሐ.8፥42)፡፡ መንግሥተ ሰማያት ቀርባለችና ንስሐ ግቡ በወንጌል እመኑ እያለ ክርስቶስ በማስተማሩ ሲጠበቅ የነበረው የመሲሑ መንግሥት በዚያኑ ጊዜ እንደ ተጀመረ እንረዳለን (ማቴ.4፥17፤ ማር.1፥14-15)፡፡ ይህችም መንግሥት ቤተ ክርስቲያን ናት፡፡ ከንጉሡ ናቡከደነፆር ጀምሮ እስከ ሮም ቄሣሮች ከዚያም በኋላ የነበሩት መንግሥታት ሁሉ ፈርሰዋል፡፡ የማትፈርሰው መንግሥት ቤተ ክርስቲያን ግን ለዘላለም ትኖራለች፡፡ ምክንያቱም መሥራቿ "ኃያል አምላክ፥የዘላለም አባት፥ የሰላም መሪ . . ." ስለሆነ ነው (ኢሳ.9፥6)፡፡

የእርሷ ግዛት በሰው ልቡና ውስጥ ነው፡፡ ሥራዋም ዓላማዋም ኃጢአትን በማስወገድ ጽድቅን ለማስፋፋት ነው፡፡ አስተዳደሯም በግድ ሳይሆን በፍቅር፤ በጦርነት ሳይሆን በሰላም ነው፡፡ ይኸን ሁሉ ከመሥራቿ አግኝታዋለችና፡፡ እርሱ የቀ መዛሙርቱን ሰብስቦ፥ ሐዋርያትን ...



ጋይ ታላቅ ተራራ ሆነ ምድርንም ፈጽሞ ሞላ" (ዳን.2፥35) የተባለው በክርስቶስ የተመሰለው ድንጋይ ከፍ ከፍ እያለ ታላቅ ተራራ መሆኑ፥ አካሉ የሆነችው ቤተ ክርስቲያን እንደ ተራራ ከፍ ከፍ በማለት ማደጓንና በምድር ላይ ሁሉ መስፋፋቷን ያስረዳናል፡፡ ስለዚህ ክርስቶስንና ቤተ ክርስቲያንን ማለያየት አይቻልም፤ ምክንያቱም ከሁሉ በፊት የራሱ አካልና አባል አድርጎ መሥርቷታልና ነው፡፡

## *የቤተ ክርስቲያን ሥራና የሥልጣነ ክህነት መዋቅር*

እንግዲህ ቤተ ክርስቲያን እንደ ክርስቶስ አካልነቷ እርሱን ወክላ እንደ እርሱ ሆና እንድትኖርና እንድትሠራ ጌታ ፈቅዶላታል፡፡ ቤተ ክርስቲያንንም እንዲጠብቋት የሾማቸውን ሐዋርያትን የእርሱ እንደራሴዎች አድርጓቸዋል፡፡ ጌታም "የሚሰማችሁ እኔን ይሰማል፥ እናንተንም የጣለ እኔን ይጥላል፤ እኔንም የጣለ የላከኝን ይጥላል" በማለት ለእነርሱና ለተተኪዎቻቸው የእንደራሴነትን ሥልጣን ሰጥቷቸዋል (ሉቃ.10፥16)፡፡

ስለዚህም ክርስቶስ የራሱን ሥራና ሥልጣን ይዛ እንድትሠራ ለቤተ ክርስቲያኑ ሦስት ዐበይት ዓላማዎችና ሥራዎችን ሰጥቷታል፡፡ መጀመሪያ የእግዚአብሔርን ወንጌለ መንግሥት ለዓለም ሁሉ በመስበክ በክርስቶስ ስም እንዲያምኑና እንዲጠመቁ ለማድረግ (ማቴ.28፥19)፤ ሁለተኛ የሰዎችን ኃጢአት ለማስተሥረይና የጸጋ ምሥጢራትን ሁሉ ለምእመናን ለማዳረስ (ዮሐ.20፥22-23፤ ማቴ.16፥16-19፤ 18፥18፤ሉቃ.22፥19-20፤ 1ኛቆሮ.11፥23-26፤ ያዕ.5፥13-16)፤ ሦስተኛ ምእመናንን ለመጠበቅና ለማስተዳደር የሚሉት ናቸው (ዮሐ. 21፥15-17)፡፡ በተለይም መንጋውን በመጠበቅ ለነፍሳት አባትና እረኛ ለሆኑት ሁሉ ከፍተኛ የሥራ ኃላፊነት እንደሚጠብቃቸው ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ያስጠነቅቃል (የሐዋ.ሥራ 20፥28-30)፡፡

እንግዲህ ከላይ የተገለጸውን ዓላማና የሥራ ዓይነት ለመፈጸምና ለማስፈጸም ሠራተኞችንና ኃላፊዎችን መሠየም ያስፈልጋል፡፡ ስለዚህ ነው ጌታችን በመጀመሪያ ደረጃ ሐዋርያትን፣ በሁለተኛ ደረጃ አርድእትን መርጦ የሾማቸውና መመሪያ በመስጠት ሁለት ሁለት ሆነው በምድረ ፍልስጥኤም በማስተማር ሥራቸውን እንዲጀምሩ ያዘዛቸው (ማቴ.10፥1-42፤ ሉቃ.10፥1-20፤)፡፡ እርሱም ከተለያቸው ማለት ከዕርገቱ በኋላ ይህ ያዘዛቸው ሥራ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ እንዲቀጥል ለማድረግ ዘላቂ የሆነ የሥራና የአስተዳደር መዋቅር አዘጋጀላቸው፡፡

ከሁሉ አስቀድሞ ጌታ ወደዚህ ዓለም የመጣበት ተልእኮ ኃጢአተኞችን ለመጥራትና ኃጢአትን ለማስተሥረይ ስለሆነ እርሱም ካህን ሊቀ ካህናት በመሆኑ ቤተ ክርስቲያኑም በዚሁ የክህነት ሥልጣንና ሥራ ላይ ተመሥርታለች፡፡ ስለዚህ ነው የመጀመሪያው የትንሣኤ ዕለት ጌታችን ለሐዋርያት ተገልጾ ሥልጣነ ክህነትን የሰጣቸው (ዮሐ.20፥22)፡፡ ስለዚህም ነው "በስሙም ንስሐና የኃጢአት ሥርየት ከኢየሩሳሌም ጀምሮ በአሕዛብ ሁሉ ይሰበካል" ብሎ ያላቸው (ሉቃ.24፥47)፡፡ ሊቀ ካህናት ኢየሱስ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያኑን ... ኃጢአት ማስተሥረያ ሥልጣን ምልክት የሆነውን ...

www.ethiopianorthodox.org

እነርሱም ለተተኪዎቻቸው ለጳጳሳት አስተላልፈዋል:: ይኸም ሐዋርያዊ ትውፊት በአንብሮተ እድ ሐዋርያዊ መንበር ባላቸው ቤተ ክርስቲያን ይሠራበታል፡፡ የእውነተኛዋ ቤተ ክርስቲያን አመሠራረትና ሥሪት ታሪካዊ አመጣጥ ይህን ይመስላል::

ቤተ ክርስቲያን የክህነት መንግሥት ሆና በቅዱስ ጴጥሮስና በሌሎችም ሐዋርያትም ላይ በጠንካራ ዐለት ላይ ተሠርታለች:: የመንግሥተ ሰማያት መክፈቻዎች በእጇ ስለሆነ በእውነትም ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔር መንግሥት ናት:: " የገሃነም ደጆችም አይችሏትም" (ማቴ.16፥18)፤ የክፋት ኃይሎችም አይደፍሯትም:: እርሷ ኃጢአተኞችን በመጥራትና ለበደላቸው ይቅርታ በማስጠት ከፈጣሪያቸው ጋር እንዲታረቁና እንዲቀርቡ በማድረግ መልካም የእግዚአብሔር መንግሥት ዜጐች እንዲሆኑ ታበቃቸዋለች:: እንደዚህም በማድረጓ የእግዚአብሔር መንግሥት ሠራተኛ መሆኗን ታረጋግጣለች::

ማንም ማን ቢሆን ከነክፋቱና ከነበደሉ ወደ እግዚአብሔር ሊቀርብ አይችልም:: ስለዚህም እግዚአብሔር በታላቅ ፍቅሩ ሰዎችን ከራሱ ለማስታረቅ ስለፈለገ ልጁን ልኮ በክርስቶስ ጸጋ አማካኝነት የክህነት ሥልጣንና የኃጢአት ሥርየትን ለቤተ ክርስቲያን ሰጠ:: እንዲህም ማድረጉ ሰዎች ከኃጢአታቸው እየታጠቡ፥ ከበደላቸው እየነጹ ወደ እርሱ እንዲቀርቡና እንዲታረቁ ቸርና ርኅሩኅ አምላክ ለሰዎች ሁሉ ያዘጋጀው የምሕረት መንገድ ነው::

እንግዲህ ቤተ ክርስቲያን በመሥራቿ የተሰጣትን ከላይ የተገለጹትን ሦስቱን ዐበይት የሥራ ክፍሎች ታከናውናለች:: በክርስቶስ የተገኘውን የኃጢአት ይቅርታና እርቅ በስብከተ ወንጌል ታሰማለች:: እሷም በተሰጣት ሥልጣን ለበደለኞች በንስሐ አማካይነት ለኃጢአታቸው ይቅርታን እያሰጠች ከእግዚአብሔር ጋር ታስታርቃለች:: በእቅፏ የሚገኙ ልጆቿንም ትመክራለች፣ ትጠብቃለችም::

ይህንና የመሳሰለውን ሁሉ ለማከናወን የምትችለው ከሐዋርያት ጀምሮ ሲወርድ ሲዋረድ በመጣው ክህነታዊ የሥልጣን መዋቅሯ በመደራጀት ነው:: መዋቅሩም በሦስት ደረጃዎች ተቋቁሟል::

በመጀመሪያ ደረጃ ሙሉ የክህነት ሥልጣን ያላቸው የሐዋርያት ተተኪዎች ጳጳሳት (ኤጲስ ቆጶሳት) ናቸው:: እነርሱ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በመሆናቸው ሥልጣናቸውና ማዕረጋቸው ከሁሉም ይበልጣል:: ጉባኤያቸውም እንደ ሐዋርያት ጉባኤ በመንፈስ ቅዱስ የሚመራ ስለሆነ የተቀደሰ ጉባኤ ነው::

ከእነርሱ ቀጥሎ እንደ ጌታ አርድእት የሚቆጠሩ ቀሳውስት በሁለተኛ ደረጃ ይገኛሉ:: እነርሱ ሜሮን ከመባረክና ሥልጣነ ክህነት ከመስጠት በቀር እንደ ጳጳሳት ከፍ ያለ የክህነት ሥልጣን አላቸው::

በመጨረሻም ዲያቆናት በሦስተኛው የሥልጣን ደረጃ ይገኛሉ:: እነርሱ ለጳጳሳቱና ለቀሳውስቱ አገልግሎት ይ[illegible]



የቅድስና አኗኗርና በጎ ምግባር እንዲስፋፋ ያልተቆጠበ ጥረት ታደርጋለች:: ምእመናንም ለመንፈሳዊና ማኅበራዊ ተግባር መሳካት ካህናት ብቻ ሳይሆኑ የክርስቶስ አካል አባላት ስለሆኑ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደርጋሉ:: አማኞች ሁሉ የክርስቶስ አካል አባላት ስለሆኑ እያንዳንዱ የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስና የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ ነው:: ሰውነታችን የእግዚአብሔር እንጂ የእኛ አይደለም:: ምክንያቱም በከበረ ደሙ ተገዝተናልና:: ስለዚህም ከኃጢአት ሁሉ እንድንሸሽና በሰውነታችንም እግዚአብሔርን እንድናከብር ተጽፏል (1ኛቆሮ.6፥12-20):: ክፉውን ሁሉ ከመካከላችን እንድናስወግድ ታዘናል (1ኛቆሮ.5፥9-13)::

እንግዲህ ምእመናን ሁሉ ክፉውን በማስወገድ የቅድስናን ኑሮ በመኖርና በመሥራት፥ መልካም አርአያን በማሳየት፥ የፍቅርና የጽድቅን ሥራ በመሥራት፥ ችግረኞችን በመርዳት፥ ምጽዋትና ልዩ ልዩ አስተዋጽኦ በማድረግ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ጉልቶ የሚታይ ኃላፊነት አላቸው:: ይልቁንም በክርስቶስ ለቤተ ክርስቲያን የተሰጠውን ሥልጣነ ክህነት አክብረው እንዲያስከብሩ፥ ኃጢአትን በማራቅ፥ ጠብቀው እንዲያስጠብቁ ከፍተኛ ኃላፊነት ተጥሎባቸዋል:: የርሱንም ክህነት በመጠበቅና በማስጠበቅ፥ የክርስቶስን ቅድስና በመከተል፥ ምእመናን ሁሉ ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ በጽድቅና በፍቅር ሥራ ላይ የተሰማሩትን ምእመናን ሁሉ ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ " የተመረጠ ትውልድ፥ የንጉሥ ካህናት፥ ቅዱስ ሕዝብ፥ ለርስቱ የተለየ ወገን ናችሁ፤"ይላቸዋል (1ኛ ጴጥ.2፥9)::

"የንጉሥ ካህናት" የሚለውን ይዘው አንዳንድ ወገኖች ምእመናንም ሥልጣነ ክህነት ሊኖራቸው ይገባል በማለት ይናገራሉ:: እንዲህማ እንዳይባል በብሉይ ኪዳን የነበሩ ሕዝበ እሥራኤል ሁሉ "የካህናት መንግሥት የተቀደሰም ሕዝብ" ተብለው ይጠራሉ (ዘፀአ.19፥6):: ይህም ማለት በቤተ መቅደስ ገብተው ካህናተ ኦሪት የሚሠሩትን ሥራ ይሠራሉ ማለት እንዳልሆነ ግልጽ ነው:: በሐዲስ ኪዳንም ጌታ ሁሉን ሐዋርያት ሁሉንም አርድእት አድርጎ አልሾማቸውም:: ይህም ማለት ያልተሾሙት የክርስቶስ አካል አይደሉም ማለት አይደለም:: በክርስቶስ አምነው የተጠመቁ ምእመናን ሁሉ የክርስቶስ አካልና አባላት ናቸው:: እነርሱን የሚጠብቁ እነርሱን የሚያገለግሉትን ከመካከላቸው አንዳንዶቹን መርጦ በቅደም ተከተልና በየደረጃቸው ሾሞላቸዋል::

ስለዚህም ጉዳይ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እንደሚከተለው ጽፏል:: "እናንተም የክርስቶስ አካል ናችሁ እያንዳንዳችሁም ብልቶች ናችሁ:: እግዚአብሔርም በቤተ ክርስቲያን አንዳንዶቹን፥ አስቀድሞ ሐዋርያትን፥ ሁለተኛም ነቢያትን፥ ሦስተኛም አስተማሪዎችን፥ ቀጥሎም ተአምራት ማድረግን፥ ቀጥሎም የመፈወስን ስጦታ፥ ርዳታን አገዛዝንም፥ የልዩ ልዩ ዓይነት ልሳኖችንም አድርጓል" (1ቆሮ.12፥27-28)::

በዚህ ጥቅስ ላይ እንደምንመለከተው ከአንድ እስከ ሦስት በየደረጃው በቅደም ተከተል የተገለጹት ተመርጠው የተሾሙትን የቤተ ክርስቲያን መሪዎችንና ረዳቶቻቸውን ያሳየናል:: ከዚያ ቀጥሎ የተዘረዘሩት ግን ልዩ ልዩ [illegible] ይገልጹልናል:: ይህም የመጀመሪያዋ የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን [illegible] ይዘታና የአስተዳደር ሥሪት እንዴት እንደነበረ

www.ethiopianorthodox.org

እንግዲህ የቤተ ክርስቲያን ሐዋርያዊ ሥሪት እንዲህ ከሆነ አንዳንድ ተቃዋሚዎች ሥልጣነ ክህነት ለሁሉም መሰጠት ይኖርበታል የሚሉት ፈጽሞ ስሕተት እንደሆነ ማወቅ ይኖርብናል፡፡ ስለዚህ ነው ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ "ሁሉ ሐዋርያት ናቸውን? ሁሉስ ነቢያት ናቸውን? ሁሉስ አስተማሪዎች ናቸውን?" ያለው (1ኛቆሮ.12፥29)፡፡ ይልቅስ እውነትንና ፍቅርን በመከተል እንደየ ስጦታችንና ችሎታችን ቤተ ክርስቲያንን እያገለገልን እርስ በእርሳችን እየተሳሰብን አንዱ የሌላውን ሸክም በመሸከም እየተቻቻልን ብንረዳዳ የክርስቶስ አካልና አባላት መሆናችንን በተግባር ለመመስከር እንችላለን፡፡ ይህንን ሁሉ ለማድረግ የምንችለው በመንፈስ ቅዱስ ረድኤት ስለሆነ በእውነትና በመንፈስ ሆነን መጸለይ ይኖርብናል፡፡

## *የመጀመሪያዋን ቤተ ክርስቲያን አርአያ ስለመከተል*

በክርስቶስ ደም የተመሠረተችው ቤተ ክርስቲያን ዓላማዋና ተግባሯን ለመፈጸም የቻለችው የመንፈስ ቅዱስን ኃይል ካገኘች ጊዜ ጀምሮ ነበር፡፡ በበዓለ ኀምሳ መንፈስ ቅዱስ በሐዋርያት ላይ ሲወርድ ቤተ ክርስቲያን በመንፈስ ተጠምቃ በመንፈስ ተወለደች፡፡ በአደባባይ በይፋ ተገለጠች፡፡ የምሥራቿንም ወንጌል ሰበከች፥ ስለ ትንሣኤውም መሰከረች፡፡ የክርስቶስ አካልም መሆኗ በግልጽ ታወቀ፡፡ በዚያም ዕለት በሺህ የሚቆጠሩ ሰዎችን የክርስቶስ አካልና አባላት እንዲሆኑ አደረገች (የሐዋ.ሥራ2፥1-41)፡፡ እንግዲህ በክርስቶስ የተመሠረተች ቤተ ክርስቲያን በመንፈስ ቅዱስ ጸንታ ተቋቋመች፥ ታነጸች፥ ተደራጀች፥ ኃይልንም አግኝታ ሥራዋንና አገልግሎቷን እስከ ምድር ዳርቻ አስፋፋች የምንለው የታሪክ ምስክርነትን ይዘን ነው፡፡

የታሪካችን ሁሉ መጀመሪያው ምንጩ ራሱ ክርስቶስ ሲሆን፥ እርሱ ደግሞ ሥራውን እንዲቀጥሉለት ከብዙዎች መካከል መርጦ ያዘጋጃቸው አንድ መቶ ሃያ ቤተሰብ ነበሩ፡፡ እነርሱም አሥራ ሁለቱ ሐዋርያት፥ ሰባ ሁለት አርድእትና ሠላሣ ስድስቱ ቅዱሳት አንስት እንደነበሩ በአንቀጽ ፳ (ሐ) ገልጸናል፡፡ የጌታ እናትም ከመካከላቸው ነበረች (የሐዋ.1፥13-15)፡፡

በእነዚህ ላይ ነበር መንፈስ ቅዱስ በእሳት ልሣን አምሳያ በእያንዳንዳቸው ላይ የወረደው፡፡ እነዚህ በእውነት የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ የእግዚአብሔር ቤት ናቸው፡፡ "ቤቱም" ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እንዳለው " የእውነት ዓምድና መሠረት፥ የሕያው እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን ነው" (1ኛጢሞ.3፥15)፡፡

እንግዲህ ይህ የመቶ ሃያው ቤተሰብ ከጌታ እናት ጋር ሆኖ የምናየው የመጀመሪያዋ የቤተ ክርስቲያን እውነተኛ ገጽታ ነው፡፡ ይህ ቤተሰብ ከእውነተኛ እናቱ ጋር እንደነበረ እናስተውል፡፡ የጌታ እናት የምሥጢረ ሥጋዌ ምልክት ሆና በቤተ ክርስቲያን ተገኝታለች፡፡ መስቀል፥ "ትእምርተ አድኅኖ" ማለት የመዳን ምልክት እንደሆነ እንደዚሁም የጌታ እናት "ትእምርተ ሥጋዌ" ማለት የምሥጢረ ሥጋዌ እውነተኛ ምልክት ናት፡፡ ነቢዩ ኢሳይያስ " ጌታ ራሱ ምልክት ይሰጣችኋል" ያለው የእርሷን በድንግልና መውለድ ነው (ኢሳ. 7፥13-14)፡፡ ስለዚህ ከእናቱና ከመንፈስ ቅዱስ በቀር ይህንን ምሥጢረ ልደት ማንም እንደ እርሷ አድርጐ ሊመሰክር ...



ምስክር ሆና በመካከላቸው ተገኝታለች፡፡ እኛም የመጀመሪያዋን ቤተ ክርስቲያን አርአያ በመከተል በመንፈስ በመካከላችን እንደ እናትና እንደ ምስክር እንዳለች በማመን " እንተ ይእቲ ስምዕየ ማርያም ጽዮን ለዓለመ ዓለም" በማለት በጸሎታችን እናስባታለን፡፡ ይህችም የዘላለም መጠጊያ እናቴ ምስክሬ ማርያም ናት እንላለን፡፡

ከዚህም ሌላ የቤተ ክርስቲያን መሥራች ክርስቶስ በመስቀል ላይ ሆኖ ሳለ በአጠገቡ ሆና የልጇ ደም ሲፈስስና ያን ሁሉ መከራና ሕማማት ሲቀበል እያየች ከልብ የማይወጣ እጅግ የከፋ መራራ ኀዘን ስላደረባት የልጇ ሕማማተ መስቀል ተካፋይ ሆናለች፡፡ ስለዚህ ነው ነቢዩ ስምዖን የወለደችውን ልጇን ከቤተ መቅደስ በአርባኛው ቀን ያቀረበችው ዕለት "በአንቺም ደግሞ በነፍስሽ ሰይፍ ያልፋል" ብሎ ያላት (ሉቃ.2፥35)፡፡ ይህም በአንድ ልጇ የደረሰው ሕማምና ሞት እንደ ሰይፍ የሚያሰቃይና የሚያስለቅስ የልብ ኀዘንና መከራ እንደሆነ የሚያመለክት ነው፡፡ በስምዖን ትንቢት መሠረት መከራው በልጇ ብቻ ሳይሆን "በአንቺም ደግሞ" እንደዚሁ የሕማሙና የኀዘኑ ጽዋ ይደርሳል ማለት እንደሆነ እንረዳለን፡፡

ስለዚህ በጌታ ሕማምና ሞት ስለተመሠረተችው ቤተ ክርስቲያን ስናወሳ፥ የጌታ እናትንም መራራ ኀዘንና ልቅሶ አብረን እናስባለን፡፡ በእርግጥ የጌታ እናት የቤተ ክርስቲያንም እናት ናት፡፡ ምክንያቱም በእግረ መስቀሉ ሥር ለነበረው ሐዋርያ እናት እንድትሆነው ጌታ የሰጠው በነገረ መስቀሉ ለምናምን ለሁላችንም እናት እንድትሆነን ነው (ዮሐ.19፥26-27)፡፡ በመዝሙረ ዳዊት እንደ ተጻፈው "ሰው እናታችን ጽዮን ይላል፥ በውስጧም ሰው ተወለደ፤ እርሱ ራሱም ልዑል መሠረታት"ተብሏልና (መዝ.86፥5)፡፡ ሰው ሁሉ አብርሃምን በእምነት አባታችን ከሚሉት በበለጠ አኳኋን ሰው ሁሉ የጌታን እናት በክርስቶስ ጸጋ እናታችን ይሏታል፡፡ ስለሆነም እመቤታችን እመ ብዙኀን ትባላለች፡፡ እንግዲህ የመጀመሪያይቱ የቤተ ክርስቲያን አመሠራረት ከጌታ እናት ጋር እንደሆነ ግልጽ ነው፡፡ ስለዚህም እውነተኛይቱ ቤተ ክርስቲያን ዛሬም ከጌታ እናት ጋር ከሐዋርያት ጋር ከአርድእት ጋር ከሌሎችም ቅዱሳን ጋር እንጂ ብቻዋን እንዳልሆነች ሁልጊዜ በምታቀርበው ትምህርት፥ ጸሎትና ምልጃ እያረጋገጠች በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ሥራዋን ታከናውናለች፡፡

ምእመናኑዋንም የእነርሱን አርአያ እንዲከተሉ ትመክራለች፡፡ ይህንንም ለምእመናኑ ለማስረዳት የእመቤታችን፥የሐዋርያት፥ የጻድቃን፥ የሰማዕታትና የሌሎችም ቅዱሳን ሥዕሎች በቤተ ክርስቲያን ይገኛሉ፡፡ በእነርሱም አማካይነት የሚመሰገነውን እግዚአብሔርን በዓይን ለማያዩቷን ቤተ ክርስቲያን፥ በመላእክት የሚመሰገነውን እግዚአብሔርን በዓይነ ልቡናችን ለማየት ይረዱናል፡፡ ስለዚህ የተቀደሱ ሥዕሎችን ምእመናን በአክብሮትና በመንፈሳዊነት በመመልከት ከፍተኛ መንፈሳዊ ጥቅም አግኝተውበታል፡፡ በቃልና በሥዕል በመማር፥ ምእመናን ስለመጀመሪያይቱ ቤተ ክርስቲያን ማወቅ ብቻ ሳይሆን እነርሱን ለመምሰልና እንደነርሱም ሠርተው ወደ ሰማያዊ ሀገራቸው ለመግባት ልቡናቸው ይነሣሣል፡፡ ቤተ ክርስቲያንም እንደ መንፈሳዊ ሙሽሪት ሆና በሰማይ ያለውን መሥራቿን ለማየትና ፍቅሩንም ለማግኘት ትናፍቃለች (ራእይ.21፥9፤ 22፥17)፡፡

... ቤተ ክርስቲያን ...

www.ethiopianorthodox.org

ዲት" ፡ "ቅድስት"፡ "ከሁሉ በላይ በምትሆን" (ወይም ኵላዊት) እና "ሐዋርያዊት" የተባሉት ናቸው፡፡ እነርሱንም እንደሚከተለው በአጭሩ እን ገልጻቸዋለን፡፡

## ቤተ ክርስቲያን አንዲት ስለ መሆኗ

በመጀመሪያ "አንዲት" የሚለው ቅጽል ለቤተ ክርስቲያን መሠረታዊ መለያዋ ነው፡፡ ምክንያቱም ጌታችን አንዲት ቤተ ክርስቲያን እን ሌላ አልመሠረተም፡፡ እርሷንም በደሙ ዋጅቶ በመመሥረት የራሱ አካል አ ዳደረጋት ከላይ ተመልክተናል፡፡ እንግዲህ ክርስቶስ አንድ አካል አለው እን ሁለት አካላት የሉትም፡፡ አንዷን ቤተ ክርስቲያኑን ከምሥራቅ ሌላውን ከም ራብ ያቋቋመ አይደለም፡፡ እንዲያውም ጌታችን ከምሥራቅም ከምዕራብም ከ ሰሜንም ከደቡብም ያሉትን በጐቹን ሰብስቦ ሁሉንም አንድ መንጋ አንድ እረ እንዲሆኑ ለማድረግ አንዲት ቤተ ክርስቲያንን ብቻ መሥርቷል (ማቴ.8፥11 ዮሐ.10፥16፤ ሉቃ.13፥29)፡፡

ስለዚህም ቤተ ክርስቲያን ቅርንጫፎቹዋ ብዙ ቢሆኑም በቦታና በጊዜም ቢራራቁም በብሔርና በቋንቋም ቢለያዩ ከአንድ ወይን ግንድ እንደ ወጡ ቅርንጫፎች ይቆጠራሉ (ዮሐ.15፥1-11)፡፡ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ "በአንድ ተስፋ እንደተጠራችሁ አንድ አካልና አንድ መንፈስ አለ፤ አንድ ጌታ አንድ ሃይማኖት አንዲት ጥምቀት፤" ሲል አንዲት ቤተ ክርስቲያን ብቻ እንዳለች ያመለክታል(ኤፌ.4፥4-6)፡፡ ምክንያቱም በጥቅሱ ላይ "አንድ አካል" የሚለው ቤተ ክርስቲያንን ነው፡፡ በአንድ ክርስቶስ የተጠመቅን የአንድ ክርስቶስን ሥጋና ደም የተቀበልን ሁሉ "ከክርስቶስ ሥጋ ጋር ኅብረት" አለን፡፡ ስለዚህም አንድ የክርስቶስ አካል እንሆናለን፡፡ ምክንያቱም ሐዋርያው እንደጻፈው " እኛ ብዙዎች ስንሆን አንድ ሥጋ ነን፤ ሁላችን ያን አንዱን እንጀራ እንካፈላለን ና" (1ቆሮ.10፥16-17)፡፡ እንግዲህ ሁላችንም አንድ ሥጋ ከሆንን አንዲት ቤተ ሰብ ነን፤ አንዲት ቤተ ክርስቲያንም ነን ማለት ነው፡፡

## ቤተ ክርስቲያን ቅድስት ስለ መሆኗ

የቤተ ክርስቲያን ሁለተኛው መለያዋ "ቅድስት" የሚለው ቃል ነው፡፡ ቤተ ክርስቲያን ስትመሠረት በጌታ ደም የነጻች ስለሆነ በእውነት ቅድስት ናት፡፡ የቅድስና ባለቤት መንፈስ ቅዱስ ባደረባት ጊዜ ፈጽሞ ቀድሷ ታል፡፡ የቅድስናና የጸጋው ሁሉ መዝገብ አድርጓታል፡፡ የጸጋውንም ምሥጢር በማደል አባላቷን ሁሉ ከኃጢአት የተፈቱ ንጹሐን ታደርጋቸዋለች፡፡ ምንም አን ድ አንድ አባላቷ በኃጢአት ቢሰናከሉም እርሷ ለዘላለም ቅድስት ናት፤ ምክን ያቱም የመሥራቿ የክርስቶስ የቅድስና ጸጋ ስለማይለያት ነው፡፡ ይህም ጸጋ ለቤተ ክርስቲያን የተሰጣት የኃጢአት ሥርየት ጸጋ ነው፡፡ ቤተ ክርስቲያን በሥልጣነ ክህነት ሥራ የተቋቋመች ስለሆነ የተሰናከሉ አባላቷን በንስሐ ጉዳና መልሳ፥ የኃጢአት ይቅርታ አሰጥታ፥ የቅድስናን ጸጋ በክርስቶስ ታጐናጽፋቸዋለች፡፡ ራሷ ተቀድሳ ሌሎችንም የምታነጻና የምትቀድስ፥ ዓላማና ሥራዋም በቅድስና ተልእኮ ላይ የተመሠረተ ...

www.ethiopianorthodox.org



ሚስቶቻችሁን ውደዱ፤ በውኃ መታጠብና ከቃሉ ጋር አንጽቶ እንዲቀድሳት ስለ እርስዋ ራሱን አሳልፎ ሰጠ፤ እድፈት ወይም የፊት መጨማደድ ወይም እንዲህ ያለ ነገር ሳይሆንባት ቅድስትና አለ ነውር ትሆን ዘንድ ክብርት የሆ ነችን ቤተ ክርስቲያን ለራሱ እንዲያቀርብ ፈለገ" (ኤፌ.5፥25-27)፡፡ እንግዲህ በሙሽሪት የምትመሰል ቤተ ክርስቲያኑን ክርስቶስ በመንፈስ ቅዱስ ጸጋ ለዘላለም ቅድስት አድርጐ ይጠብቃታል (ራእይ.21፥9)፡፡

## ቤተ ክርስቲያን በሁሉ የምትገኝ ኵላዊት ስለ መሆኗ

ሦስተኛው የቤተ ክርስቲያን መታወቂያ "ከሁሉ በላይ በምትሆን" ወይም "ኵላዊት" የሚለው ቃል ነው፡፡ ይህ የሚያመለክተን ቤተ ክርስቲያን በሁሉም ቦታ ማለት በየአጥቢያው በየብሔሩ በየሀገሩ የምትገኝ ዓለም አቀ ፋዊት መሆኗን ነው፡፡ ጌታ ሐዋርያትን ከኢየሩሳሌም ጀምረው እስከ ዓለም ዳርቻ ወንጌልን እንዲሰብኩ ባዘዛቸው ጊዜ የቤተ ክርስቲያን ዓለም አቀፋዊነት ታወቀ (የሐዋ.ሥራ1፥8፤ ማቴ.28፥19፤ ሚል.1፥11፤ ማር.16፥8)፡፡ ከዚያ በፊት የነበረችው የእሥራኤል ሃይማኖት በዘርና በጐሣ በቦታም የተወሰነች ነበረች፡፡ በክርስቶስ የተገኘች የወንጌል ሃይማኖት ግን ለዓለም ሁሉ ተሰበ ከች፡፡ ቤተ ክርስቲያንም የሁሉም ሆነች (ቆላስ.3፥11)፡፡ ይህ ብቻ አይደለም፡፡ ቤተ ክርስቲያን በቦታ ብቻ ሳይሆን በጊዜም አትወሰንም፡፡ ከሐዋርያት ጀም ሮ ከዚያም በፊት በክርስቶስ ተስፋ የነበሩትን ሁሉ ይዞ ወደፊትም የሚመጡትን ሁሉ የምታጠቃልል ስለሆነች ቤተ ክርስቲያን በእውነት ኵላዊት ሁሉን አቀፍ ትባላለች፡፡ ከላይ በቤተ ክርስቲያን ትርጉም ላይ እንደተመለከት ነው ቤተ ክርስቲያን በምድር ብቻ ያለችው ሳትሆን በሰማያዊ ስፍራ የምትገኘውን የክርስቶስን ቤተሰቦች ያጠቃልላል፡፡ ስለዚህ የቤተ ክርስቲያን ኵላዊነት በሰማይም በምድርም፥ ጥንትም ዛሬም ወደ ፊትም ያሉትንና የሚመጡትን ሁሉ ያካትታል፡፡

እንግዲህ ቤተ ክርስቲያን ከመሥራቿ ጋር በሰማይ በአፀደ ነፍስ ያሉትንና በምድርም በአካለ ሥጋ ያሉትን ሁሉ አንድነት በክርስቶስ ፊት እን ደ ተሰበሰቡ አድርጋ ትመለከታቸዋለች፡፡ ስለዚህም ቤተ ክርስቲያን በሞት የተለያዩትን በቦታና በጊዜ የተራራቁትን በአንድ ቦታና በአንድ ጊዜ ተቀራርበው ሊገናኙ የሚችሉት በመንፈስ ቅዱስ ጸጋ ነው፡፡ ይህም ጸጋ ለቤተ ክርስቲያን ስለ ተሰጠ በአንድ መንፈስ የተጠመቁ ሁሉ በዚሁ መንፈስ ሊገናኙ ይችላሉ፡፡ የአንድነትና የኵላዊነት ጸጋ ለቤተ ክርስቲያን የተሰጠው ለዚህ ነው፡፡ በአንዲትና ኵላዊት ቤተ ክርስቲያን እናምናለን ስንል ይህንን ሁሉ በማሰብ ነው፡፡

ቤተ ክርስቲያንን በሚታየው በምድራዊ ድርጅትዋ ብቻ የምናውቃት ከሆነ ተሳስተናል፡፡ የአንድ ሰውን እግሩን ብቻ አይቶ ራሱን እን ዳለማየት ይቆጠራል፡፡ የቤተ ክርስቲያን ራሷ በሰማይ ይኖራል፡፡ ስለዚ ህም አማኞቿ ሁሉ ማለት በአፀደ ነፍስ ያሉት በሰማያዊ ስፍራ ተሰብስበ ዋል፡፡ በሥጋም ያሉት በልባቸውና በመንፈሳቸው ከሚወዱት ጌታ ጋር በሰ ... ላይ በመጻተኝነት (በእንግድነት) እና በስደት ... በሥጋም ... ቢሆኑም በጌታ ተስፋ ደስ ይላቸዋል፥

www.ethiopianorthodox.org

ቤተ ክርስቲያን ኵላዊት ስለሆነች ተልዕኮዋና አገልግሎቷ ለሁሉም ወገኖች በሁሉም ቋንቋ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ በሁሉም አገር ያሉት አብያተ ክርስቲያናትና አገልግሎታቸው የአንድ የክርስቶስ ስለሆነ እንደ ተበታተኑና እንደ ተለያዩ ነገሮች አይቆጠሩም፡፡ ምክንያቱም በሰማይም በምድርም የሚገኙት ሁሉ በአንድ የክርስቶስ አባልነታቸው በመንፈስ ቅዱስ ሱታፌ በሥራና በጸሎት ይገናኛሉ፡፡ ስለዚህም ኵላዊነትና አንድነት የተገናዘቡ የማይለያዩ የቤተ ክርስቲያን መታወቂያዎች ናቸው፡፡

## ቤተ ክርስቲያን ሐዋርያዊት ናት

የእውነተኛዋ ቤተ ክርስቲያን አራተኛው መታወቂያ "ሐዋርያዊት" መሆኗን ይገልጻል፡፡ በመጀመሪያ ቤተ ክርስቲያን የተመሠረተችው የተሠራችው፥ የመሥራቿን ማንነት በሚያውቁና በሚያምኑ፡ በዓይን ያዩ፡ በጆሮ የሰሙ፡ በእጅ የዳሰሱ፥ የቃሉ መልእክተኞች በነበሩ፡ ትንሣኤውን በመስከሩ በሐዋርያት ላይ ነው፡፡ ጌታ ሐዋርያትን በትምህርት በተአምራት አዘጋጅቶ የቤተ ክርስቲያንን ሥራና ኃላፊነት አስረክቧቸዋል፡፡ እናንተን የሰማ እኔን ይሰማል በማለት በቤተ ክርስቲያን ላይ ሙሉ ሥልጣንን ሰጥቷቸዋል (ሉቃ.10፥16)፡፡ የእርሱ የሆነውን፥ የነቢይነትን፥ የክህነትንና የንጉሥነትን ይህም ማለት የትምህርትን፥ የሥርየተ ኃጢአትን፡ የጥበቃና የአስተዳደር ሥራና ሥልጣን ለእነርሱ አውርሷቸዋል (ማር.16፡15-16፤ዮሐ.20፥22-23፤ 21፥15-17)፡፡

ስለዚህም የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን በእነርሱ ተመሥርታለች ብለን እናምናለን፡፡ ክርስቶስ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ መሆኑን በመሰከረው በቅዱስ ጴጥሮስ ላይ ጌታ፥ ቤተ ክርስቲያኑን እንደሠራ፥ የመንግሥተ ሰማያትን መክፈቻዎችም እንደሰጠው ተጽፏል (ማቴ.16፥16-19)፡፡ ስለዚህ የቤተ ክርስቲያን ምሥረታ በቅዱስ ጴጥሮስና በሐዋርያት ላይ እንደነበረ ይህ ግልጽ ማስረጃ ነው፡፡

እንግዲህ ሐዋርያዊነት የእውነተኛይቱ ቤተ ክርስቲያን ዓርማ ምልክት ሆኖ ይኖራል፡፡ ስለዚህ ነው ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ የኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን ምእመናን "እንግዶች" ማለት ባይተዋር ሳይሆኑ በሐዋርያት መሠረት የታነጹ የክርስቶስ ቤተሰቦች መሆናቸውን ያስታወቃቸው፡፡ "እንግዲያስ ከእንግዲህ ወዲህ ከቅዱሳን ጋር ባላገሮችና የእግዚአብሔር ቤተሰብዎች ናችሁ እንጂ እንግዶችና መጻተኞች አይደላችሁም፡፡ በሐዋርያትና በነቢያት መሠረት ላይ ታንጻችኋል፥ የማዕዘኑም ራስ ድንጋይ ክርስቶስ ኢየሱስ ነው፤" (ኤፌ. 2፥19-20) በማለት በግልጽ አስረድቷቸዋል፡፡

እንግዲህ ቤተ ክርስቲያንን ከሐዋርያት በስተቀር ሌሎች ሰዎች እንደ ዳልመሠረቷት በታሪክ የተረጋገጠ ነው፡፡ ታዲያ ለምንድር ነው ለቤተ ክርስቲያን "ሐዋርያዊት" በሚለው ምልክትና ዓርማ እንድትታወቅ ያስፈለገበት የሚል ጠያቂ ቢኖር የእውነተኛዋን ቤተ [illegible] በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ



በሐዋርያት ትምህርት በቅዱሳት መጻሕፍት ቃል ላይ በተመሠረተችውና በመንፈስ ቅዱስ በምትመራው እውነተኛዋ ሐዋርያዊት ቤተ ክርስቲያን ብቻ እናምናለን፡፡

የጌታን ትምህርትና ትእዛዝ በዘመናት ሁሉ ሳይዛባ በትክክል ለማስተላለፍ ለመፈጸም የተቻለው በመሠረቱ በመንፈስ ቅዱስ ጸጋና ረድኤት ሲሆን በውስጥ አሠራሩ ደግሞ ሐዋርያዊ ትውፊትንና ቅዱሳት መጻሕፍትን በመከተል ነው፡፡ በመጀመሪያ ሐዋርያት ከጌታ የተማሩትንና የታዘዙትን ሐዋርያዊና ክህነታዊ ሥራና ሥልጣን ለተተኪዎቻቸው ለጳጳሳት አስተላልፈዋል፡፡ ጳጳሳትም ከሐዋርያት የተቀበሉትን ሥራና ሥልጣን ለተተ ኪዎቻቸው በማስተላለፍ ሲወርድ ሲዋረድ ከእኛ ደርሷል፡፡ በየዘመኑ ያጋጠማትን የመናፍቃንን ፈተናና ተቃውሞ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል እየተቋቋመች ሐዋርያዊት ቤተ ክርስቲያን ሁሉን የሰጣት ጌታዋ ዳግመኛ እስኪመጣ ድረስ ትኖራለች፡፡ እንግዲህ ሐዋርያዊት ቤተ ክርስቲያን ማለት ከጌታና ከሐዋርያት ጀምሮ የሐዋርያዊነትና የክህነት ሥልጣን በአንብሮተ እድ የተሰጣት ማለት ነው፡፡

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን "ሐዋርያዊት" ቤተ ክርስቲያን ትባላለች፡፡ ምክንያቱም ከጌታ ጀምሮ ለአሥራ ሁለቱ ሐዋርያት፥ ለሰባ ሁለቱ አርድእት፥ ለሰባቱ ዲያቆናት በመንፈስ ቅዱስ ጸጋ በአንብሮተ እድ ሲወርድ ሲዋረድ በውርስ የመጣውን ሐዋርያዊ ሥልጣንና ተግባር ከምሥራቅ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ አብያተ ክርስቲያናት ጋር ተካፋይ ስለሆነች ነው፡፡ ቤተ ክርስቲያናችን ጥምቀትን ሐዋርያት ከሾሟቸው ከሰባቱ ዲያቆናት አንዱ ከሆነው ከፊልጶስ በ34 ዓ.ም. አግኝታለች (የሐዋ.6፥5፤8፥26-40)፡፡

የጵጵስናዋን ማዕረግ ደግሞ ይህ የምንማረው የሃይማኖት ቀኖና ሲዘጋጅና ሲወሰን ለሦስት መቶ አሥራ ስምንት ሊቃውንት ከእለእስክንድሮስ ጋር በመሆን መሪና አስተባባሪ ከነበረው ከቅዱስ አትናቴዎስ ከእስክንድርያው ፓትርያርክ ከመንበረ ማርቆስ ወንጌላዊ በ330 ዓ.ም. ተቀብላለች፡፡ ስለዚህ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በሐዋርያዊ ትውፊት ላይ የተመሠረተች፥ በሐዋርያዊ መንበር ላይ የምትገኝ፥ የክርስቶስን ትምህርትና የሐዋርያትን ሃይማኖት ሳይፋለስ በትክክል እንዳለ ጠብቃ የምታስጠብቅ እውነተኛ ቤተ ክርስቲያን ናት፡፡

## የቤተ ክርስቲያን ደረጃዎች (ሁኔታዎች)

እንግዲህ እስካሁን በተመለከትነው መሠረት በአንዲት፥ ቅድስት፥ ኵላዊትና ሐዋርያዊት በሆነች ቤተ ክርስቲያን እናምናለን፡፡ ከዚህ ቀጥሎ ደግሞ ቤተ ክርስቲያን በሦስት ደረጃዎችና ሁኔታዎች ተመድባ የምትገኝ መሆኗን በአጭሩ ለማየት እንሞክራለን፡፡

## [illegible]ስለ ምትገኘው ቤተ ክርስቲያን

www.ethiopianorthodox.org

በአንደኛ ደረጃና በከፍተኛ ቦታ የምትገኘው ሰማያዊት ቤተ ክርስቲያን አባላት በዕለተ ዓርብ ከሲኦል ወጥተው ገነት የገቡት የቅዱሳን ሆነዋል፡፡ ከእነዚህም ጋር በዕለተ ዓርብ ከሲኦል ወጥተው ገነት የገቡት የቅዱሳ ነፍሳት ሁሉ የሰማያዊቱ ቤተ ክርስቲያን፥ እናታችን የምንላት የላይኛይቱ ኢ ሩሳሌም አባላት ናቸው (ገላ.4፥26፤ ሉቃ.23፥43፤1ኛ ጴጥ.3፥19፤ ዕብ. 12፥22-24)፡፡ እነዚህ ሁሉ ከመላእክት ጋር ሆነው ፈጣሪያቸውን ያመሰግናሉ፤ ለሰ ዎችም ደኅንነት ይጸልያሉ፡፡

## በጉዞ ላይ በምድር ስላለችው ቤተ ክርስቲያን

በሁለተኛ ደረጃ የምትገኘው ቤተ ክርስቲያን በምድር ላይ ያለችው ናት፡፡ እርሷም የመጀመሪያዋን ቤተ ክርስቲያን ፈለግ በመከተል የክርስቶስን መስቀል ተሸክማ በፈተናና በተጋድሎ ትገኛለች፡፡ የውጭ ጠላቶች እያሳ ደዱዋት፥ የውስጥ ባለጋራዎቿ እየተቃወሟት ብትገኝም የእግዚአብሔር ረድኤ ት ሳይለያት በመንፈስ ቅዱስ እየተጽናናች ተጠብቃ ትኖራለች፡፡ ምንም በችግርና በመከራ ውስጥ የምትኖር ብትሆንም ቤተ ክርስቲያን የመሥራቿን ትእዛዝ በመጠበቅ፥ ወንጌልን በማስተማርና የሰዎችን ኃጢአት በማስተሥረይ ከፈጣሪያቸው ጋር በማስታረቅ የተሰጣትን ሥራና ኃላፊነት ሁሉ ለመወጣት ጥረት ከማድረግ አትቆጠብም፡፡

በዓለም ውስጥ የምትኖረው ቤተ ክርስቲያን ከዓለም ስላልሆነች በዚህ ምድር ላይ እንደ እንግዳ መፃተኛ እንደ ስደተኛም ለመኖር ትገደዳለች፡፡ በደስታ ሆኖም በጸጋ መንፈስ ቅዱስና በተስፋ መንግሥተ ሰማያት ልቡናዋ በደስታ እየታደሰ ከፈጣሪዋና ከሰማያዊት ቤተ ክርስቲያን ጋር በጸሎት መገናኘቷን አታ ቋርጥም፡፡ ይህ ግንኙነት በመንፈስ ቅዱስ የተመሠረተ ስለሆነ በምድር ላይ የምትገኘው ቤተ ክርስቲያን ከሰማያዊቷ ጋር ሆና በእውነትና በመንፈስ ስትጸልይ የሁለቱም ጸሎትና ምልጃ በቅድመ እግዚአብሔር ደርሶ ለሰዎች ልጆች ሁሉ ምሕረትንና በረከትን ያስገኛል፡፡

ወደ ተስፋው ሀገር እስኪገቡ ድረስ ቤተ እሥራኤል አርባ ዓመት ሙሉ በበረሃ እንደተንከራተቱ እንዲሁም ቤተ ክርስቲያን በዚህ ምድር ላይ እንደ መን ገደኛ በመሆን ወደሰማያዊ ሀገሯ እስክትገባ ድረስ በመጓዝ ላይ ትገኛለች፡፡ ስለዚህም ምድራዊ በሆነ ነገር ሁሉ ተስፋ አታደርግም፡፡ በዚህ ዓለም ላይ ስትኖር በቤት ውስጥ ለጊዜው እንደ ተቀመጠ እንግዳ ትመስላለች፡፡ በምንም ነገር ላይ ሐሳቧን ጥላና ተደላድላ የምትኖርበትና የምትመካበት ዓለማዊ ሀብት እንዲኖራት አትፈልግም፡፡

አባላቷም ሁሉ በእምነትና በተስፋ እንዲጸኑ፥ በችግርና በመከራ የተነሣ ከዓላማቸው እንዳይሳሳቱ ቤተ ክርስቲያን ትመክራቸዋለች፡፡ በፍቅርም እርስ በእርሳቸው እንዲተሳሰቡና እንዲረዳዱ ከማስተማር አትቆጠብም፡፡ እምነትና ምግባርን አስተባብረው የያዙትን ምእመናን ቤተ ክርስቲያን በአክብሮት ትመለከታቸዋለች፡፡ በምድራዊ ጉዞ ላይ መሆናቸውን አውቀው ወደ ሰማያዊ ሀገራቸው ለመግባት የሚዘጋጁ ምእመናን ሁሉ ብፁዓን ናቸው፡፡



እስኪጨርሱ እንደሚጠበቁ እንደ አንድ የተለየ የኅብረተሰብ ክፍል በመቆጠር በዝቅተኛ ደረጃ ይታያሉ፡፡ ስለዚህም በሦስተኛ ደረጃ ወይም በልዩ ሁኔታ የሚገኙ የቤተ ክርስቲያን አባላት ሊባሉ ይቻላል፡፡ በዚህ ደረጃ የተመደቡ አባ ላት በዚህ ሁኔታ ይኖራሉ ማለት አይደለም፡፡ ይህ ደረጃና ሁኔታ ወደ ከፍተኛ ደረጃ መሸጋገሪያ እንጂ ቀዋሚ አይደለም፡፡ ምክንያቱም በመጨረሻው ጊዜ በደረጃ የተከፋፈለችው ቤተ ክርስቲያን በአንዲት ሰማያዊት ቤተ ክርስቲያን በአ ዲስቱ ኢየሩሳሌም ስለምትጠቃለል ነው፡፡

ወደ ቤተ ክርስቲያን የሚመጡትን አዲስ ተጠማቂዎች እንደ ንዑሰ ክርስቲያን በመቀበል በመምከርና በማስተማር ወደ ከፍተኛ ደረጃ እንዲደርሱ ቤተ ክርስቲያን ያልተቆጠበ ጥረት ስታደርግ ቆይታለች፡፡ ነባር አባሎችዋም በኃጢአት የተነሣ ትተዋት ቢሄዱ እነርሱን ፈልጐ ለመመለስ በትጋት ትከታተላ ቸዋለች እንጂ ከዚያው በጠፉበት ሁኔታና ደረጃ እንዲቀሩ አትፈልግም፡፡ ይልቁንም እነርሱ የቤተ ክርስቲያን አባላት እንደ መሆናቸው መጠን የንስሐውን ጸጋ እንዲቀበሉ፥ ለሥጋውና ለደሙ እንዲበቁ ጥሪ ታደርጋለች፥ ጸሎትም ታደርግላቸዋለች፡፡

ከዚህ ዓለም በሞት ከመለየታቸውም በፊት ንስሐ እንዲገቡ፥ ኃጢአ ታቸውን እንዲናዘዙ፥ ፍትሐት እንዲያገኙ፥ ቀኖናቸውን እንዲፈጽሙ የተቻላትን ሁሉ ታደርጋለች፡፡ በንስሐ ውስጥ የሚገኙ በአመክሮ ላይ ያሉ ንዑሰ ክርስቲያን ሁሉ በመንፈስ ቅዱስ ጸጋና ረድኤት ቀኖናቸውንና አመክሯቸውን ሲጨርሱ ወደ ከፍተኛ ደረጃ ይሻገራሉ፡፡

ቀኖናቸውን ሳይጨርሱ ለሞቱት ተነሳሕያን ቤተ ክርስቲያን ጸሎተ ፍትሐት ታደርሳለች፥ ልዩ ጸሎት ታደርጋለች፥ ትማልዳለች፡፡ ቀኖናቸውን ጨርሰው ገነት ማለት ከሰማያዊት ቤተ ክርስቲያን እንዲገቡ ከምድር የምትገኘው ቤተ ክርስቲያን ለእነርሱ ጾም ጸሎት እንዲያዝላቸው፥ ዝክርና ምጽዋት እንዲደረግላቸው ታሳስባለች (ማቴ.12፥32 ወንጌል ቅዱስ ንባብና ትርጓሜው)፡፡

በሰማይም በምድርም ያሉት የቤተ ክርስቲያን አባላት የሙታን ነፍሳት ከእግዚአብሔር ምሕረትን እንዲያገኙ ይጸልያሉ፡፡ ይልቁንም ጻድቃን በምልጃ ቸው ብዙ ነፍሳትን ያድናሉ (ያዕ.5፥16)፡፡ በአካለ ነፍስ ያሉት በአካለ ሥጋ ካ ሉት ጋር በክርስቶስ አማካይነት ግንኙነት አላቸው፡፡ ምክንያቱም የመንፈስ ቅዱስ ተሳትፎ ያላቸው አማኞች ሁሉ እርስ በእርሳቸው የጸጋ ግንኙነት ስላላቸው ነው፡፡ ሱታፌ መንፈስ ቅዱስ ካለበት ሱታፌ ቅዱሳን ይኖራል፡፡ የአን ድ አማኝ ሕይወት ከሌላው አማኝ ጋር የተሣሠረ ስለሆነ አንድ አባል ሲታመም አባላቱ በሙሉ ያስባሉ፥ ይጨነቃሉ (1ኛቆሮ.12፥26)፡፡ ስለዚህ ነው አንዱ ለሌላው የሚጸልየውና የሚማልደው፡፡ እንግዲህ ምንም በሁናቴና በደረጃ ብትለያይና ብትበላለጥ፥ በሰማይም ሆነ በምድር የምትገኘው ቤተ ክርስቲያን አንዲት የክርስቶስ አካል መሆኗን እናምናለን፡፡

## አንቀጽ ፲

www.ethiopianorthodox.org